LAW
EDUCATION
DISCUSSION
OPPORTUNITY
A STRONGER
SOCIETY

"Where there is no law, there is no freedom."
J. Locke

ትንሣኤ

TINSAE LEGAL FORUM

"ignorance of law is no excuse"

KEEP LEARNING.
STAY CONNECTED.

Join Tinsae Legal Forum for legal insights, learning materials, and practical resources.

TELEGRAM
Legal updates & discussions
OPEN →

YOUTUBE
Legal education videos
OPEN →

FACEBOOK
Community & announcements
OPEN →

LAW | ETHIOPIA | A BETTER TOMORROW

የተሻሻለውን የቤተሰብ ህግ
ለመገንዘብ
የሚረዱ አንዳንድ ነጥቦች

(ቅጽ ሁለት)

በመሐሪ ረዳኢ
ረዳት ፕሮፌሰር
1999 ዓ.ም.

Scanned by CamScanner

ምስጋና

ይህንን ጽሁፍ ሳዘጋጅ ብዙ ሰዎች በተለያየ መልኩ እገዛ አድርገውልኛል፡፡ በተለይም የመጀመሪያውን ቅጽ ያነበቡ ሰዎች ሁለተኛ ቅጽ በተቻለ ፍጥነት አዘጋጅቼ ለህትመት እንዳበቃ የማበረታቻ ግፊት አድርገውልኛል፣ አመሰግናለሁ፡፡

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህግ ፋኩልቲም የአንድ ዓመት ሙሉ የእረፍት ፈቃድ (sabbatical leave) ስለፈቀደልኝ ይህንን ጽሁፍ ለማዘጋጀት ምቹ ሁኔታ ፈጥሮልኛል ለዚሁም ምስጋናየ የላቀ ነው፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚደንት የሆኑት አቶ መንበረ ፀሃይ ታደሰ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳች ዙሪያ ሃሳባቸውን ያካፈሉኝ ሲሆን ለያዝኩት ጉዳይ አግባብነት ያላቸውን የፍርድ ውሳኔዎችም በመጠቀም ረገድ ከፍ ያለ እገዛ አድርገውልኛል፡፡ ከፍ ያለ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

ጽሁፉን ወደ ኮምፒውተር በመገልበጥ ረገድና ለህትመት በሚያመች መልክ በማደራጀት አቶ ሰለሞን ኩምሳ ላደረጉልኝ ትብብር ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ ጽሁፉን እንዳዘጋጅ ላነሳሳኝ፣ አስጀምሮም ላስጨረሰኝ ታላቁ ሃይል ከፍ ያለ ምስጋና ይድረሰው

በመጨረሻም ወደቤቴ ልግባና አሁንም ባለቤቴ ወይዘሮ ክብራ ከበደ እንዲሁም ልጆቼ ሐበንና ሊያ መሐሪ በቅጽ አንድ የተገለፀው አገልግሎታቸው የቀጠሉበት ስለሆነ በድጋሚ ምስጋና ይገባቸዋልና ይህንኑ ይድረሳቸው ብያለሁ፡፡

Scanned by CamScanner

ማውጫ

መግቢያ

ምዕራፍ አንድ - ስለመወለድ 1
ክፍል አንድ - አጠቃላይ የመነሻ ሃሳብ 1
ክፍል ሁለት - አባትነትን በህግ ግምት ስለመወሰን 5
ክፍል ሦስት - ልጅነትን ስለመካድ 16
3.1. አጠቃላይ መነሻ ሃሳብ 16
3.2. በቀጥታ የሚቀርብ የመካድ ክስ 17
3.3. ፍርድ ቤትን በማስፈቀድ የሚቀርብ የመካድ ክስ 19
3.4. የመካድ ክስ በማንና መቼ ይቀርባል? 22
3.4.1. የመካድ ክስ የሚቀርበው በማነው? 23
3.4.2. የመካድ ክስ መቼ ይቀርባል? 27

ክፍል አራት - ልጅነትን ስለመቀበል 30
4.1. አጠቃላይ የመነሻ ሃሳብ 30
4.2. ልጅነትን የመቀበሉ ሥርዓት 33
4.2.1. በአባት በኩል 33
4.2.2. በእናት በኩል 37
4.2.3. በልጁ በኩል 38

ክፍል አምስት - በፍር ቤት ውሳኔ አባትነት እንዲታወቅ ማድረግ 41
5.1. አጠቃላይ የመነሻ ሃሳብ 41
5.2. የመደፈር ወይም የመጠለፍ ተግባር ሰለባ ስለመሆን 42
5.3. በሥልጣን ያለአግባብ መጠቀም ወይም የተስፋ ቃል መስጠት 45
5.4. አባት ነው እንዲባል በተፈለገው ሰው የተጻፉ የግል ሰነዶች የሚኖራቸው ፋይዳ 47

Scanned by CamScanner

5.5. ልጅን እንደአባት ሆኖ መንከባከብ የሚኖረው ህጋዊ ውጤት 49
5.6. ማጠቃለያ 52

ክፍል ስድስት - አባትነት በመወሰን ላይ ስለሚኖረው የህግ ግምትና አፈታቱ 55
6.1. አጠቃላይ የመነሻ ሃሳብ 55
6.2. ግምቱን በስምምነት ስለመፍታት 57
6.3. ግምቱን በህግ ግምት ስለመፍታት 58
6.4. አባትነትን ለሌላ ሰው ስለማስተላለፍና ሥርዓቱ 61

ክፍል ሰባት - ስለልጅነት ማስረጃ 65
7.1. አጠቃላይ የመነሻ ሃሳብ 65
7.2 የልደት ምስክር ወረቀት 68
7.3. የልጅነት ሁኔታ መኖር 69

ምዕራፍ ሁለት - ስለጉዲፈቻ 82
8.1. አጠቃላይ የመነሻ ሃሳብ 82
8.2. የጉዲፈቻ ስምምነት 87
8.2.1. የስምምነቱ ወገኖች 87
8.2.2. የስምምነቱ ቅርጽ (ፎርም) 89
8.2.3. የጉዲፈቻ ልጁ ከተፈጥሮ ዘመዶቹ ጋር ስለሚኖረው ዝምድና 90
8.2.4. የጉዲፈቻ አድራጊው የዕድሜ ወለል (minimum age) እና የጉዲፈቻ ልጁ ከፍተኛ ዕድሜ (maximum age) 92
8.2.4.1. የጉዲፈቻ አድራጊው ዝቅተኛ ዕድሜ 92
8.2.4.2. የጉዲፈቻ ልጁ ከፍተኛ ዕድሜ 95
8.2.5. የጉዲፈቻ እራጊው ቤተሰባዊ ሁኔታ 97

Scanned by CamScanner

8.3. የአለማቀፍ ድርጅቶች ሚና በጉዲፈቻ 101

8.4. የውጭ አገር ዜጋ ጉዲፈቻ አድራጊ ሲሆን 103

ምዕራፍ ሦስት - ቀለብ የመስጠት ግዴታ 109
9.1. አጠቃላይ የመነሻ ሃሳብ 109
9.2. ቀለብ የመስጠት ግዴታ ስላለባቸው ወገኖች 111
9.3. የግዴታው ይዘት 113
9.4. ግዴታው ቀሪ ስለሚሆንበት ሁኔታ 118

ምዕራፍ አራት - አካለመጠን ስላልደረሱ ሰዎች 123
10.1. አጠቃላይ የመነሻ ሃሳብ 123
10.2. አካለመጠን ያልደረሰ ሰው ማን ነው? 124
10.3. የአሳዳሪና የሞግዚት አሿሿም 126
10.4. የአሳዳሪና የሞግዚት የሥራ ድርሻ 133
10.5. የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥራ መሠረታዊ ባህርያት 134
10.6. የአሳዳሪውና የሞግዚቱ ተጠያቂነት 136
10.7. የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥራ ቀሪ ስለሚሆንበት ሁኔታ 140
10.7.1. ሥራው እንዲያከናባው በተሾመው ሰው ምክንያት ቀሪ ስለሚሆንበት ሁኔታ 140
10.7.2. አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ በመነጨ ምክንያት ቀሪ ስለሚሆንበት ሁኔታ 143

አባሪ - I የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ከአንቀጽ 123 እስከ 318 149-192
አባሪ - II የዋቢ ሰነዶች ዝርዝር 193-194

Scanned by CamScanner

መግቢያ

በዚህ መጽሐፍ በቅጽ አንድ መግቢያ ሥር በተገለጸው መሠረት በዋናነት በህፃናት ጉዳይ ላይ የሚያተኩረው ክፍል እነሆ በዚህ መልክ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

የአሁኑ መጽሐፍ አራት ምዕራፎች የያዘ ሲሆን ምዕራፍ አንድ "ስለመወለድ" ምዕራፍ ሁለት "ስለጉዲፈቻ ሥርዓት" ምዕራፍ ሦስት "ቀለብ የመስጠት ግዴታ" እንዲሁም አራተኛውና የመጨረሻው ምዕራፍ "አካለመጠን ስላልደረሱ ሰዎች" በሚል ተደራጅቶ ቀርቧል፡፡ እነዚህ ምዕራፎችም በውስጣቸው ክፍሎችና ንዑስን ክፍሎች የተካተቱባቸው ሲሆን በይዘት በቋንቋና በቃላት አጠቃቀም ቀለል ያለው የቅጽ አንዱን ዓይነት አካሄድ በመከተል የቀረበ ነው፡፡

ይህ እንዲሆን የተደረገበት ምክንያት የዚህ ጽሁፍ ባለአድራሻዎች የህግ ባለሙያዎች ብቻ ሳይሆኑ የሌላ የሙያ ዘርፍ አባላት ብሎም አጠቃላይ ማህበረሰቡ ስለሆነ ለእነርሱም በማይጎረብጥ መልክ ተዘጋጅቶ መቅረብ እንዳለበት ታሳቢ ተደርጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ጽሁፉ ለአንዳንዶች እጅግ ቀላልና ክእቅም በታች እንደሚሆንባቸው ቢገመትም ለአብዛኛው አንባቢ የሚመጥንና ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ በኛ በኩል ቁም ነገሩ እርሱ ነው ብለን እናምናለን፡፡

በርግጥ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ረቂቅ በየአውደጥናቱ እየቀረበ ውይይት ሲደረግበት በነበረ ጊዜ ሁሉ ሰፊ ውይይትና የማሻሻያ ሃሳቦች ሲቀርቡበት የነበረው ርእስ ጉዳይ በአብዛኛው በቅጽ አንድ የተካተተው ጉዳይ ነው፡፡ ቢሆንም በዚህ ክፍልም ሥር ተላል የማይባሉ ለውጦች ተደርገዋል፡፡ በተለይም የቀድሞው የፍትሐብሔር ህግ ህፃናትን በወላጆች ፍጹማዊ ሥልጣን (absolute parental authority) ሥር የሚያስተምጥ ነው በሚል ሲቀርብበት የነበረውን ትችት በማርገብ ረገድና የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ድንጋጌዎች ከህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ጋር ለማጣጣም ተገቢ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይህ ጽሁፍ ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ በዚህ ረገድ የተደረገው ጥረት ለማሳየት ይሞክራል፡፡

የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ፀድቆ ከወጣ ከ1992 ወዲህ አንዳንድ ክልሎችም በየክልላቸው ውስጥ ተፈፃሚ የሚሆኑ የቤተሰብ ህጎች አፅድቀው በሥራ ላይ አውለዋል፡፡ በዚህ ረገድ የአማራ የኦሮሚያና የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መስተዳድሮች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ ክልሎችም በጉዳዩ ላይ እየሰሩበት እንደሆነ ይሰማል፡፡ እስካሁን ከፀደቁት ክልላዊ የቤተሰብ ህጎች መገንዘብ እንደቻልነው ህጎቻቸው ከተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ድንጋጌዎች ጋር ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ (እንዲያውም በብዙ ነጥቦች አንድ ዓይነት) ናቸው፡፡ ስለሆነም የተሻሻለው የቤተሰብ ህግን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀው ይህ ፅሑፍ ሌሎችንም የክልል የቤተሰብ ህጎች በአግባቡ ለመገንዘብ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

በመጨረሻም በዚህ ጽሑፍ ጉዳዩን በተሻለ ሁኔታ ለመገንዘብ ይጠቅማል በሚል እምነት በበታች ፍርድቤቶች ደረጃም ሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በኩል የህግ ትርጉም የተሰጠባቸውን ጥቂት የፍርድ ውሳኔዎች አግባብነት አላቸው በተባለበት ቦታ ሁሉ ለማካተት ጥረት አድርገናል፡፡ ይህም ድንጋጌዎቹ በተግባርና በዕለት ተዕለት ማህበራዊ ግንኙነት ምን ዓይነት ፍቺ እየተሰጣቸው እንደሚገኝ ለማሳየት እንደሚረዳ ተስፋ አለን፡፡

የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በአንዳንድ ነጥቦች ላይ ከተከተለው የክርክር መስመር ጋር አንባቢያን ላይስማሙ እንደሚችሉ ሁሉ በፍርድ ውሳኔዎቹም ላይ እንዲሁ ከዚያ የተለየ ሃሳብ እንደሚኖራቸው ይገመታል፡፡ የህግ ሙያ አንዱ ጣዕም ይኸው ነው፡፡ የብዙ ሃገሮች ህጎች የዳበሩትና አሁንም በመዳበር ላይ የሚገኙት በህግ ጽሁፎችና በፍርድ ውሳኔዎች ላይ በሚጻፉ ትችቶችና ትችቶቹን ተከትለው በሚቀርቡ የአፀፋ ትችቶች መሆኑ ታውቆ በዚህ ረገድ ብዕራችሁን እንድታነሱ በዚህ አጋጣሚ ጥሪ እናስተላልፋለን፡፡

Scanned by CamScanner

ምዕራፍ አንድ፡- ስለመወለድ

ክፍል አንድ አጠቃላይ የመነሻ ሃሳብ

ተደጋሞ ሲል በቅጽ አንድ ላይ እንደተገለጸው በዚህ ቅጽ ሥር የሚዳሰሱት ርዕሰ ጉዳዮች በዋናነት በተወላጆችና አካለመጠን ባልደረሱ የቤተሰብ አባላት ዙሪያ የተደነገጉትን የቤተሰብ ህጉ ድንጋጌዎችን የሚመለከተው ክፍል ነው፡፡ ይህም የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ከአንቀጽ 123 እስከ 318 ያሉትን የሚሸፍን ነው፡፡

የጋብቻ አንደኛው ምናልባትም ዋነኛው ዓላማ ዘር ማፍራት ወይም ዘርን መተካት መሆኑ ስለሚታመን እናትነትና አባትነት በህግ የሚታወቅበትን ሥርዓት ማመቻቸት የቤተሰብ ህጉ አንዱ የሥራ ድርሻ መሆኑ ይታመንበታል፡፡ ዘር በማፍራቱ ረገድ ያልተሳካላቸው ጋብቻዎችም ቢሆኑ በዚሁ ምክንያት ትዳሩን ከማብትንት ይልቅ ጉዲፈቻ ለሚባል ተቋም ህጋዊ መሠረትና ውጤት በመስጠት ተፈጥሮ የነፈገቻቸውን ዘር የማፍራት ፀጋ በሰው ሰራሽ ህግ በኩል ተመሳሳዩን እንዲያገኙ በማድረግ ጋብቻን የመጠበቅ ግቡን ለማሳካት ጥረት ያደርጋል፡፡

በእርግጥ ጉዲፈቻ ዘር ማፍራት ያልቻሉ ተጋቢዎች ብቻ የሚያከናውኑት ህጋዊ ድርጊት ተደርጐ ሊወሰድ አይገባም፡፡ እንዲያውም በመናዊው አስተሳሰብ ጉዲፈቻ የጉዲፈቻ አድራጊዎቹን (አድራጊውን) ለመጥቀም ሳይሆን የጉዲፈቻ ተደራጊውን ጥቅም ተደጋግና መሠረታዊ ዓላማ አድርጐ

የሚከናወን ጉዳይ ነው[1]፡፡ ሆኖም እግረ መንገድም ቢሆን የጉዲፈቻ ሥርዓት እላይ የገለጽነውን የተፈጥሮ ክፍተት በህግ ለመድፈን አገልጋይነቱ አጠያያቂ አይመስልም፡፡ ስለሆነም የጉዲፈቻ ሥርዓቱንና ውጤቱም እንደቤተሰብ ህግ አንዱ ክፍል በዚህ ቅጽ ውስጥ የሚታይ ይሆናል፡፡

ሌላው ስለህጻናትና አካለመጠን ያልደረሱ ሰዎች ሲወሳ መታየት ያለበት ነጥብ ምንም እንኳ ከልደት ጀምሮው (አንዳንዴም ከጽንስ ጀምሮው) የመብት ባለቤቶች ቢሆኑም አካለ መጠን እስኪደርሱ ወይም ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እስኪወጡ ድረስ በመብታቸው ሊሰሩበት (Exercise of right) በህግ ስለማይፈቀድላቸው ይህንኑ በእነርሱ ስም የሚያከናውኑላቸው ህጋዊ ተቋሞች ማደራጀት የግድ ይላል፡፡ የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ኃላፊነቶችም ከሞላ ጐደል ለዚሁ ዓላማ የሚደራጁ ናቸው፡፡ እነዚህንም በዚህ ቅጽ ሥር እናያቸዋለን፡፡

በመጨረሻም ቀለብ የመስጠት ግዴታ በህግ የሚመነጨው በሥጋና በጋብቻ ዝምድና ላይ ተመስርቶ በመሆኑና ይህም ዞሮ ዞሮ ከቤተሰብ ግንኙነት የሚመነጭ ስለሆነ በአብዛኛውም ይህ ግዴታ የሚኖረው አካለመጠን ላልደረሱ ወገኖች ስለሚሆን ህጻናትና አካለመጠን ያልደረሱ ሰዎች ከሚመለከቱ ድንጋጌዎች ጋር አብሮ መታየቱ አግባብነት ያለው ይመስለናል፡፡

የጋብቻ ብሎም የትዳር አንዱ (ምናልባትም ዋነኛው) ዓላማ ዘር ማፍራት ወይም ዘር መተካት ነው ብለናል፡፡ የሰው ዘር ደግሞ የህብረተሰብ መሠረትና የቀጣይነቱ ማረጋገጫ ሂደት ነው፡፡ በዚህ የህብረተሰብ መሠረትነቱ ነው እንግዲህ መንግስትና

[1] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ 34 እንዲሁም የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 194(2) ይመለከቷል

ማህበረሰብ ኃብቻን ትኩረት ሰጥተው ጥበቃ የሚያደርጉለት የሚል እምነት አለ፡፡

መውለድ ዘር ለመተካት አንድ እርምጃ ወደፊት መሆኑ ቢታወቅም ወልዶ ማሳደግ ፣ በትምህርትና በጤና ተንከባክቦ ማኖር ግን ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ የተወለደው ህጻን እነዚህን እንክብካቤዎች ከማን ሊያገኛቸው እንደሚገባ በህግ መወሰን ደግሞ ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም የልጁ እናትና አባት ማንነት መወሰን ወሳኝ ጉዳይ ይሆናል ምክንያቱም የማሳደግና የእንክብካቤ ዋናው ኃላፊነት የሚያርፈው በእነርሱ ላይ ነውና፡፡

በተፈጥሮአዊው ሂደት እናት ልጁን ለወራት ያህል አርግዛ የምትወልደው ስለሆነች የእናቲቱን ማንነት ለመወሰን ብዙም የሚያስቸግር አይሆንም ፡፡ በእርግጥ በዘመናዊው ዓለም ተፈጥሮአዊው የማርገዝና የመውለድ ሂደት የሳይንስና የሰው ልጅ እጅ ጣልቃ እየገባበት የእናቲቱ ማንነትም ለመወሰን አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል ይታሰባል፡፡ ሆኖም በመታደል ይሁን ባለመታደል እነዚህ ሳይንሳዊ የእድገት ደረጃዎች በቅርብ ርቀት ሃገራችን ውስጥ ገብተው ሰፊ ሽፋንና ተቀባይነት ይኖራቸዋል ተብሎ ስለማይታሰብ በኢትዮጵያችን ሁኔታ ተፈጥሮአዊው ሂደት ገዢ ሆኖ መቀጠሉ አይቀርም፡፡ በመሆኑም በህጉ እምነት "እናት የተባለችው ሴት ልጁን በመውለድዋ ብቻ እናትነትዋ እንደሚታወቅ"[2] ተደንግጎ እናገኘዋለን፡፡

በርግጥ በሰለጠነው ዓለም በማህፀን ኪራይ ውል ወይም በቤተ ሙከራ በሚከናወን የፅንስ ዘዴ ተፈጥሮአዊ የወሊድ ሂደት ለውጥ እያሳየ መጥቷል፡፡ ፅንሱን ለወራት የምትሸከመውና አምጣ የምትወልደው "አደራ አስቀማጭ እንጂ እናት አይደለችም" የሚባልበት ዘመን ተደርሷል፡፡ ይህ የቤተሰብ ህግ

[2] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 124

ግን የዘመኑን የሳይንስ ግኝት በሚያስተናግድ መልኩ የተቀረፀ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የእናትነት ማረጋገጫው መውለድ እና መውለድ ብቻ እንደሆነ ደንግጓል፡፡ ዘሩ ከየትም ይምጣ ከየት የወለደችው እናት ነች፡፡ ዘር አቅራቢዋ እስካልወለደች ድረስ በኢትዮጵያ ህግ እናት የምትሆንበት የህግ መሠረት የለም፡፡ እንዲህ በመሆኑ በዚህ ረገድ ህጉ "ዘመናዊነት ያልተላበሰና ወግ አጥባቂ" ሊባል ይችል ይሆናል፡፡ ሆኖም እነዚህን ጉዳዮች በሚያስተናግድ መልኩ ከመቀረጹ በፊት እንደማህፀን ኪራይ ውል የመሳሰሉ ድርጊቶች ላይ የፖሊሲ ውሳኔና አቋም መውሰድ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ድርጊቱን የሚያበረታቱና የሚያወግዙ አመላካከቶች ይነፀባረቃሉና፡፡ ስለሆነም የፖሊሲ ውሳኔው ሲታወቅ ህጉን "ዘመናዊ" ማድረግ አግባብ ይሆናል፡፡ ለጊዜው ግን በነበረበት እንዲቀጥል ማድረጉ ተመራጭ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ማንነት በማወቅ ረገድ አስቸጋሪ የሚሆነው ከእናት ይልቅ የአባት እንደሆነ ይታመናል፡፡ በእርግጥ በሰለጠነው ዓለም አባትነትም ቢሆን በሳይንሳዊ ምርመራ (DNA Test) ማረጋገጥ በመቻሉ አስቸጋሪነቱ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ቢሆንም በእኛና እኛን በመሰሉ ሃገሮች ግን አስቸጋሪነቱ መቀጠሉ አይቀርም፡፡ ስለሆነም ይህንን አባትነት የማረጋገጥ ችግር በመገንዘብና የአባት መታወቅ አስፈላጊነት በማመን ህጉ የራሱ አባትነትን መወሰኛ መንገዶች አደራጅቷል[3]፡፡

ህጉ አባትነት የሚወሰንባቸው ሶስት መንገዶች አመቻችቶአል፡፡ አንደኛው ህጉ ራሱ የሚወስደው ግምት ሲሆን[4] ሁለተኛው አባት ነኝ የሚለው ሰው የሚወስደው እርምጃ ነው[5]፡፡ ሶስተኛውና የመጨረሻው ደግሞ ገለልተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል

[3] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 125
[4] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 126
[5] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 131 እና 132

Scanned by CamScanner

(ፍርድ ቤት) "የዚህ ልጅ አባት አንተ ነህ" ብሎ የሚሰጠው ውሳኔ ነው[6]፡፡ እነዚህን አንድ ባንድ ለማየት እንሞክራለን፡፡

ክፍል ሁለት፡- አባትነትን በህግ ግምት ስለመወሰን

ሀጋችን ልጅ በሚፀነስበት ወይም በሚወለድበት ጊዜ በልጁ እናትና በአንድ ወንድ መካከል በህግ የታወቀ ግንኙነት መኖሩ ከተረጋገጠ ወንድየው የልጁ አባት ነው[7] የሚል የህግ ግምት ይወስዳል ፡፡ ይህ ማለት ህጉ ይህን ግምት እንዲወስድ ቢያንስ ሁለት ነገሮችን ማስረዳት ይገባል፡፡ አንደኛው በልጁ እናትና በወንድየው መካከል በህግ የታወቀ ግንኙነት እንዳለ ወይም እንደነበረ ማሳየት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ልጁ የተፀነሰው ወይም የተወለደው ያ በህግ የታወቀው ግንኙነት ፀንቶ ባለበት ጊዜ መሆኑን ማሳየት ይገባል፡፡

እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ ህጉ "በህግ የታወቀ ግንኙነት" ሲል ምን ዓይነት ግንኙነቶችን ለማመላከት ነው? የሚል ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ በአንዲት ሴትና በአንድ ወንድ መካከል ከሚኖሩት በህግ የታወቁ ግንኙነቶች አንዱና ዋናው ጋብቻ ነው፡፡ ጋብቻ የህግ እውቅናና ጥበቃ የሚደረግለት ተቋም ስለመሆኑ ቀደም ሲል ተመልክቷል፡፡ የጋብቻ እውቅና ከመደበኛ ህግ (ordinary legislation) የሚመነጭ ብቻም አይደለም፡፡ ከህገ መንግሥቱ ከራሱም ጭምር ነው[8]፡፡ ጋብቻ በተጋቢዎቹ መካከል ከሚጥለው አንዱ ግዴታም አብሮ መኖርና መደበኛውን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈጸምን ነው[9]፡፡የባልና ሚስት የመተማመን

[6] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 143
[7] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 126
[8] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ 35
[9] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 53

ግዴታም አብሮ ተጥሏል[10]፡፡ የጋብቻ ግንኙነት ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሁሉ ከሌላ ወንድ ወይም ሴት ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸምም በወንጀል የሚያስቀጣ የዝሙት ተግባር ነው[11]፡፡ ይህ ሁሉ ተጠቃልሎ ሲታይ ከእንዲህ ዓይነት የአንድ ወንድና የአንድ ሴት ግንኙነት ልጅ የመወለድ እድሉ ሰፊ ነው ብቻ ሳይሆን የሚወለደው ልጅ የሰውየው ልጅ ነው ብሎ የህግ ግምት መውሰድም ተገቢ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ አበው ሲተርቱ "እናትነት እውነት ነው አባትነት ግን እምነት ነው፡፡" ይላሉ ህጉም ተመሳሳይ አቋም የወሰደ ይመስላል፡፡

ሌላው በዚህ ረገድ የህግ እውቅና የተሰጠው ግንኙነት ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት ዓይነት ግንኙነት የሚፈጥር ነው፡፡ በእርግጥ ግንኙነቱ ህግ እውቅና የሰጠው እንጂ ህግ የፈጠረው ስላልሆነ አብሮ የመኖር ግዴታ ፣ የመተማመን ግዴታ ፣ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት የመፈጸም ግዴታ የመሳሰሉት በህግ የተቀመጡለት ግልጽ ግዴታ የሉትም፡፡ እንዲያውም ግንኙነቱን በፈለጉ ጊዜ ማቋረጥ መቻላቸው ሲታይ አብሮ የመኖር ግዴታ የለባቸውም ሊባል ይችል ይሆናል፡፡ ቢሆንም በኑሮ ልማድና አኗኗር በዚህ ግንኙነት የተሳሰሩ ሰዎች እላይ የተመለከቱት የባልና ሚስት ግዴታዎች ቢያንስ በሞራል ግዴታ ደረጃ መኖራቸው አይቀርም፡፡ ምክንያቱም እራሳቸውን እንደባልና ሚስት ሊቆጥሩና ቤተዘመዶቻቸውና ማህበረሰቡ እንደተጋቡ ሰዎች ሊቆጥራቸው ይችል ዘንድ እነዚህ ግዴታዎች በውስጠ ታዋቂነት (implied duties) ይኖሩባቸዋል፡፡ ግንኙነቱ በፈለጉ ጊዜ ለማቋረጥ የሚችሉ ቢሆኑም እስካልተቋረጠ ድረስ ግን አብሮ የመኖር ግዴታው እንደተጠበቀ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን በርግጥ ግንኙነታቸው ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ነው ብሎ ለመናገርም የሚያስደፍር አይሆንም፡፡

[10] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 56
[11] የወንጀል ህግ አንቀጽ 652(1) (አዋጅ ቁጥር 414/1996)

Scanned by CamScanner

ስለሆነም ይህ ግንኙነት ባለበት ጊዜ ሁሉ ከሴትየዋ የሚወለደው ልጅ የሌላ ሰው ልጅ ከመሆን ይልቅ ከሴትየዋ ጋር እንደባል አብሮ የሚኖረው ሰው ልጅ ለመሆን የበለጠና አሳማኝ ምክንያት ይኖራል፡፡ ስለዚህ ህጉ ይህንን ግምት መውሰዱ አግባብነት ያለው ይመስለናል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሊነሣ የሚችል ጥያቄ "መተጫጨት በህግ የታወቀ ግንኙነት በመሆኑ በትጭጭት ወቅት ባለበት ሁኔታ እጮኛይቱ ልጅ ከወለደች እጮኛው የልጁ አባት ነው የሚል የህግ ግምት ሊወሰድ አይገባም ወይ? የሚል ነው፡፡ በእርግጥ ይህ ጥያቄ ለፌደራሉ የቤተሰብ ህግ አግባብነት የለውም፡፡ ምክንያቱም በፌዴራሉ የቤተሰብ ህግ በቅጽ አንድ እንደተገለጸው መተጫጨት ከልከላ ባይደረግበትም እውቅና የተሰጠው ግንኙነት አይደለምና፡፡ ጥያቄው ተገቢ የሚሆነው መተጫጨትን በህግ እውቅና ሰጥተው በደነገጉ የክልል የቤተሰብ ህጎች ሥር ነው፡፡

በክልል የቤተሰብ ህጎችም ቢሆን መተጫጨት "እጮኛውና እጮኛይቱ ወደፊት ጋብቻ እንፈጽማለን ብለው የሚያደርጉት ስምምነት ነው[12]" በመሆኑም መተጫጨት አሁን ባለው ትርጉም ስለወደፊቱ እንጂ ስለአሁኑ የእጮኛውና የእጮኛይቱ ግንኙነት የሚያመለክተው ነገር የለም፡፡ ለልጅ መውለድ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ አብሮ የመኖር ግዴታ፣ የሩካቤ ሥጋ የመፈጸም ግዴታ የመሳሰሉት በእጮኛውና በእጮኛይቱ ላይ አይጥልም፡፡ ስለሆነም እንደጋብቻ ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ተቆጥሮ አላይ በተመለከተው የህግ ግምት የሚሸፈን አይሆንም፡፡ ለነገሩ በቀድሞው የፍትሐብሄር ህግም ቢሆን መተጫጨት እውቅና የተሰጠው ህጋዊ ግንኙነት የነበረ

[12] የትግራይ ክልላዊ ምቤት የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 11፣የአማራ ክልል ም/ቤት የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 1

ቢሆንም ለአባትነት የህግ ግምት ግን እውቅና የተሰጣቸው የህግ ግንኙነቶች ጋብቻና ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር እንደነበሩ የፍትሐብሄሩ ከቁጥር 741 እስከ 745 ያሉትን ድንጋጌዎች በመመርመር መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንዲያውም በሌሎች ብዙ ሃገሮች የአባትነት የህግ ግምት ተፈጻሚ የሚሆነው የጋብቻ ግንኙነት ባለበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ከዚያ ውጪ የህግ ግምቱ ተፈጻሚ አይሆንም[13]፡፡ በመሆኑም በትጭጭት ወቅት ልጅ ከተወለደ የሚኖረው እድል በእጮኛውና በእጮኛይቱ መካከል ያለው (የነበረው) ግንኙነት ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር መሆኑን ማሳየት ይገባል፡፡ ይህንን ማሳየት የማይቻል ከሆነ ግን አባት ነው የተባለው ሰው ልጁን በፈቃዱ በልጅነት ካልተቀበለው ወይም የፍርድ ውሳኔ ካላረፈበት በቀር ልጁ ከእናቱ በስተቀር ከሌላ ሰው ጋር ማናቸውም ዓይነት የአባትነት ህጋዊ ግንኙነት አይኖረውም ማለት ነው፡፡

ሁለተኛው ነጥብ በህጉ መሠረት የህግ ግምቱ ተጠቃሚ የሚሆኑት ተወላጆች በህግ እውቅና በተሰጣቸው ግንኙነቶች ጊዜ የተጸነሱ ወይም የተወለዱ ልጆች ናቸው፡፡ ቀደም ሲል እንደገለጽነው በዚህ ረገድ የህግ እውቅና የተሰጣቸው ግንኙነቶች ስንል ጋብቻ ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የህግ ግምቱ ተጠቃሚ አንደኛ በጋብቻ ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ የተፀነሰ ልጅ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ በጋብቻ ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ የተወለደ ልጅ ነው፡፡

አንድ ልጅ የተወለደው በጋብቻ ውስጥ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ብዙም አወዛጋቢነት አይኖረውም፡፡ የተወለደበት ቀን በሰውም ሆነ በሌላ ማስረጃ ማስረዳት

[13] Lasok, POLISH FAMILY LAW, page 147

ስለሚቻልና ጥያቄው በዚያው ቀን ጋብቻው ነበረ ወይ? ስለሚሆን ነገሩ ቀላል ነው፡፡ ምክንያቱም ጋብቻው በዚያው ቀን ስለመኖሩ ከጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓቶች አንጻር ታይቶ በማስረጃ ምዘና የሚወሰን ነው፡፡ ልጁ መቼ ተወለደ? የሚለው የፍሬ ነገር ጥያቄ (question of fact) ሲሆን ልጁ ሲወለድ ጋብቻው ነበር ወይ? የሚለው ደግሞ የህግ ጥያቄ (question of law) ነው፡፡ ቢሆንም ለመወሰን አስቸጋሪ ጭብጦች አይደሉም፡፡ ልጁ የተወለደው ወላጆቹ ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ ነው ወይ? የሚለውም እንዲሁ የተጨባጭ እውነታዎች (facts) ጥያቄ ስለሚሆን፤ ነው? ወይም አይደለም? ብሎ ለመወሰን ብዙም ላያስቸግር ይችላል፡፡

ጉዳዩ አስቸጋሪ የሚሆነው ልጁ የተፀነሰው በህጋዊ ግንኙነት ውስጥ ነው ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ልጅ መቼ ተፀነሰ የሚለውን ጥያቄ የመመለስ ጉዳይ መቼ ተወለደ የሚለውን ያህል ቀላል ስላልሆነ ነው፡፡ በርግጥ በዘመኑ ሣይንስ ይህም ጥያቄ ቢሆን ቀላል እየሆነ መጥቷል፡፡ ሆኖም ለኛ ሃገርና ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንኑ የሳይንስ እድገት በአጭር ርቀት የሚደርስ ስላልሆነ የዚህ ጭብጥ አስቸጋሪነት አብሮን መቀጠሉ አይቀርም፡፡ በመሆኑም ይህንን ክፍተት መሙላት አስፈላጊ ስለሆነ ህግ አውጪው የህግ ግምት አስቀምጦ የማስረዳት ሸክሙን ማርገብ መርጧል፡፡

ስለሆነም በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 128(1) ሥር "አንድ ልጅ ጋብቻው ከተፈጸመ ከ180 ቀናት በኋላ ወይም ጋብቻው በፈረሰ በ300 ቀናት ውስጥ የተወለደ እንደሆነ ልጁ በጋብቻው ውስጥ እንደተፀነሰ ይቆጠራል" የሚል ግልጽ ድንጋጌ የተቀመጠ ሲሆን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(2) ሥር "ለዚህ ከዚህም ጋር ተያይዞ እነዚህ ድንጋጌዎች በጋብቻ ተሳስረው

በሚገኙ ተጋቢዎች ላይ ብቻ ሳይሆን ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩ ጥንዶችም ላይ ተፈጻሚ መሆናቸው ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል[14]፡፡ ስለዚህ ህግ አውጪው አንድ ልጅ መቼ ተፀነሰ የሚለውን አስቸጋሪ ጥያቄ ለመመለስ የተጠቀመው ዘዴ ልጁ የተወለደበት ቀን መሠረት በማድረግ ወደ ኋላ በመቁጠር የመፍታት አቀማመጥ ነው፡፡

አልፎ አልፎ የሚነሣው ጥያቄ አንድ ልጅ ባልና ሚስቱ ጋብቻ በፈጸሙ በሰስተኛው ወይም በአራተኛው ወራቸው ቢወለድ የዚህ የህግ ግምት ተጠቃሚ ይሆናል ወይ የሚል ነው? አንዳንድ ወገኖች ልጁ የዚህ የህግ ግምት ተጠቃሚ የሚሆነው ጋብቻ ከተፈጸመ ቢያንስ በስድስተኛው ወር (180 ቀን) ከተወለደ እንጂ ከዚያ በታች ባለ ጊዜ ከተወለደ በዚህ ሥር ተጠቃሚ አይሆንም[15] ይላሉ፡፡ በሌላ በኩል ግን የህጉ አቀራረጽ በጥሞና ሲታይ የህግ ግምቱ ተጠቃሚዎች የሚሆኑት በጋብቻ ውስጥ የተፀነሱ ወይም በጋብቻ ውስጥ የተወለዱ ልጆች ናቸው፡፡ "ወይም" የሚለው ቃል የአማራጭ ቃል መሆኑ ስለሚታወቅ በዚህ በያዝነው ጉዳይ የተወለደው ልጅ ምንም እንኳ ሀጉ ባስቀመጠው ግምት መሠረት በጋብቻ ውስጥ የተፀነሰ ባይሆንም በሁለተኛው አማራጭ ማለትም በጋብቻ ውስጥ የተወለደ በመሆኑ የህግ ግምቱ ተጠቃሚ ይሆናል የሚል ዕምነት አለን[16]፡፡

ከተጨባጭ የዕለት ተዕለት ግንኙነትም አንጻር ሲታይ በዘመናችን ብዙ ጥንዶች እርግዝና መፈጠሩን ካረጋገጡ በኋላ ወደ ጋብቻ መፈጸም የሚያመሩ ስለሆነ ከእውነታ ያፈነገጠ የህግ

---

[14] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 130(2)

[15] ዶ/ር ከፍሌ ታደሰ፡ በኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ሕግ የቤተሰብ ሕግ ገጽ 172 (በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የታተመ (1990)

[16] አቶ መንበረ ፀሃይ ታደሰ ለህግ የባችለር ዲግሪ ማሟያ ባቀረቡት ጽሁፍ ይህንኑ አቋም ይደግፋሉ (የጽሁፉ ገጽ 17 ይመልከቱ) (ህግ ት/ቤት ቤተ መጻህፍት)

Scanned by CamScanner

ግምት ነው ተብሎ የሚተችም አይደለም፡፡ ከፍትህ አንፃርም ሲታይ አንድ ወንድ የሚያገባት ሴት እርጉዝ መሆንዋን እያወቀ ካገባት እርግዝናው የኔ ነው ብሎ ተቀብሎታል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለዚህ በኛ እምነት አንድ ልጅ ጋብቻው በተፈጸመ በነጋታው እንኳን ቢወለድ የልጁ አባት ያው "አዲሱ ሙሽራ" ነው ማለት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አተረጓጎም ልጁ ያለአባት እንዳይቀር ከማድረግ አልፎ የአዲስ ጋብቻ ቀጣይነትንም የሚያረጋግጥ ስለሆነ ጋብቻ የመንግስት ጥበቃ ይደረግለታል የሚለውን ህገ-መንግስታዊ መርህ የሚያጠናክር ይመስለናል፡፡

እዚህ ላይ ምናልባት ሊነሳ የሚችለው መከራከሪያ ነጥብ በህግ አባትነት የሚሰጠው ሰው ልጁ ከመወለዱ በፊት በ300ኛውና በ180ኛው ቀን መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ከልጁ እናት ጋር በግብረ ሥጋ ላለመገናኘቱ ተቃራኒ ማስረጃ በማይገኝበት አኳሃን ያስረዳ እንደሆን የተባለውን ልጅ ልጄ አይደለም ለማለት ይችላል[17] በሚል የተደነገገ ስለሆነ የህግ ግምቱ ተፈጻሚነት በጋብቻ ውስጥ ለተፀነሱ ብቻ ነው ሊባል ይችል ይሆናል፡፡

ሆኖም የህግ አውጪው ድንጋጌዎች አንዱ ከሌላው ጋር ተዋህደው መተርጎምና ውጤት መስጠት ስላለባቸው (harmonious construction principle of interpretation) ይህ አንቀጽ የህጉ አንቀጽ 126ን በሙሉም ሆነ በከፊል ውጤት አልባ የማድረግ ውጤት በሚኖረው ሁኔታ ሊተረጎም አይገባም፡፡ በመሆኑም በአንቀጽ 168 መሠረት የመካድ ክስ ማቅረብ የሚችለው ልጁ በጋብቻ ውስጥ አልተፀነሰም በሚል የሚከራከር አባት እንጂ ልጁ በጋብቻ ውስጥ የተወለደ ከሆነ በሌሎቹ የመካድ ክስ ማቅረቢያ አንቀጾች እንጂ በአንቀጽ 168 ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም የሚል እምነት አለን፡፡

[17] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 168

በመጨረሻም በዚህ ርዕስ ሥር መገለጽ ያለበት ጉዳይ ይህ የህግ ግምት ጠፉ ተብለው የፍርድ ውሣኔ በተባለፈባቸው ሰዎች ላይ ተፈጻሚነቱ እንዴት ነው? የሚል ይሆናል፡፡ በቀድሞው ፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 744 "ልጁ የተወለደው ባልዬው በአገር የለም ተብሎ <u>በፍርደ ከተነገረ በኋላ የሆነ እንደሆነ</u> የተባለው ባል የልጁ አባት አይደለም" (ሥረዝ የተጨመረ) በሚል ተደንግጎ ነበር፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ውስጥ ግን "... በህግ አባት ነው የሚባለው ሰው መጥፋቱ በተነገረበት ፍርድ ላይ <u>ስለመኖሩ ወሬ የተሰማበት የመጨረሻ ቀን</u> ነው የተባለበት ከ300 ቀናት በኋላ ለተወለደ ልጅ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡ (ሥረዝ የተጨመረ) በሚል ተስተካክሏል፡፡ ይህ ማስተካከያ ማድረግ ያስፈለገበት ምክንያት በአግባቡ ለመገንዘብ ነጥቡ በፍትሐብሔሩ ህጉ "ስለ ሰዎች" በሚለው መጽሐፍ ሥር ከቁጥር 154 እስከ 173 ድረስካሉት ድንጋጌዎች ጋር አብሮ መመርመር ያለበት ነው፡፡

በህግ ቋንቋ "መጥፋት" ሲባል በተለምዶ ከምናውቀው መጥፋት ከሚባለው ቃል ጋር አንድ አይነት ትርጉም አይሰጠውም ፡፡ ለህጉ ዓላማ አንድ ሰው ጠፋ የሚባለው ቢያንስ ሁለት ዓመት ከመኖሪያ ቦታው የተሰወረና፣ አየሁት ወይም ስለሱ ወሬ ሰምቻለሁ የሚል ሰው ሲታጣ የሚፈጠር ክስተት ነው[18]፡፡ እነዚህ ክስተቶች መሟላታቸው የሚያረጋግጥ አቤቱታ ለፍ/ቤት ሲቀርብለት ፍ/ቤቱም በራሱም በኩል አስፈላጊውን ማጣራት አድርጎ ውጤት ያላገኘ እንደሆነ የመጥፋት ውሳኔ ይሰጣል፡፡ በውሳኔውም ላይ ለመጨረሻ ጊዜ ታየ ወይም ወሬው ተሰማ የተባለበት ቀን እንደመጨረሻ ቀን ይወስደዋል፡፡

[18] የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 154(1)

ይህ የፍትሐብሄሩ የህግ ክፍል ከተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ጋር አገናዝበን ስናየው በመጥፋት የፍርድ ውሳኔው ላይ የመጨረሻ ቀን ተብሎ ከተያዘው ቀን አንስቶ 300 ቀናት ካለፈ በኋላ ከጠፋው ሰው ሚስት ልጅ ከተወለደ ይህ ልጅ የጠፋው ሰው ልጅ ነው ተብሎ አይወሰድም ማለት ነው፡፡

ነገሩን በምሳሌ ለማብራራት ያህል የሚከተለውን ሥዕል መፍጠር ይቻላል፡፡ አቶ በቀለና ወይዘሮ ፀሐይነሽ ጥር 23 ቀን 1991 ዓ.ም ጋብቻ ፈጽመው ትዳር መሠረቱ እንበል፡፡ ከዚያም ለሁለት ዓመታት ያህል በናዝሬት ከተማ አንድ ወንድ ልጅ ወልደው በሰላምና በደስታ ሲኖሩ አቶ በቀለ ግንቦት 28 ቀን 1993 "አሰላ ከተማ ደርሼ ልምጣ" ብለው እንደወጡ የውሀ ሽታ ሆነው ይቀራሉ ፡፡ ወ/ሮ ፀሐይነሽ የባለቤታቸው መሰወር ያሳደረባቸው የልብ ስብራት ሳያንስ ህፃኑ ልጃቸው ወንድ ባየ ቁጥር አባባ! እያለ ሲጣራ እንጀታቸው እየተላወሰ ወደ ውስጥ ያለቅሳሉ፡፡

ጐረቤት የሚያመጣላቸው ወሬ የተምታታ ነው ፤ አንዳንዱ "አቶ በቀለ ጅቡቲ ታዩ" በዚያው አሜሪካ ይገቡ ይሆናል ሲላቸው፣ ሌላው ደግሞ በሙያቸው ጤና ረዳት የነበሩት አቶ በቀለን "የጭነት መኪና ከነተሳቢው እየነዱ ሚዛን ተፈሪ ታዩ" ይላቸዋል፡፡

እንዲህ ባልተጨበጡ ወሬዎች ዓመታት አለፉ ፤ የወ/ሮ ፀሐይነሽና የልጃቸው ተስፋም ተሟጠጠ፡፡ ስለሆነም በህግ ረገድ ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዲያማክሮዋቸው አንድን ጠበቃ ሲያማክሩ ጠረታ እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ጥቅማ ጥቅሞች እንዲያገኙና ለወደፊት ኑሮአቸውም አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር የመጥፋት ውሳኔ እንዲወሰንላቸው ለፍርድ ቤት እንዲያመለክቱ በመምከር

የአቤቱታው ይዘትም እኚሁ ጠበቃ አዘጋጅተው ሰጥተዋቸዋል፡፡

መጋቢት 13 ቀን 1996 አቤቱታውን ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ያቀርባሉ፡፡ ፍርድ ቤቱም ባገኘው የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች መሠረት ግለሰቡ ሰኔ 7 ቀን 1993 ዓ.ም ደብረዘይት ከተማ አንድ ቡና ቤት ውስጥ ቢራ እየጠጡና ከሰዎች ጋር ሲጨዋወቱ እንደታዩ አስተማማኝ ማስረጃ በማግኘቱ ህዳር 19 ቀን 1997 በዋለው ችሎት ውሳኔ ያሳረፈ ሲሆን በውሳኔውም ላይ አቶ በቀለ ከሰኔ 7 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ የጠፉ መሆናቸውን ጠቅሶ ፋይሉን ዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት መልሶታል፡፡

ወ/ሮ ፀሐይነሽ ምንም እንኳ የመጥፋት ውሳኔ እንዲሰጣቸው መጋቢት 13 ቀን 1996 ዓ.ም አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም የአባቷ ማንነት ለእርሳቸው ካልሆነ በቀር ለሌላ ያልታወቀ ሴት ልጅ ሐምሌ 27 ቀን 1994 ዓ.ም ተገላግለዋል፡፡ጥያቄው እንግዲህ ይህች ልጅ የአቶ በቀለ ልጅ ልትባል ይገባል ወይ? የሚል ነው፡፡

በርግጥ ቀደም ሲል እንዳየነው በጋብቻ ውስጥ የተወለደ ልጅ አባቱ የሴትየዋ ባል ነው ብለናል፡፡ ወ/ሮ ፀሐይነሽና አቶ በቀለም እንደተጋቡ ከላይ ተገልጾልናል፡፡ ጋብቻቸውም በህጉ አግባብ አልፈረሰም ምክንያቱም ጋብቻ የሚፈርስባቸው ሥርዓቶች በህጉ እንደተመለከተው ከሁለቱ አንደኛው በሞት ሲለይ ወይም የመጥፋት ውሳኔ ሲወሰንበት ወይም በፍቺ ነው[19]፡፡

---

[19] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 75

አሁን በያዝነው ጉዳይ አቶ በቀለ ስለመሞታቸው የቀረበ ማስረጃ የለም፡ ጋብቻቸውም በፍቺ እንዳልፈረሰ ተመልክተናል፡የመጥፋት ውሳኔ በአቶ በቀለ ላይ የተላለፈውም ህዳር 19 ቀን 1997 በመሆኑና ልጅቷ ግን ሐምሌ 27 ቀን 1994 የተወለደች ስለሆነ የተወለደችው ከጋብቻው መፍረስ በፊት መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ በህጉ አግባብ ሴትዋ ልጅ የተወለደችው በጋብቻ ውስጥ ስለሆነ አባትዋ አቶ በቀለ ናቸው ተብሎ ይገመታል፡፡

ሆኖም የጉዳዩ ዝርዝር ከላይ እንደተመለከትነው አቶ በቀለ ከቤት ወጥተው ሳይመለሱ የቀሩት ከግንቦት 28 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑን ገልጸናል፡፡ ስለሆነም ከአንድ ዓመት በላይ ቆይታ በኋላ (ሐምሌ 27 ቀን 1994) የተወለደችው ሴት ልጅ የአቶ በቀለ ልጅ ናት ለማለት የሳይንስ ድጋፍ አይኖረንም ፡፡ ምክንያቱም በተለምዶ የሰው ልጅ ፅንስ ከአንድ ዓመት በላይ የሚቆይበት ሁኔታ የለምና ነው፡፡

በተቻለ መጠን የህግና የሳይንስ አለመጣጣም ማጥበብ ስለሚገባ ህግ አውጪው የሚያቀራርብ መፍትሔ በህጉ አንቀጽ 129 ላይ አስቀምጦ ይገኛል፡፡ በዚህ አንቀጽ መሠረት በፍርድ ቤቱ የመጥፋት ውሳኔ ላይ የመጨረሻው ቀን ነው ከተባለበት ከ300 ቀናት በኋላ ለተወለደ ልጅ በአንቀጽ 126 ሥር የተመለከተው መርህ ተፈጻሚ እንዳይሆን የሚገድብ ነው፡፡ ይህም ማለት በዚህ በያዝነው ጉዳይ የአቶ በቀለ የመጥፋት ውሳኔ ሲሰጥ የመጨረሻ ቀን ተብሎ የተያዘው ሰኔ 7 ቀን 1993 ዓ.ም ስለሆነና ልጅቷ የተወለደችው ግን የ300 ቀናት ጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ማለትም ሐምሌ 27 ቀን 1994 በመሆኑ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው አንቀጽ 126 ሳይሆን አንቀጽ 129 ይሆናል ማለት ነው፡፡ በውጤቱም ልጂቱ የአቶ በቀለ ልጅ ናት ልትባል አትችልም ማለት ነው፡፡ በፍትሐብሄር ህጉ አቀራረጽ

ሂደን ቢሆን ግን ልጂቷ የተወለደችው የመጥፋት ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ማለትም ፍርዱ የጠተሰጠው ህዳር 19 ቀን 1997 ዓ.ም. ሆኖ የተወለደችው ግን ሐምሌ 27 ቀን 1994 ዓ.ም በመሆኑ የአቶ በቀለ ልጅ ናት ልትባል ነበር ማለት ነው፡፡

ክፍል ሦስት፡- ልጅን ስለመካድ

3.1. አጠቃላይ የመነሻ ሃሳብ

ህጉ በህግ እውቅና የተሰጣቸው የወንድና የሴት ግንኙነቶች (ጋብቻና ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር) ለመጠበቅ ሲልና ህጻናት ያለአባት እንዳይቀሩ በማሰብ ከላይ የተመለከተው የህግ ግምት የደነገገ ቢሆንም ግምቱ ሊፈርስ ወይም ሊሻር የሚችልበት ጠባብ አማራጭም አብሮ አስቀምጧል፡፡ ይህም ልጅን መካድ (disowning) የሚባል ሥርዓት ነው፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ህጋችንም ከአንቀጽ 167 እስከ 179 ባሉት ድንጋጌዎች ሥር የምናገኘው ነው፡፡

ልጅን የመካድ ክስ ሁለት ጥቅሞችን ለማስታረቅ የሚያገለግል ሥርዓት በማበጀት ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ እነዚህም ጥቅሞች በአንድ በኩል የልጁ ጥቅም ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በህግ ግምት አባት ነህ የተባለው ሰው ጥቅም ነው፡፡ እላይ እንደተመለከትነው በህግ ግምት አባትነት የሚታወቅበት ሥርዓት ጠንካራና ሰፊ በመሆኑ ብዙዎቹ ህፃናት ያለህጋዊ አባት እንዳይቀሩ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ሁኔታ ግን የህፃኑ አባት ሊሆን የማይችል ወይም የማይገባው ሰው አባት ነህ ሊባል የሚቻልበት ዕድልም ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ ሰዎች ከአብራካቸው ላልተወለዱ ልጆች የአባትነት ግዴታ እንዳይጫንባቸው የማድረግ አስፈላጊነት የሚያጠያይቅ አይሆንም፡፡ ይህም ህጉን በተቻለ መጠን ከባዮሎጂካዊ ውጤት ጋር ለማጣጣም ይችል

Scanned by CamScanner

ዘንድ ነው የመካድ ክስ ሥርዓት በቤተሰብ ህጎችን ውስጥ የተካተተው፡፡

በህጉ መሠረት የመካድ ክስ ሁለት አይነት ሥርዓቶች ያሉት ሲሆን እነርሱም በቀጥታ የሚቀርብ የመካድ ክስና[20] ፍርድ ቤት በማስፈቀድ የሚቀርብ የመካድ ክስ[21] ናቸው፡፡

በመግቢያው ላይ አንድ ሰው የአንድ ልጅ አባት ነው የሚባልባቸው ሦስት መንገዶች አይተናል፡፡ እነዚህም በህግ ግምት የሚሰጥ አባትነት፣ አባት ራሱ ልጄን ልጄ ነው ብሎ እውቅና የሚሰጥበት ሥርዓትና ፍርድ ቤት ይህ ልጅ የእገሌ ልጅ ነው ብሎ የሚወስንበት ሥርዓት ተብለው ይመደባሉ፡፡ እነዚህ ሁሉም ግን አይደሉም የመካድ ክስ አቅርበው የአባትነት ሸክማቸውን ማውረድ የሚችሉት፡፡ የመካድ ክስ ተጠቅመው የአባትነት ሸክማቸውን ማስወገድ የሚችሉት በህግ ግምት አባትነህ የተባሉ ብቻ መሆናቸው መገንዘብ ይጠቅማል፡፡ ይህ ስለመሆኑም ከህጉ አቀራረጽ በአጠቃላይ በተለይ ደግሞ ከአንቀጽ 168፡170 እንዲሁም 174 መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የልጅን አባትነት ፈቅደው የተቀበሉና በፍርድ ውሳኔ አባት ነህ የተባሉ ሰዎች የመካድ ክስ ለማቅረብ የህግ መሰረት አይኖራቸውም፡፡

ይህን አጠቃላይ መንደርደሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ ቀጥለን ለመካድ ክስ መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ፍሬ ነገሮችን ለማየት እንሞክራለን፡፡

3.2. በቀጥታ የሚቀርብ የመካድ ክስ

[20] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 168
[21] ዝኒ ከማሁ 170

የፍርድ ቤት ፈቃድ መጠየቅ ሳያስፈልግ በቀጥታ የመካድ ክስ የሚቀርበው በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 168 የተመለከተው ሁኔታ ሲያጋጥም ነው፡፡ ይህም የልጁ አባት ነህ ተብሎ በህግ አባትነት የሚሰጠው ሰው ልጁ ከመወለዱ በፊት በ300ኛውና በ180ኛው ቀናት መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ከልጁ እናት ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ላለመፈፀሙ በማያጠራጥር ሁኔታ ያስረዳ እንደሆነ የተባለውን ልጅ ልጄ አይደለም ለማለት ይችላል፡፡

ጉዳዩን በምሳሌ ለማስረዳት አንድ ባል ለሁለት ዓመት የከፍተኛ ትምህርት ለመከታተል ከኢትዮጵያ ውጪ ይሄድና ትምህርቱን አጠናቅቆ ሲመለስ ሚስቱ ከሶስት ወር በፊት ተገላግላ የሶስት ወር ህፃን ታቅፋ ትጠብቀዋለች፡፡ በዚህ ሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሚስት ባለቤትዋን ለመጎብኘት ወደ ውጪ ሃገር አለመሄድዋ ከታመነና ባልም በትምህርቱ መሃከል ወደ አገር ቤት አለመምጣቱ ከታመነ ህፃኑ የባልየው ልጅ ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም በመጨረሻዋ የመለያያቸው ቀን እርግዝና ተፈጥሮአል ብንል እንኳ እርግዝናው በምንም መልኩ አንድ ዓመት ከዘጠኝ ወር ያህል ሊቆይ ስለማይችል ነው፡፡

በህጉ ግምት የባልየው ለሁለት ዓመታት ወደውጪ ሃገር መሄድ ጋብቻውን የማፍረስ ውጤት ስለማይኖረውና ህፃኑም የተወለደው በጋብቻ ውስጥና ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ በመሆኑ የህፃኑ አባት ያው ለትምህርት ሄዶ የነበረው ባል ነው ተብሎ ይወሰዳል፡፡ ስለዚህ ይህ ባል ሁለት አማራጭ ይኖሩታል፡፡ አንደኛው አማራጭ የህፃኑ የተፈጥሮ አባት ባይሆንም የህግ አባቱ ስለሆነ ለትዳሩ ፀንቶ መቀጠል ሲል በዝምታ አባትነቱን ተቀብሎ ትዳሩን ባለበት ሁኔታና ሳይናጋ ማስቀጠል ሲሆን ሁለተኛው አማራጭ ግን የመካድ ክስ በማቅረብ የዚህ ህፃን አባትነትን ማስወገድ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ባልየው ሁለተኛውን

Scanned by CamScanner

አማራጭ ለመጠቀም ከወሰነ ጉዳዩ በዚህ አንቀጽ ሥር ሊስተናገድ ይችላል ማለት ነው፡፡

3.3. ፍርድቤትን በማስፈቀድ የሚቀርብ የመካድ ክስ

ሌላው የመካድ ክስ ማቅረብ የሚቻልበት ሁኔታ ባልና ሚስቱ አብረው በሚኖሩበትና መደበኛው የግብረሥጋ ግንኙነት እየፈፀሙ ባሉበት ሁኔታም ሊያጋጥም የሚችል ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም ከዚህ በላይ ከገለፅነው ሁኔታ በዓይነቱ የተለየ ነው፡፡ የክስ አቀራረብ ሥርዓቱም እንዲሁ የተለየ ነው፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር የመካድ ክስ ለማቅረብ መጀመሪያውኑ የፍርድ ቤት ፈቃድ ያስፈልጋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የመከሰስ ፈቃዱን በቀላሉ የሚሰጥበት ሁኔታ አልተቀመጠም፡፡ የመካድ ክሱ ቢፈቀድ በአሸናፊነት ሊወጣ ይችላል የሚያሰኙ (... በሳይንስ እውቀት ተለይተው የሚታዩ ተጨባጭ መረጃዎች ወይም እናትዬው ከእርግዝና አንስቶ እስከ ወሊድ ድረስ ሁኔታዎችን ባል የተባለው ሰው እንዳያውቃቸው የመሸፋፈን ድርጊቶች የሚመነጩና ሚዛን የሚደፉ መረጃዎች ሊቀርቡለት ይገባል)[22]፡፡

ፍርድ ቤት የመካድ ክስ እንዲቀርብ ለመፍቀድ የሚጠይቀው መረጃ ቀለል ያለ እንዲሆን ከተደረገ ሰዎች በሆነውና ባልሆነው ምክንያት እየተነሱ በትዳር ጓደኞቻውና በልጆቻው ላይ የመካድ ክስ እንዲመሰርቱ በር የሚከፍት ስለሚሆን ግለሰቦችን በቂ መሠረት በሌለው ምክንያት በክስ ማስጨነቅ (harassment) ይሆናል ብቻ ሳይሆን የትዳርን

[22] ዝኒ ከማሁ 172

አንድነትም የሚያናጋ ይሆናል፡፡ በመሆኑም "ህፃኑ ምኑም እኔን አይመስልም"፣ "ፀጉሩ ወይም አፍንጫው ወይም የእጁ ጣት ወዘተ የእኔን አይመስልም" በሚል ውጫዊ ግምገማ ብቻ ተነስቶ የመካድ ክስ ለማቅረብ ፈቃድ ሊጠየቅ አይገባም ቢጠየቅም ፍርድቤቶቻችን ሊፈቅዱ የሚገባ አይመስለኝም፡፡

ህጉ በዚህ ረገድ እንዲቀርቡ የሚጠብቃቸው መረጃዎች በሳይንሳዊ ዘዴ ሊደገፉ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ባል መውለድ የማይችል መካን (sterile) መሆኑ በሐኪም ከተረጋገጠ በኋላ ሚስቱ እርግዛ ከወለደች ወይም በዘመናዊ የምርመራ ዘዴ (DNA Test) የህፃኑና አባት ነው የተባለው ሰው ባዮሎጂካዊ አፈጣጠር የማይመሳሰል ሆኖ ከተገኘ የመካድ ክስ ለማቅረብ የፍርድ ቤት ፈቃድ ለማስገኘት የሚያስችል ይመስለኛል፡፡

ከሳይንሳዊ መረጃ ውጪ የመካድ ክስ ለማቅረብ የፍርድ ቤት ፈቃድ ለማስገኘት የሚያስችለው ፈቃድ ለመስጠት በህጉ አገላለፅ "...ከባድ ምልክት ሲኖር ብቻ ነው"[23]፡፡

ይህ ምልክትም ሚስት በባልየው አባትነት ላይ ጥርጣሬ በሚያሳድር አኳኋን የልጁን መውለድ ወይም እርግዝናዋን ከባልየው የመደበቅ ድርጊት ስታሳይ[24] የሚከሰት ሁኔታ ነው፡፡ በመደበኛው ሁኔታ አንዲት ሚስት እርግዝናዋን ወይም መውለድዋን ከባልዋ የምትደብቅበት አንዳች ምክንያት ይኖራል ተብሎ አይታሰብም፡፡ እርግዝናው ወይም ህፃኑ የባልየው አይደለም የሚል ሥጋትና እምነት ካላደረባት በስተቀር በዚህ ድርጊት ውስጥ አትሰማራም፡፡ ይህ ድርጊት ሲፈፀም ሚስት

[23] ዝኒ ከማሁ 171(2)
[24] ዝኒ ከማሁ 172(2)

Scanned by CamScanner

ጥፋትዋን አምና ግን ልትደብት ጥረት እያደረገች ስለመሆንዋ ግምት የሚያስወስድ ነው፡፡

እንዲያውም በአንዳንድ ሃገሮች ይህ ድርጊት የፍርድ ቤት ፈቃድ መጠየቅ ሳያስፈልግ በራሱ ልጅን ለመካድ በቂ ምክንያት ነው፡፡ ከቤተሰብ ህጎችን ጋር ጥብቅ ቁርኝነት አለው በሚባልባቸው ፈረንሳይና ሉዊዚያና የቤተሰብ ህጎች ውስጥ ሚስት እርግዝና ወይም ወሊድ ከባልየው ከደበቀች የፍርድ ቤት ፈቃድም ሆነ ተጨማሪ ማስረጃ ሳያስፈልግ የመካድ ክስ ለማቅረብ በቂ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በኛዉ የቤተሰብ ህግ ግን ሁኔታው ለየትና ጠበቅ ያለ ነው፡፡ ሚስት እንዲህ ዓይነት ድርጊት መፈጸምዋ የመካድ ክስ ለማቅረብ ፈቃድ ለማግኘት ያስችላል እንጂ ይህ ድርጊት ብቻውን ለመካድ በቂ አይደለም፡፡ ባል በዚሁ ከባድ ምልክት ምክንያት የመክሰስ ፈቃድ ካገኘ በኋላ በአንቀጽ 170 በተመለከተው መሠረት ባል የዚህ ልጅ አባት ሊሆን አለመቻሉን በማያጠራጥር አኳኋን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የሚስቲቱ እርግዝናዋን ወይም ወሊድዋን ከባልዋ መደበቅ የመካድ ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ ማስረጃ ቢሆንም በቂ ግን አይደለም፡፡

በርግጥ በማያጠራጥር አኳኋን የእርሱ ልጅ አለመሆኑን ለማረጋገጥ እየቻለም ቢሆን ባል የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚከለከልበት ልዩ ሁኔታ ይኖራል፡፡ ይህም በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 178 ተመልክቶ ይገኛል፡፡ በዚህ አንቀጽ መሠረት " ባልየው <u>በጽሑፍ በሰጠው ፈቃድ</u> መሠረት ህፃኑ በሰው ሰራሽ ዘዴ የተፀነሰ ለመሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን በሌላ ጊዜ ተመልሶ ህፃኑን ለመካድ ዕድል አይሰጠውም፡፡ (ሠረዝ የተጨመረ)

እንደሚታወቀው ዘመናዊው ሳይንስ በሠው ሰራሽ ዘዴ ፅንስ የሚፈጥርባቸው ሁለት ዋንኛ ዘዴዎች አሉት፡፡ አንደኛው ባልየው የራሱ የዘር ፍሬ በሰው ሰራሽ ዘዴ ተወስዶ ከሚስቱ የዘር ፍሬ ጋር ተዋህዶ የሚፈጠር ፅንስ (Artificial Insemination Husband (AIH)) ሲሆን ሁለተኛው ዘዴ ደግሞ የባልየው ሳይሆን የሌላ ሦስተኛ ሰው የዘር ፍሬ በሰው ሰራሽ ዘዴ ተወስዶ ከሚስቲቱ የዘር ፍሬ ጋር በማዳቀል የሚፈጠር ፅንስ ነው (Artificial Insemination Donor (AID))፡፡ የመጀመሪያው ዘዴ ተፈጥሮአዊው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ባለመከናወኑ ካልሆነ በስተቀር ህፃኑ የባልና ሚስቱ የዘር ፍሬ ውጤት ስለመሆኑ በባዮሎጂካዊ መረጃ ሊረጋገጥ የሚችል ነው፡፡ በመሆኑም አንቀጽ 178 ይህንን ጉዳይ የሚመለከት አይደለም፡፡ የዚህ አንቀጽ አግባብነት የሚነሳው ሁለተኛው ዘዴ ማለትም የባልየው ሳይሆን የሌላ ሦስተኛ ሰው የዘር ፍሬ በሠው ሰራሽ ዘዴ ተወስዶ ከሚስቲቱ የዘር ፍሬ ጋር በማዳቀል ፅንስ ተፈጥሮ ህፃን ሲወለድ ነው፡፡ እንዲህ ባለ ሁኔታ ባልየው የህፃኑ ባዮሎጂካዊ አባት እንደማይሆን እሙን ነው፡፡ በማያጠራጥር አኳኋንም የህፃኑ አባት ሊሆን እንደማይችል ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ቢሆንም ይህ ባል ይህ ሰው ሰራሽ ዘዴ በሚስቱ ላይ እንዲከናወን በጽሑፍ የፈቀደ ስለሆነ የመካድ ክስ እንዲያቀርብ ህጉ አይፈቅድለትም፡፡ ነገር ግን በዚህ ረገድ ባልየው ፈቃዱን ሰጥቶአል ለማለት ፈቃዱ በጽሑፍ የተሰጠ መሆን ይኖርበታል፡፡ ህጉ ፈቃዱ በጽሑፍ እንዲሆን የፈለገበት ምክንያትም ድርጊቱ በአግባቡ ታስቦበት፣ በእቅድና በቅድመ ዝግጅት የተከናወነ መሆኑን ለማሳየትና ባልየውም ፈቃዱን በማያጠራጥርና በማያሻማ መንገድ የገለፀ መሆኑን ለማመላከት እንዲያመች ታስቦ ይመስለናል፡፡

3.4. የመካድ ክስ በማንና መቼ ይቀርባል?

በመጨረሻም ከመካድ ክስ ጋር ተያይዞ መወሳት ያለበት ጉዳይ ክሱ በማን ላይ ይቀርባል? ማን ያቀርባል? መቼ

Scanned by CamScanner

ይቀርባል? የሚሉ ሥነ ሥርዓታዊ ነጥቦችን መዳሰስን ይመለከታል፡፡

3.4.1. የመካድ ክስ ማቅረብ የሚችለው ማነው?

የመካድ ክሱን ማቅረብ የሚችለው ማን ነው? የሚለውን በተመለከተ የቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 174 የተደነገገ ሲሆን ይህም "... የልጁ አባት ነህ ተብሎ በህግ ግምት የሚሰጠው ሰው ብቻ ነው" ተብሏል፡፡ በመሆኑም በህግ ግምት አባት ነህ የተባለ ሰው አባትነቱን በራሱ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ሰው ሊነጥቀው እንደማይችል ህጉ ጥበትና ሰጥቶታለ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ የህፃኑ አባት ባልየው ሳይሆን ሌላ ግለሰብ ነው በማለት የህፃን እናት የምትሰጠው የእምነት ቃል ወይም ሌላ ግለሰብ ህፃኑ የባልየው ልጅ ሳይሆን የእኔ ልጅ ነው በማለት የህግ አባትነቱን ሊያሳጣው አይችልም ማለት ነው፡፡

በዚህ ረገድ በአንድ ወቅት (እ.ኤ.አ) በአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቀረበ ጉዳይ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ወይዘሮ ካሮልና አቶ ጀራልድ (እ.ኤ.አ. 1976) ጋብቻ ፈፅመው አብረው መኖር ይጀምራሉ፡፡ ሆኖም ወይዘሮዋ ከ1978 ጀምሮ በጉርብትና ከሚኖር ሚካኤል ከተባለ ሰው ጋር በዝሙት ድርጊት ውስጥ መሳተፍ ጀምራ ረዘም ላለ ጊዜ ትቀጥልበታለች፡፡ በ1981 ቪክቶሪያ ብለው የሚጠሯት ሴት ልጅ በሰላም ትገላገላለች፤የአባትዋ ስምም አባወራው ጀራልድ መሆኑ ተጠቅሶ በልደት ምስክር ወረቀትዋ ላይ ይመዘገባል፡፡ ነገር ግን ካሮል ሚካኤልን ቪክቶሪያ ያንተ ልጅ ናት ብላ ትነግረዋለች፡፡

ከእለታት አንድ ቀን ጀራልድ በሥራ ምክንያት ከመኖሪያ በታው ራቅ ወዳለ ስፍራ ለመሄድ ወስኖ ቢሄድም ካሮል ግን እዚያው ለመቆየት ወሰነች፡፡ ይህንኑ አጋጣሚ ተጠቅመው ወ/ሮ ካሮልና አቶ ሚካኤል የራሳቸውንና የህፃንዋን ደም አስመረመሩ፤ በውጤቱም ሚካኤል 98.07% የቪክቶሪያ አባት ሊሆን እንደሚችል ሳይንሳዊ ግምት ተሰጠ፡፡

ሚካኤል የቪክቶሪያ አባት መሆኑን በማረጋገጡ ወ/ሮ ካሮል ልጁን የመጎብኘት መብት እንድታመቻችለት መወትወቱን ተያያዘው፡፡ ካሮል ግን ይህ ሁኔታ ከህጋዊ ባልዋ ጋር ያላትን ግንኙነት እንደሚያበላሸው በመገመት ፈቃደኛ ሳትሆን ትቀራለች፡፡ ሚካኤል የቪክቶሪያ አባት መሆኑ እንዲታወቅለትና ልጁን የመጎብኘት መብት እንዲከበርለት በፍርድ ቤት ክስ መሰረተ፡፡ ካሮል ግን ቪክቶሪያ በጋብቻ ውስጥ የተወለደች ስለሆነች አባትዋ ባልየው ጀራልድ ነው በማለት ክሱን ተቃወመች፡፡

ጉዳዩ በእንጥልጥል ላይ እያለ ሚካኤልና ካሮል የድብቅ ግንኙነታቸው እንደገና ቀጠሉና ለስምንት ወራት ያህል አብረው ቆዩ፤ቪክቶሪያንም የሚካኤል ልጅ መሆንዋን ለወዳጅ ዘመድ ማስተዋወቅ ጀመሩ፡፡ ይባስ ብለውም በ1984 ሚካኤልና ካሮል የቪክቶሪያ ተፈጥሮአዊ አባት ሚካኤል መሆኑ ተፈራረሙ፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን የጀራልድና የካሮል ጋብቻ ጀራልድ በስራ ምክንት ራቅ ወዳለ የአሜሪካ ግዛት ከመሄዱ በስተቀር እንደፀና ነው፡፡ ከስምንት ወራት ተለያይቶ ቆይታ በኋላ ካሮል ከህጋዊ ባልዋ (ጀራልድ) ጋር አብራ መኖር ጀመረች፡፡

ሚካኤል ተደም ቢል የከፈተው የክስ ፋይል እንደገና እንዲንቀሳቀስና ፍርድ ቤቱ ፍትህ እንዲሰጠው አጥብቆ ተማፅኗል፡፡ ለጉዳዩ አግባብ ሆኖ የተገኘው የአሜሪካን አንድ ግዛት ህግ እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

" ... (t)he issue of a wife cohabiting with her husband who is not impotent or sterile, is conclusively presumed to be a child of the marriage. The presumption may be rebutted by blood tests, but only if a motion for such tests is made, within two years from the date of the child's birth either by the husband or, if the natural father has failed on affidavit acknowledging paternity by the wife."

ይህ ድንጋጌ በግርድፉ ወደ አማርኛ ሲተረጎም "ባልና ሚስት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ሁሉ ሚስት ልጅ የወለደች እንደሆነ ባለየው መሃን ወይም ስንፈተወሲብ ያለበት ካልሆነ በቀር ልጁ የጋብቻው ልጅ እንደሆነ ይገመታል፡፡ ይህ ግምት ሊሻር የሚችለውና የደም ምርመራ እንዲደረግ የሚታዘዘው ልጁ በተወለደ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ባለየው ምርመራ እንዲደረግ የጠየቀ እንደሆነ ወይም የተፈጥሮ አባቱ የልጁ አባት መሆኑ በቃለ መሃላ ከተቀበለና እናት የደም ምርመራ እንዲከናወን ስትጠይቅ ብቻ ነው" ይላል፡፡

ጉዳዩን ሲመረምር የነበረው ፍርድ ቤት በውሳኔው ሲያትት እንዲህ ብሎ ነበር፡፡ "ወ/ሮ ካሮልና አቶ ጀራልድ በልጂቱ መፀነስና መወለድ ጊዜ በባልና ሚስትነት አብረው ሲኖሩ እንደነበር ታምኗል፡፡ በዚህ ወቅት ጀራልድ መሃንነት ወይም ስንፈተወሲብ እንደነበረበት የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡

በመሆኑም ቪክቶሪያ የጀራልድ ልጅ እንደሆነች ይገመታል፡፡ ይህ ግምት ሊሻር ከተፈለገ ጀራልድ የደም ምርመራ እንዲደረግ መጠየቅ አለበት ወይም ሚካኤል የልጅቷን አባትነት በቃለ መሃላ ከተቀበለ በኋላ ወ/ሮ ካሮል የደም ምርመራ እንዲከናወን ከጠየቀች ብቻ ነው፡፡ አሁን በተያዘው ጉዳይ ግን ጀራልድ የደም ምርመራ እንዲደረግ አልጠየቀም በርግጥ ሚካኤል የልጅቷን አባትነት በቃለ መሃላ የተቀበለ ቢሆንም ካሮል የደም ምርመራ እንዲደረግ አልጠየቀችም፡፡ በዚህ ሁኔታ የህጉ ግምት የሚሻርበት የህግ መሠረት ስለሌለ ቪክቶሪያ የጀራልድ የህግ ልጅ ናት" በሚል የድምፅ ብልጫ በመወሰን የሚካኤልን ጥያቄ ውድቅ አደረገው፡፡ ስለዚህ በአንዳንድ አገሮችም ቢሆን ልክ እንደኛው ሃገር በህግ ግምት አባት የሚባል ሰው ራሱ የመካድ ክስ (የደም ምርመራ ጥያቄ) ካላቀረበ በቀር ሌላ ሰው አባትነቱን ሊንጥቀው አይችልም የሚባልበት ሁኔታ አለ[25]፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ግን በህግ ግምት አባት ነህ የተባለ ሰው የሞተ ወይም ችሎታውን ያጣ እንደሆነ በእርሱ እግር ተተክተው የመካድ ክስ ማቅረብ የሚፈቀድላቸው እነማን እንደሆኑ በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 177 ተመልክተው እናገኛለን፡፡

ከዚህ በላይ የመካድ ክስ ማቅረብ የሚገባው ማን ነው ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመሻት ሞክረናል፡፡ ቀጥለን ደግሞ ክሱ የሚቀርበው በማን ላይ ነው ወይም በሌላ አነጋገር ተከሳሽ መሆን ያለበት ማን ነው የሚለውን እናያለን፡፡

በብዙ የቤተሰብ ጉዳዮች ክስ ሲቀርብ ሚስትነቱ ይታወቅልኝ፣ሞግዚትነቱ (አሳዳሪነቱ) ይታወቅልኝ፣ ወራሽነቱ

[25] በርግጥ በሌሎች ሃገሮች ለምሳሌ በፖላንድ የቤተሰብ ህግ የመካድ ክስ በህግ አባትነህ ከተባለው ሰው በተጨማሪ የልጁ እናት፣ የተወለደው ልጅ ወይም ዐቃቤ ህግ ማቅረብ እንደሚችሉ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ (Lasok, Polish Family Law, ገጽ 148 ይመለከቷል)

ይረጋገጥልኝ ወዘተ እየተባለ መልስ ሰጪ (ተከሳሽ) በፋይል ውስጥ ማካተት ሳያስፈልግ የሚረጋገጫ ፍርድ (declaratory judgment) የሚጠየቅበት ፍትሐብሄራዊ ሥርዓት እንዳለ ይታወቃል፡፡ የመካድ ክስ ግን እንዲሁ አባት አለመሆኔ ይረጋገጥልኝ (ይታወቅልኝ) በሚል የሚቀርብ ክስ አይደለም፡፡ ሥርዓቱ ተከሳሽ ቀርቦ መልስ የሚሰጥበትና መደበኛ ክርክር የሚካሄድበት ነው፡፡ ተከሳሽ ሆነው እንዲቀርቡ የሚጠበቁትም ህፃኑና እናቱ ናቸው፡፡ ይህም በህጉ አንቀጽ 179 በመመልከት መገንዘብ ይቻላል፡፡

3.4.2. የመካድ ክስ መቼ ይቀርባል?

ሌላው በዚህ ርእስ ዙሪያ መወሳት ያለበት ጉዳይ ክስ መቅረብ ያለበትን የጊዜ ገደብ ነው፡፡ አሁን ባለን ህግ መሠረት የመካድ ክስ መቅረብ ያለበት "... የልጁ መወለድ ከታወቀበት ወይም መታወቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ በ180 ቀናት ውስጥ ነው"[26]፡፡ በመሆኑም የመካድ ክስ መቅረብ ካለበት በተቻለ ፍጥነት መቅረብ እንዳለበት መገንዘብ ይገባል፡፡ በአባትየው እግር ተተክተው የመካድ ክስ ማቅረብ የሚፈቀድላቸው ወገኖችም ቢሆኑ ይህ የጊዜ ገደብ ይፀናባቸዋል፡፡ ይህም ህፃኑ የአባቱ ማንነት የማወቅ መብቱ ላልተወሰነ ጊዜ በእንጥልጥል መቆየቱ ተገቢም ፍትሃዊም ስለማይሆን ነው፡፡

በቀድሞው የፍትሐብሄር ህግ መሰረት የመካድ ክስ መቅረብ የነበረበት "... ልጁ ከተወለደ በኋላ በሚከተሉት 180 ቀኖች ውስጥ[27]..." እንደሆነ መደንገጉ ይታወሳል ቢሆንም የጊዜ ገደቡ መቆጠር መጀመር ያለበት ከልጁ መወለድ ሳይሆን ከሳሽ የልጁ መወለድ ካወቀበት ወይም ማወቅ ከሚገባው ጊዜ ጀምሮ

[26] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 176(1)
[27] የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 792(1)

እንዲቆጠር ማድረጉ ከከሳሽ አንፃር አግባብነት እንዳለው በመታመኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ይህንኑ ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡

በመጨረሻ ከዚሁ ጋር መወሳት ያለበት ጉዳይ በህጉ የተቀመጠው የ180 ቀናት የጊዜ ገደብ የይርጋ ጉዳይ (መከላከያ) ነው? ወይስ የህግ ገደብ (ክልከላ) የሚል ነው፡፡ በዚህ ረገድ አንዱ ወይም ሌላኛው አቋም መያዙ የተለያየ የህግ ውጤት ይኖረዋል፡፡

የ180 ቀናት ጊዜ ገደቡ ይርጋ ነው የሚባል ከሆነ መከላከያ ነው ማለት ነው፡፡ ይህም ሲባል የመካድ ክሱ የቀረበው የ180 ቀናት ካለፈ በኋላ ቢሆንም ተከሳሹ በመጀመሪያ ክስ መልስ ማቅረቢያው ቀን ክሱ በይርጋ ይታገዳል ብሎ ካላቀረበ ክሱ ይቀጥላል ማለት ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ክሱ ጊዜ አልፎበታል በማለት ፋይሉን የመዝጋት መብት የለውም[28] ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል ግን የ180 ቀናት የህግ ገደብ ነው የሚባል ከሆነ ክልከላ ነው ማለት ነው፡፡ ይህም ሲባል የመካድ ክሱ የተጠቀሰው የ180 ቀናት የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ከቀረበ ወይም ተከሳሹ ክሱ በህግ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አልቀረበም ብሎ ክሱን ሊቃወም ይችላል ካልሆነም ተከሳሹ ይህንኑ

[28] በፍትሐብሄሩ ህጉ በቁጥር 1856(2) ስር የይርጋ ጉዳይ ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት ሊያነሳው እንደማይችል ተመልክቷል፡፡ በርግጥ ይህ ድንጋጌ በውል ህግ ሥር ያለ ስለሆነ አግባብነቱ ለውል ጉዳዮች ብቻ ነው ሊባል ይችል ይሆናል፡፡ ሆኖም በፍትሐብሄሩ ህግ ቁጥር 1677 ሥር "ግዴታዎቹ ከውል የተገኙ ባይሆኑም የውሉ ድንጋጌ ደንቦች ይፈጸሙባቸዋል" ስለተባለ አንቀጽ 1856(2) ደግሞ ከውል ህግ ደንቦች አንዱ ስለሆነ ከውል ውጪ ላሉት ጉዳዮችም አግባብነት ያለው በመሆኑ አሁን ለያዝነው ነጥብም ተገቢነት አለው፡፡

Scanned by CamScanner

ባያቀርብም ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ክሱ በህጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ አልቀረበም በሚል ፋይሉን ሊዘጋው ይችላል ማለት ነው፡፡

ይህንን ጭብጥ ለመፍታት የድንጋጌውን አቀራረጽ በጥንቃቄ መመርመር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ህግ አውጪው የሚጠቀምባቸው ቃላት በአግባቡ የተመረጡ ናቸው ከሚል መደምደሚያ መነሳት ያለብን ይመስለናል፡፡ በዚህ ረገድ ህግ አውጪው አንዳንዴ "...በዚህ ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ክሱ በይርጋ ይታገዳል" የሚል ወይም ተመሳሳይ አገላለጽ ይጠቀማል በሌላ ጊዜ ደግሞ "...ክሱ በዚህ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት" የሚል ወይም ተመሳሳይ አገላለጽ ይወስዳል፡፡ በመሆኑም ለእነዚህ የተለያዩ የህግ አውጪው አገላለጾች የተለያየ ውጤት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የይርጋ ጉዳይ በተጠቀሰበት ድንጋጌ ጉዳዩ ከይርጋ ህግ አንጻር መታየት ሲኖርበት፣ ህጉ በአስገዳጅ አገላለጽ (mandatory) በተጠቀመበት ሁኔታ ግን የጊዜ ገደቡ ካለፈ በኋላ የሚቀርበው ክስ ክሱ ተቃውሞ ቢቀርብበትም ባይቀርብበትም ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡

ከዚህ አንፃር ያሁኑ ድንጋጌ ሲታይ የእኔ ልጅ አይደለም የሚል የመካድ ክስ የልጁን መወለድ ካወቀበት ወይም ማወቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ <u>በ180 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት</u>፡፡ (ሠረዝ የተጨመረ) በሚል ኃይለቃል የተገለፀ ስለሆነ ከይርጋ ጉዳይ ጋር ተያይዞ ሳይሆን በአስገዳጅ ድንጋጌነቱ መታየት እንዳለበት ይሰማናል፡፡ ይህ ዓይነት አተረጓጎም ቀደም ሲል እላይ ከተገለፀው የህፃኑ አባቱን የማወቅ መብቱ ላልተወሰነ ጊዜ በእንጥልጥል ማቆየት ፍትሐዊ አይደለም ከሚለው መነሻችን ጋርም የተጣጣመ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡

እርግጥ ነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 17361 በሰጠው ውሳኔ "በፍትሐብሄር ሥነ-ስርዓት ህግ የተቀመጡት የጊዜ ገደቦች በተከራካሪ ወገኖች ባይቀርቡም ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን የሚያነሳቸው ሲሆኑ በፍትሐብሄር ህግ ውስጥ የተቀመጡት የጊዜ ገደቦች ግን በተከራካሪ ወገኖች በኩል በመከላከያነት ካልተነሱ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት የሚያነሳቸው አይደሉም" የሚል አቋም ይዟል፡፡ በእኔ እምነት ግን በፍትሐብሄር ህግ ውስጥ የተቀመጡት የጊዜ ገደቦችም ቢሆኑ በሁለት ተከፍለው እንደአቀማመጣቸው እየታየ መወሰን ያለበት ይመስለኛል፡፡ ይህም ማለት በድንጋጌው ውስጥ "በዚህ ጊዜ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል" ወይም "በይርጋ ቀሪ ይሆናል" ከተባለ በተከራካሪ ወገኖች ካልቀረበ ፍርድ ቤቱ በራሱ የሚያነሳው አይደለም፡፡ ነገር ግን "በዚህ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት" በሚል አስገዳጅ ድንጋጌ መልክ ከተቀመጠ ግን በተከራካሪ ወገኖች ባይነሳም ፍርድ ቤቱ በራሱ ማንሣት የሚገባው ነው ብዩ እምናለሁ፡፡ ምክንያቱም ህግ አውጪው የተለያየ አገላለጽ ሲጠቀም የተለያየ ውጤት እንዲኖር አስቦ ነው ተብሎ ሊወሰድ ይገባል ባይ ነኝ፡፡

<u>ክፍል አራት፡- ልጅነትን ስለመቀበል</u>

<u>4.1. አጠቃላይ የመነሻ ሃሳብ</u>

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው በጋብቻ ውስጥ ወይም ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩ ጥንዶች ውስጥ ልጅ ከተወለደ ወይም ከተፀነሰ አባቱ ማን እንደሆነ በህግ በኩል ያለውን ግምት ተመልክተናል፡፡ ሆኖም ልጆች የሚወለዱት ከእንዲህ ዓይነቶች ውሱን ግንኙነቶች ብቻ አይደለም ፡፡ እንዲያውም ጋብቻ ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም

Scanned by CamScanner

እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ሳይኖር ብዙ ልጆች ይወነሳሉ፣ ይወለዳሉ ፣ ያድጋሉ፡፡

ነገር ግን ከእንዲህ ዓይነት ሁኔታ የሚወለዱ ልጆች ከላይ በተመለከተው የህግ ግምት ተጠቃሚ ሊሆኑ ስለማይችሉ አባታቸው እንዴት ይታወቃል? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡

በሀገሩ አግባብ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ የተወለዱ ልጆችም አባቶቻቸውን የማወቅና የእነርሱን እንክብካቤ የማግኘት እንዲሁም በጋብቻ ከተወለዱ ህፃናት ጋር እኩል መብት እንዲኖራቸው ህገ-መንግስታዊ መብት ስላላቸው[29] በዚህ ረገድ ህጉ ድጋፍ ሊሰጣቸው እንደሚገባ በማመን በብዙ ሃገራት አባት ልጁን ስለሚቀበልበት ሥርዓት (recognition or acknowledgement of paternity) የሚባል ህጋዊ ሥርዓት ተበጅቶ እናገኛለን፡፡ በኛም ሃገር ከ1952ቱ የፍትሐብሄር ህግ ጀምሮ የቤተሰብ ህግ ስርዓታችን አካል ሆኖ ቆይቷል፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ህጋችንም "አባትነት ማወቅ" በሚል በቀድሞው የፍትሐብሔር ህግ ተቀርጾ የነበረው ፅንሰ ሃሳብ "ልጅነትን መቀበል" በሚል ተስተካክሎና መጠነኛ የይዘት ለውጦች ታክለውበት እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ (የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 131-142)

በመሠረቱ ልጅነት የመቀበል ጉዳይ በህግ ግምት አባትነት ከሚታወቅበት ሥርዓት ጋር ተገናዝቦ መታየት ያለበት ነገር ነው፡፡በህግ ግምት አባትነት ስለሚታወቅበት ሁኔታ ከዚህ በላይ በዝርዝር የተመለከትነው ስለሆነ እዚህ መድገሙ ተገቢ

[29] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 36(4)

አይሆንም፡፡ እንደሚታወሰው ይህ የህግ ግምት አግባብነት የሚኖረው በህግ በታወቀ ግንኙነት ላይ ባሉ ጥንዶች ነው፡፡ በዚህ የህግ ግምት ለማይሸፈኑ ተወላጆች ከተቀመጠላቸው የአባትነት ማሳወቂያ ሥርዓት አንዱና ቀዳሚው "ልጅነትን በመቀበል" በኩል ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ሥርዓት ተፈጻሚ የሚሆነው በህግ ግምት አባትነት የሚታወቅበት ሥርዓት ተፈጻሚ የማይሆን ሲሆን ወይም በህግ ግምት አባት ነው የተባለው ሰው በመካድ ክስ አባትነቱን ያስወገደ እንደሆነ ነው፡፡ በመሆኑም ልጅነትን የመቀበል ሥርዓት ከዚህ አንፃር ሲታይ ሁለተኛ ደረጃ አማራጭ ነው ሊባል ይቻላል፡፡ ምክንያቱም አንደኛ ደረጃው አማራጭ (የህግ ግምት አባትነት) ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ ወደ ሁለተኛው አማራጭ መሄድ ስለማይቻል ነው፡፡

በህግ ግምት አባትነት የሚታወቅበት ሥርዓት ስሙ እንደሚያመለክተው አባት ነህ የተባለው ሰው ቢወድም ቢጠላም በህግ ሚና አባት ነህ ተብሎ የሚታወቅበት ሲሆን ልጅነት የመቀበል ጉዳይ ግን አባት ነኝ ባዩ በሙሉ ፈቃዱና ፍላጎቱ "ይህ ልጅ የኔ ልጅ ነው" ብሎ የሚቀበልበት ሥርዓት ነው፡፡ ይህ ልዩነት እንዳለ ሆኖ ግን አባትነቱ በህግም ተሰጠ በፍላጎት በውጤታቸው ላይ ምንም ልዩነት አይኖርም፤ ማለትም በአባትየው የአባትነት መብትም ሆነ ሃላፊነት ላይ እንዲሁም በልጁ መብት ላይ አባትነቱ የተረጋገጠበትን ሥርዓት ላይ ተመስርቶ የሚፈጠር ልዩነት የለም፡፡

በርግጥ በአንዳንድ ሃገሮች በህግ ግምት አባት የተመደበለት ልጅ በልጅነት መቀበል በኩል አባት ካገኘ ሰው ይልቅ ሰፋ ያለ መብት ሲኖረው ይስተዋላል፡፡ ለምሳሌ በውርስ ጉዳይ በህግ ግምት አባት የተመደበለት ልጅ አባቱን ያለኑዛዜም ቢሆን መውረስ ሲችል በልጅነት መቀበል ሥርዓት አባቱ

Scanned by CamScanner

የታወቀ ልጅ ግን አባቱ በኑዛዜ ወራሽነቱን ካልጠበቀለት በቀር ያለ ኑዛዜ የአባቱ ወራሽ ሊሆን አይችልም የሚሉ ሃገራት አሉ፡፡ በኛ ሃገር ግን በድሮው የፍትሐብሄር ህጋችንም ሆነ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ እንዲህ ብሎ ነገር የለም፡፡ አባትነቱ በየትኛውም ሥርዓት የተረጋገጠ ቢሆን እኩል መብት አላቸው፡፡ ለነገሩ በፌዴራል ህገ-መንግስታችንም ቢሆን ከጋብቻ ውጪ የተወለዱ ህፃናት በጋብቻ ከተወለዱ ህፃናት ጋር እኩል መብት አላቸው[30] በሚል ተደንግጎ እናገኘዋለን፡፡

4.2. ልጅነት የመቀበል ሥርዓት

4.2.1. በአባት በኩል

ልጅነት የመቀበል ሥርዓት እንዲሁ ተቀብያለሁ ስለተባለ ብቻ የሚጠናቀቅ አይደለም፡፡ የአባትነት ሃላፊነት በቀላሉ የማይታይና አንዴ ከተሰጠም እንዳይሻር ሆኖ የተቀረጸ ስለሆነ በአግባቡ ታስቦበት የተሰጠ ፈቃድ እንዲሆን ይፈለጋል፡፡ ስለሆነም ልጅነት የመቀበል ሥርዓት ህጋዊ ውጤት እንዲኖረው ከተፈለገ በጽሁፍ እንዲደረግ ህጉ ያስገድዳል፡፡ ጽሁፍ ሲባልም እንዲሁ ግላዊ የጽሁፍ ሰነድ (private document) ሳይሆን መንግስታዊ ሰነድ (public document) መሆን ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም በክብር መዝገብ ሹም ፊት ወይም በሌላ ለዚሁ ዓላማ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት በመቅረብ የሚሰጥ ልጅነት የመቀበል ፈቃድ ሲሰጥ ብቻ ተፈላጊው ህጋዊ ውጤት እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ በርግጥ ከእነዚህ መንግስታዊ ሰነዶች ውጪ በኑዛዜም ልጅነትን መቀበል እንደሚቻል በህጉ ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ ይህም ቢሆን ግን ሁሉም ዓይነት ኑዛዜ ሳይሆን በጽሁፍ በሚደረግ ኑዛዜ ላይ ብቻ የተገደበ ነው፡፡

[30] ዝኒ ከማሁ

በሥራ ላይ ባለው የውርስ ህጋችን መሠረት በጽሁፍ የሚደረጉት ኑዛዜዎች ሁለት ዓይነት ሲሆኑ እነዚህም በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜና በተናዛዥ ጽሁፍ የሚደረግ ኑዛዜ ተብለው ተመድበዋል፡፡ ስለሆነም ልጅነት የመቀበሉ ሥርዓት በኑዛዜ በኩል ሲፈጸም ህጋዊነቱን ለመመርመር አግባብ ካላቸው የውርስ ህጉ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ ማየት ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ኑዛዜው በህግ ፊት የማይጸና ሆኖ ከተገኘ እንደልጅነት መቀበያ ሰነድም ማገልገሉ አጠያያቂ ስለሚሆን ነው[31]፡፡

እንደሚታወቀው በፍትሐብሄር ህጋችን መሠረት ልጅነትን መቀበል በጽሁፍ ካልሆነ ምንም ውጤት አይኖረውም በሚል ተደንግጎ ነበር፡፡ ሆኖም ይህ የሚሰጠው ቃል አባትነትን ማወቅ የሚያስከትለው ውጤት እንዲኖረው ሲባል የተደረገ ለመሆኑ አስፈላጊ አይደለም[32] የሚል ድንጋጌ አብሮ ስለተቀመጠበት ፍርድቤቶቻችን የእለት ተእለት ጉዳዮች ውስጥ በጡረታ ቅጽ፣ በቀበሌ ቅጽ፣ በእድር ቅጽ፣ በትምህርት ቤት መመዝገቢያ ቅጽ፣ ወዘተ ልጄ ነው ብለው ያስመዘገብዋቸው ልጆች አባትነትን ተቀብለዋል ይባልልን እየተባለ አቤቱታ ሲቀርብ እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡

በዚህ ወኅኛነትም አንዳንድ ፍርድቤቶች የጡረታ ቅጽ ወይም የቀበሌ ቅጽና የመሳሰሉትን መሠረት በማድረግ በምን ሁኔታና ምክንያት እንደተጻፉ የሚያስረዱ ምስክሮች አቅርበው በማስመስከር አንድ ወንድ የአንድ ልጅ አባት ነው ምክንያቱም በዚህ የጽሁፍ ሰነድ ልጅነቱን ተቀብሎታል የሚል ውሳኔ ሲያስተላልፉ ቆይተዋል፡፡

[31] የፍትሐብሄር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 936/80 (የምርጥ ፍርዶች ሁለተኛ መጽሐፍ ገጽ 362-364) በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ህግ ፋክልቲ የተጠረዘ

[32] የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 747

Scanned by CamScanner

ፍርድቤቶቻችን እንደማሳመኛነት ያቀርቡዋቸው ከነበሩት ምክንያቶች አንዱም "የልጁ አባት እኔ ነኝ የሚል ጽሁፍ በማስረጃነት መቅረብ አለበት ሲባል መተኮር ያለበት በጽሁፉ ይዘት ላይ እንጂ በቅርፁ ላይ ብቻ መሆን የለበትም። ይህን ስንልም አባትየው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አገላለጽ አባትነቱን በማወቅ ጽፎ ከተገኘ የጽሁፉ ማስረጃ ህጋዊ ውጤት ሊሰጠው ይገባል ማለታችን ነው ይሉ ነበር"[33]።

ከዚህ ጋር በተዛመደ በአንድ ወቅት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፓናል ችሎት የቀረበ ጉዳይ የሚከተለውን ይመስላል። ጉዳዩ አንድ ወንድና አንዲት ሴት በህግ የታወቀ ግንኙነት ሳይኖራቸው ከአብራካቸው አንዲት ህፃን ተወለደች ተባለ። ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ወንድየው ከዚህ ዓለም በሞት ተለየና ሴትየዋ ህፃንዋን በህይወት ዘመኑ የተቀበላት መሆኑን ይታወቅልኝ የሚል ክስ አቀረበች። የሟች ወላጆች ጥያቄውን ተቃወሙ። ሴትየዋ ሟች በህይወት ዘመኑ ክርስትና ማስነሳቱን፣ በክርስትና ምስክር ወረቀቱ ላይ አባት በሚለው ሥር ስሙ መጠቀሱን፣ የሟች ታናሽ እህት የህፃንዋ የክርስትና እናት በመሆን በክርስትናው እለት መገኘትዋን አስመሰከረች። እነዚህ ፍሬ ነገሮች ለልጅነት መቀበል በቂ መሆናቸው በማረጋገጥ ፓናል ችሎቱ እንዲህ ብሎ ነበር። "የልጅነት ማወቅ ማስረጃ ምንም ብናጠብቀው ይህን ዓይነቱን ማስረጃ ላለመቀበል ያስቸግራል። ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ጽሁፍ አካል ማስረጃ ብለን የምንወስደው ይህን መሰሉን ማስረጃ ነው። በእነኝህ ሁሉ ምክንያቶች እገሊት የተባለችው ከወይዘሮ

[33] የጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍ/ይ/መ/ቁ. 1808/79
[34] የጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍ/ይ/መ/ቁ. 1808/79
የጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 683/76 (አንስተኛው ድምፅ ይህን ለቀቅ ያለ አተረጓጎም አልተቀበለውም።)

እገሊት የተወለደችው ልጅ አባቷ አቶ እገሌ አባትነቱን ያወቀላት ልጅ ናት ብለን በድምጽ ብልጫ ወስነናል"[34] ብሏል።

እንዲህ ያለ ለቀቅ ያለ የህግ አተረጓጎም በዳኞች አካባቢ በውሳኔዎች ላይ የተለየ ሃሳብ (dissenting opinion) በማስመዝገብ እንዳልተቀበሉት ለማሳየት የሞከሩ ሲሆን በሌሎች የህግ ባለሙያዎች አካባቢም ይህ ለቀቅ ያለ አተረጓጎም ወደ ቅድመ ፍትሐብሄር ህጉ ዘመን እንዳይመልሰን ያሰጋል በማለት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሥጋታቸውን ሲገልጹ ይደመጡ ነበር።

እንደሚታወቀው በቅድመ ፍትሐብሄር ህግ በነበረው ባህላዊ ህግ መሠረት በህግ የታወቀ ግንኙነት ሳይኖር ልጅ ከተወለደ እናት በመሃላ ሥር ሆና የልጁ አባት እገሌ ነው ብላ ካረጋገጥች አባት ነው የተባለው ሰው አባትነቱ እንዲቀበል የሚያስገድድ ነበር[35]።

የቤተሰብ ህጉን ለማሻሻል ሲታሰብ እነዚህ ዓይነቶቹን ስጋቶች ግምት ውስጥ ለማስገባት ጥረት ተደርጓል። ለቀቅ ያለው የህጉ አተረጓጎም ልጅ ያለአባት እንዳይቀር በማድረግ ረገድ ጠቀሜታው የጎላ ቢሆንም ልጅነትን ለመቀበል ሃሳቡ ያልነበራቸውና አባት ሊሆኑ የማይችሉ ሰዎችን የአባትነት ግዴታ እንዲሸከሙ የሚያደርግ ዕድሉ ሰፊ እንደሆነ ግን ይታመናል።

[34] የጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 683/76 (አንስተኛው ድምፅ ይህን ለቀቅ ያለ አተረጓጎም አልተቀበለውም።)
[35] በ1111ኛ የኢትዮጵያ የጥንት ፍርዶች መዝገብ ቁጥር 77/83 ሥር "ኪታብም ውጪ ሆና ዲቃላ የወለደች ሴት አባቱ ነው ከምትለው ሰው ጋር ግንኙነት ያላት መሆኑ ሲታወቅ በቁስ ተገዝታ ለዚያው ለወለደችለት ሰው መስጠት ይገባታል" የሚል ነበር።

በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ሁለቱም ስጋቶች (ማለትም ልጅ ያለአባት እንዳይቀር በአንድ በኩል ሰዎች በተጨበጠውና ባልተጨበጠው ጉዳይ አባት ነህ በሚል እንዳይጉላሉ በሌላ በኩል) ተገቢ ዋጋ ተሰጥቶአቸዋል[36]:: ምናልባትም ጠበቅ ብሎ በተቀረጸው የልጅነት መቀበል ሥርዓት ተጠቃሚ የማይሆኑና መብታቸው ይጣበባል ተብለው የሚታሰቡ ህፃናት ቢኖሩ አባትነት በፍርድ ውሳኔ በሚታወቅበት ሥርዓት ሥር ተጠቃሚ ይሆኑ ዘንድ አባትነት በፍርድ ውሳኔ የሚታወቅባቸው ነጥቦች ከፍትሐብሄሩ ዘመን ከነበረበት ይልቅ ሰፋ ብለው እንዲቀረጹ ተደርገዋል:: (ይህንን ወደ ኋላ የምናየው ይሆናል)

4.2.2. በእናት በኩል

ወንድየው ልጄ ነው ብሎ ህጉ በሚጠይቀው የጽሁፍ ሰነድ ማረጋገጥ ልጅነትን ለመቀበል አስፈላጊ ቢሆንም ይህ በራሱ ግን በቂ አይደለም:: የልጁ እናት የተቀባዩን አባትነት እውነትነት ያለው መሆኑን ካላመነች በህግ ፊት ውጤት አይኖረውም[37]:: እንዲህ ዓይነት ድንጋጌ በማስቀመጥ ህጉ ከልጁ እናት ጋር ምንም ዓይነት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያልነበረው ሰው ልጅነትን ተቀብያለሁ በማለቱ ብቻ የአባትነት ሃላፊነትና መብት እንዳይሰጠው ለመከላከል ጥረት ያደርጋል::

[36] በመሆኑም በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ድንጋጌዎች መሠረት የልጅነት መቀበል ጉዳይ የፍትሐብሄር ህጉ ውስጥ ከነበረው አቀራረጽ ይልቅ ጠበቅ ያለ እንዲሆን ለማድረግ ተሞክሮአል::

[37] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 136(1) ለነገሩ በቅድመ ፍትሐብሄር የነበረን ልማዳዊ ህግም እናት አባትነቱን አምና ልትቀበለለት እንደሚገባ ተመልክቶ ነበር:: እንዲህም ይነበባል "ማንኛውም ሰው የተወለደውን ዲቃላ በጉባኤም ሆነ በክርክር ልጄ ነው ብሎ ለመውሰድ ቢፈልግ እናቱ ካላመነችለትና ካልፈቀደች ወይም ልጄ ነው ባይ በቂ ማስረጃ ካላቀረበ በጉባዔ ብቻ ልጅ ሊሆን አይገባም":: (የኢትዮጵያ ጥንታዊ ፍርዶች መዝገብ ገጽ 65)

ሆኖም ከህጉ አቀራረጽ መገንዘብ የሚቻለው የእናትየው የእምነት ቃል የአባትየውን የልጅነት የመቀበል ያህል በጠበቀ ሥነ-ስርዓት የታጠረ አይደለም:: ምክንያቱም በመጀመሪያ ደረጃ የእናትየው የእምነት ቃል በጽሁፍ እንዲሆን አይጠበቅበትም:: በሁለተኛ ደረጃ እንዲያውም አባት ልጁን መቀበሉን ካወቀችበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተቃውሞዋን ካላቀረበች ዝምታዋ አባትነቱን አምና እንደተቀበለች የሚያስቆጥርባት ነው[35]:: ከዚህ ላላ ያለ ሥነ-ስርዓት መረዳት የሚቻለው የእናትየው የእምነት ቃል የተፈለገው ወንድየው ከእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የነበረው ስለመሆኑ ለማረጋገጥ እድል ለመስጠት በመፈለግ ነው እንጂ ከዚህ ውጪ ልጅነት መቀበሉን ለማፅደቅ ወይም ለመሻር ሥልጣን እንዲኖራት ለማድረግ አይመስለንም:: በሌሎች ብዙ ሃገራትም ልምዱና አሠራሩ የሚያሳየን ይህንኑ ነው[39]::

4.2.3. በልጁ በኩል

ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ መወሳት ያለበት ነጥብ ልጅነት የመቀበሉ ጉዳይ የህግ የጊዜ ገደብ የሌለው ስለሆነ ልጁ አካለመጠን ከደረሰ በኋላም ቢሆን አባት ልጁን እቀበላለሁ ሊል ይችላል:: እንዲህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም የህጉ አቋም ምን ይመስላል? የሚለው ማየቱ ጠቃሚ ነው::

[38] ዝኒ ከማሁ 138

[39] Lasok Polish Family \law, p.155 የፖላንድ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአንድ ወቅት እንዲህ ብሎ ነበር

"In spite of these requirements that the mother should consent, recognition remains unilateral act of the father. The mother's consent cannot be regarded as in any sense contractual. It follows that the courts will not permit a bargain between the parties to be detrimental to the interests of the infant child, who is not a party to the transaction."

Scanned by CamScanner

በመሠረቱ በህጉ እምነት ልጁ አባት የሚያስፈልገው እንክብካቤና ክትትል በሚፈልግበት የህፃንነት ዘመኑ ነው፡፡ በህፃንነት ዘመኑ የአባቱና የእናቱ ማንነት፣ የእነርሱ ፍቅርና እንክብካቤ የሚፈልግበት ወቅት ነው፡፡ ይህ ሁሉ አልፎ ልጁ በአእምሮና በጉልበት ዳብሮ ራሱን መምራት ሲችል የሚመጣ አባት ነኝ ባይ በጥንቃቄ መታየት ይገባዋል፡፡ እውነት አባት ከሆነ ለምን እስከዚህ ጊዜ ድረስ ዝምታን መረጠ ያሰኛል፡፡ በመሆኑም እንዲህ ላለው ሁኔታ ህጉ የተለየ ሥርዓት አበጅቷል፡፡ ይኸውም ልጅነት መቀበሉ ህጋዊ ውጤት ይኖረው ዘንድ የልጁ እናት ብቻ ሳትሆን ልጁ ራሱ የሰውየውን አባትነት ሊቀበለው ይገባል[40]፡፡ በዚህ ረገድ የህጉ ሥጋት ልጁ አካለመጠን ከደረሰ በኋላ ልጅነቱን እቀበላለሁ ብሎ የሚቀርብ "አባት" ልጁን ለማሳደግና ለመንከባከብ በአጠቃላይም አባታዊ ግዴታውን ለመወጣት በማሰብ ሳይሆን ለራሱ ጥሪና ቀባሪ ከመፈለግ የመነጨ ይሆናል የሚል ይመስላል፡፡ ለዚህም ይመስላል በዚህ ሁኔታ ልጅነትን የመቀበሉ ጉዳይ ህጋዊ ውጤት ይኖረው ዘንድ የሦስትዮሽ (አባት፡እናትና ልጅ) ግንኙነትና ፈቃደኝነት እንዲሆን ያደረገው፡፡

በመጨረሻም ከልጅነት መቀበል ጋር መታየት ያለባቸው ነጥቦች አንደኛ የልጅነት መቀበል ጉዳይ ግላዊ (personal) በመሆኑ አባት ነኝ ባዩ አካለመጠን ያልደረሰ ቢሆንም መቀበል ያለበት ራሱ መሆኑን[41]፣ ሁለተኛ ልጅነት አንዴ ከተቀበሉት

[40] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 137
[41] በርግጥ በልዩ ውክልና ሥልጣን በወኪል መቀበል ይቻላል፡፡ እንዲሁም በአንቀጽ 135 በተመለከተው መሰረት የልጁ አባት የሞተ ወይም ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል በሆነ ጊዜ ከአባትየው ወላጆች አንዱ በእርሱ ስም ልጁን ሊቀበል እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ በአንድ ወቅት በዚህ ነጥብ ፍርድ ቤት የቀረበ ጉዳይ ነበር የሚከተለውን ይመስላል፡፡

መሻር የማይቻል መሆኑን[42]፣ ሦስተኛ አንድ ልጅ አንድ አባት ከተቀበለው ይህንኑ የተቀበለበት ሥርዓት ሳይሻር ሌላ ሰው ይህንኑ ልጅ ሊቀበል ህጉ እንደማይፈቅድ መገንዘብ ጠቃሚ ነው፡፡

እናት በህግ ከታወቀ ግንኙነት ውጪ የወለደቻቸውን ልጆች አባትነት እንዲታወቅላቸው አባት እንዲባል በተፈለገው ሰው ላይ ክስ ይመሰርታሉ፡፡ ሰውየውም ልጆቹ እንዳልሆኑ ክዶ ተከራከረ፡፡ በዚሁ ሳይሉ ከተዘጋ በኋላ አባት እንዲባል የተፈለገው ሰው በሞት ከተለየ በኋላ የአባትነት ይታወቅልኝ ጥያቄ የልጆቹ እናት እንደገና ለፍርድ ቤት አቀረቡ፡፡

የሰውየው እናትም የፍትሐብሄር ህጉን ቁጥር 750(1) (የአሁኑ ህግ አንቀጽ 135) መሠረት በማድረግ ልጆቹን እቀበላለሁ ብለው ቀረቡ፡፡ የዞን ፍርድ ቤትም አባት በህይወት በሌለ ጊዜ ወይም ፈቃዱን መግለጽ በማይችልበት ጊዜ አያት የልጅነቱን መቀበል ሊያከናውን እንደሚችል ስለሚደነግግ ልጆቹ የሟቹ ልጆች ናቸው ብለናል ማስረጃውም ለአመልካች ይሰጣት ብሎ ወሰነ፡፡

ይህንኑ ውሳኔ የሻረው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ "... የዐቻ (የሰውየው) እናት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 750(1) መሠረት በሟች እግር ተተክተው ልጆቹ የልጃቸው ልጆች መሆናቸውን አውቀዋል ለተባለው የፍ/ብ/ህ/ቁ. 750(1) የሚደነግገው ሟች ፈቃዱን ሳይሰጥ ከሞተ ወይም ፈቃዱን መስጠት በማይችልበት ሁኔታ ካለ በአባት በኩል ያለ ወንድ አያት ወይም ሴት አያት የማስታወቁን ሥራ ይፈጽማል ይላል፡፡ ይህ ድንጋጌ የሚያመለክተው አባትየው በህይወት እያለ ልጁን የተቀበለው ሆኖ ይህን መቀበሉ በጽሑፍ ሳይገለጽ በመቅረቱ ወይም ይህን ለመፈጸም ችሎታ በሌለው ጊዜ አባትየው በህይወት ቢኖር ኖሮ ወይም ፈቃዱን መስጠት ቢችል ኖሮ ልጁን ይቀበል ነበር ተብሎ በሚገመትበት ሁኔታ እሱን ተክተው ወላጆቹ ልጁን መቀበል እንደሚችሉ የሚደነግግ እንጂ አባትየው በህይወት እያለ ልጆቹ አይደሉም በማለት ክዶ በጽሑፍ የሰጠው ቃል የሚቃረን ከሱ ፈቃድ ውጪ በራሳቸው ሃሳብ መነሻነት ፈቃድ እንዲሰጡ የሚፈቅድ ህግ ባለመሆኑ... ሟች በህይወት እያለ ልጆቹ አይደሉም በማለት በፍርድ ቤት በጽሑፍ ገልጾ እያለ እና ልጅነት ማወቅ ደግሞ በእርሱ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ መሆን ሲገባው የዞን ፍርድ ቤት ሟች በህይወት እያለ ያልተቀባላቸው ልጆች የፍ/ብ/ህ/ቁ. 750(1) ትርጉም በማዛባት የሟች እናት የሰጡት ቃል በመቀበል የሰጠው ውሳኔ ሽረነዋል" የሚል ነበር፡፡ (የፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 1354/1641/88 ሠረዝ የተጨመረ)
[42] በኢትዮጵያ ጥንታዊ ፍርዶች መዝገብም ቁምር ዲቃላ የወለደችለት ሴት ለዳኛ አስታውቃ ለወለደላት ሰው ከሰጠች በሃላና የወለደላትም ሰው ልጁ ነው ብሎ ከተቀበለ በሃላ እንደገና ልጄ አይደለም ብሎ ሊክደው አይችልም የሚል ድንጋጌ ነበረን (የኢትዮጵያ ጥንታዊ ፍርዶች ገጽ 64)

ክፍል አምስት

በፍርድ ቤት ውሳኔ አባትነት እንዲታወቅ ስለማድረግ

5.1. አጠቃላይ የመነሻ ሃሳብ

ቀደም ባለው የመፅሐፉ ክፍል አባትነት በህግ ግምት ስለሚታወቅበት ሥርዓት፡ አባት ልጄን ልጄ ነው ብሎ ስለሚቀበልበት ሥርዓት በተመለከተ ያሉትን ህጋዊ መስፈርቶች ለማየት ሞክረናል፡፡ እነዚህም ሥርዓቶች በቅደም ተከተል እንጂ ጎን ለጎን እንደማይሄዱ አይተናል፡፡ ይህም ማለት በህግ ግምት አባት የተገኘለት ልጅ ሌላ ሰዉ መጥቶ ልጅነቱን እቀበላለሁ ማለት አይችልም ማለት ነው ምክንያቱም ህጉ ቀደም ብሎ አባት ሰጥቶታልና፡፡

በእርግጥ እነዚህ ሥርዓቶች በመከተል ብዙ ልጆች ህጋዊ አባት እንደሚኖራቸው ይታመናል፡፡ ሆኖም ሁሉም ልጆች በእነዚህ ሥርዓቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ ማለት አይደለም፡፡ በህግ ግምትም የማይሸፈኑ፣ አባት ነኝ ብሎ ልጄን በፈቃደኝነት የሚቀበል ሰውም ሳይኖር አንድ ልጅ ከአንድ እናትና አባት (የተፈጥሮ) ሊወለድ ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ህጉ ምን ሁኔታ አበጅቷል? የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡

በዚህ ረገድ ህጉ ሦስተኛና የመጨረሻ የሆነው አባትነት የሚታወቅበት ሥርዓት አደራጅቶ እናገኘዋለን፡፡ ይህም አባትነት በፍርድ ውሳኔ የሚታወቅበት ሥርዓት ተብሎ ይታወቃል፡፡ ይህ ሥርዓት ሦስተኛና የመጨረሻ አማራጭ ነው፡፡ ሦስተኛ የተባለበት ምክንያት ከዚህ በላይ አባትነት የሚታወቅባቸው ሁለት ሥርዓቶች ያብራራን ስለሆነ ይህ ሦስተኛ በመሆኑ ነው፡፡ የመጨረሻ አማራጭ ነው የተባለበት ምክንያት

ደግሞ ሁለቱም አማራጮች በቅደም ተከተል ተፈጻሚ ለማድረግ ተሞክሮ ውጤት ሳይገኝ ሲቀር የምንጠቀምበት የመጨረሻ ዕድል ስለሆነ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህን የመጨረሻ ዕድል ተጠቅመን አንድን ልጅ አባት ልናገኝለት ካልቻልን ህጋዊ አባት ሳይኖረው ይቀራል ማለትን ስለሚያስከትል በዚህም በኩል የመጨረሻ ነው ማለት ነው፡፡ ቀጥለን አባትነት በፍርድ ውሳኔ ሊታወቅ የሚችልባቸው ሁኔታዎች አንድ ባንድ ለማየት እንሞክራለን፡፡

5.2. የመደፈር ወይም የመጠለፍ ተግባር ሰለባ ስለመሆን

በቀድሞው የፍትሐብሄር ህግ መሠረት አባትነት በፍርድ ውሳኔ ለማረጋገጥ የሚቻለውና የሚፈቀደው "ልጁ በተፀነሰበት ወራት በእናቲቱ ላይ የመጠለፍ ወይም የመደፈር ሥራ ደርሶባት"[43] እንደሆነ ነው፡፡ የመጥለፍ ወይም የመድፈር ሥራ ደግሞ ኃይል፣ ዛቻ፣ ተንኮል ወይም ማታለል የታከለበት እርምጃ በመውሰድ ሴትየዋን ፈቃደኛ በማድረግ ወይም ለመቃወም በማትችልበት በማናቸውም ሁኔታ እንድትገኝ በማድረግ የግብረሥጋ ግንኙነት በመፈጸም ስለሆነ[44] የወንጀል ድርጊት ነው፡፡ ይህን መሰል የወንጀል ድርጊት ለመፈጸም ዝግጁና ፈቃደኛ የሆነ ሰው በዚህ ድርጊት መነሻነት የተፈጠረን ፅንስ ወይም ልጅ በፈቃዱ ይቀበላል ለማለት እጅጉ ይከብዳል፡፡ ለዚህም ይመስላል የፍርድቤት ጣልቃ ገብነት አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው፡፡ በመሆኑም በዚህ ሥር ተጠቃሚ ለመሆን በአንድ በኩል ከነዚህ የወንጀል ድርጊቶች አንዱ ወንድየው በሴትየዋ

[43] የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 758

[44] የወንጀል ህግ አንቀጽ 620 (አንዳንድ የሃገራችን ማህበረሰቦች ጠልፋ የጋብቻ ማስፈጸሚያ እንዱ መንገድ አድርገው ስለሚቆጥሩት ወደ ጋብቻ ካመራ አባቱ በህግ ግምት ይታወቃል ይህ ግን ሊበረታታ የሚገባው ባህል አይመስለንም)

Scanned by CamScanner

ላይ መፈጸሙን ማሳየት በሌላ በኩል ደግሞ ልጁ የተፀነሰው በዚያ ወቅት መሆኑን ማሳየት ይጠበቃል፡፡ የመጥለፍ ወይም የመድፈር ድርጊት ስለመፈጸሙ በፍሬ ነገሮች ማስረዳት የሚጠበቅ ሲሆን ልጁ መቼ ተፀነሰ ለሚለው ግን የህጉን ግምት በመጠቀም የማስረዳት ሸክሙን ማቃለል ይቻላል፡፡ ስለዚህ የመጥለፍ ወይም መድፈር ተግባር በሴትየዋ ላይ በተፈጸመ ከ181ኛው ቀን እስከ 300ኛው ባሉት ቀናት ልጁ ከተወለደ የተፀነሰው በጠለፋው ወይም በመድፈሩ ጊዜ ነው ብሎ ለማሳመን በቂ ነው ብለን እናስባለን፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አባትነት በፍርድ ውሳኔ የሚታወቅበት ሁኔታ ሰፋ ብሎ እንዲቀረጽ ተደርጓል፡፡ ይህም የፍትሐብሄር ህጉ ቁጥር 758 እና የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 143 በማነጻጸር ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ እንዲህ ማድረግ ያስፈለገበት ምክንያት በአንድ በኩል ህፃናት ወላጆቻቸውን የማወቅና ከወላጆቻቸው እንክብካቤ የማግኘት ህገ-መንግስታዊ መብታቸውን በተቻለ መጠን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ አባቶች ልጅነት በፈቃደኝነት የሚቀበሉበት ሥርዓት (acknowledgment of paternity) በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ውስጥ ጠበብ ብሎ የተቀረጸ ስለሆነ በቀድሞው ህግና በፍርድቤቶቻችን ለቀቅ ያለ አተረጓጎም ምክንያት በዚያ ሥር ሲሸፈኑ የነበሩ ጉዳዮች በአሁኑ የህጉ አቀራረጽ የማይሸፈኑ ስለሆነ በዚህ ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል በማሰብ ነው፡፡ ስለዚህ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አቀራረጽ በፍርድ ውሳኔ አባትነት የሚረጋገጥበት ሥርዓት ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ በእናቲቱ ላይ የመደፈር ወይም የመጠለፍ ተግባር የተፈጸመባት መሆኑ አንድ ምክንያት እንጂ ብቸኛው ምክንያት ግን አይደለም፡፡ በፍትሐብሄር ህጉ ውስጥ ግን ብቸኛው ምክንያት እርሱ ነበር፡፡

እዚህ ላይ ግን ወደሌሎች አባትነት በፍርድ ወደሚወሰንባቸው ምክንያቶች ከመሄዳችን በፊት መታየት ያለበት ነጥብ አለ፡፡ ይህም የመድፈርን ወይም የመጥለፍን ተግባር መሠረት በማድረግ በፍርድ ውሳኔ አባትነት ለማስወሰን ሲባል ጠላፊው ወይም ደፋሪውን በድርጊቱ በወንጀል ክስ ማስቀጣት ቅድመ ሁኔታ ነው ወይ? የሚል ነው፡፡

አንዳንድ ወገኖች መድፈርና መጥለፍ የወንጀል ድርጊቶች ስለሆኑ ድርጊቱ መፈጸሙ የሚረጋገጠው ደግሞ በወንጀል ችሎት ውሳኔ ስለሆነ ይህ ሳይከናወን አባትነት በፍርድ ውሳኔ ይታወቅልኝ ብሎ ጥያቄ ሊኖር አይችልም ምክንያቱም ሊቀርብ የሚገባው ማስረጃ የወንጀል ችሎቱ የፍርድ ውሳኔ መሆን አለበትና ነው[45] ይላሉ፡፡

እዚህ ላይ ግን ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባ ጉዳይ ያለ ይመስለኛል፡፡ ይኸውም የወንጀሉ ፋይል በጥፋተኛው ላይ የወንጀል ቅጣት የማሳረፍ ግብ ይዞ የሚከናወን ሥርዓት ሲሆን የፍትሐብሄሩ ፋይል ግን ጥፋተኛው ልጅ የወለደ ስለሆነ የአባትነት ሃላፊነት እንዲሸከም ይወሰንልኝ የሚል ዓላማ ይዞ የሚከናወን የክስ ሥርዓት ነው፡፡ ስለዚህ የሁለቱም ዓላማና ግብ የተለያየ ነው፡፡ በዚያው መጠንም ሁለቱም የሚጠይቁት የማስረጃ ክብደት በእጅጉ ይለያያል፡፡ በተለምዶ ለወንጀሉ ፋይል የሚጠየቀው ማስረጃ ድርጊቱ መፈጸሙ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ ውጪ የሚያረጋግጥ (beyond reasonable doubt) ማስረጃ ሲሆን ለፍትሐብሄሩ ጉዳይ ግን በማስረጃ ምዘና የትኛው ሚዛን ይደፋል (balance of probabilities) የሚለው መለኪያ በቂ ሆኖ ይገኛል፡፡ ስለዚህ በከባዱ የወንጀል ማስረጃ መመዘኛ በቂ አይደለም የተባለ ማስረጃ ቀለል ባለው ለፍትሐብሄሩ

[45] በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ከአንዳንድ የሥራ ባልደረቦቼ ጋር ያደረግኩት ውይይት እንዲህ ዓይነት አመለካከት እንዳለ ለመገንዘብ አስችሎኛል፡፡

ማስረጃ ፍላጎት በቂ ሊሆን ይችላል ማለት ነው:: ለዚህም ነው በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2149 ሥር "በፍትሐብሔር በኩል ጥፋት ተደርጓል ብሎ ለመወሰን በወንጀል ፍርድ ተከሳሹ ነፃ መለቀቁ ወይም በወንጀል ሊያስከስሰውም ተብሎ መበየኑ ዳኞቹን (የፍትሐብሔር ችሎት ዳኞች ማለት ነው) አያግዳቸውም" የተባለው:: በመሆኑም በኔ አስተያየት መደፈርን መጠለፍን መሠረት በማድረግ አባትነት በፍርድ ውሳኔ እንዲታወቅ የክስ ፋይል ሲከፈት የፍትሐብሔር ችሎት በፍትሐብሔር የማስረጃ ክብደት መስኪያ መሠረት የመድፈር ወይም የመጥለፍ ተግባር መከናወኑን ሊመዝን ይገባል እንጂ መድፈርና መጥለፍ የወንጀል ድርጊቶች ናቸው ስለተባለ ብቻ ከያዘው ፋይል ዓላማ ውጪ የሚያገለግል የወንጀል ማስረጃ መመዘኛ ሊገለገል አይገባም ባይ ነኝ::

5.3. በሥልጣን ያለአግባብ መጠቀም ወይም የተስፋ ቃል መስጠት

ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ብዙ ሴት እህቶቻችን ከአንዳንድ ወንዶች "አገባሻለሁ" የሚል የተስፋ ቃል በመስጠት ወይም ስልጣናቸውን አላግባብ በመጠቀምና በመሳሰሉት በማባበል ወይም በማታለል ከእነርሱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲፈጽሙ ካደረጉ በኋላ እርግዝና ሲከሰት ወይም ልጅ ሲወለድ አላውቅልሽም እያሉ ህፃናትን የማሳደጉ ሃላፊነት በእናትየው ጫንቃ ላይ ሲወድቅ ይታያል:: ሁላችንም እንደምናውቀው ደግሞ ብዙ እናቶች በኢትዮጵያ ሁኔታ ኢኮኖሚያዊ አቅማቸው እጅግ ደካማ ነው:: ስለሆነም ኑሮ እንደነገሩ ይገፋሉ ህፃናትም እንደነገሩ ያድጋሉ:: ይህ ሁኔታ ላይ ላዩን ሲታይ በእናቶች ላይ የወደቀ ሸክም ቢመስልም ዋናዎቹ ተጎጂዎች ግን ወደውና ፈቅደው ያልተወለዱት ህፃናት ናቸው:: ህጉ ይህንን ክፍተት ለመድፈን ካልቻለ (ቢያንስ

ለመድፈን ካልሞከረ) ቁጥራቸው የማይናቅ የነገ ሃገር ተረካቢ ዜጎች አስተዳደጋቸው ያልተሟላና የተዛባ ይሆናል:: በህፃንነት ዘመናቸው ወቅት ህጉ በቂ ጥበቃ ሲያደርግላቸው ስላላዩም በህጉ ሥርዓት ላይ ቂም ቋጥረው ማደጋቸው አይቀርም የማታ ማታም የጉልበት አቅማቸው ሲፈቅድ በህግ ሥርዓቱና በማህበረሰቡ ላይ በማመጽ የሥርዓት አልበኝነት ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ::

የቀድሞ የፍትሐብሔር ህግ አባትነት በፍርድ ውሳኔ የሚረጋገጥበት ሥርዓት ከጠለፋና ከመድፈር ጋር ብቻ ስላያያዘው ከጠለፋና ከመድፈር በመለስ ያሉ የማባበል የማታለል ተስፋ የመስጠትና መሰል የተለመዱ ድርጊቶች ከህጉ ሽፋን ወጥተው ቆይተዋል:: የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ግን አድማሱን በማስፋት ከጠለፋና መደፈር በተጨማሪ እነዚህ ድርጊቶችም አባትነት በፍርድ ውሳኔ ለማረጋገጥ በሚደረግ ጥረት የህግ መሠረቶች ሆነው እንዲካተቱ አድርጓል::በርግጥ ጠለፋ ወይም መድፈር ብቻውን አባትነት በፍርድ ውሳኔ ለማሳወቅ በቂ እንዳልሆነ ሁሉ የተስፋ ቃል መስጠት፣ ማባበል፣ ማታለል የመሳሰሉት ድርጊቶችም ብቻቸውን በቂ አይደሉም:: በእናትየውና አባት ነው እንዲባል በሚፈለገው ሰው መካከል የግብረ ሥጋ ግንኙነት መደረጉ መረጋገጥ ይኖርበታል[46]:: ይህ ብቻም አይደለም ልጁ የተወለደው ይህ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በተደረገ በ181ኛና እስከ 300ኛ ቀን ባለው ጊዜ መሆኑ ማሳየት ይጠይቃል::

[46] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 143(ለ)

Scanned by CamScanner

5.4. አባት ነው እንዲባል በተፈለገው ሰው የተጻፉ የግል ሰነዶች የሚኖራቸው ፋይዳ

ከዚህ በተጨማሪ አባትነት በፍርድ እንዲወሰን ለማስደረግ እንዲያስችል የተካተተው ነጥብ አባት ነው በተባለው ሰው "የተጻፉና በማያሻማ ሁኔታ አባትነቱን የሚያረጋግጡ ደብዳቤዎች ወይም ሌሎች ጽሁፎች ከተገኙ"[47] በፍርድ ውሳኔ አባት ነው ለማሰኘት እንደመነሻ ማስረጃ ማቅረብ የሚቻል መሆኑ ነው፡፡

በቀድሞው ህግ (በፍትሐብሄር ህግ ማለት ነው) አባት ነው እንዲባል የሚፈለገው ሰው ልጁን በስሙ ትምህርት ቤት አስመዝግቦታል፣ በልጁ የትምህርት ማስረጃ ላይ የወላጅ ፊርማ በሚለው ስር ፊርማውን አኑሯል፣ በልጁ የክርስትና ምስክር ወረቀት ላይ የአባት ስም በሚለው ስር የሰውየው ስም ተመዝግቧል፣ ሰውየው ለልጁ እናት በጻፈው የፍቅር ደብዳቤ ላይ የልጄ የእገሌን ጉዳይ አደራ፣ ልጄን እገሌን ሳሚልኝ፣ እያሉ የሚጽፏትን ነገር መሰረት በማድረግ ሰውየው የልጁን አባትነት ተቀብሎአል ይባልልኝ የሚሉ አቤቱታዎች በተደጋጋሚ ሲቀርቡ እንደነበር ይታወሳል፡፡ እነዚህን ማስረጃዎች መነሻ በማድረግና ተጨማሪ የቃልና የአካባቢ ማስረጃዎች በማከል ልጅነቱን ተቀብሎታል እየተባለ ሲወሰን እንደነበር አይተናል፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ግን እንዲህ ዓይነት ድርጊቶች የልጅነት መቀበል (acknowledgement of paternity) ጉዳዮች ሳይሆኑ አባትነት በፍርድ ውሳኔ የሚታወቅበት ሥርዓት (judicial declaration of paternity) ዘርፍ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ ግን እነዚህ የግል ሰነዶች (private documents) ለክስ መነሻ ይሆኑ እንደሆን እንጂ

[47] ዝኒ ከማሁ

ብቻቸውን የተፈለገውን ውጤት (አባትነት በፍርድ ውሳኔ ለማስወሰን) በቂ አይሆኑም፡፡ ጉዳዩ የአባትነት ጥያቄ ስለሆነ ሰውየው ከልጁ እናት ጋር የነበረው ግንኙነትም ምን ይመስል እንደነበር መመርመር ተገቢነቱ አያጠያይቅም፡፡ ምክንያቱም ዋናው ግብ የልጁ አባት ሰውየው ነው ብሎ የፍርድ መደምደሚያ ለመስጠት ነውና ነው፡፡

ሌላው በዚህ ክፍል ሥር እንዲሸፈን የተደረገው ነጥብ በህግ የታወቀ ግንኙነት ሳይኖራቸው እንዲሁ በእጮኛነት ወይም በተመሳሳይ ግንኙነት አንድ ወንድና አንዲት ሴት አብረው ሲገቡና ሲወጡ ልጅ ከተወለደ አባት እንዲኖረው የማስቻል ጉዳይ ነው፡፡ በርግጥ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ውስጥ መተጫጨት የህግ እውቅና እንዳልተሰጠውና እንዳልተካተተ ከነምክንያቱ በማብራሪያው በቅጽ አንድ ገልጸናል፡፡ ቢሆንም እውቅና ባይሰጠውም መተጫጨት የህግ ክልከላ የተደረገበት አይደለም፡፡ ስለዚህ ባህልን መሰረት በማድረግ የትውውት ሥርዓቱ መቀጠሉ አይቀርም፡፡ በዚሁ ግንኙነት መነሻነትም ጋብቻ ሳይፈፅሙ ወይም እንደባልና ሚስትም አብረው መኖር ሳይጀምሩ ከመካከላቸው ልጅ ሊወለድ ይችላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ደግሞ አባትነት በህግ ግምት የሚታወቅበት ሥርዓት ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም፡፡

በቀድሞ ህግ መሠረት እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲከሰት ልጁ አባት ሊያገኝ የሚችለው ልጅነትን በመቀበል ሥርዓት (acknowledgment of paternity) በኩል ብቻ ነበር፡፡ አባትየው ይህን ሥርዓት ተጠቅሞ ልጁን በፈቃዱ ካልተቀበለው ግን ልጁ የተፈጥሮ አባት እንዳለው የሚታመን ቢሆንም በህግ ረገድ ግን ግንኙነቱ ከእናቱ ጋር ብቻ ይሆን ነበር፡፡ ምክንያቱም በፍርድ ውሳኔ አባቱ እንዲይወሰን ሲትየዋ ተጠልፌ ወይም ተደፍሬ ነበር ብላ ማስረዳት ስለማትችል ነበር፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ

መሠረት ግን ከእንዲህ ዓይነት ግንኙነት የሚወለዱ ህፃናት በልጅነት መቀበል ሥርዓት በኩል አባታቸውን የማወቅ ዕድል እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ካልተሳካም በፍርድ ውሳኔ አባትነት በሚታወቅበት ሥርዓት በኩል አንድ ተጨማሪ ዕድል ተመቻችቶላቸዋል:: ይህ ነው እንግዲህ በተሻሻለው የቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 143(መ) ሥር ተደንግጎ የሚገኘው::

5.5. ልጁን እንደ አባት ሆኖ መንከባከብ የሚኖረው ህጋዊ ውጤት

በመጨረሻም በዚህ ክፍል ሥር እንዲገባ የተደረገው በህጉ አንቀጽ 143 (ሠ) ላይ የተመለከተው ሁኔታ ነው:: ይኸውም "አባት ነው የተባለው ሰው ልጁን በመንከባከብ ወይም በማስተማር ወይም በማሳደጉ ላይ እንደአባት በመሆን የተሳተፈ እንደሆነ" በፍርድ ውሳኔ አባትነህ የሚባልበት ሥርዓት የሚያመቻች ነው::

አንዳንዴ አንዳንድ ወንዶች ከልጁ እናት ጋር ያላቸው ግንኙነት ጤናማ እያለ የተወለደው ልጅ ልጃቸው መሆኑን በተግባር ተቀብለው ሲንከባከቡ ሲያስተምሩ ከቆዩ በኋላ ከእናትዬዋ ጋር የነበረው ግንኙነት በሆነ ምክንያት ሲሻክር ግን አላውቅልሽም የሚል መልስ ሲሰጡ ይደመጣል:: በዚህ ጊዜ የእናትዬዋና የልጁ የኑሮ ሁኔታ ምስቅልቅሉ ይወጣል:: አባት ነው የተባለው ሰው ልጅነቱን ተቀብሎታል እንዳይባል በተግባር ሲያከናውነው ከነበረው የማስተማርና የእንክብካቤ ድርጊት ውጪ ህጉ ለልጅነት መቀበል የሚጠይቀውን በጽሁፍ የተቀመጠ ሰነድ አይገኝም:: በህግ ግምት አባት ነው እንዳይባል ደግሞ በእናትየውና በሰውየው መካከል በህግ የታወቀ ግንኙነት እንደነበረ ማስረዳት አይቻልም:: ስለዚህ ልጁ አባት እንዲኖረው

ከተፈለገ (ሊኖረው ይገባል) ቀሪው የህጋዊ አባት ማስገኛ ዘዴ ይኸኛው ብቻ ነው::

በርግጥ ሁሉም ልጁን ተንከባክቦ ያስተማረ ሁሉ አባት ነህ ሊባል ነው ወይ? እንዲህ ከተባለ ሰዎች በጎ ነገር ከመሥራት ሊነሱ እንደሚችሉ አይችልም ወይ? የሚሉና ተዛማጅ ተገቢ ጥያቄዎች ይነሳሉ::

ሆኖም ህጉ በጥሞና ከታየ እንዲህ ዓይነት "ባንረስኩ እጄን ተነከስኩ" የሚያሰኝ ውጤት አያስከትልም:: ምክንያቱም አንደኛ በህግ ግምት አባት ያልተገኘለት ወይም የተካደ እንደሆነ ወይም ልጁን በአባትነት የተቀበለው ሰው የሌለ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ የአንቀጽ 143 መግቢያ በግልጽ ያመለክታል:: ይህም ማለት ልጁ በህግ ግምት መሠረት ወይም ልጅነት በመቀበል ሥርዓት መሠረት አባት ያለው ከሆነ እነዚህ ሥርዓቶች ሳይሻሩ በፍርድ ውሳኔ አባት ማግኘት አይችልም ማለት ነው:: ሁለተኛ ህጉ የማስተማር ወይም የመንከባከብ ድርጊት ብቻውን አባት ያሰኛል አይልም:: አባት ነው እንዲባልልኝ ብሎ ለመጠየቅ የመንከባከብ ወይም የማስተማር ድርጊቱ የተከናወነው እንደአባት በመሆን (ሠረዝ የተጨመረ) ሊሆን ይገባል:: በመሆኑም ልጁን በአጎትነት ወይም በክርስትና አባትነት ወይም በበጎ አድራጊነት ያስተማረ ወይም የተንከባከበ ሰው እንክብካቤውን ያደረገው በዚያው መሠረት እንጂ እንደአባት በመሆን እንዳልሆነ በማሳየት ክሱን ሊቃወም ይችላል ማለት ነው:: ሦስተኛ እንክብካቤው ሲያከናውን የነበረው ሰው እንደአባት በመሆን መሆኑን ለማሳየት ሰውየው ከልጁ እናት ጋር የነበረው ግንኙነት ልጅ ለመውለድ የሚያስችል ግንኙነት እንደነበረ ማሳየት ይጠይቃል:: ይህም ሩቅ ሳንሄድ አንቀጽ 143ን ከአንቀጽ 144 ጋር አብሮ በማንበብ የሚደረስበት ድምዳሜ ነው:: ስለዚህ ይህ ንዑስ አንቀጽ

Scanned by CamScanner

በቁንጽልና በተናጠል መታየት ያለበት ሳይሆን ከአጠቃላይ የህጉ ቅርጽና ይዘት በተለይም ከድንጋጌው በፊትና በኋላ የተቀመጡት የህግ አንቀጾች ጋር ተዛምዶ መሆን ስላለበትና ከዚህ አንጻር ከታየ ደግሞ ኢፍትሃዊ ውጤት ይኖረዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡

ከዚህ ጋር በተዛመደ በአንድ ወቅት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይህ ንዑስ አንቀጽ ተጠቅሶ አባትነቱ በፍርድ ውሳኔ እንዲታወቅ የቀረበን ጉዳይ ውድቅ ሲያደርግ እንደሚከተለው ብሎ ነበር፡፡

... *ምስክሮች (የከሳሽ) በተመሳሳይ ሁኔታ የተናገሩት አንድ ቃል ብቻ ነው፡፡ ይኸውም ሺመልስ የፌቃዱ ኅብለድንግል ልጅ ነው የሚል ነው፡፡ ለምን ይሆን ሊሉ እንደቻሉ ግን በርግጠኝነት ሊያስረዱ አልቻሉም፡፡ ልጅ ነው ለሚለው እምነታቸው እንደ ማረጋገጫ አድርገው ሊያቀርቡ የሞከሩት ትምህርት ቤት አስገብቶታል፤ በእጁ ይዞ እየተተተ ሲወስደው አይተናል፤ ልጅ ነው ብሎ ነግሮናል ወዘተ የሚሉ አነጋገሮች ብቻ ናቸው፡፡ የሰጡት የምስክርነት ቃል በአጠቃላይ ሲታይ እንዳቸውም ቢሆን በፌቃዱ ኅብለድንግልና የሺመልስ እናት ነች በተባለችው ወ/ሮ አበበች በሻህ መካከል ግንኙነት የነበረ ወይም ደግሞ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሊፈፅሙ ይችላሉ የሚል ግምት ሊያሳድር የሚችል ቅርበት እንኳን የነበራቸው መሆኑን ለማሳየት የሚችል የምስክርነት ቃል አልሰጡም*[43] ... ብሎ ነበር፡፡ (ሠረዝ የተጨመረ)

[43] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት (የፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 12046)

5.6. ማጠቃለያ

በመጨረሻም ይህን ርእስ ጉዳይ ከማጠቃለላችን በፊት ሁለት ነጥቦችን ማንሳት ተገቢ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ አንደኛው ጉዳይ በመጠለፍ ወይም በመደፈር በተፈጠረ ፅንስ ወይም የተወለደ ልጅ አባትነት በፍርድ ውሳኔ እንዲታወቅ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ክስ ለመመስረት የጠላፊው ወይም የደፋሪውን ማንነትና አድራሻ ማወቅ የግድ ነው፡፡ ምክንያቱም በፍትሐብሄር ክስ ጉዳይ የተከሳሹን ማንነት ሳያውቁ ክስ መመስረት አይቻልምና፡፡ ነገር ግን ሁሉም ባይባሉም (ብዙዎቹ ደፋሪዎች) የቅርብ ሰዎች ቢሆኑም ማንነታቸውን በጭንብል ደብቀው፣ ድምጻቸውን አጥፍተውና በጨለማ ነው ድርጊቱን የሚፈጽሙት፡፡ ስለሆነም ተደፋሪዋ የደፋሪዋን ማንነት ለማወቅ ስለምትቸገር የልጁን አባት ለማወቅ የሚደረገውን ጥረት በአንዳንድ ሁኔታዎች ውጤት አልባ የመሆን ዕድል ያጋጥመዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በእኛው ህብረተሰብ ያለመታደል ሆኖ አሳፋሪው ጉዳይ ሆኖ የሚታየው መድፈር ሳይሆን መደፈር ሆኖ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ተደፈርኩ ብሎ በአደባባይ ወጥቶ ክስ መመስረት ለብዙ እህቶቻችን በጣም ፈታኝ ነው፡፡ ከዚህም በመነጨ ብዙ ልጆች "አባት ሳይገኝላቸው እየቀረ" የእናታቸው ልጆች ብቻ ሆነው እንዲቀሩ የግድ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ህጉ ሁሉም ህፃናት ህጋዊ አባት እንዲኖራቸው የሚያደርገውን ጥረት ያህል ሙሉ በሙሉ ይሳካለታል ማለት አይደለም ማለት ይቻላል፡፡

ሁለተኛው ጉዳይ አባትነት በፍርድ ውሳኔ እንዲታወቅ ለማስወሰን ክሱን ለማቅረብ ያለው የጊዜ ገደብ ምን ያህል ነው? የሚለው ይሆናል፡፡ በፍትሐብሄር ህግ ውስጥ "ልጁ ከተወለደ ወይም መጠለፋን ወይም መድፈሩን በሚመለከተው ጉዳይ በወንጀል ውሳኔ ከተሰጠ ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ ክስ ለማቅረብ

አይቻልም"[49] የሚል ድንጋጌ ታክሎበት ነበር፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ግን ይህን የመሰለ ድንጋጌ ሳይካተት ቀርቷል፡፡ ስለዚህ በአዲሱ ህግ መሠረት ክሱ የሚቀርብበት የጊዜ ገደብ ሳይኖር በተፈለገ ጊዜ ሁሉ እንዲቀርብ ተፈቅዶአል ማለት ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡

በርግጥ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ውስጥ የክስ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ አለመካተቱ በግድፈት ምክንያት ካልሆነ በቀር ጥያቄውን ያለጊዜ ገደብ ለማቅረብ እንዲቻል ተፈልጎ አይመስለኝም፡፡ ያም ሆነ ይህ የጊዜ ገደብ በሌለበት ሁኔታ ምን ሊደረግ ይችላል? ጥያቄውን ያለጊዜ ገደብ እንዲቀርብ ሊፈቀድ ይገባል? ወይስ የተለየ መፍትሄ አለን? የሚል ነው፡፡

በኔ አስተያየት ያለጊዜ ገደብ የመክሰስ መብት በልዩ ሁኔታ ያውም በወንጀል ጉዳይ በሰብአዊ ፍጡር ላይ በሚፈጸም ወንጀል (crimes against humanity) ወይም በዘር ማጥፋት ወንጀል (Genocide) ካልሆነ በቀር ለዘልአለሙ የሚሰጥበት የህግ ሥርዓት የለንም[50]፡፡ በወንጀሉም ሆነ በፍትሐብሄር ህጉ እንደነገሩ ሁኔታ የተለያየ የጊዜ ርዝመት ያላቸው የጊዜ ገደቦች ተቀመጥዋል፡፡ አሁን የያዝነው ጉዳይም ከዚህ አጠቃላይ የህግ ማዕቀፍ ውጪ የሚሆንበት አሳማኝ ምክንያት የለም፡፡ ችግሩ ግን የራሱ የጊዜ ገደብ ይዞ ባልመጣበት ሁኔታ እንዴትና በምን የህግ መሠረት እንገድበዋለን ነው፡፡

እንግዲህ ምንም እንኳ ለሁሉም በአንቀጽ 143 ለተመለከቱት ሁኔታዎች ሁሉ የሚያገለግል የጊዜ ገደብ

[49] የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 759(2)
[50] በቅርቡም ከሙስና ወንጀል መስፋፋትና አደገኛነት የተነሣ በድርጊቱ ፈፃሚዎች ላይ በጊዜና በቦታ የማይገደብ የመክሰስ መብት እንዲኖር የተቀናጀ ዓለም አቀፍ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ እንዳለ ይሰማል፡፡

ባይሆንም ከመደፈርና ከመጠለፍ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ከውል ውጪ የሚደርስ አላፊነት ሥር ያለው የጊዜ ገደብ ለዚህ ጉዳይ ልንገለገልበት እንችላለን ብዩ እስባለሁ፡፡ እንደሚታወቀው የወንጀል ድርጊቶች የፍትሐብሄር ሃላፊነት የሚያስከትሉ ተግባሮች ናቸው፡፡ ይህም በፍትሐብሄር ህጉ ቁጥር 2035 ተደንግጎ እናገኘዋለን፡፡ መጥለፍና መድፈር ደግሞ የወንጀል ድርጊቶችም እንደሆኑ ቀደም ሲል አይተናል፡፡ ስለሆነም ከውል ውጪ የሚደርስ አላፊነት የሚያስከትሉ ድርጊቶች ሆነዋል ማለት ነው፡፡ በዚሁ የህግ ዘርፍ መሠረትም "ተበዳዩ ክስ ማቅረብ የሚችለው ካሣ የሚጠይቅበት ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ነው"[51] ይላል፡፡ ይህም ድንጋጌ አሁን ከያዝነው ጉዳይ ጋር ስናዛምደው የተደፈረች ወይም የተጠለፈች ተበዳይ በዚሁ ድርጊት ምክንያት ያለፍላጎትዋ የወለደችውን ልጅ የማሳደጉ ሃላፊነት እንዲሸከም ይወሰንበት ዘንድ በጠላፊው ወይም በደፋሪው ላይ ልጁ ከተወለደበት ቀን አንስቶ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ክስ ማቅረብ ይኖርባታል ማለት ነው፡፡

ምናልባት እዚህ ላይ ሊነሳ የሚችል ነጥብ አባትነት በፍርድ ውሳኔ እንዲታወቅ የሚቀርብ ክስ የካሳ ይከፈለኝ ጥያቄ ስላልሆነ በዚህ አንቀጽ ስር ሊሸፈን አይችልም የሚል ነው፡፡ ነገር ግን ከውል ውጪ የሚደርስ ሃላፊነት ዋናው የሃላፊነት ማውረጃ መንገድ ለተበዳይ ካሣ በመክፈል ቢሆንም "በሌላ አኳሃን ስለመካስ" የሚለው የህጉ ክፍል ከካሣ በተጨማሪ ወይም በካሣ ምትክ ይቅርታ በመጠየቅ፣ የስም ማደሻ ማስታወቂያ በማውጣት፣ ተከሳሹ አንድን ሥራ እንዲሰራ በማዘዝ ወይም እንዳይሰራ ማገድና የመሳሰሉት ትዕዛዞች ሊተላለፉ ስለሚችሉና[52] እነዚሁ ትዕዛዞች ለማስገኘት የሚቀርበው ክስም በቁጥር 2143 ውስጥ ባለው የጊዜ ገደብ የሚሸፈን ስለሆነ

[51] የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 2143
[52] ዝኒ ከማሁ ከቁጥር 2018-2121

Scanned by CamScanner

አባትነቱን በፍርድ ውሳኔ እንዲቀበል የሚያደርግ ውሳኔ ለማስተላለፍም ይህ የጊዜ ገደብ አግባብነት ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ክፍል ስድስት

አባትነት በመወሰን ረገድ ስለሚኖረው የህግ ግጭትና አፈታቱ

6.1. አጠቃላይ የመነሻ ሃሳብ

በዚህ ርእስ ሥር አባትነት በመወሰን ረገድ የህግ ግጭት ሊፈጠር ለመወሰን የሚረዱ ድንጋጌዎች ተካትተው ይገኛሉ፡፡ልጅነት በመቀበል ሥርዓት አንድን ልጅ አንድ አባት ተቀብሎት እያለ ሌላ አባት ልጄ ነው ብሎ እንዲቀበለው ህጉ ስለማይፈቅድ[53] በዚህ ረገድ የአባትነት ግጭት ሊፈጠር አይችልም፡፡ በፍርድ ውሳኔ አባትነት በሚታወቅበት ሥርዓትም ልጁ በህግ ግምት አባት ያለው ከሆነ ወይም ልጅነቱን የተቀበለው ሰው ካለ በፍርድ ውሳኔ አባትነት ወደሚታወቅበት ዘዴ መሄድ አይቻልም፡፡ ስለሆነም የህግ ግጭቱ የሚፈጠረው በህግ ግምት አባትነት በሚታወቅበት ሥርዓት ስለሆነ የዚህ የህግ ክፍል ጠቃሚነት በህግ ግምት አባትነት ለሚወሰንበት ሥርዓት ነው፡፡

በተፈጥሮአዊ አካሄድ አንድ ልጅ ሊወለድ የሚችለው ከአንድ አባት ብቻ ነው፡፡ በህግ ግምት አባትነት በሚታወቅበት ሥርዓት ግን የህግ ግምቱ ሽፋን ሰፊ ስለሆነ ከአንድ በላይ የሆኑ ወንዶች የአንድን ልጅ ህጋዊ አባት ናችሁ ሊባሉ የሚችሉበት ዕድል አለ፡፡

[53] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 142

ጉዳዩን በምሳሌ ለማብራራት አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ለአምስት ዓመታት ያህል በትዳር ከቆዩ በኋላ ተፋቱ እንበል፡፡ ከተፋቱ በ190ኛው ቀን ሴትየዋ ሌላ ባል ታገባለች፡፡ ሁለተኛ ባል ባገባችም በ90ኛው ቀን "ወንድ ልጅ ክንታቁሉ" በሠላም ትገላገላለች፡፡ የዚህ ልጅ ህጋዊ አባት ማን ሊባል ነው? የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡

በህጉ መሠረት ልጁ የተወለደው የመጀመሪያው ጋብቻ በፈረሰ ሦስት መቶ ቀናት ከመድረሱ በፊት (እንዲያውም በ280ኛው ቀን) ስለሆነ ልጁ በጋብቻ ውስጥ እንደተፀነሰ ይቆጠራል፡፡ በጋብቻ ውስጥ የተጸነሰ ልጅ ደግሞ አባቱ ባልየው ነው ስለሚል የመጀመሪያው ባል በዚህ የህግ ግምት መሠረት የልጁ ህጋዊ አባት ነው ሊባል ነው ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ልጅ የተወለደው ሁለተኛው ጋብቻ በተመሰረተ በ90ኛው ቀን ስለሆነ በጋብቻ ውስጥ የተወለደ ስለሆነ በሌላኛው የህግ ግምት መሠረት ደግሞ የኋለኛው ባል የልጁ ህጋዊ አባት ነው ማለትን ያስከትላል፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳ አንድ ልጅ በተፈጥሮ ከአንድ አባት ብቻ እንደሚወለድ የሚታወቅ ቢሆንም በህግ ግምቱ መሠረት ግን ሁለት ህጋዊ አባቶች እንዲኖሩት ተደርጓል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ህጉን ከተፈጥሮ ጋር ለማጣጣም ይቻል ዘንድ ግጭቱ የሚፈታበት ሥርዓት ማመቻቸት አስፈላጊ ነው፡፡ የህጉ ደንበኛው ክፍልም ለዚሁ ዓላማ ተመሳሳይ ጉዳዮች ተብሎ የተቀረፀ ነው፡፡

የአባትነት ግጭቱ መፍቻ መንገድ ተብለው በህጉ የተቀመጡትም በአንድ በኩል የህግ ግምት አባት ናችሁ የተባሉት ሰዎች በመካከላቸው በሚያደርጉት ስምምነት አንዱ ለሌላው አባትነቱን የሚለቅበት ሥርዓት ሲሆን ይህ የማይሳካ ቢሆን ደግሞ ህጉ ሌላ የህግ ግምት በማስቀመጥ ግጭቱን ለመፍታት ጥረት ያደርጋል፡፡ በመጨረሻም በህግ ግምት አባት

Scanned by CamScanner

ነህ የተባለ ሰው አባትነቱን ለሌላ ፈቃደኛ ሰው የሚያሸጋግርበት ሥርዓት በጠባቡ ተደንግጎ እናገኛለን፡፡

በርግጥ አባትነትና እናትነትን ስለማወቅ የተመለከቱት የህግ ድንጋጌዎች በስምምነት ሊለወጡ እንደማይችሉና አስገዳጅ እንደሆኑ አጠቃላይ በሚለው የዚህ ምዕራፍ ክፍል በግልፅ ተመልክ□ል፡፡ ሆኖም ያው የህግ ክፍል ራሱ "ህጉ በግልፅ የሚፈቅድ ካልሆነ በቀር..."[54] የሚል ሐረግ ስለታከለበት ህጉ በግልፅ ከፈቀደ ግን አባትነትና እናትነት ስለማወቅ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በስምምነት ሊለወጡ ይችላሉ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ አሁን እየተነጋገርንባቸው ያሉት አባትነትን በስምምነት ለማስተላለፍ የሚፈቅዱ የህጉ ድንጋጌዎች የአጠቃላዩ መርሁ ልዩ ሁኔታዎች መሆናቸው መገንዘብ ጠቃሚ ነው፡፡ በመሆኑም በጠባቡ እንዲተረጎሙ የህግ አጠቃላይ መርህ የግድ ይላል፡፡

6.2 ግጭቱን በስምምነት ስለመፍታት

በህጉ ረገድ የአባትነት ግጭቱ ቀዳሚው የመፍቻ መንገድ ህጋዊ አባት ናችሁ የተባሉት ሰዎች በመካከላቸው በሚያደርጉት ስምምነት ከሁለቱ አንደኛው አባትነቱን ለሌላኛው ወገን እንዲለቅ ማድረግ ነው[55]፡፡ በእውነቱ ሁለቱ ወገኖች በዚህ ነጥብ ላይ ስምምነት ከደረሱ ትልቅ እርምጃ ወደፊት ነው፡፡ ሆኖም ግን የእነርሱ ስምምነት ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ስምምነቱ በሶስት ምስክሮች እንዲረጋገጥና ፍርድ ቤት እንዲያፀድቀው ህጉ ያስገድዳል[56]፡፡ በርግጥ ስምምነቱ በጽሁፍ ሊሆን ይገባል የሚል

[54] ዝኒ ከማሁ 123
[55] ዝኒ ከማሁ 146
[56] ዝኒ ከማሁ 147(1) በነባሩ የፍትሐብሄር ህግ መሠረት ስምምነቱ ህጋዊ ውጤት ይኖረው ዘንድ በአራት ምስክሮች መረጋገጥ ነበረበት (የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 763(1) ይመለከቷል)

ግልጽ የህግ ድንጋጌ የለም፡፡ ቢሆንም ስምምነቱ ምስክሮች እንዲያረጋግጡት ሲፈለግ ወይም ፍርድ ቤት እንዲያፀድቀው ሲጠየቅ የሚረጋገጥ ወይም የሚፀድቅ ሰነድ ታሳቢ በማድረግ እንደሆነ በማመን ዞሮ ዞሮ ስምምነቱ በጽሁፍ እንዲሆን መጠየቁ አይቀርም፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳ በህግ (in law) በጽሁፍ እንዲደረግ ባይጠየቅም በተጨባጭ (in fact) ግን ከጽሁፍ ውጪ ሊታሰብ የሚችል አይመስልም፡፡

እዚህ ላይ እንግዲህ አጠቃላዩ የማህበረሰባችን አመለካከት ሲመዘን እንዲህ ዓይነት አባትነትን በስምምነት የመወሰን ሥርዓት ስኬታማነቱ በእጅጉ አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም ሁለት ወንዶች ከአንዲት ሴት የተወለደን ልጅ የህግ አባቶች ሆነው ሲቆጠሩ እንኳን ስምምነት ላይ ሊደርሱ ይቅርና ቃሉ ብለው ሊወያዩ የሚችሉበት ሁኔታም በጣም ጠባብ መስሎ ይታያል፡፡ ቅናቱም ትዕቢቱም ለውይይቱና ለስምምነቱ እንቅፋት እንደሚሆን ይታሰባል፡፡ ስለሆነም በዚሁ ሥርዓት መፍትሄ ከተገኘ ቀዳሚና የሚመረጥ ቢሆንም በዚሁ ብቻ ተማምኖ ሌላ አማራጭ መፍትሄ አለማደራጀት ግን የዋህነት ይሆናል፡፡ ስለዚህ ህጉ ምናልባት ይህ ካልተሳካ በሚል ታሳቢ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ አማራጭ መፍትሄ አደራጅቶ እናገኘዋለን፡፡

6.3. ግጭቱን በህግ ግምት ስለመፍታት

በዚህ ረገድ ሁለተኛ ደረጃ የአባትነት ግጭቱ መፍቻ መንገድ ተደርጎ የተወሰደው የህግ ግምት ነው፡፡ መጀመሪያውንም ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርነው የግጭቱ መንስኤ የሆነው የህግ ግምት ነው፡፡ በመሆኑም የመፍትሄ አቅጣጫውም የተቀየሰው በህግ ግምት ምክንያት የተፈጠረን

ግጭት በሌላ የህግ ግምት የመፍታት አቅጣጫን መሠረት ያደረገ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ሁለት የግጭት መፍቻ የህግ ግምቶች ተቀምጠዋል፡፡ አንደኛው የግጭት መፍቻ ዘዴ የአባትነት ግጭቱ የተፈጠረው በአንድ ጋብቻ ሳይፈጸም ከልጁ እናት ጋር እንደባል አብሮ በሚኖርና በሌላ ከሴትየዋ ጋር ጋብቻ ፈፅሞ በባልነት የሚኖር ሰው መካከል የሆነ እንደሆነ የህግ አባትነቱ ሃላፊነት መስጠት ያለበት ለህጋዊ ባል ነው[57] የሚል ነው፡፡ ቀደም ሲል ባነሳነው ምሳሌ የልጁ እናት ለአምስት ዓመታት ያህል ጋብቻ ሳትፈጽም እንደሚስት ሆና ስትኖር ከቆየች በኋላ ይህን ግንኙነት አቋርጣ ከተለያየች በኋላ በ190ኛው ቀን ሌላ ባል አግብታ ከጋብቻው በኋላ በ90ኛው ቀን ልጅ ብትወልድ ሁለቱም ወንዶች ከተስማሙ የልጁን አባትነት አንዱ ለሌላው ሊለቅለት የሚችል ሲሆን ይህ ካልተሳካ ግን በዚሁ የህግ ግምት መሠረት የልጁ ህጋዊ አባት የሚሆነው ህጋዊ ጋብቻ የፈጸመው ሰው ማለትም ሁለተኛው ሰው ይሆናል[58] ማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ እንግዲህ የምንገነዘበው ምንም እንኳ ጋብቻና ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር በህግ እውቅና የተሰጣቸው ግንኙነቶች ቢሆኑም ከሁለቱ አንዱ የመምረጥ ጉዳይ ሲመጣ ግን ህጉ ከጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ ከመኖር ይልቅ ጋብቻን እንደሚመርጥ ፍንጭ እየሰጠን ይመስላል፡፡

[57] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 148(ሀ)

[58] ለነገሩ ልጁ ሲፀነስ ከነበረው ባል ወይም እንደባል የሚኖር ሰው ይልቅ ልጁ ሲወለድ ለነበረ ባል ወይም እንደባል አብሮ የሚኖር ሰው የልጁ አባትነት ሊሰጥ ይገባል በሚለው መርህም መሰረት የልጁ አባት የሚሆነው ሁለተኛው ሰው ነው፡፡

ይህ የግጭት መፍቻ መንገድ በመጠቀም የተወሰኑትን ችግሮች መፍታት እንችል ይሆናል እንጂ ሁሉንም ችግሮቻችንን ግን የሚፈታ አይሆንም፡፡ እላይ የተመለከተውን ምሳሌ እንኳ ተከትለን ብንሄድ ለምሳሌ አንዱ ጋብቻ ያልፈጸመ ሌላው ጋብቻ የፈጸመ መሆናቸው ቀርቶ ሁለቱም ከልጁ እናት ጋር ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባል አብረው የሚኖሩ ወይም ሁለቱም በቅደም ተከተል ከልጁ እናት ጋር ጋብቻ የፈጸሙ ከሆኑ ይኸኛው የህግ ግምት መፍትሄ የሚሰጠን አይሆንም፡፡ ስለዚህ ወደ ሁለተኛው የህግ ግምት መሸጋገር ይገባናል ማለት ነው፡፡ ይኸኛው የህግ ግምት እንዲህ የሚል ነው፡፡ ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ ከነበረው ባል ወይም ከሴትየዋ ጋር እንደባል አብሮ ይኖር ከነበረው ሰው ይልቅ እናቲቱ ልጁን ስትወልድ የነበራት ባል ወይም እንደባል አብሮ የሚኖር ሰው የልጅ አባት ነው ማለት ይገባል[59] ይላል፡፡ ይህን ንዑስ አንቀጽ በተመለከተ በቀድሞው የፍትሐብሄር ህግ ውስጥ በአማርኛውና በእንግሊዘኛው ቅጅ መካከል የይዘት ልዩነት ነበር[60]፡፡ የእንግሊዘኛው ቅጅ ልጁ ሲፀነስ ከነበረው ወንድ ይልቅ ልጁ ሲወለድ ለነበረው ወንድ ቅድሚያ ሊሰጥ እንደሚገባ ሲደነግግ የአማርኛው ቅጅ ግን እናቲቱ ልጁን በወለደችበት ጊዜ ላላት ባል ልጁ ነው ከማለት ይልቅ ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ ለነበራት ባል ልጁ ነው ማለት ይገባል የሚል ነበር፡፡ ይህንኑ የይዘት ልዩነት መሠረት በማድረግ ቢያንስ በህግ ትምህርት ተቋሞች አካባቢ የአማርኛው ወይስ የእንግሊዘኛው ቅጅ ማስፈጸም እንደሚገባ አስመልክቶ ብዙ ውዝግቦች ነበሩ፡፡

[59] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 148(ለ)

[60] የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 764 የአማርኛውና የእንግሊዘኛው ቅጂዎች አይቶ ማነፃፀር ይጠቅማል፡፡

Scanned by CamScanner

በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ይህ ቀደም ሲል በአማርኛውና በእንግሊዘኛው ቅጅ መካከል ተፈጥሮ የነበረው የትርጉም መዛነፍ እንዲወገድ የተደረገ ሲሆን በቀድሞው የእንግሊዘኛ ቅጅ ውስጥ የነበረው መሠረተ ሃሳብ ተቀባይነት እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡ በሁኑ እምነት የእንግሊዘኛው ቅጅ ይዘት የጋብቻውን ሀንቁ መቀጠል የሚያበረታታ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ምክንያቱም አንድ ባል ሚስቱ እርጉዝ መሆንዋን እያወቀና ተቀብሎ ልጅ ከተወለደ ይህንን ልጅ የሌላ ሰው ልጅ ነው ብሎ በሞቀ ትዳር ውስጥ ቀዝቃዛ ውሃ ከመቸለስ ይልቅ ልጁ እናትየው ልጁን ስትወልድ አብሮአት የነበረው ባል ልጅ ነው መባሉ ተመራጭ ሆኖ ይታያል፡፡ አሁን የተደረገውም ይህንኑ ነው፡፡

በህገ-መንግስታችንም ሆነ ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት ህፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በፍርድ ቤቶች በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በህግ አውጪ አካላት የህፃናት ደህንነት (the best interest of the child) በቀዳሚነት መታሰብ አለበት[61] ተብሎአል፡፡ ህግ አውጪው ይህንኑ ግምት ውስጥ በማስገባት የቀድሞው የእንግሊዘኛ ቅጅ ይዘት የጋብቻውን ቀጣይነት ብቻ ሳይሆን የልጁን ዘላቂ ጥቅምና አስተዳደግ በተሻለ ሁኔታ ያሳካል በሚል እምነት ይህንኑ እንዲከተት አደርጓል፡፡

6.4. አባትነትን ለሌላ ሰው ስለማስተላለፍ ሥርዓቱ

[61] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሀገ-መንግስት አንቀጽ 36(2) እና የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 3(1)፡፡ ይህ ኮንቬንሽን በሽግግር ወቅት የነበረው የተወካዮች ምክር ቤት ህዳር 29 ቀን 1984 ተቀብሎ ያፀደቀው ስለሆነ የሃገራችን የህግ አካል ነው፡፡

በመጨረሻም በዚህ ክፍል ሥር እንዲካተቱ የተደረጉት አባትነትን በስምምነት ስለማስተላለፍ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ አንዳንድ ወገኖች በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ በአንቀጽ 146 እና 149 መካከል ልዩነት እንደሌለ[62] አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ፡፡ ይህ ግን ትክክለኛ ግንዛቤ አይመስለኝም፡፡

እንደእውነቱ ከሆነ አንቀጽ 149 አባትነት በመወሰን ላይ ስለሚኖረው የህግ ግምት በሚል ርእስ ሥር የሚካተት አይደለም፡፡ ምክንያቱም በዚህ አንቀጽ ስር የአባትነት ግምት ጨርሶ የለም፡፡ በአንቀጹ መሠረት በህግ ግምት አባት ነው የሚባለው አንድ ሰው ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ልጁ የተወለደው ጋብቻው በተፈፀመ ወይም ጋብቻው ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ከተጀመረ በ210 ቀናት ውስጥ ከሆነ ወይም ጋብቻው ከፈረሰ ወይም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖሩ ከተቋረጠበት ቀን በኋላ 210 ቀኖች አሳልፎ የተወለደ እንደሆነ የልጁን አባትነት ለሌላ ፈቃደኛ ሰው የሚያስተላልፍበት ሥርዓት ነው[63]፡፡

ቀደም ሲል ጋብቻ በተፈፀመ በ180ኛው ቀን የተወለደ ልጅ በጋብቻው ውስጥ እንደተጸነሰ እንደሚቆጠር አይተናል፡፡ በጋብቻ ውስጥ የተፀነሰ ልጅ ደግሞ አባቱ ባልየው ነው ተብሎ እንደሚገመት ተገንዝበናል፡፡ ይህ መርህ ጋብቻ ሳይፈፀሙ እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩ ሰዎች ላይ ተፈጻሚ እንደሆነ መግለጻችን ይታወሳል፡፡ አሁን እንግዲህ ህግ አውጪው አንቀጽ 149 በማስቀመጥ የዚሁ መርህ ልዩ ሁኔታ (exception) እየፈጠረ ነው ማለት ነው፡፡

[62] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ድንጋጌዎችን አፈጻጸም ለመተግበር ተዘጋጅተው በነበሩ አውደ ጥናቶች ካንዴም ሁለቴ ይህ ዓይነት የክርክር መስመር ሲነሳበት አጋጥሞኛል፡፡

[63] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 149

እንደሚታወቀው 210 ቀናት ሰባት ወር ነው፡፡ በተለምዶ ደግሞ እጅግ ቢፈጥን በሰባት ወር እንጂ ሰባት ወር ከመሙላቱ በፊት ልጅ አይወለድም ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለሆነም ጋብቻው ተፈፅሞ ሰባት ወር ከመሙላቱ በፊት ልጅ ከተወለደ ባልየው አባቱ ሊሆን አይችልም የሚል ጥርጣሬ ስለሚፈጥር ምንም እንኳ በመሠረታዊው የህግ ግምት አባት መሆኑ ቢታመንም የህግ አባትነት (legal father) ከተፈጥሮ አባትነት (biological father) ጋር በተቻለ መጠን ማጣጣም ይቻል ዘንድ እርሱም አባትነቱን ማውረድ ከፈቀደ ሌላ ሰውም የልጁን አባትነት ለመቀበል ከፈቀደ በህግ ፈቃድ አባትነቱ ከአንዱ ወደ ሌላው የሚተላለፍበት ሥርዓት ነው፡፡ ጋብቻው ከፈረሰ በኋለም እንዲሁ ምንም እንኳ እስከ ሦስት መቶ ቀናት ድረስ ልጅ ከተወለደ በህግ ግምት መሠረት ሀጋዊ አባቱ ባልየው ቢሆንም ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ ሰባት ወር አልፎ ልጅ ከተወለደ ግን በልዩ አስተያየት የህግ ግምቱ በስምምነት የሚለወጥበት ሁኔታ ለመፍጠር ነው ይህ አንቀጽ የተቀመጠው ተብሎ ይታመናል፡፡ እንግዲህ በህጉ እምነት የልጁን አባትነት ከሀጋዊው አባት ለመቀበል ፈቃደኛ የሚሆነው ሰው ምናልባት ከልጁ እናት ጋር ከጋብቻው መፈጸም በፊት ወይም ከጋብቻው መፍረስ በኋላ እላይ ከተጠቀሱት ሀጋዊ ግንኙነቶች ውጪ አብሮ የሚኖር ሰው ሊሆን ይችላል ተብሎ ይገመታል፡፡

በመሆኑም አባትነት በስምምነት ስለመወሰን (አንቀጽ 146) እና አባትነትን በስምምነት ስለማስተላለፍ (አንቀጽ 149) የተለያየ ዓላማ ያላቸውና የተለያዩ ጽንሰ ሃሳቦች መሆናቸው መገንዘብ ይገባል፡፡ አባትነት በስምምነት የሚወሰነው የህግ ግምቱ በሁለቱም ላይ የሀጋዊ አባትነት ሃላፊነት በሰጠበት ሁኔታ ተፈፃሚ የሚደረግ ሲሆን አባትነት በስምምነት ማስተላለፍ ግን የህግ ግምቱ አባትነቱን ለአንድ ሰው ሰጥቶ እያለ ይህ ሰው ልጅነቱን ለመቀበል ለፈቀደ (ግን በህግ ግምት አባትነህ ላልተባለ) ሰው ማስተላለፍ የሚያስችለው የህግ ሥርዓት ነው፡፡

ከዚህ ውጪ ግን ሁለቱም የሚያመሳስልዋቸው ብዙ ነጥቦች አሉ፡፡ አንደኛ ሁለቱም አባትነትን ስለማወቅ የተመለከቱት የህጉ ድንጋጌዎች በስምምነት ሊለወጡ አይችሉም ለሚለው አጠቃላይ መርህ ልዩ ሁኔታዎች (exceptions) ናቸው፡፡ ሁለተኛ ሁለቱም በጽሁፍ ሊደረጉ፣ በሦስት ምስክሮች ሊረጋገጡና በፍርድቤት ሊጸድቁ ይገባል፡፡ ሦስተኛ በሁለቱም ሥርዓቶች ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላገጠመ በቀር የልጁን እናት ቃል መቀበል እንደሚገባ ተመልክቶአል፡፡ ይህም ከእናቲቱ ጋር ምንም ዓይነት የግብረሥጋ ግንኙነት ያልነበረውና የልጁ የተፈጥሮ አባት ሊሆን የማይችል ሰው ልጅነቱን አቀባለለሁ ስላለ ብቻ የአባትነት ሃላፊነት እንዳይወስድ ለመከላከል ይረዳል፡፡ አራተኛ በሁለቱም ሥርዓቶች ስምምነቱን ማከናወን ያለባቸው ባለጉዳዮቹ ራሳቸው እንጂ በወኪል ሆኖ ሲገኝ ወኪሉ በፍርድቤት የጸደቀ ልዩ የውክልና ሥልጣን መያዝ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ አምስተኛ በሁለቱም ሥርዓቶች ስምምነቱ ከተፈፀመ በኋላ ሊሻር የሚችል አይደለም፡፡ ስምምነቱ ሊሻር የሚችልበት ጠባብ ዕድል ስምምነቱ የተደረገው በማስገደድ የተገኘ መሆኑ ማስረዳት ሲቻል ነው፡፡ የማስገደድ ምንነት በመተርጎም ረገድና ስምምነቱ ለማፍረስ ይቻል ዘንድ መቅረብ ስላለበት የጊዜ ገደብ አጠቃላዩ የውል ህግ ድንጋጌዎች አግባብነት ይኖራቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

ነገር ግን ስምምነቱ በማስገደድ የተደረገ ከሆነ ደግሞ ምንም እንኳ ሦስት ምስክሮችም ከአስገዳጁ ጋር ተባብረው ሊፈርሙ ይችላሉ ሊባል ቢችልም በፍርድ ቤት ሊፀድቅ ሲቀርብ ተገድጄ ነው የሚል ተቃውሞ ማቅረብ የሚቻልበት ዕድል ሰፊ

Scanned by CamScanner

ነው፡፡ ስለዚህ ስምምነቱ በፍርድ ቤት ከፀደቀ በኋላ ተገድጀ ነው ስምምነቱን የፈረምኩት ብሎ ለማስረዳት አስቸጋሪ ይመስለናል ምክንያቱም ፍርድቤት ሰነዱን ሲያፀድቅ ሁለቱም ወገኖች አስቀርቦ በዚህ ረገድ ፈቃዳቸው ሙሉና ነፃ ስለመሆኑ ሳያረጋግጥ ሰነዱን ያፀድቀዋል ተብሎ አይታሰብምና ነው፡፡

ክፍል ሰባት

ስለ ልጅነት ማስረጃ

7.1. አጠቃላይ የመነሻ ሃሳብ

የማስረጃ ጉዳይ ሲነሳ ያለ ወይም የነበረን ሃቅ የማረጋገጥ ጥረት ነው፡፡ ማስረጃ አዲስ ነገር የሚፈጥር ሳይሆን ያለውን ወይም የነበረውን የሚያረጋግጥ ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም ማስረጃ የማረጋገጫ ዘዴ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የልጅነት ማስረጃ ሲባል ልጁ የእገሌ እና(ወይም) የእገሊት ልጅ ነው ብሎ ማረጋገጥ ማለት ነው፡፡

እንግዲህ ዘመናዊው የልጅነት ማስረጃ የልደት ምስክር ወረቀት ነው፡፡ እንደሚታወቀው የልደት ምስክር ወረቀት አንድ ህፃን እንደተወለደና ወዲያውኑ ጾታው፣ክብደቱ፣ስሙ፣ የአባቱና የእናቱ ስም መዝግቦ የያዘ ሰነድ ነው፡፡ በብዙ በበለፀጉ ሃገራት ይህ አሠራር የተለመደ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የልጁ ወላጆች ማንነት እንዲሁም የልጁ ዕድሜ አስመልክቶ ብዙም አወዛጋቢ ጉዳይ አያጋጥማቸውም፡፡ በኛና እኛን በመሰሉ ታዳጊ ሃገሮች ግን እንዲህ ዓይነት ወጥ አሰራር ያልተደራጀ ቢደራጅም ቀጣይነት እንዲኖረው የማይደረግ ስለሆነ በዚህ ረገድ የመረጃ ክፍተት መኖሩ አይካድም፡፡

በርግጥ በነባሩ የፍትሐብሄር ህግም ቢሆን አንድ ልጅ ሲወለድ መወለዱን ለክብር መዝገብ ሹም ማስታወቅ እንደሚገባ በህግ ተደንግጎ ያለና የነበረ ነው፡፡ ይህንን የማስታወቅ አላፊነትም በመጀመሪያ ደረጃ በልጁ አባት፣ አባቱ የሌለ ሲሆን በልጁ እናት ወይም አሳዳጊ እነዚህም ባይኖሩ ልጁን አግኝቶ ያነሳው ሰው ሊገልጽ ይገባዋል[64] ተብሎ ተደንግጎ ነበር፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ህጉም የልጅን መወለድ አለማሳወቅ በወንጀል የሚያስቀጣ ጥፋት ስለመሆኑ[65] በግልጽ ተቀምጦ ይገኛል፡፡ ቢሆንም የምዝገባ ሥርዓቱን ያከናውናል ተብሎ ታስቦ የነበረው የክብር መዝገብ ሹም ጽ/ቤት ሳይቋቋም በመቅረቱ በዚህ ረገድ የነበረው ጥረት ሁሉ መና ቀርቷል ሊባል ይቻላል፡፡

በቅርቡ ኢትዮጵያ ያፀደቀችው የህፃናት መብት ኮንቬንሽንም ህፃናት እንደተወለዱ ወዲያውኑ መመዝገብ እንዳለባቸው[66] ይደነግጋል፡፡ ይህ በኢትዮጵያ የፀደቀው ዓለም አቀፍ ስምምነትም የሃገሪቱ የህግ አካል ስለሆነ አስገዳጅነቱ አጠያያቂ አይደለም፡፡ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግም የልደት ምዝገባን አስፈላጊነት በመገንዘብ የፌዴራሉ መንግስት ይህ ህግ (የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ) በሥራ ላይ በዋለ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ህጉ ተፈፃሚ ለሚሆንባቸው መስተዳድሮች (አዲስ አበባና ድሬደዋ) የሚያገለግል የምዝገባ ህግ ያወጣል፤ አስፈላጊ ተቋሞችንም ያደራጃል[67] በሚል ቃል ገብቶ ነበር፡፡ አሁንም ግን ለጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶ የምዝገባ ሥርዓቱ በአግባቡ የተደራጀ አይመስልም[68]፡፡ በመሆኑም በሃገር ደረጃ ይቅርና ትላልቅ

---

[64] የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 101(2)

[65] የወንጀል ህግ አንቀጽ 656(1) ይመለከቷል፡፡ በቀድሞው የ1949 ወንጀለኛ መቅጫ ህግም ተመሳሳይ ድንጋጌ ተቀምጦ ነበር፡፡

[66] የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 7(1)

[67] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 321(1)

[68] በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ቀደም ሲል "የውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት" ይባል የነበረው ተቋም "የውልና የክብር መዝገብ ማስረጃ አገልግሎት" በሚል

Scanned by CamScanner

በሚባሉት ከተሞችም ቢሆን በዚህ ረገድ ወጥነት ያለው የምዝገባ ሥርዓት የለንም።

ይህ ችግር እንዳለ ሆኖ ግን በልጅነት ማስረጃ ረገድ ህጉ ያስቀመጣቸው ድንጋጌዎች ይዘት መመርመሩ አግባብነት አለው። የልጅነት ማስረጃ ሲወሳ ቀደም ሲል በዚህ መጽሐፍ በቅጽ አንድ ስለጋብቻ ማስረጃ ያነሳናቸው ችግሮች ለዚህም አግባብነት ያላቸው ናቸው። የልጅነት ማስረጃም እንደጋብቻ ማስረጃ አወዛጋቢ ከሚባሉት የህጉ ክፍል አንዱ ነው።

የጋብቻ ማስረጃ ባልና ሚስት ነን በሚሉት ሰዎች መካከል ቀደም ሲል ከሦስቱ የጋብቻ ማስፈጸሚያ ሥርዓቶች በአንዱ ጋብቻ መፈጸማቸውን ማመላከት የሚጠበቅበት ሲሆን የልጅነት ማስረጃም ከሦስቱ አባትነት የሚወሰንባቸው ሥርዓቶች በአንዱ በልጁና አባት ነው በተባለው ሰው መካከል የአባትና የልጅ ግንኙነት የተፈጠረ ስለመሆኑ ማሳየት ይጠበቅበታል። "በትዳር ሁኔታ" ጋብቻን ማስረዳት አራተኛ የጋብቻ ማስፈጸሚያ ሥርዓት መሆን የሌለበትን ያህል "በልጅነት ሁኔታ" መኖር ልጅነት ማስረዳትም አራተኛ የአባትና የልጅ ግንኙነት መፍጠሪያ ሥርዓት ሆኖ ሊያገለግል አይገባም። ለምን ቢባል ማስረጃ ያለውን የሚያስረዳ እንጂ አዲስ ነገር ወይም ጭብጥ መፍጠሪያ ዘዴ አይደለምና። በተጨባጭ የእለት ተእለት የፍርድ ቤት

እንደገና የተደራጀ ሲሆን ከሌሎች ስራዎቹ በተጓዳኝ ልደትን፣ ጋብቻን፣ ፍቺንና ሞትን በመመዝገብ ላይ እንደሚገኝ ይነገራል። ሆኖም ይህ ተቋም (reactive) በራሱ አነሳሽነት ምዝገባ የሚያከናውንና ለዚሁ በሚያመች መልኩ የተደራጀ አይደለም። ስለዚህ በህጉ የታሰበው በራሱ አነሳሽነት ጭምር ምዝገባ የሚያከናውን ተቋም(proactive) በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 29 መሠረት የሚሠራ ተቋም ገና አልተደራጀም ማለት ይቻላል። አሁንም እግረመንገዳችን ይህንን ጉዳይ እንዲታሰብበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

ሥራ ግን እነዚህ መሰረተ ሃሳቦች አልፎ አልፎ ሲረሱ ይስተዋላል።

7.2. የልደት ምስክር ወረቀት

ከዚህ አጠቃላይ መንደርደሪያ አንጻር እንግዲህ የልጅነት ማስረጃ ድንጋጌዎች ይዘት ምልከታችንን እንቀጥል። አሁን ባለን ህግ (በድሮም ቢሆን በህግ ደረጃ) በልጅነት ማስረጃ ረገድ ቀዳሚውና ተመራጩ ማስረጃ የልደት ምስክር ወረቀት ነው[69]። ለነገሩ ለጋብቻ መኖርም ቀዳሚና ተመራጩ ማስረጃ የጋብቻ የምስክር ወረቀት መሆኑን ቀደም ብለን አይተናል። ይህ ሲባል ግን የልደት ምስክር ወረቀት ጥያቄ የማይነሳበት ወሳኝ (conclusive) ማስረጃ ነው ማለት አይደለም። ለምሳሌ በህግ ግምት መሠረት አባት ነው ተብሎ የሚገመተው ሰው አንድ ሰው ሆኖ በልጁ የልደት ምስክር ወረቀት ላይ ግን የሌላ ሰው ስም በአባትነት ተመዝግቦ ከተገኘ የልደት ምስክር ወረቀቱ ከህግ ግምቱ ጋር ይጣጣም ዘንድ ይታረማል እንጂ በዚህ ሁኔታ ለልደት ምስክር ወረቀቱ ህጋዊ ፋይዳ አይሰጠውም[70]። ይህም ማስረጃ የማረጋገጫ ዘዴ እንጂ አዲስ ህጋዊ ሁኔታ የሚፈጥር አይደለም የሚለው መሠረታዊ ሃሳብ የሚያጠናክር ነው።

ህጉ የልደት ምስክር ወረቀት ቀዳሚ ማስረጃ አድርጎ ቢወስደውም ብቸኛ ግን አይደለም። የልደት ምስክር ወረቀት ሲታጠል፣ ሲጠፋ፣ ሲቀደድ ወይም ጨርሶ ያልተዘጋጀ በሆነበት ሁኔታ የሁለተኛ ደረጃ ማስረጃ በህጉ ተመልክቶአል። ይህም

[69] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 154
[70] ዝኒ ከማሁ 127(2)

"የልጅነት ሁኔታ መኖርን" ማሳየት ነው[71]፡፡ የልጅነት ሁኔታ መኖር ደግሞ በህጉ በራሱ ትርጉም የተሰጠው ሲሆን አንድ ሰው የልጅነት ሁኔታ አለው የሚባለው በማህበረሰቡ ዘንድ የእርሱ ወይም የእርሷ ልጅ ነው እየተባለ የሚገመት ሲሆን ነው[72] ተብሎ ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡ እንደሚታወሰው በጋብቻ ጉዳይም የጋብቻ ምስክር ወረቀት ባልቀረበበት ሁኔታ የሁለተኛ ደረጃ ማስረጃ ተደርጎ የተወሰደው የትዳር ሁኔታ መኖር ሲሆን ለዚሁም በተመሳሳዩ የህግ ትርጉም በቦታው ተሰጥቶታል፡፡

እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ ግን ከአንደኛ ደረጃ ማስረጃ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ማስረጃ ለመሸጋገር በቂና አሳማኝ ምክንያት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን በማስረጃዎች መካከል ደረጃ ማውጣቱ ፋይዳ቎ ቢስ ሊሆን ነው ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የልደት ምስክር ወረቀት የለም ስለተባለ ብቻ እንዲሁ እንግዲያውስ በልጅነት ሁኔታ መኖር ይረጋገጥ ወደሚል ውሳኔ ሊወሰደን አይገባም፡፡ ላለመኖሩ የቀረበው ምክንያት በቂ ማለትም ለምሳሌ የምስክር ወረቀቱ የጠፋ፣ ማቅረብ የማይቻል፣ የተቃጠለ ወይም የተቀደደ መሆኑን ማስረዳት ይገባል፡፡ ጨርሶ ያልተዘጋጀ ከሆነም ምዝገባ ሥርዓቱ ባለመደራጀቱ ምክንያት ምዝገባ አለመከናወኑን ወይም ተመሳሳይ አሳማኝ ምክንያት ሊቀርብ ይገባል፡፡

7.3. የልጅነት ሁኔታ መኖር

ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ በአንደኛ ደረጃ ማስረጃ የማስረዳት ግዴታ በአሳማኝ ምክንያት ተወግዶ በሁለተኛ ደረጃ ማስረጃ ማለትም በልጅነት ሁኔታ መኖር ልጅነት ማስረዳት

[71] ዝኒ ከማሁ 155
[72] ዝኒ ከማሁ 156

ሲፈቀድ ማስረጃው ምን ምን ፍሬጉዳዮች ሊያረጋግጥ ይገባል? የሚል ይሆናል፡፡

በርግጥ የልጅነት ሁኔታ መኖር በህጉ ትርጓሜ የተሰጠው ስለሆነ በትርጓሜው መሠረት ከማህበረሰቡ አባላት የተወሰኑት በምስክርነት ቀርበው ልጁ የእገሌ ልጅ ነው ብለን እንገምታለን በማለት የግምታቸው መሠረትም ካቀረቡ በቂ ነው ሊባል ይችል ይሆናል፡፡ የህጉን ድንጋጌዎች እንዱ ከሌላው ነጥለን ከተረዳናቸውና (mechanical understanding of the law) አንቀጽ 156ም ለብቻው ነጥለን ከተገነዘብነው እዚህ መደምደሚያ ላይ እንደርስ ይሆናል፡፡

ነገር ግን ይህ በቂና ተገቢ አይመስለንም ምክንያቱም የእህት ልጅ ወይም የወንድም ልጅ አብሮ ሲኖር የቤተሰቡ ሁኔታና ግንኙነት ባግባቡ ያልተገነዘበ ሰው ልጁ ከሰውየው ጋር ወጣ ገባ ማለቱን በማየትና በመሳሰሉት ሁኔታዎች የሰውየው ልጅ ነው ብሎ ግምት መውሰድ ይችላል፡፡ ግምቱ ተጨባጭ ይሆን ዘንድ ግን ምስክሩ የልጁ እናት ማን መሆኗን ማወቅ ከዚያም አልፎ የልጁ እናት አባት ነው እንዲባል ከተፈለገው ሰው ጋር ያላት ወይም የነበራት ግንኙነት አስመልክቶ ምስክርነቱን ሊሰጥ ይገባል፡፡ ስለዚህ በዚህ ረገድ መመስከር ያለበት ፍሬነገር ልጁ የእገሌ ልጅ ነው ብለን እንገምታለን በሚል ብቻ የታጠረ ሳይሆን የልጁ እናትና አባት ጋብቻ ፈፅመው ልጁን የወለዱ መሆናቸው ወይም ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ ልጁ ከአብራካቸው የተወለደ መሆኑን ወይም ከእነዚህ ግንኙነቶች ውጪ በሆነ ሁኔታ የልጁ እናትና አባት ልጁን መውለዳቸውና አባትየው ልጅነቱን የተቀበለው መሆኑን እንደሚያውቁ እንዲያስረዱ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በመሆኑም ፍርድቤቶች ፍትሃዊና ህጋዊ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ሲሉ ለምስክሮቹ በሚያቀርቧቸው የማጣሪያ ጥያቄዎች ላይ አመስካከሩ በእነዚህ ጭብጦች ዙሪያ እንዲያጠነጥን በአግባቡ ሊመሩት ይገባል ብለን እናስባለን፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ "ይህ ልጅ የእገሌ ልጅ ነው ብለን እንገምታለን" ስለተባለ ብቻ በቂ ምስክርነት ነው ከተባለ ከሦስቱም የአባትና ልጅ ግንኙነት መፍጠሪያ ሥርዓቶች (Establishment of paternity) ውጪ በሆነ ሁኔታና በአቋራጭ በዚሁ "የልጅነት ሁኔታ መኖር" በሚለው በኩል የአባትና የልጅ ግንኙነት እንዲፈጠር በር የሚከፍት ነው፡፡ እንዲህ ሲሆን የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 125 ዋጋ ቢስ የሚያደርግ አካሄድ ብቻ ሳይሆን የልጅነት ሁኔታ መኖር የማስረጃ ዘርፍ መሆኑ ቀርቶ ራሱን የቻለ አራተኛ የአባትና የልጅ ግንኙነት መፍጠሪያ ሥርዓት ሆኖ እያገለገለ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የህግ አውጪው ሃሳብ የሚገኘው በእያንዳንዱ አንቀጽ ወይም ንዑስ አንቀጽ በተናጠል ሳይሆን በርእስ ጉዳዩ ላይ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘት ነው፡፡ ስለሆነም የህግ ድንጋጌዎች በተናጠል የሚታዩ ሳይሆኑ አንዱ ከሌላው ጋር ውስጣዊ አንድነትና (inherent unity) ትስስር እንዳላቸው መገንዘብ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡

ሌላው እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት ጉዳይ "የልጅነት ሁኔታ መኖሩ ከተረጋገጠ ፍርድ ቤቱ ልጅ ነው ሲል የህግ ግምት ይወስዳል" ተብሎ ተደንግጓል፡፡ ይህ ግን ለህፃኑ ጥቅም ሲባል ቀለል ባለ የማስረዳት ሸክም አባት ይኖረው ዘንድ ለማስቻል የተቀመጠ የህግ ግምት በመሆኑ ይህንን ግምት የማስተባበል ሸክም አባት ነው ወደተባለው ሰው የማዞር ውጤት ይኖረዋል እንጂ ማስተባበል የማይፈቀድበት የህግ ግምት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ህግ አውጪው ማስተባበል የማይፈቀድበት የህግ ግምት (Irrebutable presumption) ሊያደርገው አስቦ ቢሆን ኖሮ ሁሌም እንደሚያደርገው ይህንኑ በግልጽ ጠቅሶ ያስቀምጠው ነበር ተብሎ ይታመናል፡፡ ህግ አውጪው ዝም ባለበት ሁኔታ ግን ሊወሰድ የሚገባው ግምት ሊስተባበል የሚችል (rebuttable presumption) ተደርጎ መወሰዱ አግባብ ነው እንላለን፡፡ እንዲያውም በአንቀጽ 157(2) ሥር ግምቱን ማፍረስ እንደሚቻል በግልጽ ተመልክቷል፡፡

ስለዚህ የልጅነት ሁኔታ መኖሩ ከተረጋገጠ አባት ነው የተባለው ሰው ይህን የህግ ግምት የሚያፈርስበት የህግ መሠረት ካለው እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ እድል ሊሰጠው ይገባል፡፡ ለምሳሌ ልጁ የልጅነት ሁኔታ መኖሩ ካረጋገጠ በኋላ አባት ነው እንዲባል የተፈለገው ሰው ከልጁ እናት ጋር በህግ የታወቀ ግንኙነት ("ማለትም ጋብቻ ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር) እንዳልነበረ ካስረዳ ወይም ልጁን በህጉ በተመለከተው መሠረት እንዳልተቀበለው ካረጋገጠ ወይም በፍርድ ውሳኔ "አባት ነህ" እንዳልተባለ ካስረዳ የህግ ግምቱ ሊናድና ሊፈርስ ይገባል የሚል እምነት አለን፡፡

ለነገሩ የልጅነት ሁኔታ መኖር እንደማስረጃ መቅረብ ያለበት መጀመሪያውኑ የልጁ እናትና አባት እንዲባል የተፈለገው ሰው በህግ የታወቀ ግንኙነት ማለትም በጋብቻ ወይም ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ የተወለደ ልጅ ሲሆን ነው የሚል ጠንካራ ክርክር[72] አልፎ አልፎ ሲቀርብ ይደመጣል፡፡ ለዚህ አቋም እንደምክንያት የሚቀርበውም ልጅነት የመቀበል ሥርዓት በጽሁፍ ካልሆነ ውጤት የለውም

[72] ቁጥራቸው ቀላል በማይባል የቤተሰብ ክርክር ፋይሎች ውስጥ ጠበቆች ይህንን የክርክር መስመር ይዘው የተከራከሩባቸው መዛግብት አይተናል፡፡ በፍርድ ውሳኔ ደረጃም ይህንን የክርክር መስመር የሚቀበሉ የፍርድ ውሳኔዎች አጋጥመውናል፡፡ በዕለት ተእለት ከሙያ ባልደረቦች ጋር በምናካሂዳቸው መደበኛ ያልሆኑ ውይይቶችም ተመሳሳይ ነጥቦች ሲነሱ አስተውለናል፡፡ የክርክር ነጥቡ ራሱም አሳማኝ መስሎ ይታያል፡፡

የሚል ህግ አለን፡፡ በፍርድ ውሳኔ አባትነት ሲወሰንም ይህንኑ የሚያረጋግጥ በጽሁፍ የተቀመጠ ፍርድ መኖሩ አይቀርም፡፡ ስለሆነም በህግ ግምት አባትነት ከሚታወቅበት ጉዳይ ውጪ ባሉት ሁኔታዎች እነዚህን የተጻፉ ሰነዶች ማቅረብ እየተቻለና እነዚህኑ ማቅረብ ሲገባ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ባስረዳ ተብሎ ወደሰው ምስክርነት ለመሸጋገር የሚፈቀድበት አሳማኝ ምክንያት የለም በሚል ነው፡፡

ህጉ ግን በዚህ ረገድ ግልጽ ሆኖ የተቀመጠ ባለመሆኑ ይህ አቋም እንዳለ ለመቀበል የሚያስቸግር ይመስላል፡፡ ሆኖም ግን የልጅነት ሁኔታ መኖር በህግ በታወቀ ግንኙነት ውስጥ ለተወለዱ ልጆች ብቻ የሚያገለግል ሳይሆን ለሌሎቹ የአባትና ልጅ ግንኙነት መፍጠሪያ ዘዴዎችም ጭምር ያገለግላል ከተባለም የአገልግሎቱ አድማስ የልጅነት መቀበያ የጽሁፍ ሰነድ የመኖር አስፈላጊነትና የልጅ አባት አንተ ነህ የሚለውን የፍርድ ውሳኔ የማቅረብ አስፈላጊነትና ግዴታ ፋይዳ በማያሳጣ መልክ መከናወን ያለበት ይመስለናል፡፡

የፍርድ ቤቶቻችን የእለት ተእለት ውሳኔዎች ግን ቀደም ሲል እንደገለጽነው አንድ ወጥ አይደሉም፡፡ ጥቂቶቹን ቀጥለን ለማየት እንሞክራለን፡፡

በአንድ ወቅት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ በቀረበ ጉዳይ ላይ በሚከተለው መደምደሚያ ላይ ተደርሶ ነበር፡፡ ጉዳዩ ከጋብቻ ውጪ በተፈጸመ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የተወለደችን ልጅ (ማርያ) ልጅነት እንዲረጋገጥ የቀረበ ጥያቄ ነበር፡፡ ይህንኑ "በልጅነት ሁኔታ" መኖር መረጋገጡን በመቀበል ፍርድ ቤቱ እንዲህ ብሎ ነበር፡፡

"....... ምስክሮቹ የሰጡት ቃል ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ የሚገኝ ስለሆነ ተመልክተነዋል፡፡ እንደተመለከትነውም በማርያ እናትና በጆርጅ (አባት ነው እንዲባል በተፈለገው ሰው) መካከል ረዘም ላለ ጊዜ የቆየ ግንኙነት እንደነበረ፣ ጆርጅ አልፎ አልፎም ቢሆን ከማርያ ጋር እያደረ ይሄድ እንደነበረ፣ በዚህ መሃልም ማርያ መወለድዋንና ጆርጅ እቤት ድረስ እየመጣ" ልጄ ነች በማለት ያቅፋት እንደነበር "ማርያ" ብሎም ስም ያወጣላት እርሱ መሆኑን ከዚህ በተጨማሪም እስከእለተ ሞቱ ድረስ አባት ለልጁ የሚያደርገውን ሁሉ ሲያደርግላት እንደነበር እንደሚያስረዱ ተገንዝበናል፡፡

እንግዲህ ከምስክሮቹ አመሰካከር ልንረዳ የቻልነው በይግባኝ ባይ (የማርያ እናት) እና በጆርጅ መካከል የቆየ ግንኙነት መኖሩን ብቻ ሳይሆን ይህ ግንኙነት ለማርያ መወለድ ምክንያት መሆኑን ጭምር ነው፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ማርያ ከተወለደች በኋላ ጆርጅ ያሳየው የነበረው ድርጊት ልጂቱ የሱ መሆንዋን ለመገመት የሚያስችል እንደሆነ ነው ከምስክሮቹ አመሰካከር መገንዘብ የሚቻለው፡፡ የምስክሮቹ ቃል የዚህ ዓይነት ግምት ለመውሰድ የሚያስችል ከሆነ ደግሞ ይግባኝ ባይ ልጅነትን በልጅነት ሁኔታ መኖር ለማስረዳት ችላለች ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 157(1) እንደተደነገገው እኛም ማርያ የጆርጅ ልጅ ነች የሚል የህግ ግምት ወስደናል"[74] ብሏል፡፡

[74] የፍትሐብሄር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1536/88 (ፌ/ጠ/ፍ/ቤት)

በሌላ ጊዜና በሌላ ጉዳይ ደግሞ ጭብጡ ከዚህ በፊ ከተመለከትነው ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የተለየ መደምደሚያ ላይ ደርሷል:: በርግጥ በዚህ ጉዳይ ፍርድ ቤቱ ለውሳኔው መሠረት ያደረገው የነባሩ የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎችን ነው:: ቢሆንም በዚህ ረገድ ከተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ድንጋጌዎች ጋር የጎላ ልዩነት ስለሌላቸው ጉዳዩና መደምደሚያው አሁን ለያዝነው ጉዳይም አግባብነት ያለው ነው:: እንግዲህ ጉዳዩ የሚከተለውን ይመስላል::

> አመልካች(እናት) ልጇ ፍቅርተ ካሳሁን ከአቶ ካሳሁን ውቤ ጋር ባደረግኩት ከጋብቻ ውጪ ግንኙነት የወለድኳት ሲሆን ልጅ ከመውለዴ በፊት ገንዘብ ሲረዱኝ የቆዩ ሲሆን በወለድኩም ጊዜ የገንፎ እህል ልከውልኝ እንዲሁም ለክርስትና ጤፍና ገብስ ልከውልኛል:: ልጅቷንም ለልብስ፣ ለት/ቤትና ለቀለብ የሚሆን ገንዘብ እየሰጡ ይረዱኝ ነበር:: አቶ ካሳሁን በ30/9/82 ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ የፍቅርተ ካሳሁን ልጅነት ይታወቅልኝና ማስረጃ ይሰጠኝ ብለው አመለከቱ::

የሟች ህጋዊ ሚስት የነበሩት በተቃዋሚነት ቀርበው ፍቅርተ ከባለቤቴ ለመወለድዋ የቀረበ ማስረጃ የለም:: ባለቤቴ በህይወት እያለ ልጅነቷን አልተቀበላትም:: <u>ልጅነት በሰው ምስክርነት ማረጋገጥ የሚቻለው እንደባልና ሚስት አብረው በመኖር ላይ እያሉ የተወለደ በሆነ ጊዜ ብቻ ነው</u>::ብለው ተከራከሩ:: (ሠረዝ የተጨመረ)

ፍ/ቤቱም የአመልካችን ምስክሮች አስቀርቦ በሰጡት የምስክርነት ቃል ፍቅርተ ካሳሁን ከአቶ ካሳሁን ውቤ የተወለደች መሆኑን ይህንንም ለማለት የቻሉት አቶ

ካሳሁን ውቤ ከወ/ሮ ጌጤነሽ ይማም (አመልካች) ጋር ወጣ ገባ ይሉ እንደነበር እና ለክርስትናም እህል መላካቸው የገለጹ ሲሆን አቶ ካሳሁን እና ወ/ሮ ጌጤነሽ በአንድ ቤት ሲኖሩ እንደማያውቁ መስክረዋል::

ፍ/ቤቱም በበኩሉ አባትነት የሚረጋገጥበት መንገድ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 740(1) ፣ 741 እና 745 እንደተደነገገው ከእናቲቱ ጋር ጋብቻ የፈጸመ ባል ወይም ከጋብቻ ውጪ በግብረ ሥጋ ግንኙነት በፍ/ህ/ቁ. 740(2) 746 747 እና 748 መሠረት የልጅ አባት መሆኑን በጽሁፍ ያረጋገጠ እንደሆነ ወይም እናቲቱ ላይ የመጠለፍ ወይም የመድፈር ወንጀል ፈጽሞ የተቀጣ ሰው በውሳኔ አባት እንደሚባል በፍ/ብ/ህ/ቁ. 740(3) እና 750 ተመልክቷል:: ልጅነት ከሚታወቅበት መንገድ አንዱ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ መሆኑን የፍ/ብ/ህ/ቁ. 770 እና 771 በምስክር ተመልክቷል:: <u>ይህ የሚያገለግለው ግን ልጅ የተወለደው በጋብቻ ወይም ከጋብቻ ውጭ በሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት አብሮ መኖር የተወለደ ሲሆን</u> ነው በሚል አቤቱታውን በርሀ ፍቅርተ የአቶ ካሣሁን ውቤ ልጅ አይደለችም በማለት ወሰነ::(ሠረዝ የተጨመረ)

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ሃተታ እንዲህ ይላል::

"ይግባኝ ባይ (የፍቅርተ እናት) ከሟች ከአቶ ካሳሁን ውቤ ጋር በጋብቻ ወይም ከጋብቻ ውጪ በሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት አብረን ስንኖር ልጅቷ ተወለደች አላሉም፣ ወይም አቶ ካሳሁን ፍቅርተ ልጄ ናት ሲሉ አባትነታቸውን ያረጋገጡበት ጽሁፍ አላቀረቡም፣

Scanned by CamScanner

አለበለዚያም ፍቅርተ የተወለደችው ከአቶ ካሳሁን በደረሰባቸው መጠለፍ ወይም መደፈር መሆኑን በፍርድ አላረጋገጡም፡፡ የይግባኝ ባይ ክርክር አቶ ካሳሁን የፍቅርተ አባት መሆናቸው በምስክርነት አረጋግጠለሁ የሚል ነው፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ 748(1) አባት ልጁ ነው በማለት የማወቁ ሁኔታ በጽሁፍ ካልሆነ ውጤት እንደሌለው ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ አባትነትን በምስክር ማረጋገጥ እንደማይቻል በግልጽ አስቀምጦታል፡፡ ስለዚህ ይግባኝ ባይ ፍቅርተ ካሳሁን የአቶ ካሳሁን ልጅ ናት በማለት ላቀረቡት ክርክር በህግ የተደገፈ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔን አጽንተነዋል[75]" ብሏል፡፡

በሌላ ጉዳይ ደግሞ ይኸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከዚህ በላይ ከተመለከተው ለየት ያለ አቋም ወስዶ ነበር፡፡ ጉዳዩ ከጋብቻ ውጪ እንዲያውም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር በሌለበት ሁኔታ የተወለደች ልጅ አባት እንዲባል የተፈለገው ሰው በሞት ከተለየ በኋላ የልጅነት ማስረጃ እንዲሰጣት ጥያቄ ታቀርባለች፡፡

አባት እንዲባል የተፈለገው ሰው ወራሾች ደግሞ በተቀዋሚነት ቀርበው.... ትእግስት ሽፈራው (አመልካች) ነኝ ያለችውን ሟች ሻምበል ሽፈራው ደምሴ በህይወት በነበሩበት ጊዜ ልጄ ናት ብለው ለቤተሰቦቻቸው ያላስተዋወቋትና የሟች ወራሾችም የማያውቋት መሆኑን ሟችም በፍ/ብ//ህ/ቁ. 747 እና 748 መሠረት

[75] የፍትሐብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1768/88 (ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት)

ልጄ ናት ብለው በጽሁፍ የተቀበሉበት መንገድ ስለሌለ በአጠቃላይ የቀረበው ጥያቄ መሠረዝ እንደሚገባው የሚገልጽ የክርክር ሁኔታ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን የስተናገደው የሥር ፍርድ ቤትም በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 708 እና 740(1) መሠረት አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ከጋብቻ ውጭ በግብረሰጋ ግንኙነት እንደባልና ሚስት መስለው አብረው ሲኖሩ ተፀንሶ የተወለደው ልጅ ከሆነ በሰው ምስክር በማረጋገጥ ከሴትዮዋ ጋር የነበረው ወንድ አባት ስለመሆኑ ማስረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ ውጭ በሆነ በግብረሰጋ ግንኙነት የተወለደ ልጅ ከሆነ ግን አባትነትን ማስረዳት የሚቻለው አባትነቱን ያወቀበትን ወይም የተቀበለበትን የጽሁፍ ማስረጃ በማቅረብ ብቻ ስለሆነና አመልካችም ይህንኑ ህጉ የሚጠይቀውን የጽሑፍ ማስረጃ በማቅረብ ስላላየያዘች ጥያቄዋ ቀጥሎ ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡ እናቷ ከሟች ቤት በሠራተኛነት ገብታ እንደተወለደች እየተናገረች በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ላይ ምስክር ማሰማት ጠቀሜታ ስለማይኖረው ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኖ መዝገቡን በመዝጋት አሰናበትናቸው፡፡

በዚሁ መነሻነትም ወ/ት ትእግስት (የስር አመልካች) ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቀረበች፡፡ይዘቱም የልጅነት ጉዳይ በሰው ማስረጃነት ለማስረዳት የቆጠርኳቸውን ምስክሮች ፍ/ቤቱ ሳይሰማና በህጉ አግባብ ሳይረጋገጥ በጽሁፍ ማስረጃ ካልሆነ ማስረዳት አይቻልም በማለት ጥያቄውን ያለአግባብ ውድቅ አድርጎብኛልና በይግባኝ ይታረምልኝ የሚል ነበር፡፡

Scanned by CamScanner

ይህንኑ ጉዳይ በይግባኝ የመረመረው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት፡ "....የልጅነት ሁኔታ መኖርን በሚረጋገጥ ወይም በአንዲት ሴትና ወንድ መካከል ተፈጸመ የተባለን የግብረሥጋ ግንኙነት በሚረጋገጥ አባትነቱን ማስረዳት ይቻላል አይቻልም የሚለው ማስረጃ ከተመናተተ በኋላ ከሆኑ አኳያ ታይቶና ተረጋግጦ የሚወሰን እንጂ ከመነሻው ማስረጃውን በመግታት ወደፊት ማስረጃው ውጤት ሊኖረው አይችልም የሚል ሃሳብ በመያዝ መሆን የሚገባው አይደለም፡፡ <u>ይግባኝ ባይ ባመለከተችው መንገድ ምስክር ለማቅረብና ለማሰማት የሚከለክል ሀግ የለም</u> በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔን በፍ/ሥ/ሥ/ሀ.ቁ. 348/1/ መሠረት በመሻር መዝገቡ እንደገና ተንቀሳቅሶ ምስክሮቹ ተሰምተው ግቹ ቫምበል ሺፈራው ደምሴ በሆኑ አግባብ አባቷ ሊሰኝ የሚችሉ መሆን ያለመሆን ተረጋግጦ[76] እንዲወሰን" በማለት መዝገቡን ወደ ስር ፍ/ቤት መልሶ ልኮታል፡፡ (ሠረዝ የተጨመረ)

ከዚህ በላይ በናሙናነት ከተረቡ ጉዳዮች መገንዘብ የሚቻለው "የልጅነት ሁኔታ መኖር" የሚባለው የማስረጃ ዘርፍ የተፈጻሚነት ወሰን የት ላይ ነው? በሚለው ነጥብ ላይ በዳኞቻችን መካከል የሃሳብ ልዩነት እንዳለ ነው፡፡ አንዳንዶች የልጅነት ሁኔታ መኖር እንደማስረጃ በሰው ምስክርነት መጠቀም የሚፈቀደው የልጁ እናትና አባት ነው እንዲባል የተፈለገው ሰው ቢጋቡ ወይም ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው በመኖር አያሉ የተወለደ ልጅ ከሆነ ብቻ ነው የሚል ሃሳብ አላቸው፡፡ ለዚህም ምክንያታቸው ሌሎቹ ማለትም ልጅነትን መቀበልም ሆነ በፍርድ ውሳኔ አባት ነህ በሚባልበት ስርዓት ሥር የልጅነት ማስረጃው ልጅነቱን የተቀበለበት ሰነድ ወይም

[76] የፍትሐብሄር መዝገብ ቁጥር 901/88 (ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት)

የፍርድ ውሳኔው ግልባጭ ቀድም ብለው የተዘጋጁ ማስረጃዎች (Pro-constituted proof) መኖር ስላለባቸው እነዚህን በማቅረብ መከናወንና መወሰን ያለበት ነው በሚል ነው፡፡

ሌሎች ደግሞ "የልጅነት ሁኔታ መኖር" በማስረጃነት የሚያገለግለው ህጋዊ ግንኙነቶች ተብለው በህግ በሚታወቁት ግንኙነቶች ውስጥ ለተወለዱ ልጆች ብቻ ሳይሆን በልጅነት መቀበልም በኩል ሆነ በፍርድ ውሳኔ አባት ነህ በተባለበት ሁኔታም ቢሆን የሚያገለግል ነው የሚል ሃሳብ አላቸው፡፡ ለዚህ አቋም እንደማጠናከሪያ የሚቀርበው ነጥብም የልጅነት ሁኔታ መኖር የሚለው ፅንሰ ሃሳብ ያለበት የህጉ ክፍል ራሱ በጥቅሉ "የልጅነት ማስረጃ" በሚል ሥር የተቀረፀ ስለሆነ ይህ ክፍል በህግ ከታወቀ ግንኙነት ለተወለዱ ልጆች ብቻ የሚያገለግል ነው ብሎ ደፍሮ ለመከራከር ያስቸግራል ባዮች ናቸው[77]፡፡

በርግጥ ቀደም ሲል እንደገለጽነው የህጉ አቀራረጽና ይዘት ሁለቱንም የክርክር መስመሮች ለመውሰድ በር የሚከፍት ሆኖ ይታያል፡፡ ሆኖም ከነዚህ ሁለት የክርክር መስመሮች የተውጣጣ አማካይ መስመር መፍጠር የሚቻል ይመስላል፡፡ ይኸውም የልጅነት ሁኔታ መኖር በአጠቃላይ "የልጅነት ማስረጃ" በሚል ክፍል ስር የተቀመጠ ስለሆነ የተፈጻሚነት ወሰኑ በህግ በታወቀ ግንኙነት ውስጥ ለተወለዱ ልጆች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የአባትና ልጅ ግንኙነት መፍጠሪያ ስርዓቶች እንደማስረጃ ሊያገለግል ይገባል ማለት ይቻላል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ግን የልጅነት ሁኔታ መኖሩ መረጋገጡ ፍ/ቤቱ ሰውየው የልጁ አባት

[77] ለነገሩ "ልጅን ስለመካድ" የሚለው ጽንሰ ሃሳብም ራሱ በጥቅሉ ለማንኛውም ልጅ በሚያመለክት መልክ የቀረበ ቢሆንም ወደይዘቱ ስንገባ ግን በህግ ግምት አባትነት ለሚታወቅበት ሥርዓት እንጂ ለሌሎች የአባትና ልጅ ግንኙነት መፍጠሪያ ሥርዓቶች ማለትም ልጅነት ለመቀበል ወይም በፍርድ ውሳኔ አባትነት ለሚታወቅበት ሥርዓት የመካድ ክስ እንደማያገለግል ተመልክተናል፡፡ እዚህም ላይ ተመሳሳይ አ ም መውሰድ ይቻላል፡፡

Scanned by CamScanner

ነው የሚል ግምት እንዲወሰድ የሚያስችልና የማስተባበል ሸክም አባት ነህ ወደተባለው ሰው የሚያዞር እንጂ የመጨረሻ ውሳኔ የሚያስጥ ማስረጃ ተደርጎ ሊወሰድ ግን አይገባም ባዮች ነን፡፡ በመሆኑም አባት ነህ የሚል ግምት ያረፈበት ሰው ይህንኑ ግምት የሚያፈርስበት ማስረጃ ካለው ይህንኑ እንዲያቀርብ እድል ሊሰጠው ይገባል፡፡ ይህንን ለማፍረስ ሊቀርቡ ከሚችሉ ማስረጃዎች ጥቂቶቹ ደግሞ በተለይ ልጁ በህግ ከታወቀ ግንኙነት ውጪ የተወለደ ከሆነ ልጅነቱን የተቀበለክበት ጽሁፍ አልተረበም ወይም አባት ነህ ተብዬ የተወሰነብኝ የፍርድ ውሳኔ አልተረበም የሚሉ ሊገኙበት ይችላሉ፡፡

ምናልባትም ይህ ጉዳይ ጋብቻን በትዳር ሁኔታ ከማስረዳት ጋር አያይዞ መገንዘብ ተገቢ ይሆናል፡፡ ጋብቻ መፈፀሙን በትዳር ሁኔታ ማስረዳት እንደሁለተኛ ደረጃ ማስረጃ እንደሚወሰድ በዚህ መጽሐፍ በቅጽ አንድ አይተናል፡፡ አንደኛው ወገን በትዳር ሁኔታ ጋብቻ መፈጸሙን ካስረዳ ፍርድቤቱ ጋብቻ ተፈጽሟል ሲል ግምት ይወስዳል፡፡ ነገር ግን ሌላኛው ወገን ከጋብቻ ማስፈጸሚያ ሦስት ሥርዓቶች በአንዱ እን ጋብቻ አለመፈጸሙን ካሳየ ፍርድቤቱ ቀደም ሲል ይዞት የነበረው ግምት ውድቅ ሊያደርግ እንደሚገባ አመልክተናል፡፡ በዚህ ጉዳይም ልንከተል የሚገባን ሥነ-አመክንዮ (ሎጂክ) ይህንኑ መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል እንላለን፡፡ ከዚህ ጋር አብሮ መወሳት ያለበት ነጥብ ላላና ቀለል ያለ የልጅነት ማስረጃ ተግባራዊ ማድረግ ህፃናት ያለአባት እንዳይቀሩ በማድረግ ረገድ አዎንታዊ ውጤት ይኖረዋል ሊባል ቢችልም በመደበኛው ማስረጃ ልጅ መሆን የማይገባው ሰውም ልጅ ነው እየተባለ የሌሎች ህጋዊ ልጆችን መብት የማጥበብ አሉታዊ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል መገንዘብ ጠቃሚ ነው፡፡

ምዕራፍ ሁለት
ስለ ጉዲፈቻ ሥርዓት

8.1. አጠቃላይ የመነሻ ሃሳብ[78]

‹ጉዲፈቻ› የኦሮሚኛ ቃል ሲሆን በአማርኛም "የጡት ልጅ" ወይም "የማር ልጅ" በሚል መጠሪያ ይታወቃል፡፡ በይዘቱም ከሌላ ሰው አብራክ የተገኘን ልጅ ከሌላ ሰው የተወለደ መሆኑን አምኖና ተቀብሎ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መብቱን ጠብቆ እንደልጅ ማሳደግ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡

እንደሚታወቀው የተፈጥሮ ወላጅ ለህፃናት የተሟላ ሁለንተናዊ እድገት ወሳኝ ነው፡፡ ህፃናት ከተፈጥሮ ወላጅ የሚያገኙትን ደስታ፣እንክብካቤና ፍቅር ምትክ እንደሌለው የማህበራዊ ደህንነትና የሥነ-ልቦና ሊቃውንት የሚያረጋግጡት ሲሆን ህብረተሰቡም በልማድ የሚቀበለው ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ችግሮች ሳቢያ ህፃናት ወላጆቻቸውን የሚያጡበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ በአካልም ሆነ በአእምሮ ያልበሰሉ ህፃናት የተሟላ እድገታቸው ተስተጓጉሎ ላልታሰበ ችግርና አደጋ ይጋለጣሉ፡፡ ታዲያ ይህ ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ እነዚህን ህፃናት የማሳደጉና ለእነከለመጠን የማድረሱ ሃላፊነት በመንግስትና በህብረተሰቡ ዘንድ መውደቁ አይቀሬ ይሆናል፡፡

[78] ይኸኛው የጽሑፉ ክፍል አቶ ተድላ ደረሰ "የጉዲፈቻ አገልግሎት በኢትዮጵያ" በሚል ርእስ ሥር በቤተሰብ ህጉ ረቂት ላይ በተደረገ ውይይት በ1991 ዓ.ም. ካቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ የተወሰደ ነው፡፡ (ያልታተመ)

Scanned by CamScanner

የተለያዩ መንግስታትና ህብረተሰቦች ይህንን ፃላፊነታቸውን ለመወጣት ከረዥም ዘመናት አንስተው መፍትሔ ሲያፈላልጉ የቆዩ ሲሆን የጉዲፈቻ ሥርዓት ማመቻቸት ከመፍትሄዎቹ አንዱ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ጉዲፈቻ የተጀመረው በግብፅ ሲሆን በግሪኮችና በሮማዊያን ዘንድም ከረዥም ጊዜ አንስቶ ሲሠራበት እንደነበረ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡ በዓለም ታሪክ የተፃፉ ህጎች ሲጠቀሱ ቀዳሚ ሆኖ የሚጠቀሰው የሀሙራቢ ህግም ጉዲፈቻን የሚመለከቱ አንቀጾች እንደነበሩት በጥናት ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ በተለያዩ ሃገራት የሚከናወኑ የጉዲፈቻ ግንኙነቶች እንደየአገሮቹ ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ እድገት የተለያዩ ናቸው፡፡

ጥንታዊው የህብረተሰብ የአኗኗርና የአስተዳደር ሥርዓት የቆሚና የማይንቀሳቀስ ንብረትን የወራሽነት መብት ለወንድ ብቻ የሚሰጥ ስለነበረ ወንድ ልጅ ያልነበራቸው ቤተሰቦች ከሌላ አብራክ የተገኙ ልጆችን በጉዲፈቻ ልጅነት በመቀበል የዘር ግንዳቸውን ቀጣይነት በማረጋገጥ የሃብታቸው ወራሽ ለማድረግ ይጣጣሩ ነበር፡፡ ስለሆነም ጥንታዊው ጉዲፈቻ እንደዘመናዊው ጉዲፈቻ ህፃኑን በመርዳት ላይ ያተከረ ሳይሆን የወራሽነት መብትን ለማስጠበቅ ወይም ህፃኑን ከቤተሰባቸው ጋር በመቀላቀላቸው ብቻ ከፈጣሪ ዘንድ ሙገሳና ጽድቅ እንደሚያገኙ በማመን የሚያከናውኑት ነበር፡፡

በአውሮፓ ክፍለ ዓለም የጉዲፈቻ ሥራ በስፋት እየተለመደ የመጣው በአንደኛው የዓለም ጦርነት ምክንያት በርካታ ህፃናት ወላጆቻቸውን በማጣታቸውና ከጋብቻ ውጪ በሚወለዱ ህፃናት መብዛት ምክንያት ሲሆን በቀጣይነትም በሁለተኛ የዓለም ጦርነት ወቅት እነዚህኑ ህፃናት በጉዲፈቻ መርዳት ጠቃሚ መሆኑን ሳይኮሎጂስቶች፣ ሳይካትሪስቶችና

የማህበራዊ ደህንነት ባለሙያዎች ከፍተኛ ግፊት በማድረጋቸው እንደሆነ በጥናት ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ጉዲፈቻ በህግ እየተደገፈና እየተጠናከረ በእንግሊዝ፣ በፈረንሳይ፣ በጀርመን ፣ በስዊድንና በሌሎችም ሃገሮች በስፋት በሥራ ላይ መዋል ቀጠለ፡፡

በኢትዮጵያ ጉዲፈቻ ጎልቶ የሚሰራበት በኦሮሞ ማህበረሰብ ሲሆን በባህላዊው መንገድ ለረዥም ዘመናት በሰፊው ሲሰራበት የኖረ አገልግሎት ነው፡፡ ቃሉም ራሱ የተገኘው ከዚሁ ማህበረሰብ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ከዚህም አልፎ በጊዜ ሂደት በአማራው ማህበረሰብ ዘንድ "የጡት ልጅ" ወይም "የማር ልጅ" በሚል ስም ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ አገልግሎት ሲሰጥ ይታያል፡፡

በኦሮሞ ማህበረሰብ ጉዲፈቻ የሚካሄደው ባብዛኛው ሰዎች ወንድ ልጅ መውለድ ሳይሳካላቸው ሲቀርና የወንድን የዘር ሃረግ ግንድ ለማስተላለፍና የሃብት ወራሽ ለማግኘት፣ ሰዎች የወለድዋቸው ህፃናት በተከታታይ ሲሞቱባቸው ለሌላ ሰው በጉዲፈቻ ቢሰጡ ያድጉልናል ብለው ስለሚያምኑ፣ መውለድ ያልቻሉ ቤተሰቦች የጉዲፈቻ ልጅ ቢወስዱ መውለድ እንደሚችሉ በማመን፣ በእርጅናና በድካም ዘመን ጧሪና ቀባሪ ለማግኘት በማሰብ መሆኑ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በአማራው ባህል ወላጅና አሳዳጊ ያጡ ህፃናትን የሚያሳድጉ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ መሃኖች የሆኑና ጧሪ ቀባሪና የሃብት ወራሽ ለማግኘት ሲሉ ሲሆን መነኩሳትና ሌሎች ግን የጡት ልጅ ወይም የማር ልጅ የሚይዙት ለዕድቅና መንግስተ ሰማያት ለመውረስ ነው፡፡ የጉዲፈቻ አሰራር በተለያዩ የሃገራችን ብሄረሰቦች ዘንድም በተለያየ ስምና ለተለያየ ዓላማ እንደሚካሄድ ይነገራል፡፡

ይህ ሁሉ ሲታይ በአለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በሃገር አቀፍ ጥንታዊው የጉዲፈቻ ሥርዓት የጉዲፈቻ ልጅን ጥቅም ግምት ውስጥ የሚያስገባ ነበር ለማለት የሚያስደፍር አይደለም። ይልቁንም ጉዲፈቻው ይከናወን የነበረው ጉዲፈቻ አድራጊውን ለመጥቀም ሲባል ነበር ለማለት ይቻላል። ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ጉዲፈቻ አድራጊው በሚያረጅበት ወይም እርዳታ በሚያሻው ወቅት የጉዲፈቻ ልጅ ተፈላጊው ግልጋሎት እንዲያበረክትለት በማሰብ የሚደራጅ የጉዲፈቻ ሥርዓት ቁጥሩ ቀላል አልነበረም። በጉዲፈቻ አድራጊው ቤተሰብና በጉዲፈቻ ተደራጊው ልጅ ቤተሰብ መካከል ዝምድና ለመፍጠር ሲባልም ጉዲፈቻ ይፈጸም እንደነበር የታሪክ መዛግብት ይጠቁማሉ። ለጽድቅ ተብሎ የሚከናወን ጉዲፈቻም የማይናቅ ቁጥር ነበረው።

ነገር ግን ዘመናዊው የጉዲፈቻ ሥርዓት ከዚህ በዓይነቱ የተለየ ነው። ጉዲፈቻ እንዲደረግ የሚፈለገው በዋናነት የልጅን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል ነው። በርግጥ በዚህ ሂደትም ጉዲፈቻ አድራጊውም ተጠቃሚ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል። ይህ ግን አግረ መንገድ (incidental) እንጂ ዋናው ግብ ተደርጎ አይወሰድም። ከዚህ አንፃር የ1952ቱ የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ህግም ይህንኑ ዓላማ ለማክበር ሙከራ ያደረገ ይመስላል። ለዚህም በቁጥር 805 ሥር የጉዲፈቻ ልጅ ለመሆን የሚያስፈልገው ትክክለኛ ምክንያት ሲኖርና ጉዲፈቻ ለሚሆነው ልጅ ጥቅም ያለው ሆኖ ሲታይ ብቻ ነው። (ሥረዝ የተጨመረ) በሚል ተደንግጎ ይገኛል። ነገር ግን ከፍትሐብሔር ህጉ መውጣት በኋላም ቢሆን ባህላዊው የጉዲፈቻ ሥርዓት በጽሁፍ ከተቀመጠው ህጋዊ ሥርዓት ውጪ በባህሉ መሠረት መከናወኑ የቀጠለ ስለሆነ ህጉ ከወረቀት ያለፈ ፋይዳ ነበረው ለማለት የሚያስደፍር አይደለም።

ኢትዮጵያ በ1984 ዓ.ም. "የህፃናት መብት ኮንቬንሽን" በመባል የሚታወቅ አለም አቀፍ ሰነድ ማፅደቋ ይታወቃል። ይህ ሰነድ የህፃናትን መብትና ደህንነት በተመለከተ ብዙ ጠቃሚ ድንጋጌዎች የያዘ ሲሆን ከእነዚህም አንዱ በጉዲፈቻ ዙሪያ የተደነገገው በሰነዱ አንቀጽ 21 ውስጥ የተመለከተው ነው። በዚህ አንቀጽ ሥር የጉዲፈቻ ነገር ሲነሳ ዋናው መሠረቱ የህፃኑ ደህንነትና ጥቅም መሆን እንዳለበት በግልፅ አመላክቶአል። በፌዴራል ህገ-መንግስታችን መሠረት ሰነዱ የኢትዮጵያ የህግ ሥርዓት አካል ስለሆነ[79] በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ይህ እንዳለ ሆኖም የሰነዱ መሠረታዊ መርሆዎች በ1987 ዓ.ም. በጸደቀው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት ውስጥ ቃል በቃል ተጽፈው ይገኛሉ። በዚህም መሠረት ህፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግስታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፣ ፍርድቤቶች፣ በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በህግ አውጪ አካላት የህፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት[80]። (ሥረዝ የተጨመረ) የሚል ህገ-መንግስታዊ መርህ አለን። ጉዲፈቻ ደግሞ ቀደም ሲል እንዳየነው ህፃናትን ከሚመለከቱ እርምጃዎች አንዱ ነው። ከዚህም አልፎ ህገ-መንግስቱ "መንግስት ለእጓለማውታን ልዩ ጥበቃ እንደሚያደርግላቸው፣ በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻችና የሚያስፋፋ እንዲሁም ደህንነታቸውና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሠረቱ እንደሚያበረታታ"[81] ቃል ገብቷል።

[79] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አንቀጽ 9(4)
[80] ዝኒ ከማሁ 36(2)
[81] ዝኒ ከማሁ 36(5)

Scanned by CamScanner

እንግዲህ አሁን በሥራ ላይ ያለው የጉዲፈቻ ህጎችን መቃኘት ያለበት ከዚህ በላይ የተመለከተው ታሪካዊ አመጣጥና እድገት መሠረት በማድረግ ሊሆን ይገባዋል፡፡ በተለይም ከህገ መንግስታዊ መርሆና ኢትዮጵያ ካፀደቀችው የህፃናት መብት ኮንቬንሽንና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ሰነዶች አንፃር መመርመርና መፈጸም ያለበት ነው፡፡

8.2. የጉዲፈቻ ስምምነት

8.2.1. የስምምነቱ ወገኖች

ወደ ዋናው ጉዳይ ስንገባ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ጉዲፈቻ ሰው ሰራሽ (ህግ ሰራሽ) የዝምድና መፍጠሪያ ሥርዓት ነው፡፡ የዝምድናው መሰረትም የጉዲፈቻው አድራጊውና የጉዲፈቻ ልጁ ስምምነት ነው[82]፡፡ እንደ ስምምነቱ ህጋዊ ሂደቱን ተከትሎ ከተመሠረተ በኋላ ግን ህጉ ገብቶ "... የጉዲፈቻ ልጅ በማናቸውም ረገድ ቢሆን እንደጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ ይቆጠራል"[83] ይለዋል፡፡

የጉዲፈቻው ስምምነት በጉዲፈቻ አድራጊውና በጉዲፈቻ ልጁ መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው ብለናል፡፡ ቢሆንም ህጉ የተፀነሰ ልጅም በጉዲፈቻ ሊያዝ እንደሚችል[84] ይናገራል፡፡ እንዲሁም ልጁ አካለመጠን ያልደረሰ ከሆነ ስምምነት የመመስረት ስልጣን የለውም[85]፡፡ በጉዲፈቻ ልጅነት መያዝ የሚችለው ደግሞ እድሜው ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች

82 የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 180
83 ዝኒ ከማሁ 181
84 ዝኒ ከማሁ 187
85 ዝኒ ከማሁ 215(3) የጉዲፈቻ ስምምነት መፈፀሚያ ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል ህጋዊ ድርጊት በመሆኑ አካለመጠን ላልደረሰ የሚሰጠውን አይደለም ምክንያቱም በህግ በግልጽ የተፈቀደለት ብቻ የሰጣል

የሆነና አካለመጠን ያልደረሰ ሰው ነው[86]፡፡ ከዚህ አንፃር ታዲያ በጉዲፈቻ አድራጊውና በጉዲፈቻ ልጁ መካከል ስምምነት እንዴት ሊደረግ ይችላል? ማለትን ያስከትላል፡፡

በዚህ ረገድ ሁለት ነገሮችን ማንሳት ይቻል ይሆናል፡፡ በአንድ በኩል የህጉ አንቀጽ 180 የጉዲፈቻ ስምምነት በጉዲፈቻ አድራጊውና በጉዲፈቻ ልጁ መካከል ይደረጋል በሚል የደነገገ ስለሆነ የልጁ እድሜ ምንም ይሁን ምንም ህጉ ስለፈቀደለት አካለመጠን መድረሱ ሳያስፈልግ ስምምነቱ ልጁ ራሱ ሊመሰርተው[87] ይችላል ማለት ነው ብሎ መከራከር ይቻላል፡፡ ነገር ግን ይህ አካሄድ ሌላው ቢቀር በጽንስ ላይ ያለው ልጅስ ስምምነቱን እንዴት ሊመሰርተው ነው? ለሚለው መልስ የሚሰጠን አተረጓጎም አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ግን ባለን የህግ ሥርዓት መሠረት ስምምነት ለመመስረት በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በቀር አካለመጠን መድረስን የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለሆነም የጉዲፈቻ ልጁ ስምምነቱን ይፈጽማል ሲባል በአሳዳሪው በኩል ተወክሎ ያከናውነዋል ማለት እንጂ ራሱ ይፈጽመዋል ማለት አይደለም ሊባል ይችላል፡፡ በተለምዶም ሰዎች ከህግ ወይም ከውል በመነጨ የውክልና ስልጣን በወካዩ ስም ስምምነት እንደሚፈጽሙ የሚታወቅና ህጋዊ አሠራር ነው[88]፡፡ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 190ም ይህንኑ የክርክር መስመር የሚያጠናክር ነው፡፡ እንዲህ ብሎ ይነበባል፡፡ "ስምምነቱን ስለሚያደርጉ ወገኖች" በሚል ርእስ ስር "የጉዲፈቻው ስምምነት በጉዲፈቻ አድራጊውና በልጁ አሳዳሪ

86 ዝኒ ከማሁ 185
87 የቤተሰብ ህጉ ሥራ ላይ ከዋለ ጥቂት ዓመታት በኋላ በተካሄደ አውደ ጥናት ይህ ክርክር ቀርቦ እንደነበር ይህ ጸሃፊ ያስታውሳል፡፡
88 በፍትሐብሔር ህጉ "ስለ እንደራሴነት" የሚለውን ክፍል መመልከት ይጠቅማል (2179-2225 ይመልከቱ)

መካከል ይደረጋል" ይላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጎዳይ ኢምንት የሆኑ አንቀጽ 180 በተናጠል ሳይሆን ከሌሎች ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች በተለይም ከአንቀጽ 190 ጋር አብሮ መታየት ያለበት ነው፡፡ ሌሎች የጉዲፈቻ ምዕራፍ ድንጋጌዎችም ይህንኑ አተረጓጎም የሚደግፉ ሆነው ይታያሉ፡፡

8.2.2. የስምምነቱ ቅርጽ (ፎርም)

ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ የጉዲፈቻ ስምምነቱ ምን ዓይነት ቅርፅ (form) ሊኖረው ይገባል? የሚል ይሆናል፡፡ ማለትም በጽሁፍ ሊደረግ ይገባል ወይስ እስከተስማሙ ድረስ በቃልም ቢሆን ይበቃል? እንደሚታወቀው ባህላዊው የጉዲፈቻ ሥርዓት በጽሁፍ የሚደረግ እንዳልነበር የምንግባባ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ማንበብና መጻፍ በማይችል ማህበረሰብ ውስጥ የጽሁፍ ስምምነት እንዲኖር መጠበቅ የማይታሰብ ስለሆነ ነው፡፡ ዘመናዊው የጉዲፈቻ ህጎችንም የጉዲፈቻ ስምምነት በጽሁፍ ሊሆን ይገባል ብሎ በግልፅ ያስቀመጠው ድንጋጌ የለም፡፡ በህግ የተጣለ ግዴታ ካልተቀመጠ ደግሞ ተዋዋዮች በፈለጉት መልክ (በቃል ወይም በጽሁፍ) ስምምነታቸውን ሊመሰርቱ ይችላሉ ማለት ነው[89] ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

[89] ዝኒ ከማሁ 1719(1) እዚህ ላይ አንድ ነጥብ ማውሳት ተገቢ ሆኖ ይታያል፡፡ ነገሩ የፍትሐብሔር ህግ "የጉዲፈቻ ውል" በሚል የሚገልጸው ሲሆን ውል ሲባል በፍትሐብሔር ህጉ ቁጥር 1675 አንላለጽ ገንዘባዊ ዋጋና ውጤት ያለው ስምምነት ስለሆነና የጉዲፈቻ ግንኙነት ግን ገንዘባዊ ዋጋ እንደሌለው በመታወቅ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ውስጥ ውል ከማለት ይልቅ የጉዲፈቻ "ስምምነት" የሚለው መጠቀም ተመራጭ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለስምምነቱ ውጤታማ መሆን የፍርድ ቤት ይሁንታ ማስፈለጉም ከተራ ውል የተለየ ያደርገዋል፡፡ የሚመሳሰሉባቸው በርካታ ያሉ ነጥቦች እንዳሉም ማውሳቱ ተገቢ ነው፡፡

በሌላ አቅጣጫ ካየነው ግን የተለየ መደምደሚያ ላይ ሊያደርሰን የሚችል ነው፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡ የጉዲፈቻ ስምምነት በጽሁፍ እንዲሆን ባያስገድድም የጉዲፈቻ ስምምነት ውጤት ይኖረው ዘንድ ግን በፍርድቤት መጽደቅ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ፍርድቤት እንዲያፀድቀው ደግሞ ሊፀድቅ የሚገባ ሰነድ ሊቀርብለት ይገባል፡፡ ፍርድቤት የሚቀርቡ የፍትሐብሔር ጉዳዮች የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህጉን ተከትለው መቅረብ እንደሚገባቸው ይታወቃል፡፡ ከዚህ አንፃር ተዋዋዮች እንዲሁ በማንባርና በቃል ፍርድቤት ፊት ቀርበው የጉዲፈቻ ስምምነት ፈጽመናልና አጽድቅልን ብለው የሚጠይቁበት የሥነ-ሥርዓት አሰራር የለንም፡፡ በመሆኑም ህጉ የጉዲፈቻ ስምምነት በጽሁፍ ሊደረግ ይገባል ባይልም ስምምነቱ በፍርድቤት ካልፀደቀ ውጤት አይኖረውም የሚል ድንጋጌ በማስቀመጡ በግልጽም ባይሆን በውስጠ ታዋቂ (impliedly) የጉዲፈቻ ስምምነት በጽሁፍ እንዲደረግ ያስገድዳል ማለት ነው[90]፡፡ በኔ እምነት ይህ አካሄድ ከፊተኛው ይልቅ ሚዛን የሚደፋና አሳማኝ ይመስለኛል፡፡ ስለዚህ በዚህ ረገድ አስገዳጅ ድንጋጌዎች በግልጽ ወይም አልፎ አልፎ በውስጠ ታዋቂ ሊደነገጉ እንደሚችሉ በመገንዘብ ፈጣን መደምደሚያ ከመስጠት በፊት አጠቃላይ ህጋዊ ማዕቀፉን (legal frame work) ሰፋ ባለመልኩ መመርመር ተገቢ ነው እንላለን፡፡

8.2.3. የጉዲፈቻ ልጁ ከተፈጥሮ ዘመዶቹ ጋር ስለሚኖረው ዝምድና

ሊላው በጉዲፈቻ ሥርዓት ሥር መወሳት ያለበት ነጥብ የጉዲፈቻ ልጁ እንደጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ የሚቆጠር ከሆነ ከተፈጥሮ ወላጆቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነትና ዝምድና እንዴት ሆኖ ይቀጥላል? የሚል ነው፡፡ በዚህ ረገድ የተለያዩ ሃገራት

[90] የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በመዝገብ ቁጥር 03814 ተመሳሳይ አቋም ወስዷል፡፡

Scanned by CamScanner

የተለያየ አሠራር ይከተላሉ፡፡ ሁለት ዓይነት አሠራሮች ግን በብዙ ሃገራት የተለመዱ መሆናቸው በጉዳዩ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ እነርሱም ፍጹምና ከፊል የልጅነት ትስስር[91] በመባል ይታወቃሉ፡፡

ፍጹም የልጅነት ትስስር የሚፈጠረው ጉዲፈቻ አድራጊውና የጉዲፈቻ ልጁ ሙሉ በሙሉ የቤተሰብ መዋሃድ ሲያደርጉና ልጁ ከቀድሞ የተፈጥሮ ቤተሰቡ ጋር ያለው ግንኙነት ጨርሶ ሲቋረጥ ነው፡፡ በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ከልጁ ጋር የሚፈጠረው ግንኙነት ከሌሎች የጉዲፈቻ አድራጊው የተፈጥሮ ልጆች ጋር እኩል ደረጃ የሚሰጠው ስለሆነ ከቀድሞው ቤተሰብ ጋር ያለው ግንኙነት ይቋረጣል፡፡ የልጁ ቤተሰቦች ናቸው ተብለው የሚታወቁትም የጉዲፈቻ አድራጊው ቤተሰቦች ብቻ ናቸው፡፡ በአንጻሩ በከፊል የሚደረገው የጉዲፈቻ ግንኙነት የጉዲፈቻ ልጁ ከቀድሞው የተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ጋር ያለው ግንኙነት ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የሚደረግ ነው፡፡ በመሆኑም ከአዲስ ቤተሰቡ ጋር ሙሉ ትስስር እንደተጠበቀ ሆኖ የተፈጥሮ ቤተሰቦቹን ግንኙነት የሚጠብቅ ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ የጉዲፈቻ ህግ በነባሩ የፍትሐብሔር ህግ ጊዜም ሆነ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ከፊል የልጅነት ትስስር የሚፈጥር ሆኖ ይገኛል፡፡ ይህም ማለት ምንም እንኳ የጉዲፈቻ ልጁ የጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ እንደሆነ የሚቆጠር ቢሆንም ከተፈጥሮ ወላጆቹ ጋር ያለውን የዝምድና ትስስር እንደያዘ ይቆያል ብሎ ህጉ አብሮ ደንግጓል፡፡ በርግጥ አስገዳጅ ሁኔታ ተፈጥሮ ከሁለቱ አንዱን ቤተሰብ መምረጥ የሚያስገድድ ሁኔታ

[91] አቶ ቢሳይ ታደሠ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግሥት እና በፍትሐብሔር የቤተሰብ ህግ ስለመወለድ ያሉት ድንጋጌዎች በሚል ርእስ ሥር በ1991 ካቀረቡት (ያልታተመ) ጥናታዊ ጽሑፍ የተወሰደ፡፡

ከተፈጠረ ግን ህጉ ከተፈጥሮ ቤተሰቦቹ ይልቅ ወደ ጉዲፈቻ ቤተሰብ እንደሚያደላ[92] አብሮ ተገልጾአል፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ ግን የጉዲፈቻ አድራጊው ቤተዘመዶች (ወደላይ እና ወደጎን የሚቆጠሩ ዘመዶቹን እንጂ ወደታች የሚቆጠሩትን አይመለከትም) የጉዲፈቻ ልጁን ዝምድና እንፈልግም የሚሉ ከሆነ ይህንኑ ተቃውሞአቸው የሚያስፈጽሙበት ሥርዓት ህጉ አደራጅቶላቸዋል፡፡ ለዚህም የጉዲፈቻ ስምምነቱን የሚቃወሙት መሆናቸው በመግለጽ ስምምነቱ በፍርድቤት መጽደቁ ባወቁ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተቃውሞአቸውን በፍርድ ቤቱ መዝገብ ውስጥ ሊያሰፍሩት ይገባል[93]፡፡ ይህንን ሁኔታ ካላሟሉ ግን ዝምድናው በእነርሱም ላይ ተፈፃሚ ሆኖ ይቀጥላል ማለት ነው፡፡ የጉዲፈቻ አድራጊው ወደታች የሚቆጠሩ ዘመዶች (ልጆች) ግን እንዲህ ዓይነት ውጤት የሚያስከትል የመቃወም መብት የላቸውም፡፡

8.2.4. የጉዲፈቻ አድራጊው የዕድሜ ወለል (minimum age) እና የጉዲፈቻ ልጁ ከፍተኛ ዕድሜ (maximum age)

8.2.4.1. የጉዲፈቻ አድራጊው ዝቅተኛ ዕድሜ

ከዚህ በላይ በተመለከቱት ነጥቦች ላይ በነባሩ የፍትሐብሔር ህግና በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ መካከል የጎላ ልዩነት የሌለ ቢሆንም በአንዳንድ ነጥቦች ግን ነባሩ የፍትሐብሔር ህግና የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ የተለያየ አቋም ወስደው እናገኛቸዋለን፡፡ ከእነዚህም አንዱ የጉዲፈቻ

[92] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 183
[93] ዝኒ ከማሁ 182

አድራጊውና የጉዲፈቻ ልጁን ዕድሜ በተመለከተ ያለው ልዩነት ነው፡፡

በነባሩ የፍትሐብሔር ህግ መሠረት "ማናቸውም ሰው አካለመጠን ከደረሰ የጉዲፈቻ ልጅ ማድረግ ይችላል"[94] ይላል፡፡ የጉዲፈቻ ልጅ በተመለከተም "ዕድሜው ከአስራአምስት ዓመት በታች ከሆነ በአሳዳሪው በኩል የጉዲፈቻ ውል ሊፈጽም እንደሚችል ዕድሜው ከዚያ በላይ ከሆነ ግን ራሱ ሊፈራረም እንደሚችል"[95] ተመልክቶ ነበር፡፡ ከዚህም በመነሳት አልፎ አልፎ የጉዲፈቻ ልጅ ለመሆን የዕድሜ ገደብ የለም በመሆኑም የአስራ ስምንት ዓመት ሰው የሰላሳ አምስት ዓመት "ልጅን" በጉዲፈቻ ልጅነት መያዝ ይችላል ማለት ነው የሚል ክርክር ሲቀርብ ይደመጥ ነበር፡፡

በዚህ ረገድ በአንዳንድ አገሮች የህግ ማዕቀፍ የጉዲፈቻ ዝምድና የተፈጥሮ ተወላጅነት (natural filiation) መምሰል ስላለበት በጉዲፈቻ አድራጊውና በጉዲፈቻ ልጁ መካከል ሊኖር የሚገባ የዕድሜ ልዩነት አባትና ልጅ ወይም እናትና ልጅ ሊያስኛቸው የሚችል ስፋት ሊኖረው ይገባል ብለው ያምናሉ፡፡ በምንም ዓይነት ሁኔታም የጉዲፈቻ ልጁ እድሜ ከጉዲፈቻ አድራጊው ዕድሜ ጋር እኩል ወይም ሊበልጥ አይችልም የሚል ህግና ገደብ አላቸው[96]፡፡ ለዚህም የሚቀርበው ምክንያት የጉዲፈቻ ልጁ ዕድሜ ከጉዲፈቻ አድራጊው ዕድሜ ጋር እየተቀረበ በሄደ ቁጥር ጉዲፈቻ አድራጊው በጉዲፈቻ ልጁ ላይ ወላጃዊ ሥልጣን (parental authority) ለማከናወን አያስችለውም ተብሎ ይሰጋል፡፡

[illegible] የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 797(1)

[95] ዝኒ ከማሁ 802

[96] Lasok, Polish Family Law, p 184

የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ከዚህ በላይ በተመለከተው መልክ የተቀረጸ ባይሆንም ጉዲፈቻ መያዝ የሚቻለው ጉዲፈቻ አድራጊው ስንት ዓመት ሲሞላው ነው? የጉዲፈቻ ልጅ ለመሆን የሚቻለውስ እስከስንት ዓመት ዕድሜ ድረስ ነው? ለሚሉት ነጥቦች መልስ ሰጥቶአል፡፡ በዚህም መሠረት ጉዲፈቻ አድራጊ ለመሆን ሃያ አምስት ዓመት ዕድሜ መሙላትን እንደቅድመ ሁኔታ ይጠይቃል[97]፡፡ የጉዲፈቻ ልጅ ለመሆንም ከፅንስ ጀምሮ እስከ አስራስምንት ዓመት ዕድሜ ድረስ ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ መሆን ይገባል ተብሏል፡፡ እንዲያውም ልጁ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የወጣ ከሆነ ዕድሜው አስራ ስምንት ዓመት ባይሞላም የጉዲፈቻ ልጅ መሆን እንደማይችል ተደንግጓል[98]፡፡

እዚህ ላይ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ ጉዲፈቻ አድራጊ ለመሆን ዝቅተኛው ዕድሜ ሃያ አምስት ዓመት ማድረግ ለምን አስፈለገ? አካለመጠን መድረስ ማለትም አስራ ስምንት ዓመት መድረስ በቂ ሊሆን አይገባም ወይ? የሚል ነው፡፡

እንግዲህ ስለጉዲፈቻ ሥርዓት ስናወሳ ከአብራክ ያልተወለደን፣ የራስ ያልሆነን ልጅ እንደራስ ልጅ አድርጎ ማሳደግና መንከባከብ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ታላቅ ሃላፊነት ስለሆነ ጠንካራ የሥነ-አእምሮ ዝግጅትና ብስለት የሚጠይቅ ነው፡፡ በርግጥ የራስ ልጅ ሲሆን በአግባቡ ተንከባክቦና ተቆጣጥሮ ለማሳደግ አካለመጠን መድረስ በራሱ በቂ ሊሆን ይችላል፡፡ የሌላ ሰውን ልጅ እንደራስ ልጅ አድርጎ ለማሳደግ ግን ሰፋ ያለ የህይወት ልምድና ሰከን ያለ ባህርይ ይጠይቃል፡፡ እንዲህ ዓይነት ባህርይ ለመያዝ የሚቻለውም በዕድሜ መብሰል አንዱ ነው፡፡ ስለሆነም የጉዲፈቻ አድራጊው ዝቅተኛ ዕድሜ ወደ ሃያ አምስት ዓመት ከፍ ማድረጉ ተገቢ መስሎ ይታያል፡፡ በሌላም

---

[97] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 184(1)

[98] ዝኒ ከማሁ 185

በኩል ሲታይ ብዙውን ጊዜ ሰዎች የጉዲፈቻ ልጅ ወደማሳደግ የሚሄዱት የራሳቸው ልጅ ለማግኘት ሞክረው ሳይሳካላቸው ሲቀር ነው፡፡ የጋብቻ መፈጸሚያ ዝቅተኛው ዕድሜ ለወንዱም ሆነ ለሴቷ አሥራ ስምንት ዓመት መሆኑ ደግሞ በሕግ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም የራስ ልጅ ለማግኘት የሚደረገው ጥረት ከአስራ ስምንት ዓመት በኋላ ጥቂት ዓመታት መጠየቁ አይቀርም፡፡ ስለዚህ ከዚህም አንጻር የጉዲፈቻ አድራጊው ዝቅተኛ ዕድሜ ሃያ አምስት ዓመት መደረጉ አግባብነት እንዳለው ይታያል[99]፡፡

8.2.4.2. የጉዲፈቻ ልጅ ከፍተኛው ዕድሜ

ሌላው ነጥብ ስለጉዲፈቻው ልጅ ዕድሜ ነው ማለትም ጉዲፈቻ አድራጊው እስከተቀበለው ድረስ የጉዲፈቻ ልጅ ዕድሜ በአስራ ስምንት ዓመት ጣሪያ ላይ መገደብ ለምን አስፈለገ? የሚል ነው፡፡ እንደሚታወቀው ቀደም ሲልም እንደገለጽነው በባህሉም ሆነ በዘመናዊው የጉዲፈቻ ሥርዓት የጉዲፈቻ ልጅ ሆነው የሚቀርቡት አካለመጠን ያልደረሱ ህፃናት ናቸው፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃም ቢሆን በተለይም የህፃናት መብት ኮንቬንሽንን ስናይ ጉዲፈቻን ከህፃንነት ጋር በማያያዝ ነው የሚመለከተው፡፡ ህፃንነት ደግሞ ሰፋ ያለ ትርጉሙ እንኳ ቢወሰድ ከአስራ ስምንት ዓመት ዕድሜ በታች እንደሆነ የህፃናት

[99] እዚህ ላይ መወሳት ያለበት ጉዳይ አስራ ስምንት ዓመት መሙላት ብዙውን ሕጋዊያን ተግባራት (judicial acts) ለማከናወን መብት ይሰጣል እንጂ ሁሉንም ተግባራት ለማከናወን መብት ይሰጣል ማለት አይደለም፡፡ አንዳንድ ከፍ ያለ የኃላፊነት ስሜት የሚጠይቁ ጉዳዮች ከዚያ በላይ ከፍ ያለ ዕድሜ ይጠይቃሉ፡፡ ለምሳሌ በምርጫ ቢያንስ በህዝብ ተወካዮች ወይም ለክልል ምክር ቤት አባልነት ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብ ሃያ አንድ ዓመት የደረሰ መሆን ይገባዋል፡፡ የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ ለመሾምም ቢያንስ ሃያ አምስት ዓመት መሙላትን ይጠይቃል፡፡ ይህም ጉዳይ ከዚህ አንፃር ቢታይ መልካም ይመስለኛል፡፡

መብት ይደነግጋል[100]፡፡ ስለዚህ የጉዲፈቻ ልጅ በአስራ ስምንት ዓመት የዕድሜ ጣሪያ መወሰኑ ከአጠቃላዩ የጉዲፈቻ ሥርዓት ዓላማና ግብ ማለትም አካለመጠን ያልደረሱ ሰዎችን ጥቅምና ደህንነት መጠበቅ ከሚለው ጋር የተጣጣመ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በርግጥ አንድ ሰው ከፈለገና ከፈቀደ ከአስራ ስምንት ዓመት ዕድሜ በላይ ለሆነም ሰው ቢሆን መብትና ጥቅም ሊሰጠው ከልጆቹ እኩል እንዲጠቀሙ ሊያደርግለት ይችላል፡፡ ይህ ግን በስጦታ ህግ ወይም በውርስ ህግ ወይም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች በኩል ሊሆን ይገባዋል እንጂ በጉዲፈቻ ህግ በኩል ሊሆን አይችልም ማለት ነው፡፡ በመጨረሻም ከዚህ ነጥብ ከመውጣታችን በፊት አንድ ሰው አስራ ስምንት ዓመት ባይሞላውም ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ከወጣ በህግ መሠረት የጉዲፈቻ ልጅ ለመሆን መብት አይኖረውም፡፡ ከሞግዚት አስተዳደር እንዴት ነፃ እንደሚወጣና የሚወጣባቸው ምክንያቶች በተመለከተ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ከአንቀጽ 311 እስከ 314 ድረስ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ውጤቱም ከሞግዚትነት አስተዳደር ነፃ የወጣ ልጅ በህግ አካለመጠን እንደደረሰ ሆኖ እንደሚቆጠር ተገልጿል[101]፡፡ በመሆኑም ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ መውጣቱ አካለመጠን እንደደረሰ የሚያስቆጥረው ስለሆነ ነው ለጉዲፈቻ ልጅነት ብቁ የማይሆነው፡፡

[100] የህፃናት መብት ኮንቬንሽን አንቀጽ 1 (ኮንቬንሽኑ የኢትዮጵያ የህግ አካል መሆኑ ልብ ይሏል፡፡) በፖላንድ የቤተሰብ ህግም በጉዲፈቻ ልጅነት ሊያዝ የሚችለው አካለመጠን ያልደረሰ ከሆነ ነው፡፡

[101] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 313

8.2.5. የጉዲፈቻ አድራጊው ቤተሰባዊ ሁኔታ

ወደሌላ ነጥብ ስናመራ በአንዳንድ አገሮች የህግ ሥርዓት የጉዲፈቻ ልጅ መውሰድ የሚችሉት ባልና ሚስት ሲሆኑ ወይም እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሲሆኑ ነው:: በእነዚህ ሃገሮች ህግ መሰረት ወንደላጤ ወይም ሴተ ላጤ ሆነው የጉዲፈቻ ልጅ እንዲያሳድጉ አይፈቀድላቸውም:: ለዚህ ሁለት ምክንያቶች ይቀርባሉ:: አንደኛ የጉዲፈቻ ልጁ የተፈጥሮ ቤተሰብ በሚመስል አካባቢ (natural family environment) ማደግ ስላለበት የተፈጥሮ ቤተሰብ ደግሞ አባትና እናት ሲገኙበት ስለሆነ አንዳቸው በሌሉበት ሁኔታ ክፍተት ስለሚኖር ለልጁ አስተዳደግና ስብእና የሚበጅ አይደለም ተብሎ ስለሚታሰብ ነው:: ሁለተኛ መጀመሪያኑ ባል ለማግባት ወይም ሚስት ለማግባት ያልተዘጋጁ ወይም ያላገቡ ላጤዎች ልጅ ለማሳደግ (እንዲያውም ከአብራካቸው ያልተወለደን) ጠንካራ ዝግጁነት አይኖራቸውም ተብሎ ስለሚታመንና ስለሚገመት ነው:: በተለይም ወንደ ላጤ ሆኖ ሴት ልጅ በጉዲፈቻ ልጅነት ሊወስድ ሲል ወይም ሴተ ላጤ ሆና ወንድ ልጅ በጉዲፈቻ ልጅነት ለመውሰድ ሲታሰብ ሁኑ ከፍተኛ ጥርጣሬ ያድርበታል[102]:: በኛም ሃገር ከፍትሐብሄር ህግ በፊት በነበረን ሥርዓት እንዲህ የሚል ድንጋጌ ነበረን:: "ለዝምድና ተሳስበው ሴትና ወንድ የጡት አባት ወይም የጡት ልጅ ሊኳኋኑ ህግ አይፈቅድላቸውም"[103] የሚል ነበር:: ምናልባት የህጉ ሲጋት

[102] በዚህ ረገድ በፖላንድ የቤተሰብ ህግ ላይ በስፋት የፃፈው Lasok እንዲህ ብሎ ነበር:: "It follows that the application for the adoption order must be dismissed if, for instance, the age difference between an infant girl and her prospective adopter is such as to raise a doubt whether the adopter would be able to take a strictly parental interest in her" (Polish Family Law p. 186)

[103] 12ኛ የኢትዮጵያ የዋንት ፍርዶች መዝገብ ቁጥር 143

ግንኙነቱ የጉዲፈቻ ወላጅና ልጅ ግንኙነት መሆኑ ቀርቶ ወደልተፈለገ አቅጣጫ ሊያመራ ይችላል የሚል ይመስላል::

በፍትሐብሄር ህጉና አሁን ባለን የጉዲፈቻ ህግ ግን እንዲህ ዓይነት ገደብ ወይም ክልከላ አልተቀመጠም:: ይህም እያንዳንዱ ጉዳይ በራሱ እየታየ እንዲወሰን ለማስቻልና የጉዲፈቻ አገልግሎት ማግኘት የሚገባቸውን ህፃናት እድል ለማስፋት በማሰብ ይመስላል:: በአሁኑ ወቅት ያለን ክልከላ ጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ባልና ሚስት በሚሆኑበት ጊዜ ለጉዲፈቻ ስምምነቱ ሁለቱም ፈቃዳቸውን ካልሰጡ ስምምነቱ ሊደረግ እንደማይችል መደንገጉ ነው[104]:: ቀደም ሲል የጉዲፈቻ አድራጊው ወደላይ ወይም ወደጎን የሚቆጠሩ ዘመዶች ስምምነቱን መቃወም እንደሚችሉና ይህንኑ በተሳካ ሁኔታ ከከናወኑ የጉዲፈቻ ስምምነቱ የጸና ሆኖ የጉዲፈቻ ልጁ ግን ከእነርሱ ጋር ምንም ዓይነት ዝምድና እንደማይኖረው አይተናል:: እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ግን የጉዲፈቻ ስምምነቱን የተቃወመው ባል ወይም ሚስት በሆነ ጊዜ አይሰራም:: ከተቻለ ባልና ሚስቱ ሁለቱም ስምምነቱን ይቀበሉትና የጉዲፈቻው ግንኙነት ይቀጥላል ወይም ጨርሶ ይቀራል እንጂ ከአንደኛው ተጋቢ ጋር የጉዲፈቻ ዝምድና ተፈጥሮ ከሌላው ጋር ዝምድና ሳይፈጠር የሚቀርበት ሥርዓት የለም:: በርግጥ የጉዲፈቻ ልጁ ቀደም ሲል ከሌላ ባል ወይም ሚስት የተወለደ የባልየው ወይም የሚስቲቱ ልጅ ከሆነ ልጁ ያልሆነው ሰው ስምምነት ብቻ በቂ ነው:: ምክንያቱም ሌላኛው ወገን የራሱን የተፈጥሮ ልጅ በጉዲፈቻ ልጅነት መቀበል አስፈላጊ አይደለምና ነው::

የተፀነሰ ልጅ በህይወት ከተወለደና የሚኖር ከሆነ የራሱ ጥቅም በሚያሻበት ጊዜ ሁሉ እንደተወለደ[105] ይቆጠራል የሚል

[104] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 186(1)

[105] የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 2

ድንጋጌ በፍትሐብሔር ህጋችን ውስጥ መኖሩ አይዘነጋም:: የጉዲፈቻ ስምምነት ደግሞ በዋናነት ለህፃኑ ጥቅም መደረግ ያለበት መሆኑ ቀደም ብለን አይተናል:: በውርስ ህጋችንም የተፀነሰ ልጅ የመውረስ መብት እንዳለው[106] ተመልክቶአል። ይህ ሁሉ ለህፃኑ ጥቅም ሲባል ነው:: እንግዲህ ይህን በማገናዘብ ነው በጉዲፈቻ ህጋችንም ውስጥ የተፀነሰ ልጅ የጉዲፈቻ ልጅ ማድረግ እንደሚቻል የተደነገገው:: ይህ ዓይነት አሰራር ለህፃኑ ብቻ ሳይሆን ለጉዲፈቻ አድራጊውም ጠቀሜታ አለው:: ምክንያቱም ጉዲፈቻ አድራጊው ህፃኑ እንደተወለደ ወዲያውኑ መውሰድ ከቻለ ህፃኑ ጉዲፈቻ አድራጊውን በተሰብ የተፈጥሮ ወላጆቹ ናቸው ብሎ ለማመንና ለመቀበል ሰፊ ዕድል ይኖራል፤ ስለተፈጥሮ ወላጆቹ ምንም ዓይነት ትዝታና ትውስታ ሊኖረው አይችልምና ነው:: በሌላ በኩል ግን የተፀነሰን ልጅ በጉዲፈቻ ልጅነት መያዝ የራሱ የሆነ አደጋ አለው:: ምክንያቱም በዚህ ሁኔታ የተደረገ የጉዲፈቻ ስምምነት ለህፃኑ የተፈጥሮ እናት የተለየ መብት ይሰጣታል:: ይኸውም ልጁ በተወለደ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ስምምነቱን ሰርዛ ልጅዋን ይዛ በእናትነት ለመቀጠል የሚያስችላት ነው[107]::

ይህ ለልጁ የተፈጥሮ እናት የተለየ መብት የሚሰጠው ድንጋጌ የአጠቃላዩ መርህ ልዩ ሁኔታ መሆኑ ነው:: ምክንያቱም በመርህ ደረጃ የጉዲፈቻ ስምምነት ሊሰረዝ አይችልም:: የሚሰረዝበት ምክንያት ካለም ምክንያቱ ቀርቦ በፍርድቤት ውሳኔ የሚከናወን ነው[108]:: አሁን በያዝነው ጉዳይ ግን ከተዋዋዮቹ ወገኖች አንዱ (የልጁ እናት) የተናጠል (unilateral)እርምጃ እንድትወስድ መብት የሚያጎናጽፋት ነው:: ህግ አውጪው እናት ለዘጠኝ ወራት ያህል ልጇን በማህፀንዋ ተሸክማ ከቆየች

[106] ዝኒ ከማሁ 834
[107] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 187(2)
[108] ዝኒ ከማሁ 195

በኋላ በሰላም ተገላግላ ልጇን አትፋ ለመሳም ስትበቃና ህፃኑን ለባዕድ አሳልፋ ለመስጠት ግዴታ መግባትዋ ሲታወስ የሚፈጥርባት የስሜት መዘበራረቅ በውል የተገነዘበ ይመስላል:: በመሆኑም በእርግዝናዋ ወቅት ህፃኑን (በዚያ ወቅት ፅንሱን) አስመልክታ የገባችው ስምምነት እንድታከብር ማስገደዱ አግባብና ፍትሃዊ ሆኖ አላገኘውም:: ስለዚህ ልጁ ከተወለደ እስከስድስት ወር ጊዜ ድረስ ሃሳብዋን ለመቀየርና ስምምነቱን በተናጠል ለመሰረዝ ህጉ እድል ይሰጣታል:: ከዚያ ጊዜ በኋላ ግን በስምምነቱ ተገዳጅ ትሆናለች ማለት ነው:: ህግ አውጪው ተመሳሳይ መብት ለልጁ የተፈጥሮ አባት አልሰጠም:: ምክንያቱም ከላይ እንደገለጽነው አባት ከጽንሱና ከህፃኑ ጋር የእናትን ያህል ሥነ-ልቦናዊ ትስስር (emotional attachement) አለው ተብሎ ስላልተገመተ ነው ተብሎ ይታሰባል::

ጉዲፈቻ ብዙውን ጊዜ ልጅ መውለድ ባልቻሉ ወይም ባልወለዱ ጥንዶች የሚደረግ ቢሆንም የራሳቸው ልጆች ያሉዋቸውም የጉዲፈቻ ልጅ ሲያሳድጉ ይስተዋላል:: በመሆኑም የጉዲፈቻ ልጅ ማሳደግ የሚፈቀድለት ከአብራኩ የተገኘ ልጅ ወይም ልጆች የሌለው ብቻ ነው ብሎ ገደብ ማስቀመጥ ተገቢ አካሄድ አይደለም:: በተለይም ከአብራኳቸው የተገኙ ልጆች እድሜአቸውና አቅማቸው ፈቅዶላቸው ድረውና ጎጆአቸውን አውጥተው ጥግ ጥጋቸውን ካስያዙ በኋላ ለጽድቅና "ቤቱ ጭር እንዳይል" በማሰብ የጉዲፈቻ ልጅ ማምጣት የተለመደ ነው:: የኢትዮጵያ የጉዲፈቻ ህግም ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት ከአብራኳቸው የተገኙ ልጆች ያሉዋቸው ሰዎች የጉዲፈቻ ልጅ መያዝ አይችሉም ብሎ ለመከልከል አልከጀለም:: ይልቁንም ጉዲፈቻ አድራጊው ከአብራኩ የተገኙ ልጆች ያሉት መሆኑ የጉዲፈቻ ስምምነት ከማድረግ የሚያግደው አይሆንም በሚል ደንግጎ ይገኛል[109]::

[109] ዝኒ ከማሁ 109

እዚህ ላይ ግን ጥንቃቄ የሚያሻቸው ጉዳዮች እንዳሉ መገንዘብ ጠቃሚ ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች ከአብራካቸው የተወለዱ ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት አስገብተው እያስተማሩ የጉዲፈቻ ልጅ አምጥተው የእረኝነቱንና ሌላ ሌላ የቤት ውስጥ ሥራዎችን እንዲያከናውን የሚያደርጉበት ጊዜ አለ፡፡ ስለዚህ ጉዲፈቻ አድራጊዎች ከተፈጥሮ ልጆቻቸው ጋር በዕድሜ የሚተራረቡ ልጆችን በጉዲፈቻ ልጅነት ሲቀበሉ ብርቱ ጥንቃቄና ክትትል ማድረግ ይገባል፡፡ ለዚህም ነው የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ በአንቀጽ 188(2) ሥር ጉዲፈቻ አድራጊው ከአብራኩ የተገኙ ልጆች ያሉት መሆኑ በጉዲፈቻ ልጁ መልካም አስተዳደግና ጥቅም ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተጽእኖ ፍርድ ቤቱ ግምት ውስጥ እንዲያስገባ ግዴታ የተጣለበት፡፡

የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ በጉዲፈቻ ሥርዓት ረገድ ከነባሩ የፍትሐብሄር ህግ ለየት ባለ መልኩ ይዞአቸው ከመጡት ድንጋጌዎች ውስጥ ቀደም ሲል ጥቂቶችን ያገለጽን ሲሆን ከእነዚሁ በተጨማሪ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

8.3. የእጓለማውታን ድርጅቶች ሚና በጉዲፈቻ

እንደሚ በነባሩ የፍትሐብሄር ህግ የጉዲፈቻ ስምምነት ይደረግ የነበረው በጉዲፈቻ አድራጊውና በጉዲፈቻ ልጁ አሳዳሪ መካከል ነበር፡፡ የመንግሥትም ሆነ የግል እጓለማውታን ድርጅቶች በሥራቸው የሚተዳደሩ ህፃናትን ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ አገር ጉዲፈቻ አድራጊዎች ለማስተላለፍ የሚያስችል ግልፅ የህግ መሠረት አልነበራቸውም፡፡ ምክንያቱም ተቋሞቹ በሥራቸው ባሉት ህፃናት ላይ ያላቸው የአሳዳሪነት ስልጣን ከህግ ወይም ከፍርድቤት ውሳኔ የመነጨ ስላልነበረ በየንዳንዱ ልጅ ስም ሆነው የጉዲፈቻ ስምምነት ለመፈራረም ህጋዊ ስልጣን

አልነበራቸውም[110]፡፡ በመሆኑም ወላጆቻቸው በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ምክንያት የሞቱባቸውን፣ ተጥለው የተገኙትን፣ ጠፍተው የተገኙት ህፃናትን ወደ እጓለማውታን ከገቡ በኋላ በጉዲፈቻ ስምምነት በኩል ለማስተላለፍ በተቋሞቹ በኩል ጽኑ ፍላጎት የነበረ ቢሆንም፣ በሌላ በኩልም እነዚህን ልጆች በጉዲፈቻ ልጅነት ለመውሰድ በጉዲፈቻ አድራጊዎች በኩል ፍላጎትና ጥያቄ የነበረ ቢሆንም ግልጽ የህግ ድጋፍና ሽፋን ስላልነበረ ለአፈጻጸም አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቶአል፡፡ በዚህም ምክንያት በአንድ በኩል ተቋሞቹ በእጃቸው ያሉትን ህፃናት በጉዲፈቻ አስተላልፈው አገልግሎታቸውን ለሌሎች ተመሳሳይ ችግር ላጋጠማቸው ህፃናት ክፍት ማድረግ ሲገባቸው ይህንን ማድረግ ሳይችሉ ቆይተዋል፡፡ በሌላም በኩል ህፃናቱም ቢሆኑ ከተቋሙ ይልቅ ከጉዲፈቻ አሳዳጊዎች የተሻለ እንክብካቤ ማግኘት እየቻሉ የህግ ማዕቀፉ ባለመመቻቸቱ ብቻ ተጠቃሚ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡ በመሆኑም የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ይህንን የህግ ክፍተት (legal vacuum) ለመድፈን ይቻል ዘንድ አዲስ አንቀጽ በቁጥር 192 ሥር ደንግጓል፡፡ በነባሩ የፍትሐብሄር ህግ እንዲህ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ይዘት ያለው ድንጋጌ አልነበረም፡፡

[110] የእጓለማውታን ድርጅቶች ወላጆቻቸው የሞቱባቸውን ወይም ተጥለው የተገኙትን ህፃናት ተረክበው ሲያሳድጉ በአሠራር ደረጃ እንጂ ከህግ ወይም ከፍርድ ቤት ውሳኔ የመነጨ የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥልጣን የላቸውም፡፡ ስለሆነም ልጆን ወክለው የጉዲፈቻ ስምምነት ሊፈራረሙ አይችሉም፡፡ የቀድሞው የቤተሰብ ህግ ለማሻሻል ሲዘጋጁ በነበሩት ዓውደጥናቶች ሲካፈሉ የነበሩት የእነዚሁ ድርጅቶች ተወካዮች ሲያቀርቡዋቸው ከነበሩት ጥያቄዎች አንዱ ይህንኑ መብትና ሃላፊነት በህጉ ውስጥ እንዲካተትላቸው የሚጠይቅ ነበር፡፡ ይኸው ተካትቶላቸዋል፡፡

፩.፩. የውጭ አገር ዜጋ ጉዲፈቻ አድራጊ ሲሆን

ሁለተኛ በነባሩ የፍትሐብሔር ሕግ ውስጥ የጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ይሁን ኢትዮጵያዊ በጉዲፈቻ ስምምነት አመሰራረት ሥርዓቱ ላይ ምንም ዓይነት ልዩነት አልነበረም። እንዲያውም የጉዲፈቻ ድንጋጌዎች ጉዲፈቻ አድራጊው የውጪ ዜጋ ሲሆንም ተፈፃሚ ይሆናሉ እየተባለ በትርጉም ደረጃ ይፈጸም ነበር እንጂ ሕጉ ስለውጪ ዜጋ ጉዲፈቻ አድራጊ የሚለው ምንም ነገር አልነበረም። በተጨባጭ ግን ቁጥራቸው የማይናቅ የውጭ ዜጎች ኢትዮጵያውያን ህፃናትን በጉዲፈቻ ልጅነት ለመውሰድ ፍላጎት ሲያሳዩ ነበር አሁንም ያሳያሉ። በጉዲፈቻ ልጆች በሌሎም የተለዩ ህፃናት ወላጆችና አሳዳሪዎች ልጆቻቸው በጉዲፈቻ ልጅነት ውጭ ሃገር እንዲሄዱላቸው ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው ጠቋሚ መረጃዎች አሉ።

ግንባሩ ሊወሰድበት የሚገባው ጉዳይ ግን የውጭ ሃገር ጉዲፈቻ እንደሚታሰበው ተመራጭ አለመሆኑን ነው። ይኸውም ቋንቋው ይተካል፣ ወደተለየ አኗኗርና ባህል የሚገባበት ሁኔታ ይፈጠራል። ህፃኑ ከኢትዮጵያ የግዛት ክልል የመውጣት ሁኔታ ስለሚያጋጥመው በህፃናት ደህንነት ዙሪያ እንዲሰሩ ሀገሪቷ ሥልጣን የተሰጣቸው መንግስታዊ ተቋሞች ስለህፃኑ አስተዳደግና እያደገ ክትትል የሚያደርጉበት ዕድል ይጣበባል። ስለዚህ ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን ራሱን የቻለና የተለየ የጉዲፈቻ ሥርዓት ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በነባሩ የፍትሐብሔር ሕግ ያልነበሩ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ከአንቀጽ 193 እስከ 196 ያሉት የተጋቢቱ ድንጋጌዎች ተተምጠዋል።

ወደ ድንጋጌዎቹ ይዘት ስንገባ ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ አገር ዜጋ ሲሆን በጉዲፈቻ አድራጊውና በልጁ አሳዳሪ መካከል

በሚደረግ ስምምነትና የፍርድ ቤት ይሁንታ ብቻ አያበቃም። ፍርድቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ከማፅደቁ በፊት የሴቶ መንግስታዊ አካል ጥናትና አስተያየት ሊቀርብለት ይገባል። ጉዲፈቻ አድራጊው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሲሆን እንዲህ ዓይነት ሥነ-ሥርዓት አልተቀመጠም። ጥናቱንና አስተያየቱን እንዲያቀርብ የሚጠበቀው የህፃናት ደህንነት ለመከታተል ሥልጣን የተሰጠው መንግስታዊ አካል ሲሆን በአሁኑ ወቅት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሥር የሚገኝ መምሪያ እንደሆነ ይታወቃል። የጥናቱ ዓላማ የጉዲፈቻ ልጁ በደህና ሰዎች እጅ (in good hands) የሚገባ ለመሆኑ ለማረጋገጥ ነው። ጥናት የሚደረግባቸው ርእስ ጉዳዮች አጠቃላይ ይዘት የጉዲፈቻ አድራጊው ማኅበራዊ፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ሲሆን በዝርዝር ብለው ሲታይ የሚከተሉትን ነጥቦች ያካትታል ተብሎ በመስሪያ ቤቱ መመሪያ ተጠቅሶ ይገኛል[112]።

ሀ. ጉዲፈቻ ለማድረግ ወደሚቀርቦቹ ባለትዳር መሆን አለባቸው (በህጉ እንዲህ ዓይነት ቅድመ ሁኔታ የለም) (ሠረዝ የተጨመረ)
ለ. ጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ከሕመና ከተለዩ ሰዎች ነፃ መሆናቸው
ሐ. የልደትና የጋብቻ ምስክር ወረቀት
መ. የጤናና የትምህርት ሁኔታ (የጉዲፈቻ አድራጊዎቹ)
ሠ. የሥራና የገቢ ሁኔታ (የጉዲፈቻ አድራጊዎቹ)
ረ. የጉዲፈቻ አድራጊው ከወንጀል ነፃ መሆን

አቶ ተድላ ደረሰ (የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ስኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ህጎች አንፃር በሚል በ1991 ካቀረቡት (ያልታተመ) ጥናታዊ ጽሑፍ የተወሰደ።

ሰ. ጉዲፈቻ አድራጊው የጉዲፈቻ ልጁ አስራስምንት ዓመት እስኪሞላው ድረስ በየዓመቱ ሪፖርት ለማቅረብ[112] ግዴታ የገባበት ሰነድ ይገኝበታል፡፡

ሌላው ስለውጭ ዜጋ ጉዲፈቻ አድራጊ መወሳት ያለባቸው ነጥቦች አሉ፡፡ አንደኛ የውጭ አገር ጉዲፈቻ የመጨረሻ አማራጭ (last resort) መሆኑን ነው፡፡ ይህም ማለት አንድን

[112] ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ አገር ዜጋ ሲሆን በመመሪያው መሠረት ካለበት ግዴታዎች አንዱ ልጁ አስራስምንት ዓመት እስኪሞላው ድረስ በየዓመቱ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ይሁንና ሪፖርቱን የሚያቀርበው ለሚኒስቴር መሥሪያቤቱ ነው? ወይስ ጉዲፈቻ ልጁን አሳልፎ ለሰጠው ወገን የሚለው ጥያቄና ሪፖርቱ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ካልቀረበስ ሪፖርት ይቅረብልኝ ብሎ መጠየቅ ያለበት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ነው ወይስ ልጁን በጉዲፈቻ አሳልፎ የሰጠው ወገን በሚለው ላይ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱና በእጓለማውታን ድርጅቶች መካከል አለመግባባት እንዳለ ይሰማል፡፡

የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሪፖርት መቅረብ ያለበት ካልቀረበም እንዲቀርብለት መጠየቅ ያለበት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሳይሆን ልጁን በጉዲፈቻ አሳልፎ የሰጠው ግለሰብ ወይም ድርጅት ነው ይላል፡፡ ድርጅቶቹ ደግሞ ሪፖርቱ መቅረብ ያለበት (ግልባጭ ለጉዲፈቻ ሰጪው ሊደረግ ይችላል) ካልቀረበም እንዲቀርብ መጠየቅ ያለበት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ነው ባዮች ናቸው፡፡

በዚህ ጸሃፊ እምነት የድርጅቶቹ የክርክር መስመር አሳማኝና ሚዛን የሚደፋ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም አንደኛ መመሪያውን ያወጣው የሚኒስቴር መስሪያቤቱ ስለሆነ መመሪያውን ማስፈጸምና ተፈጻሚ ማየት በዋናነት ከእርሱ ይጠበቃል፡፡ ሁለተኛ በመመሪያው ውስጥ የተዘረዘሩት ነጥቦች ሁሉ ለሚኒስቴር መስሪያቤቱ የሚቀርቡ ሆነው ሳለ ሪፖርት መቀበል ግን የሌላ አካል ድርሻ ነው ብሎ መከራከር አሳማኝ አይመስልም፡፡ ሦስተኛ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከግለሰቦች ወይም ከተቋማት ይልቅ ከውጪው ዓለም ጋር ለመገናኘት አቅሙም መድረኩም አለው፡፡ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችንም ቢሆን ተጠቅሞ ግንኙነት ለመፍጠር የተሻለ ዘላቂ መሠረት አለው፡፡ ይህ ሁሉ ተጠቃልሎ ሲታይ የሚኒስቴር መስሪያቤቱ በዚህ ረገድ የሚያቀርበው ክርክር ከሃላፊነት ለመሸሽ የሚደረግ ይመስለኛል፡፡

ህፃን የውጭ አገር ዜጋ በጉዲፈቻ እንዲያሳድገው የሚፈቀደው በጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰብ ወይም በሌላ ተለዋጭ ዘዴ በአገር ውስጥ ሊረዳ ካልቻለ ብቻ ነው፡፡ ይህ ቅድመ ሁኔታ በህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን በአንቀጽ 21(ለ) የተመለከተ ሲሆን በተሻሻለው የቤተሰብ ህግም በአንቀጽ 194(3)(መ) የተገለጸ ነው፡፡ ሁለተኛ ጉዲፈቻ አድራጊው ጉዲፈቻ ልጁን አላግባብ መጠቀሚያ እንደማያደርገው ለመገመት የሚያስችል መረጃ ሊኖር ይገባል[113]፡፡

አልፎ አልፎ እንደሚያጋጥመው የውጭ አገር ዜጎች ኢትዮጵያውያን ህፃናትን በጉዲፈቻ ከወሰዱ በኋላ አስነዋሪ ለሆነ ግብረሰዶማዊና ወሲባዊ በደል ያጋልጧቸዋል፡፡ ከዚህም አልፎ ጠቃሚ የሆኑ የሰውነታቸው አካል ለምሳሌ እንደኩላሊት፣ ዓይን ወዘተ በቀዶ ጥገና ከወጣ በኋላ በጎዳና ላይ ይጥሏቸዋል፡፡ ይህ እንግዲህ የጉዲፈቻ ዋነኛ ዓላማ የሆነውን የህፃኑን ደህንነት የሚጎዳ ነው፡፡ ስለሆነም ይህንን አደጋ ለመከላከል ይቻል ዘንድ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ፍርድ ቤቱ የውጭ አገር ዜጋ ጉዲፈቻ አድራጊ ሲያጋጥመው ይህንን ሁኔታ ግምት ውስጥ እንዲያስገባ ያሳስበዋል፡፡ ለነገሩ የህፃናት መብት ኮንቬንሽንም "... የህፃኑ ከአገር ውጭ መሄድ ጉዳዩን ለሚያስፈጽሙ የገቢ ማግኛ ዘዴ እንዳይሆን ተገቢ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ" ያስገነዝባል፡፡

በዚህ ጽሁፍ በጉዲፈቻ ሥር በመጨረሻ ለማንሳት የታሰበው ነጥብ ጉዲፈቻ አድራጊው በውጭ አገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሲሆን ተፈፃሚ የሚሆነው ሥነ-ሥርዓት ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን የሚለው ነው? ወይስ መደበኛው ማለትም ለአገር ውስጥ ጉዲፈቻ የምንከተለው ሥነ-ሥርዓት የሚል ነው፡፡

[113] የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 21(መ)

እንግዲህ ይህ ጉዳይ የተቀላለቀለ ነገር አለበት፡፡ በአንድ በኩል ጉዲፈቻ አድራጊው ኢትዮጵያዊ ዜጋ በመሆኑ መደበኛው የጉዲፈቻ ሥርዓት ተፈፃሚ እንዲሆንለት ይጠብቃል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ልጁን በጉዲፈቻ ልጅነት ተቀብሎ ወደውጭ አገር የሚወስደውና ከኢትዮጵያ ግዛት ክልል የሚያስወጣው ስለሆነ የተለየ ጥንቃቄ ይጠይቃል፡፡ ስለዚህም ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን የምንከተለው ሥርዓት መፈጸም ተገቢነቱ ይታያል፡፡ ከዚህ በመነሣትም በአፈጻጸም ረገድ እንዲህ የተዘበራረቀ ሁኔታ ይታያል[114]፡፡

ህጉ በጥንቃቄ ከታየ ግን ይህን ያህል አወዛጋቢ ነገር ያለበት አይደለም፡፡ የትኛውን ሥርዓት እንደምንከተል የሚወስነው የጉዲፈቻ አድራጊውን ዜግነት መሠረት በማድረግ እንጂ የሚኖርበትን ቦታ መሠረት አድርገን አይደለም፡፡ በመሆኑም ጉዲፈቻ አድራጊው ኢትዮጵያዊ ዜጋ መሆኑ ከተረጋገጠ የትም ይኑር የትም፣ ልጁን የትም ይውሰደው የት፣ ተፈጻሚ መሆን ያለበት የጉዲፈቻ ሥርዓት መደበኛው የአገር ውስጥ የጉዲፈቻ አካሄድ መሆን ይኖርበታል፡፡

በርግጥ የህፃናት መብት ኮንቬንሽን የአገር ውስጥና የውጭ አገር (In-country and Inter country) ጉዲፈቻ ብሎ በመከፋፈል ለጉዲፈቻ አድራጊው ዜግነት ሳይሆን የጉዲፈቻ ልጁ ከጉዲፈቻው መመስረት በኋላ የት ይኖራል ለሚለው ነጥብ ትኩረት የሚሰጥ ይመስላል፡፡ ቢሆንም የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ጉዳዩን ከጉዲፈቻ አድራጊው ዜግነት አንጻር የሚያየው ስለሆነና

114 ከጥቂት ዓመታት በፊት በመንግሥት ሥራ ምክንያት ወደ ውጭ አገር ለመሄድ በዝግጅት ላይ የነበረ ኢትዮጵያዊ ወዳጄ በጉዲፈቻ ሊወስደው ያዘጋጀውን ህፃን የጉዲፈቻ ስምምነት በፍርድ ቤት ለማስጸደቅ ሲሄድ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የድጋፍ ደብዳቤ እንዲያቀርብ ተጠይቆ እንደነበር አጫውቶኛል፡፡ ይህ ግን የህጉ መንፈስ አይመስለኝም፡፡

ይህም ከህፃናት መብት ኮንቬንሽን መጽደቅ በኋላ የወጣ አዋጅ ስለሆነ በኢትዮጵያ ፍርድቤቶችና አስፈፃሚ አካላት አሠራር ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባው ከኮንቬንሽኑ ይልቅ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ነው ብለን እናምናለን፡፡

Scanned by CamScanner

ምዕራፍ ዘጠኝ

ቀለብ የመስጠት ግዴታ

9.1. አጠቃላይ የመነሻ ሃሳብ

የሥጋና የጋብቻ ዝምድና በጋብቻ ክልክላ በኩል ያለው ሕጋዊ ውጤት በዚህ መጽሐፍ በቀጽ አንድ ሥር ተመልክተነዋል፡፡ የዚህ ዝምድና ሌላኛው ሕጋዊ ውጤት ደግሞ በዘመዳሞቹ መካከል የሚፈጥረው አንዱ ለሌላው ያለበት ቀለብ የመስጠት ግዴታ ነው፡፡ በመጽሐፉ ይኸኛው ቅጽ በዚህ ርእስ ስር ይህንን ነጥብ ለማየት እንሞክራለን፡፡

በርግጥ ኢትዮጵያን በመሰለ ዘመደ ብዙ (extended family) ማህበረሰብ በዘመዳሞች መካከል የሚኖረው ቀለብ የመስጠት ግዴታ በህግ የተጣለ ግዴታ ብቻ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ እንዲያውም ከህግ ግዴታነቱ በላይ ባህላዊና ሞራላዊ ግዴታነቱ ሚዛን የሚደፋ ይመስላል፡፡ አብዛኛው የህብረተሰባችን ክፍል ለስጋ ወይም ለጋብቻ ዘመዱ ድጋፍ የሚሰጠው ብከለከለው ምናልባት ፍርድቤት ፊት ከሶ ያስፈርድብኛል ከሚል እሳቤ ሳይሆን እንዲሁ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ማህበረሰባዊ ግዴታዬ ነው ብሎ ስለሚያምን ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ አንዳንዱ እንኳን ለዘመድና ለባዕድም ቢሆን ተቸግሮ ባለበት ሁኔታ እርዳታ አለመስጠት ሃጢአት ነው ብሎ ያምናል፡፡ አንዳንዱ ደግሞ ዘመዱ ተቸግሮ እርዳታ ካልሰጠው ማህበረሰቡ ዝቅተኛ ግምት እንደሚሰጠው ስለሚገምት ነው፡፡ ሌሎች ደግሞ ነግ በኔ ከሚል ስሜት በመነሳ ነው ማለትም አሁን ለተቸገረ ዘመዱ ካልረዳሁ ነገ ከነገወዲያ ችግር ላይ ከወደቅሁ ዞር ብሎ የሚያየኝ አይኖርም ከሚል ሥጋት የመነጨ ነው፡፡ ሌላም ሌላም ምክንያት ይኖራል፡፡ ያም ሆነ ይህ በዚህ ረገድ ዋናው የግዴታው ምንጭ ተደርጎ የሚወሰደው ህጉ ሳይሆን

ከህጉ ወጣ ያሉት ማህበረሰባዊ ደንቦች (non-legal social norms) ናቸው ብለን እናምናለን፡፡

ይህ መቼም ቢሆን ሊበረታታ የሚገባው የመተጋገዝ ባህላችን ቢሆንም ዘመን እየሰለጠነ፣ ኑሮ እየተወደደ ሲሄድ መተሳሰቡና መረዳዳቱ በዚሁ ዓይነት ስለመቀጠሉ እጅግ አጠያያቂ ነው፡፡ በተጨባጭም "የስልጣኔ" ጭላንጭል እየደረሰባቸው ባሉት ከተሞቻችን ውስጥ ቤተሰባዊ ቁርኝቱ ያን ያህል የጠበቀ እንዳልሆነ የሚጠቁሙ የግለኝነት ባህርያት እየተከሰቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም ይህ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ለባህላዊና ለሞራላዊ ጫናዎች ብቻ መተው ግዴታው ስለመፈጸሙ አስተማማኝ ማረጋገጫ አይሰጥም፡፡ በተለይም እንደኢትዮጵያ ባሉ ድሃና አስተማማኝ ማህበራዊ ዋስትና እንዲሁም የሥራ አጥ አበል (unemployment allowance) በማይታወቅባቸው አገሮች የተወሰነው የማህበረሰቡ አባል የሥጋና የጋብቻ ዝምድናውን እንደማህበራዊ ዋስትና ይገለገልበት ዘንድ ሀጋዊ ማዕቀፍ ማደራጀት ተገቢ ሆኖ ይታያል፡፡

ነገር ግን እንዲህ ዓይነት ቤተሰባዊ ማህበራዊ ዋስትና በህግ ሲቀረጽ ተገቢ ግምት ሊሰጣቸው የሚገቡ ነጥቦች አሉ፡፡ ከእነዚህም ጥቂቶቹ፡- አንደኛ ቀለብ የመስጠት ግዴታ የሚጣለው እንዲሁ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ ነው ለተባለ ሰው ሁሉ ሳይሆን ጠበብ ብሎ ተቀርጾ በጣም ቅርብ የሆኑ ቤተዘመዶችን ብቻ ለይቶ ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል፡፡ እንዲህ ካልሆነ ግን ብዙ እርዳታ ጠያቂ ይፈጥርና የሚሰጠው እርዳታ የተበጣጠሰ ይሆንና ውጤታማ ሳይሆን ይቀራል፡፡ ሁለተኛ የግዴታው መጠንም ለቀለብ ጠያቂው ለእለት ተእለት ኑሮ መሰረታዊ የሆኑ ቁሳቁሶች በማቅረብ መወጣት የሚቻል እንጂ ሁሉም የቀለብ ጠያቂውን ፍላጎቶች እንዲያሟላ የሚያስገድድ

Scanned by CamScanner

መሆን አያኖርበትም፡፡ ሦስተኛ ቀለብ የመስጠት ግዴታው በቀለብ ጠያቂው ላይ የጥገኝነት ስሜት (dependency) በሚፈጥርበት መልኩ ሳይሆን ተቀጥሮ ወይም ሥራ ፈጥሮ ራሱን ማስተዳደር የሚችልበት ሁኔታና ስሜት በሚፈጥር መልኩ መተረጽ ይኖርበታል ተብሎ ይታመናል፡፡

ከዚህ አንጻር ሃገራችን በ1952ቱ የፍትሐብሔር ህግም ሆነ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ውስጥ "ቀለብ የመስጠት ግዴታ" በሚል ምዕራፍ ስር ቁጥራቸው የማይናቅ ድንጋጌዎችን አስቀምጣለች፡፡ በዚህ ረገድ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ውስጥ የተቀመጡት ድንጋጌዎች በጥቂት ነጥቦች ካልሆነ በቀር ከነባሩ የፍትሐብሔር ህግ አንጻር ብዙም መሠረታዊ የሚባል ለውጥ አያታይባቸውም፣ መጠነኛ ማሻሻያዎች ግን መኖራቸው አልቀረም፡፡

ወደ ህጉ ይዘት ስናመራ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ድንጋጌዎች ለማብራራት የምንሞክር ሲሆን እግረመንገዳችን የተሻሻለው የቤተሰብ ህግና ነባሩ የፍትሐብሔር ህግ በዚህ በተያዘው ቀለብ የመስጠት ጉዳይ የተለያየ አቋም የወሰዱባቸውን ነጥቦች እንመረምራለን፡፡

9.2. ቀለብ የመስጠት ግዴታ ስላለባቸው ወገኖች

በመጀመሪያ ደረጃ ቀለብ የመስጠት ግዴታ በህግ የተጣለው በእነማን መካከል ነው? የሚለውን ስናይ በቀጥታ ወላጆችና ተወላጆች ማለትም በአባትና በልጅ፣ በእናትና በልጅ እንዲሁም በልጅና በአያት መካከል ያለው አንዱ ነው[115]፡፡ ሌላው ደግሞ በቀጥታ የጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ማለትም በባልና የሚስት አባት ወይም እናት ወይም አያት ወይም ልጅ

[115] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 198

በሚስትም በኩል እንዲሁ ለባል አባት ወይም እናት ወይም አያት ወይም ልጅ ግዴታው አለ[116]፡፡ ሦስተኛው ደግሞ ወደጎን ወደሚቆጠር የሥጋ ዝምድና የሚሸጋገር ሲሆን በወንድምና በወንድም፣ በእህትና በእህት እንዲሁም በወንድምና በእህት መካከል የተጣለ ግዴታ ነው[117]፡፡ በመጨረሻም በዚህ መጽሐፍ በቅጽ አንድ ሥር በባልና ሚስት መካከል የመረዳዳትና የመተጋገዝ የህግ ግዴታ እንዳለ የገለጽን ስለሆነ ይህ የመተጋገዝ ግዴታም ቀለብ የመስጠት ግዴታንም እንደሚጨምር ተደርጎ መተርጎሙ አግባብ ስለሆነ በባልና ሚስት መካከልም ይህ ቀለብ የመስጠት ግዴታ እንዳለ[118] መገንዘብ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

እንደሚታመነው በባህልና በሞራል መሠረት ለዘመድ ቀለብ መስጠት በአጠቃላይም የተቸገረን መርዳት ከዚህ በላይ በጠቀስናቸው ጠባብ ዝርዝር ውስጥ ብቻ የታጠረ አይደለም፡፡ በተለምዶ እስከ አንትና አክስት እንዲሁም እስከአንት ልጅና የአክስት ልጅ ድረስ ይዘልቃል፡፡ የሚስት ወንድም ወይም እህት በባል በኩልም ወንድሙን ወይም እህቱን መርዳት የተለመደ ነው፡፡ አልፎ አልፎ እንዲያውም የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ሳይኖር እንዲሁ የተቸገረን መርዳት እንደግዴታ የሚወሰድበት ሁኔታ አለ፡፡ ከዚህ የምንገነዘበው በባህልና በሞራል በኩል ያለው የተቸገረን የመርዳት ግዴታ በህግ ከተቀመጠው ግዴታ የሰፋ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ህግ አውጪው የተፈጻሚነት ወሰኑ ጠበብ ያለ ቀለብ የመስጠት ግዴታ በህግ ካስቀመጠ በኋላ ከዚያ ውጪ ያለው ግን ለባህልና ለሞራል ግዴታ ትቶታል ማለት ነው፡፡ በውጤቱም የህግ ግዴታ በተጣለበት መጠን ግዴታው ካልተፈጸመ ፍርድ ቤት ክሶ በፍርድ አስገዳጅነት ግዴታውን

[116] ዝኒ ከማሁ
[117] ዝኒ ከማሁ 198 (2)
[118] ዝኒ ከማሁ

ሚስትየዋም የሚችል ሲሆን የባልና የሞራሉ ግዴታው ግን ይህንን ግዴታ መወጣት አይለቅም::

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው የሚስት ወንድም ወይም እህት ልጆች፣ እንዲሁም የባል ወንድም ወይም እህት ለሚስት የትዳር የጋብቻ ዘመዶች ስላልሆኑ እነርሱን መርዳት የባል ወይም የሞራል ግዴታ እንጂ የህግ ግዴታ አይደለም:: ይህ ግን የተሟላ እውነታ አይደለም:: ምክንያቱም ለሚስት ወንድም ቀለብ መስጠት በባለቤቷ ላይ የባህል ወይም የሞራል ግዴታ የሚኖር ቢሆንም በሚስቱ በኩል ሲታይ ግን ወንድምዋ ስለሆነ ወደነን በሚፈጠር የሥጋ ዝምድና መሠረት ለርሱ ቀለብ የመስጠት ህጋዊ ግዴታ አለባት:: ይህን ግዴታዋን ለመወጣትም ከግል ሃብትዋ ወይም ከባልና ሚስት የጋራ ሃብት ወጪ ማድረግ ትችላለች[119]:: ስለዚህ ዞሮ ዞሮ ለባል ወይም ለሚስት እህት ወይም ወንድም ቀለብ የመስጠት ግዴታ ለባልና ሚስቱ የህግ ግዴታ መሆኑን መገንዘብ ይገባል::

9.3. የግዴታው ይዘት

ቀጥለን ስለግዴታው ይዘት እንመለከታለን:: በህጉ መሰረት ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው እንደባለጉዳዮቹ ሁኔታና እንደአካባቢው ልማድ የሚስማማውን በመከተል ለቀለብ ተቀባዩ ምግብ፣ መኖሪያ፣ ልብስ ጤናውን የሚጠብቅበትና እንደሁኔታው ለትምህርት አስፈላጊ የሆነውን ነገር መስጠት ይጠበቅበታል[120]:: እንደሚታወቀው ምግብ፣ ጤና፣ ልብስ፣ ትምህርትና መጠለያ ለሰው ልጅ መሠረታዊና አስፈላጊ ናቸው:: እነዚህን ነገሮች ማግኘትም የሰብአዊ መብት መከበር አንዱ ገጽታ ተደርጎ ይወሰዳል::

[119] ዝኒ ከማሁ 71(ለ)
[120] ዝኒ ከማሁ 197

ብዙ ሃገሮች የኛን ሃገር ጨምሮ የአገልግሎቶቹን መሠረታዊነት በመቀበል አገልግሎቶቹን ለዜጎቻቸው ለማቅረብ በህገ-መንግስቶቻቸው ውስጥ ቃል ገብተዋል[121]:: ተግባራዊ አፈጻጸማቸው ላይ ግን የየሃገራቱ የኢኮኖሚ አቅም ከፍተኛ ተፅእኖ ሲያሳድርባቸው ይታያል:: "ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ለሃምሳ ሰው ጌጡ" እንዲሉ ግዴታውን ወደ ህብረተሰቡ በስስ መበተን (thin distribution) አንዱ መፍትሔ ነው:: በመሆኑም የሃገራችን ህግ አውጪ የእነዚህን አገልግሎቶች ወጪ በተወሰነ ደረጃ የአገልግሎት ጠያቂው የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመዶች እንዲሸፍኑ ለማድረግ ያመች ዘንድ ህጋዊ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንደአንድ መንግስታዊ የግዴታ መወጫ መንገድ አድርጎ ወስዶታል ማለት ነው::

ይህ እንዳለ ሆኖ በነባሩ የፍትሐብሄር ህግ ውስጥ እዳይ ከተመለከትነው መሠረታዊ ፍላጎቶች መካከል 'ትምህርት' የሚለው የተካተተ አልነበረም:: ምናልባትም ህጉ ሲወጣ ማለትም ከዛሬ አምሳ ዓመት በፊት በያኔዋ ኢትዮጵያ ትምህርት የምግብና የልብስ ያህል መሠረታዊ ፍላጎት ተደርጎ ስላልተወሰደ ይሆናል ተብሎ ይገመታል:: ዞሮ ዞሮ ግን በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የትምህርት መሠረታዊ ፍላጎት መሆን አጠያያቂ ስላልሆነ የተሻሻለው የቤተሰብ ህጉ ሲረቀቅ ይህንኑ እንዲያካትት ተደርጓል::

ሌላው ቀለብ ሰጪው እንዲሰጥ የሚጠበቅበት ድጋፍ በየትም ቦታ ለሁሉም ቀለብ ጠያቂዎች አንድ ዓይነት ሳይሆን "... እንደባለጉዳዮቹ ሁኔታና እንደየአካባቢው ልማድ..."[122] የሚለያይ ነው:: እዚህ ላይ እንግዲህ ባለጉዳዮቹ ቀለብ ሰጪውና

[121] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 41
[122] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 197

Scanned by CamScanner

ቀለብ ጠያቂው ናቸው፡፡ ይህም ማለት ለምሳሌ ቀለብ ጠያቂው አዛውንት ከሆነ ትምህርት መሠረታዊ ፍላጎቱ ነው ለማለት ይከብዳል፤ ይልቁንም የጤና አገልግሎት መሠረታዊነት ለአዛውንቱ ሚዛን የሚደፋ ነው፡፡ ቀለብ ጠያቂው ህፃን ሲሆን ደግሞ ሁኔታው ይለያል፡፡ በሌላም በኩል ቀለብ ሰጪውና ቀለብ ጠያቂው የሚኖሩት የትምህርትና የጤና አገልግሎት በማይገኝበት የገጠር አካባቢ ከሆነ ቀለብ ሰጪው ለራሱና ለልጆቹ ማቅረብ የማይችለውን ትምህርትና ጤና ለቀለብ ጠያቂው እንዲያቀርብ ማስገደዱ ተገቢነቱ ያጠያይቃል፡፡ የትምህርትና የጤና አገልግሎት ባለበትም ቢሆን ቀለብ ሰጪው አቅሙ የሚችለው ያህልና በአካባቢው የተገኘውን ያህል እንጂ ሩቅ ወስዶ፣ ውጪ ሃገር ልኮ እንዲያስተምር ወይም እንዲያሳክም መጠበቁ ተገቢ አይመስለንም፡፡ ምክንያቱም የቀለብ ሰጪው ግዴታ በመወሰን ረገድ የቀለብ ጠያቂውን ችግር ብቻ ሳይሆን የቀለብ ሰጪው አቅምንም ግምት ውስጥ ማስገባት ስለሚገባ ነው፡፡

ቀለብ የመስጠት ግዴታ ተፈጻሚ ይሆን ዘንድ በህጉ የተመለከተው የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድናና ደረጃ መኖር አስፈላጊ ቢሆንም በቂ ግን አይደለም፡፡ ይህም ማለት የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና መኖሩ ብቻ በቀለብ ሰጪው ላይ ቀለብ የመስጠት ግዴታ በቀለብ ጠያቂው ላይ ደግሞ ቀለብ የመጠየቅ መብት አያጎናጽፍም፡፡ ቀለብ ጠያቂው የዝምድናው መኖር ከማሳየት በተጨማሪ እርሱ (ቀለብ ጠያቂው) "... ሠርቶ ለኑሮው አስፈላጊ የሆነ ገቢ ለማግኘት አቅም የሌለውና ችግር ላይ የወደቀ መሆኑን"[123] ማሳየት ይጠበቅበታል፡፡

ቀደም ሲል ቀለብ የመስጠት ግዴታ በህግ ሲጣል በቀለብ ጠያቂው ላይ የጥገኝነት ስሜት በማይፈጥር መልኩ ሊቀረጽ

[123] ዝኒ ከማሁ 201

እንደሚገባው ገልጸናል፡፡ ስለሆነም ቀለብ ጠያቂው ሠርቶ ገቢ ማመንጨት እየቻለ፣ ሥራ ፈጥሮ ወይም ተቀጥሮ ኑሮውን መምራት እየቻለ፣ ሥራ ፈጥሮ ለመስራት ተነሳሽነት በማጣት ወይም ሥራን ለማማረጥ ሲል ችግር ላይ የወደቀ ከሆነ የቀለብ ጠያቂነት መብት ተጠቃሚ ሊሆን አይገባውም፡፡

በርግጥ ቀለብ ጠያቂው እድሜው ከአስራ አራት ዓመት በታች ወይም ከስድሳ ዓመት በላይ ከሆነ ሥራ ፈጥሮ ወይም ተቀጥሮ ኑሮውን መምራት ይችላል ለማለት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም በኢትዮጵያ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ መሠረት ዕድሜው ከአስራ አራት ዓመት በታች ከሆነ ሰው ጋር የሥራ ውል መዋዋል ስለማይፈቀድ[124] በዚህ ዕድሜው ተቀጥሮ ገቢ ማመንጨት ይችላል ብሎ መከራከር አይቻልም፡፡ በዚህ ዕድሜውም ሥራ ፈጥሮ መስራት ነበረበት ለማለትም ይከብዳል፡፡ ዕድሜው ከስድሳ ዓመት በላይ የሆነ ሰው ደግሞ ስድሳ ዓመት የመጦሪያ ዕድሜ ስለሆነ[125] በህጋችን መሠረት ከዚያ ዕድሜ በኋላ በመንግስት መስሪያ ቤት መቀጠር አይችልም፡፡ በግል ድርጅቶችም ቢሆን በዚያ ዕድሜ የመቀጠር እድሉ የተዘጋ ነው ማለት ባይቻልም እጅግ የጠበበ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዚህ የእርጅና ዕድሜ ሥራ ፈጥሮ ራሱን ሊያስተዳድር ይገባል ለማለትም በአብዛኛው ከባድ ነው፡፡ ስለዚህ ከመቀጠሪያ የዕድሜ ወለል በታች ያሉና ከመቀጠሪያ የዕድሜ ጣሪያ በላይ ያሉት ቀለብ ጠያቂዎች ዝምድና መኖሩንና ችግር ላይ መውደቃቸውን ከሳዩ ተጨማሪ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልጋቸው ዕድሜአቸውን በማረጋገጥ ብቻ የቀለብ

[124] የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 89(2) እንዲያውም የመንግሥት ሠራተኛ ሆኖ ለመቀጠር በመርህ ደረጃ አሥራ ስምንት ዓመት መድረስን የግድ ይላል (የፌዴራል መንግስት ሠራተኛ አዋጅ ቁ. 262/94 አንቀጽ 11(1)(ሀ) ይመለከቷል)

[125] የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/95 አንቀጽ 12(ሐ)

ጥያቄአቸውን ማቅረብ ይችላሉ ማለት ነው፡፡ አስራ አራትና ከዚህ በላይ እንዲሁም ከስድሳ ዓመት በታች ያሉ ቀለብ ጠያቂዎች ግን የተለየ የአካል ጉድለት ወይም የጤና መታወክ ካላባቸ በስተቀር ሥራ የሚቀጥረን ስላጣን ችግር ላይ ወድቀናል በማለት ብቻ የመብቱ ተጠቃሚ የሚያደርጋቸው አይሆንም ለምን ቢባል ሥራንና የሥራ ቦታን ሳያማርጡ መቀጠር ወይም ሥራ ፈጥረው የገቢ ምንጫቸውን ማደራጀት ይገባቸዋልና ነው፡፡ ስለዚህ ሥራም ባይኖራቸው የመስራት አቅሙ እስካላቸው ድረስ ሥራ ማግኘት አልቻልንምና ችግር ላይ ወድቀናል በሚል የመብቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ህጉ እንዳልፈቀደ[126] መገንዘብ የሚገባ ይመስለናል፡፡

በዚህ ረገድ በነባሩ የፍትሐብሄር ህግና በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ መካከል መጠነኛ የይዘት ልዩነት እንዳለ መገንዘብ ጠቃሚ ነው፡፡

በነባሩ ህግ "... ግዴታው እንዲፈጸምለት የሚጠይቀው ሰው <u>ሠርቶ ለመብላት የማይችል ሲሆንና በችግር ላይ የወደቀ ሲሆን ብቻ ነው</u>"[127] ይላል፡፡ (ሠረዝ የተጨመረ) የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ግን "... ቀለብ ጠያቂው <u>ሠርቶ ለኑሮው አስፈላጊ የሆነ ገቢ ለማግኘት አቅም የሌለውና በችግር ላይ የወደቀ ሲሆን ብቻ ነው</u>"[128] በሚል ይነበባል፡፡ (ሠረዝ የተጨመረ) በነባሩ ህግ

---

[126] በርግጥ ከአስራ አራት ዓመት በላይ እንዲያውም ከአስራ ስምንት ዓመት በላይ ዕድሜ የደረሱ ሆነውም በትምህርት ወይም በስልጠና ውስጥ ያሉ ከሆነ ቀለብ ሰጪው እነዚህን የመርዳት ግዴታ አለበት፡፡ በዚህ ረገድ በአንድ ወቅት የፖላንድ ፍርድ ቤት እንዲህ ብሎ ነበር፡፡ "... parents have to support even an able bodied child of full age if that child is engaged in full time study and his interest and industry shows that he deserves support (Lasok, p.202)

[127] የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 812

[128] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 201

መሠረት አልፎ አልፎ ሲቀርብ የነበረው ክርክር ሲታይ አንድ ቀለብ ጠያቂ ሥራ ለማግኘት ሞክሮ ካልተሳካለት ሠርቶ ለመብላት አልቻለም ተብሎ ሊወሰድ ይገባል፡ በዚህ ሁኔታ በችግር ላይ ከወደቀም ቀለብ ሊቆረጥለት ይገባል የሚል ነበር፡፡ ይህ አተረጓጎም ሥራ ፈጥሮ የመስራት ተነሳሽነትን የሚገድል ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ሲቀረጽ ቀለብ የመጠየቅ መብት ሥራ በማግኘትና ባለማግኘት ላይ የተንጠለጠለ ሳይሆን የመሥራት አቅም (working potential) በመኖርና ባለመኖር ላይ እንዲመሰረት አድርጎታል፡፡ ይህም ቀባሪ በማፈላለግ ላይ ተወስኖ መቅረትን አስወግዶ ሥራ ፈጥሮ እስከ መስራት ድረስ የሚዘልቅ ተነሳሽነትን በሚያበረታታ መልክ የተቀረጸ ነው፡፡ይህም ጥገኛ አመለካከትን ያስወግዳል ተብሎ ይታመናል፡፡

9.4. ግዴታው ቀሪ ስለሚሆንበት ሁኔታ

ከቀለብ የመስጠት ግዴታ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ሌላው ነጥብ ቀለብ ጠያቂው ከቀለብ ሰጪው ጋር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና እንዳለውና ሠርቶ ራሱን ለማስተዳደር አቅም የሌለው መሆኑን እንዲሁም በችግር ላይ የወደቀ መሆኑን ካስረዳም በኋላ ቢሆን መብቱ ቀሪ የሚሆንበት ሁኔታ አለ፡፡ ከእነዚህም አንዱ የቀለብ ጠያቂውና የቀለብ ሰጪው ዝምድና የጋብቻ ዝምድና ከነበረና የዝምድናው መሰረት የነበረው ጋብቻ በፍቺ ወይም የጋብቻ ሁኔታዎች ባለመሟላታቸው ምክንያት ከፈረሰ ግዴታው ቀሪ ይሆናል[129]፡፡ ጋብቻው የፈረሰው ከተጋቢዎች አንዱ መሞት ከሆነ ግን ግዴታው ቀጣይ ይሆናል፡፡ የዚህ ምክንያቱ ግልጽ ይመስለናል፡፡ ጋብቻው በሞት ሲፈርስ በተጋቢዎቹ ቤተዘመዶች መካከል ያለው ግንኙነት ጤናማ ሆኖ እያለ ጋብቻው ከአቅም በላይ በሆነ ሃይል የፈረሰ መሆኑ

---

[129] ዝኒ ከማሁ 199

የሚያል፡፡ ከዚህ ውጪ በሆኑ ምክንያቶች ጋብቻው ሲፈርስ ግን ተጋቢዎቹ እርስ በራሳቸውና የተጋቢዎቹ ቤተዘመዶች የሚኖራቸው ቀጣይ ግንኙነት ጤናማነቱ አጠያያቂ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ለጋብቻ ዘመዱ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ማስቀጠል ፍትሐዊ አይሆንም፡፡ ለዚህም ነው ቀለብ የመስጠት ግዴታው በጋብቻው መፍረስና አለመፍረስ ሳይሆን በማፍረሻ ምክንያቱ ላይ እንዲመሠረት የተደረገው፡፡

ሁለተኛ ቀለብ ጠያቂው ቀለብ የመጠየቅ መብቱን እንዲነፈግ የሚያደርገው ጉዳይ በቀለብ ሰጪው ወይም በቅርብ ዘመዶቹ ህይወት ወይም ንብረት ላይ ወንጀል ወይም የወንጀል ሙከራ የፈጸመ እንደሆነ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ከፍትህ መሠረታዊ መርሆዎች አንዱ "ማንም ሰው ከራሱ ጥፋት አትራፊ (ተጠቃሚ) መሆን የለበትም" (No one can benefit from his own fault) የሚል ነው፡፡ በዚህም ጉዳይ ቀለብ ጠያቂው ባንድ በኩል እንዲህ ዓይነት የወንጀል ድርጊት እየፈጸመ በሌላ በኩል ደግሞ ቤተዘመድ ነኝ እያለ ቀለብ እንዲሠፈርለት እንዲጠይቅ መብት መስጠቱ ይህንኑ መሠረታዊ የፍትህ መርህ የሚንድ ነው፡፡ ለነገሩ በውርስ ህጎችንም ቢሆን በህጉ የወራሽነት መብት የነበረው ሰው ከዚህ በላይ የተመለከቱት የወንጀል ድርጊቶች ከሞከረ ወይም ከፈጸመ ከውርስ ሊነቀል እንደሚገባ[130] በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

እዚህ ላይ አንድ ነጥብ አብሮ ማውሳቱ ጠቃሚ ሆኖ ይታያል፡፡ ይኸውም በነባሩ የፍትሐብሔር ህግ ውስጥ ተመሳሳይ የህግ ድንጋጌ የነበረ ሲሆን ከአሁኑ ህግ ጋር ሲነጻጸር መጠነኛ የይዘት ለውጥ ነበረው፡፡ እንዲህ ብሎ የሚነበብ ነበር፡፡

[130] የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 838

> *ቀለብ ተቀባዩ በቀለብ ሰጪው ወይም በዚሁ ሰው ወደላይና ወደታች በሚቆጠሩ ወላጆችና ተወላጆች ወይም ባል ወይም ሚስት ህይወት ላይ አደጋ በመጣል ሙከራ ተፈርዶበት እንደሆነ ቀለብ መቀበሉ ይቀርበታል*[131] *ይላል (ሠረዝ የተጨመረ)*

እዚህ ውስጥ ከተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ተመሳሳይ ድንጋጌ አንፃር ሲታይ ቢያንስ ሁለት የይዘት ለውጦች ይታያሉ፡፡ አንደኛ በነባሩ ህግ መሠረት ቀለብ ጠያቂው ቀለብ የመቀበል መብት የሚያሳጣው በቀለብ ሰጪው ወይም በህግ በተዘረዘሩት የቅርብ ቤተዘመዶች ህይወት ላይ የመግደል ሙከራ ከፈጸመ ሲሆን በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ መሠረት ግን ቀለብ ጠያቂው መብቱን የሚያጣው በቀለብ ሰጪው ወይም በቅርብ ቤተዘመዶቹ ህይወት ላይ ብቻ ሳይሆን በንብረታቸውም ላይ ቢሆን ወንጀል ከፈጸመ በቂ ነው፡፡ ስለዚህ በአዲሱ ህግ ቀለብ ጠያቂው መብቱን የሚያጣው በመግደል ሙከራ ብቻ ሳይሆን በስርቆት፣ በዘረፋ እና በመሳሰሉትም ወንጀሎችም ጭምር ሊሆን ይችላል፡፡ ሁለተኛ በነባሩ ህግ መሰረት ቀለብ ጠያቂው ቀለብ የመቀበል መብቱን የሚያጣው በመግደል ሙከራው ወንጀል ተከሶ ተፈርዶበት[132] እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ግን ወንጀሉ መፈጸሙን እንጂ[133] ተከሶ የተፈረደበት ስለመሆኑ ቅድመ ሁኔታ ተደርጎ አልተቀመጠም፡፡ ሲጠቃለልም በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ መሠረት ቀለብ ጠያቂው ቀለብ የመጠየቅ መብቱን የሚያጣባቸው ሁኔታዎች ሰፋ ብለው

[131] ዝኒ ከማሁ 811

[132] የመግደል ሙከራ በመፈጸሙና በመቀጣቱ መብቱን የሚያጣ ከሆነ ግድያውን ከፈጸመ ግን በበለጠ ምክንያት (for stronger reason) በህጉ በግልጽ ባይመለከትም መብቱ ይኖረዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡

[133] በዚህ ረገድ ለፍትሐብሔር ህጉ ዓላማ የሚበቃ ያህል ማስረጃ ከቀረበ በቂ ነው፡፡ ምክንያቱም እዚህ ላይ ዓላማውና ግቡ በሰውየው ላይ የወንጀል ቅጣት ለመጣል ሳይሆን ፍትሐብሔራዊ የመብት ገደብ ለማስቀመጥ ብቻ ነውና፡፡

Scanned by CamScanner

መተመጣቸውን ማየት ይቻላል፡፡ ይህም የቀለብ ጠያቂውን ባህርይና ሥነ-ምግባር የመግራት ግብ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

በመጨረሻም በነባሩ የፍትሐብሔር ህግ ውስጥ ተደንግጎ የነበረና በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ውስጥ እንዳይካተት የተደረገው ድንጋጌ ሲትየዋ በተጠለፈች ወይም በተደፈረች ጊዜ ልጅህ ነው ተብሎ በዳኝነት ለተነገረበት ሰው የቀለብ መስጠት ግዴታ አይገባውም[134] የሚል ነው፡፡ ቀደም ሲል አባትነት ከሚታወቅባቸው መንገዶች አንዱና የመጨረሻው በፍርድ ውሳኔ አንድ ሰው የአንድ ልጅ አባት ነህ የሚባልበት ሁኔታ እንደሆነ አይተናል፡፡ ይህም በነባሩ የፍትሐብሔር ህግ ከሴትየዋ መደፈር ወይም መጠለፍ ጋር የተያያዘ እንደነበርም ተመልክተናል፡፡ከዚህም በመነሳት ነባሩ ህግ ይህን መሰል ድርጊት የፈጸመ ሰው በዚህ ድርጊት ከወለደው ልጅ ቀለብ የመጠየቅ መብት እንዳይኖረው ለማድረግ ያመች ዘንድ እላይ የተመለከተውን ድንጋጌ አስቀምጦ ነበር፡፡

የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ሲቀረጽ እንዲህ ዓይነት አካሄድ አልተመረጠም፡፡ በየትኛውም መንገድ አባትነት ቢረጋገጥም አንዴ የአባትና ልጅ ግንኙነት ከተፈጠረ በኋላ በአባቶች መካከል የመብት ልዩነት መፍጠር ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በፍርድ አባትነህ ተብሎ የአባትነት ግዴታውን እየተወጣ ከቆየ በኋላ የመሥራት አቅም አጥቶ ችግር ላይ በወደቀበት ጊዜ እርዳታ ሊሰጠው ሲገባ የለም አባትነህ የተባልከው በፍርድ ስለሆነ ቀለብ ሊሰፈርልህ አይገባም ከተባለ ቂመኝነትን ተበቃይነትን ያሳያል፡፡ የፍትሐብሔር ህግ ደግሞ ብቀላን ዓላማ አድርጎ የሚቀረጽ አይደለም፡፡ ምናልባት በተወሰነ ደረጃ ብቀላ ተፈላጊ ነው ከተባለ በወንጀል ህግ ውስጥ የሚሸፈን እንጂ የዚህ ህግ ዘርፍ አካል

[134] የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 810

አይደለም፡፡ ለነገሩ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ሥር አባትነት በፍርድ የሚወሰንበት ሁኔታ ከመጠለፍና ከመደፈር ጋር ብቻ ሳይሆን ተጨማሪ መሠረቶች የታከሉበት ስለሆነ ብቀላውን አላስፈላጊ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ ይህ ድንጋጌ ከአዲሱ ህግ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ በውጤቱም በዚህ ሁኔታ አባትነህ የተባለ ሰውም ቢሆን ሌሎቹ ሁኔታዎች ከተሟሉ ቀለብ የመጠየቅ መብቱን አያጣም ማለት ነው፡፡

ምዕራፍ አራት
አካለመጠን ስላልደረሱ ሰዎች

10.1. አጠቃላይ የመነሻ ሃሳብ

ይህ ምዕራፍ በነባሩ የፍትሐብሄር ህግ ውስጥ የቤተሰብ ህግ አካል ሳይሆን በአንደኛ መጽሐፍ "ስለ ሰዎች" በሚለው አንቀጽ ሥር ተካትቶ እንደነበር አይዘነጋም። የቤተሰብ ህጉ ተሻሽሎና ራሱን ችሎ በኮድ (መጽሐፍ) መልክ ተቀርጾ እንዲወጣ ሲወሰን የቤተሰብ ህጉ በተቻለ መጠን የተሟላ (comprehensive) ሆኖ መደራጀት ያለበት መሆኑን በማመን አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ከየቦታው ማሰባሰብ አስፈላጊ ነበር። ስለሆነም አካለመጠን ስላልደረሱ ሰዎች የሚደነግጉት የፍትሐብሄር ህጉ የአንደኛ መጽሐፍ የተወሰኑ ድንጋጌዎች ከቤተሰብ ህጉ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳላቸው በመታመኑና የቤተሰብ ህጉ ያለእነዚህ ድንጋጌዎች የተሟላ ነው ለማለት ስለማያስደፍር በቤተሰብ ህግ ውስጥ አንድ ምዕራፍ ተሰጥቶአቸውና ተገቢ ማሻሻያዎች ታክለውባቸው አሁን የያዙትን ቅርጽና ይዘት[135] ተጎናፅፈው ይገኛሉ።

እንደሚታወቀው ሰው ከተወለደበት ቀን አንስቶ እስከሞተበት ቀን ድረስ የህግ መብትና ግዴታ አለው። እንዲያውም የራሱ ጥቅም በሚያሻበት ጊዜ ሁሉ የተፀነሰ ልጅም በህይወት የሚኖር ከሆነ ከጽንስ ጊዜ ጀምሮ መብቱ ይኖረዋል። ነገር ግን የመብት ባለቤት መሆንና (holder of right) በመብቱ ሊሰራበት መቻል (exercise of right) የተለያዩ ናቸው። ሁሉም

[135] በፖላንድ የቤተሰብ ህግም ተመሳሳይ አደረጃጀት ተደርጓል።

የመኪና ባለቤት በባለቤትነት የያዛትን መኪና ማሽከርከር ይችላል እንደማይባለው ሁሉ መብት የተጎናፀፈ ሰው ሁሉም መብቱ በራሱ ይሰራበታል ማለት አይደለም።

10.2. አካለመጠን ያልደረሰ ሰው ማን ነው?

ህጉ አካለመጠን አለመድረስን ራስን በተሟላ ሁኔታ ለመምራት የሚያስችል የአካልና የአእምሮ ብስለት ካለመኖር ጋር ያያይዘዋል። በመሆኑም አካለመጠን ያልደረሰ ሰው ምንም እንኳ የመብት ባለቤት እንደሆነ ህጉ ቢቀበልም ባለበት ያለመብሰል ችግር ምክንያት መብቶቹንና ግዴታዎቹን የሚሠራባቸው በወኪሎቹ በኩል እንዲሆን አድርጎታል። ምክንያቱም አካለመጠን ያልደረሰው ሰው ድርጊቱን የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት በአግባቡ ላይገነዘብ ስለሚችል ጥቅሙን በሚጎዳ ጉዳይ ላይ ግዴታ ሊገባ ይችላል ብቻ ሳይሆን ሌሎች ወገኖችም የእርሱን አለመብሰል በመጠቀም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ሊወስዱበት ይችላሉ ተብሎ ይሰጋል። ለነገሩ ከፍትሐብሄር ህጉ በፊት በነበረን ልማዳዊ ህግም "እድሜአቸው ለማንኛውም ሁኔታ ከማይፈቅድላቸው ህፃናት ጋር በስምምነት የውልና የእርቅ ጉዳይ ያደረገ ሰው ውሉ አይረጋለትም"[136] የሚል ድንጋጌ ነበረን።

ጥያቄው እንግዲህ አካለመጠን ያልደረሰ ሰው ማለት ማን ነው? የሚል ይሆናል። ነባሩ የፍትሐብሄር ህግም ሆነ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ የምዕራፉ የመጀመሪያ አንቀጽ ለዚሁ ትርጉም አውለውታል። እንዲህም ይነበባል "አካለመጠን ያልደረሰ ሰው ማለት ጾታ ሳይለይ ዕድሜው አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ልጅ ነው"[137] ይላል። በአንዳንድ ሃገራት

[136] 107ኛ የኢትዮጵያ የጥንት ፍርዶች መዝገብ ቁጥር 151 እና 593

[137] የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 198 እና የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 215

Scanned by CamScanner

የአካለመጠን አለመድረስ የመጨረሻው ዕድሜ እስከ ሃያ አንድ አልፎ አልፎም እስከ ሃያ ሦስት ዓመት ድረስ ያደርሱታል፡፡

ከዚህም አልፎ በራስ ጉዳይ የመወሰን ሥልጣንና በመብቶች የመሥራት ጉዳይን በተመለከተ የተለያዩ ሃገራት የተለያየ አሠራር ይከተላሉ፡፡ አንዳንዶቹ ልጁ አካለመጠን እስኪደርስ ድረስ ማንኛውም ዓይነት ህጋዊ ድርጊት በወኪሉ በኩል ይሠራበታል እንጂ እርሱ ራሱ ማከናወን አይችልም (one joint step capacity) የሚል አቋም ያራምዳሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ልጁ በመብቱ በተሟላ ሁኔታ ሊሠራበት የሚችለው ደረጃ በደረጃ እየተለማመደ ሲመጣ ነው ከሚል እምነት በመነሳት አካለመጠን ከመድረሱ በፊት አንዳንድ መሰረተኛ ጉዳዮች ላይ እንዲወስን በህግ ዕድል ይሰጡታል (progressive capacity)[138]

በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ህግ ሁለተኛውን መስመር የተከተለ ነው ብለን እናስባለን፡፡ ይህንን ለማለት ያስደፈረን እዚህም እዚያም ያሉትን አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች በማየት ነው፡፡ ለምሳሌ ልጁ በጉዲፈቻ ልጅነት ሲወሰድ አስር ዓመት የሞላው ከሆነ ፍርድ ቤቱ ስለጉዲፈቻው ተገቢነት ሲወስን ልጁ ስለጉዲፈቻው የሚሰጠው አስተያየት ግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለበት ተደንግጓል[139]፡፡ ከዚህም ሌላ በአስራ አራት ዓመቱ የሥራ ውል መዋዋል እንደሚችል በአሠሪና ሠራተኛ ህጋችን ተመልክቷል[140]፡፡ በአስራ አምስት ዓመቱ ኑዛዜ ማድረግ እንደሚችል ተገልጾአል[141]፡፡ ከባድ ምክንያት ሲያጋጥም በአስራ ስድስት ዓመቱ ጋብቻ ሊፈጽም የሚችልበት ዕድል

[138] አቶ ኪዳነማሪያም ሐጎስ "Cessation of Disability under Ethiopian Civil Code of 1960" p.43, 1986 unpublished.
[139] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 191(3)
[140] የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 89(2)
[141] የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 308(1) በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ መሠረት ወደ አሥራ ስድስት ዓመት ከፍ ብሏል (አንቀጽ 295(2))

አለ[142]፡፡ ይህ ሁሉ የሚያሳየን በኢትዮጵያ የህግ አደረጃጀት ልጁ ዕድሜው እየጨመረ በሄደ ቁጥር ደረጃ በደረጃ በራሱ ጉዳይ የውሳኔ ሰጪነት ቦታና ዕድል እያገኘ ይሄዳል ማለት ነው፡፡ ይህ ነው እንግዲህ የኢትዮጵያ ህግ በዚህ ረገድ (progressive capacity) የሚለው መርህ ይከተላል የሚያሰኘን፡፡

10.3. የአሳዳሪና የሞግዚት አሿሿም

ባንድ በኩል ሰው ከልደት እስከሞት ድረስ የመብትና የግዴታ ባለቤት ነው ብለናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አካለመጠን ያልደረሰ ሰው በመብቱ ራሱ ሊሰራበት አይፈቀድለትም መስራት ያለበት በወኪሉ በኩል ነው ተብሏል፡፡ ነገር ግን ወኪል መመደብም ህጋዊ ውጤት ያለው ድርጊት ስለሆነ አካለመጠን ያልደረሰው ሰው ራሱ ሊያከናውነው የሚቻለው አይደለም፡፡ ታዲያ እድሜው ፈቅዶለት መብቱን እንዲሰራበት ከመደረጉ በፊት እርሱን ወክለው ጉዳዩን እንዲያከናውኑለት የሚገቡ ሰዎች እንዴትና በምን ዓይነት ሥርዓት ይወከላሉ? የሚለውን ማየቱ ጠቃሚ ነው፡፡

በህጉ ቋንቋ ለመጠቀም ከተፈለገ አካለመጠን ያልደረሰ ሰው ወኪሎቹ ሆነው የሚመደቡት "አሳዳሪና ሞግዚት" ተብለው ይታወቃሉ፡፡ የውክልና ስልጣናቸውም የሚመነጨው ከህግ፣ ከኑዛዜ ወይም ከፍርድቤት ውሳኔ እንደሆነ በህጉ ተመልክቶአል[143]፡፡ ሥልጣኑ በቅድሚያ የሚመነጨው ከህግ ሲሆን በህጉም መሠረት "ልጁ ከጋብቻ ውስጥ የተወለደ ከሆነ ባልና ሚስቱ ጋብቻው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ሁሉ የልጁ አሳዳሪነትና ሞግዚትነት የጋራ ስልጣን እንዳላቸው"[144] ተደንግጓል፡፡ በርግጥ

[142] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 7(2)
[143] ዝኒ ከማሁ ከአንቀጽ 219 እስከ 225 አይቶ መገንዘብ ይቻላል፡፡
[144] ዝኒ ከማሁ 219

Scanned by CamScanner

በነባሩ የፍትሐብሔር ህግም ተመሳሳይ ድንጋጌ ነበር (ቁጥር 204 ይመለከቷል)፡፡ ሆኖም እዚያው በዚያው አለፍ ብሎ ደግሞ በቁጥር 276(1) "የልጁ አባትና እናት የአሳዳሪነት ሥልጣን ለሁለቱም በተሰጣቸው ጊዜ ሥራውን የሚያከናውነው አባት ብቻ ነው" የሚል ነበረበት፡፡ ስለሆነም ዞሮ ዞሮ አባት እስካለ ድረስ የአሳዳሪነት ሥልጣን የእርሱ ብቸኛ ሥልጣን ነበር ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተጋቢዎች በጋብቻ ጊዜ እኩል መብት አላቸው የሚለውን ህግ-መንግሥታዊ መርህ ይፃረራል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የፍትሐብሔሩ ህግ አንቀጽ 276(1) በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ውስጥ እንዳይካተት ተደርጓል፡፡

ከሁለቱ አንዱ በሞተ ጊዜ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ሥልጣኑን ለማከናወን ካልቻለ ግን አንደኛው ወገን ብቻ ሃላፊነቱን እንዲሸከም ይደረጋል[145]፡፡ ይህ አካሄድ አባትም ሆነ እናት አሳዳሪነትም ሆነ ሞግዚትነት ሥልጣን የመያዝ እኩል መብት እንዳላቸው የሚያሳይ ነው፡፡ በቅድመ ፍትሐብሔር ህግ በነበረን ልማዳዊ ህግ ግን የተለየ አካሄድ የሚከተል ነበር፡፡ እንዲህ የሚል ህግ ነበር፡፡ "አባት ለልጆቹ ሞግዚትና ወኪል ሳያደርግ ቢሞት <u>የልጆቹ እናት የምትችል መሆኗ ከታወቀና</u> እም የልጆቹን ሃብት ለመጠበቅ እችላለሁ ካለች ለመጠበቅ አትከለከልም"[146] የሚል ነበር (ሥረዝ የተጨመረ) ይህ ድንጋጌ ቢያንስ ሁለት ነገሮች ያሳየናል አንደኛ አባት በህይወት ባለበት ጊዜ ሁሉ የልጆቹ ሞግዚትነትና አሳዳሪነት ሃላፊነት ከእናት ጋር የሚጋራው ሳይሆን የግል ሥልጣኑ እንደሆነ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ አባት በመሞቱ ምክንያት የሞግዚትነትና የአሳዳሪነት ሥልጣኑ ወዲያውኑ (as of right) ወደእናትየው የሚተላለፍ ሳይሆን "ብቃት እንዳላት ተረጋግጦና" ፈቃደኝነትዋ ተገኝቶ የሚሰጣት ሃላፊነት ነበር ማለት ነው፡፡ ይህም ለሴቶች ዝቅተኛ

[145] ዝኒ ከማሁ 220(1)
[146] የኢትዮጵያ የጥንት ፍርዶች መዝገብ ቁጥር 321

ግምት ከሚሰጡ ነባር ህጎቻችን እንደ አንዱ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ባልና ሚስቱ ከተፋቱ ግን ቢቻል በስምምነት የልጆቻቸውን አሳዳሪነትና ሞግዚትነት ለማን መስጠት እንዳለበት እንዲወስኑ ህጉ ዕድል የሚሰጣቸው ሲሆን በዚሁ ሁኔታ መስማማት ካልቻሉ ግን ፍቺውን በሚወስነው ፍርድቤት በኩል አልባት የሚሰጠው ይሆናል[147]፡፡ በዚህ ረገድ ቅድመ ፍትሐብሔር ህግ ሲሰራበት የነበረው ህግ ለየት ያለ መፍትሄ አበጅቶ ነበር፡፡ ይኸውም "ባልና ሚስት በጋብቻ ሲኖሩ ልጅ ወልደው ቢፋቱና ልጁን ለመውሰድ ክርክር ቢያቀርቡ ልጁ ሦስት ዓመት እስኪሞላው ድረስ በእናት እጅ ይቆያል፡፡ ከሦስት ዓመት በኋላ ግን እስከ ሰባት ዓመት አባቱ ዘንድ ቆይቶ ከሰባት ዓመት በላይ አባቱንም ሆነ እናቱን ቢመርጥ እወደደበት ሊቀመጥ ይችላል"[148] የሚል ነበር፡፡ የጥንቱ ህጋችን ግልጽና ለማስፈጸም የማያስቸግር መሆኑ ቢታመንም ጉዳዮቹ እንደሁኔታው እየታዩ ለመወሰን የማያስችል (non-flexible) በመሆኑ የልጁን ጥቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ለመወሰን ግን እድል የሚሰጥ አይደለም ምክንያቱም ህጉ ራሱ የልጁን እድሜ መሠረት በማድረግ ውሳኔ ሰጥቶበታልና፡፡

አላይ ከባልና ሚስቱ አንዱ ሲሞት በህይወት የቀረው ወላጅ የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥልጣን እንደሚይዝ ገልጸናል፡፡ በህይወት ቀርቶ የነበረው ወላጅ ልጁ አካለመጠን ሳይደርስ ከሞተ ግን የዚህ ልጅ አሳዳሪነትና ሞግዚትነት እጣ ፈንታ የሚወሰነው ይህ ወላጁ በኑዛዜ ቃል አሳዳሪና ሞግዚት ሾሞለት[149] እንደሆነ ነው፡፡ በሆነ አጋጣሚ ይህ ወላጅ አሳዳሪ

[147] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 221
[148] 37ኛ የኢትዮጵያ የጥንት ፍርዶች መዝገብ ቁጥር 94/196
[149] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 222

Scanned by CamScanner

በኑዛዜ ሳይሾምለት ከቀረ ግን ህጉ በራሱ ለዚህ ሃላፊነት የሚሾማቸው የቅድመ ተከተል ዝርዝር አስቀምጧል[150]:: በዚህም መሠረት ህጉ ሃላፊነቱን በቅድሚያ የሚሰጠው ለልጁ አያቶች ሲሆን እነርሱ ከሌሉም አካለመጠን የደረሱ የልጁ ወንድም ወይም እህት ካሉ ለአንዳቸው ይሰጣል:: እነዚህ የሌሉ ከሆነም ወደ ልጁ አጎት ወይም አክስት ይሸጋገራል:: በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ጥረት ተደርጎ ሃላፊነቱን ሊሰጠው የሚገባ ሰው ከታጣ ግን ለፍርድ ቤት በሚቀርብ ጥያቄ ፍርድ ቤቱ ከልጁ ዘመዶች ውጪም ቢሆን አሳዳሪና ሞግዚት ይሾምለታል[151]:: በመሆኑም ከህጉ አቀራረጽ የምንገነዘበው ህጉ በተቻለ መጠን አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ያለአሳዳሪና ያለሞግዚት እንዳይቀር ለማድረግ ብርቱ ጥረት ያደረገ መሆኑን ነው:: ምክንያቱም እነዚህ ተቋሞች ለልጁ ጥቅም ጥበቃ (organs of protection) ጠቃሚ ተደርገው ይወሰዳሉ::

ለነገሩ በነባሩ የፍትሐብሔር ህግም እንዲህ ዓይነት የሃላፊነት ቅደም ተከተል ማስፈጸሚያ ድንጋጌዎች ተቀምጠው እንደነበር የሚታወስ ነው[152]:: ቢሆንም የሃላፊነት ቅደም ተከተሉ ሲቀመጥ ከልጁ የእናት ወገኖች ይልቅ ለልጁ የአባት ወገኖች ቅድሚያ የሚሰጥ የነበረ ሲሆን በተጨማሪም አካለመጠን ከደረሱ የልጁ ወንድምና እህቶች ይልቅ ሃላፊነቱን ለልጁ አጎት ወይም አክስት መስጠትን የሚመርጥ ህግ ነበር:: በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ግን ይህንኑ ለማስቀጠል አልተመረጠም:: በልጁ የአባት ወገን አያቶችና የእናት ወገን አያቶች መካከል ልዩነት ለማድረግ አልተፈለገም ሁሉም አያቶቹ ናቸውና:: በተጨማሪም ከልጁ አክስት ወይም አጎት ይልቅ አካለመጠን የደረሱ የልጁ ወንድም ወይም እህት ካሉ የሃላፊነቱ ቅድሚያ ለእነርሱ የሚሰጥ

[150] ዝኒ ከማሁ 225
[151] ዝኒ ከማሁ 227
[152] የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 210

ህግ ሆኖ ተቀርጿል ምክንያቱም ለልጁ ከአጎቱ ወይም ከአክስቱ ይልቅ ወንድሙ ወይም እህቱ የተሻለና የበለጠ ያስቡለታል ተብሎ ይታመናል ከሚል መነሻ ነው::

ይህ ግን አጠቃላይ አካሄድን የሚያሳይ እንጂ ቅደም ተከተሉ በሁሉም ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ ላይ መፈጸም ያለበት አይደለም:: ቅደም ተከተሉ ሲቀረጽ የህፃኑን ጥቅምና ደህንነት መሠረት በማድረግ ስለሆነ በቅደም ተከተሉ መሰረት ማስኬድ የህፃኑን ጥቅም ይጎዳል የሚል እምነት በፍርድ ቤቱ ካደረ ቅደም ተከተሉን እንዲከተል አይገደድም::

ከዚህ አንፃር ከፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ደረጃ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የደረሰ ጉዳይ ነበር:: ጉዳዩ ከዚህ እንደሚከተለው ይመስላል[153]::

አንዲት ከጋብቻ ውጪ የተወለደች የስድስት ዓመት ህፃን በአንድ ዓመት ልዩነት አባትና እናቷ ከዚህ ዓለም በሞት ይለዩባታል:: በመጀመሪያ የሞቱት አባት ሲሆን እናት ለአንድ ዓመት ያህል የህፃንዋን አሳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥልጣን በብቸኝነት ይዛ ቆይታ ነበር:: እናት ስትሞት ከእናትየው ጋር አብሮ ይኖር የነበረ የእናት ወንድም (የህፃንዋ አጎት) የልጅቷን የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥልጣን እንዲሰጠው ለፍርድ ቤት ያመለክታል::

የህፃንዋ የአባት ልጆች (ወንድምና እህት) የሆኑ ሰዎች በተቃዋሚነት ቀርበው የህፃንዋ እህትና ወንድሞች እያለን አጎት ይህንን ሥልጣን ሊወስዱ አይገባም ብለው ስለተከራከሩ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሞግዚትነት

[153] የፍትሐብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 20461

Scanned by CamScanner

ሥልጣን ከእናት ይልቅ ለእህት ሊሰጥ ይገባል ብሎ በመወሰን የሀፃንዋ የአባት ልጅ ለሆነችው ሴት ሰጠ፡፡

የሀፃንዋ እናት በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቀረቡ፡፡ በይግባኝ ደረጃ በተደረገው ክርክርም ሀፃንዋ በእናትዋ (ይግባኝ ባይ) ቀለብ ተቆርጦላት በክርስትና እናቷ ከትትል የምታድግ መሆንዋን፣ ከአባቷ ልጆች ጋር አድጋና ኖራ እንደማታውቅ፣ የሀፃንዋ የአባት ልጆች ሀፃንዋን ሳይጠይቁ ወራሽነታቸው ማረጋገጣቸው፣ ከውርስ ሃብቱ መካከልም የእርሷን ሙብት ሳይጠብቁ የአባቷ ውርስ ሀብት ከሆነው መካከል መኪና መሸጡን ተረጋግጧል፡፡ በመጨረሻም መልስ ሰጪ የእናት ሞግዚትነት የተቃወሙት እናት የሞግዚትነት ሥልጣናቸውን መሠረት በማድረግ ሀፃንዋን የአባቷን የውርስ ሃብት እንድታገኝ የውርስ አጣሪ እንዲሾምላቸው ሲያመለክቱ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህንኑ በመገንዘብ "... በዝምድና ደረጃ ቅደም ተከተል ብቻ ታይቶ ሞግዚትነቱ ለመልስ ሰጭ መስጠቱ የጥቅም ግጭት የሚፈጥር መሆኑን ፍርድ ቤቱ ተረድቷል፡፡ (ሠረዝ የተጨመረ) በሌላ በኩል ይግባኝ ባይ ከሀፃንዋ እናት ጋር ወንድምና እህት ሆነው አብረው ያደጉ መሆኑን እና የእህቱን ልጅም ሞግዚትነት ተቀብለው እናቷ ከሞተች ጀምሮ ከአምስት ዓመት በላይ ከደመወዙ ቀለብ እየከፈለ ማሳደጉ ሲታይና የጥቅም ግጭትም ካለመኖሩም እንጻር በአዋጁ አንቀጽ 226(4) መሠረት ለልጅቷ ስተዳደግ ደህንነትና ጥቅም የሚበጅ መሆኑን ይሀ ፍርድ ቤት አረጋግጧል በማለት የበታች ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሻረ፡፡

ጉዳዩ እንደገና በይግባኝ ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢቀርብም ይኸኛውም ፍርድ ቤት "... ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር በፍሬ ነገር ረገድ የተገነዘብነው ሀፃንዋ የተወለደችው ከጋብቻ ውጪ ሲሆን፣ ከይግባኝ ባዮች ጋር ያላት ዝምድናም በአባት በኩል ብቻ እንደሆነ፣ አባትዋ በ1993 ዓ.ም. እንደሞተ ለአንድ ዓመት ያህል እናትዋዋ የሞግዚትነትና የአሳዳሪነት ሥልጣን ይዛ መቆየትዋን፣ እርስዋ በ1994 ዓ.ም. ስትሞት ደግሞ መልስ ሰጭ (አጎት) የሞግዚትነትና የአሳዳሪነት ሥልጣን ይዞ ከራሱ ደመወዝ ተቆራጭ በመመደብ በተወለደችበት ቤት ውስጥ ከክርስትና እናትዋ ጋር በእንክብካቤ እንድታድግ እያደረገ መሆኑን፣ ሀፃንዋ ከይግባኝ ባዮች(የአባትዋ ልጆች) ጋር ኖራ እንደማታውቅ፣ ይግባኝ ባዮች የሞግዚትነት ሥልጣኑን በተመለከተ ተቃውሞ ያቀረቡት መልስ ሰጪ የሀፃንዋን የውርስ ሃብት ክፍፍል በመጠየቅ የውርስ አጣሪ ይሾምልኝ በማለት ለፍርድ ቤት አቤቱታ በማቅረቡ እንደሆነ፣ ይግባኝ ባዮች የሀፃንዋን መብት ሳይጠብቁ ከውርስ ሃብት ውስጥ ንብረት መሸጣቸውን ነው በማለት ሀፃንዋ አሁን ያለችበት የእድሜ ሁኔታ፣ ከተወለደችበት ጊዜ ጀምሮ ያለው የአስተዳደግዋ ሁኔታ፣ መልስ ሰጭ ሀፃንዋን ለማሳደግና ለመንከባከብ ያደረገውንና እያደረገ ያለው ቁርጠኝነት፣ በአንፃሩ ደግሞ ይግባኝ ባዮች በወጣትነት ዕድሜ መገኘት፣ በእነርሱና በሀፃንዋ መካከል ምንም ዓይነት ግንኙነት ወይም መለማመድ አለመኖር፣ እንዲሁም ተቃውሞ ያነሱት የውርስ ሃብት ክፍፍል ጥያቄ ሲመጣባቸው መሆኑን እና የመሳሰሉትን ሁኔታዎች አመዛዝነን... ለሀፃንዋ መልካም አስተዳደግና ደህንነት እንደዚሁም ለንብረት ነክ ጥቅሞችዋ አጠባበቅ ከይግባኝ ባዮች (ወንድምና

Scanned by CamScanner

እህቶችዎ) ይልቅ የተሻለ የሚሆነው መልስ ሰጭ (አንቀጽ) ነው የሚለው ነው፡፡ በኋላ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ እናገኛለን፡፡
በኛም እምነት ውሳኔው ከተዋቶኛ የሆኑ ቃላት ማለትም ከእናትና ከአክስት ይልቅ ወንድምና እህት ቅድሚያ ይሰጣቸዋል ከሚለው ያፈነገጠ ቢመስልም ከህጉ መንፈስና ዓላማ ጋር ግን የተጣጣመ ነው ብለን እናምናለን፡፡

10.4. የአሳዳሪና የሞግዚት የሥራ ድርሻ

ከዚህ ቀጥለን የአሳዳሪና የሞግዚት የሥራ ድርሻ ምን እንደሆነ ለማየት እንሞክራለን፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ግን መታወቅ ያለበት ነጥብ አሳዳሪና ሞግዚት ስንል ሃላፊነቱ የሚሰጣቸው የግድ ሁለት ሰዎች ሊኖሩ ይገባል ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም ሁለቱም የሥራ ድርሻዎች በአንድ ሰው እጅ መያዝ እንዳለባቸው ህጉ በመርህ ደረጃ ይቀበላል[154]፡፡

ወደ ሥራ ድርሻው ስንመጣ ሃላፊነቶቹ ከልጁ ጥቅሞች አንጻር የተቃኙ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ልጁ ሦስት ትላልቅ ጥቅሞች እንዳሉት ይታመናል፡፡ የልጁ ደህንነትና መልካም አስተዳደግ (welfare of the child) አንደኛው ሲሆን ገንዘባዊ ጥቅም (pecuniary interest) ደግሞ ሁለተኛው ነው፡፡ በመጨረሻም በልጁ ስም ህጋዊ ድርጊት የሚያከናውንለት (legal representation) ወኪል ማግኘት ሌላው ነው፡፡ ደህንነቱንና መልካም አስተዳደጉን ይከታተል ዘንድ አሳዳሪ የሚሾምለት ሲሆን[155] ገንዘባዊ ጥቅሙ እንዲጠበቅለት ደግሞ ሞግዚት ይሾምለታል[156]፡፡ ህጋዊ ድርጊቱን በልጁ ስም በማከናወን ረገድ

[154] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 231(1)
[155] ዝኒ ከማሁ 216(1)
[156] ዝኒ ከማሁ 216(2)

እንደነገሩ ሁኔታ በአሳዳሪ ወይም በሞግዚት ይወከላል ማለትም ድርጊቱ የልጁን መልካም አስተዳደግና ደህንነት ህጋዊ የሚመለከት ከሆነ በአሳዳሪ ገንዘባዊ ጥቅሞቹን የሚመለከት ከሆነ ደግሞ በሞግዚት ይወከላል ማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ ግን መወሳት ያለበት ነጥብ አልፎ አልፎ (እንዲያውም ብዙውን ጊዜ) የልጁ ገንዘባዊ ጥቅም የሚመለከተው የቱ ነው? መልካም አስተዳደጉን የሚመለከተውስ የቱ ነው? ብሎ ለመለየት አዳጋች ነው ምክንያቱም ጥቅሞቹ የተሳሰሩና አንዱ ባንዱ ላይ የሚንጠለጠልበት ጊዜ እጅግ በርካታ ነው፡፡ ለዚህም ነው አሳዳሪነትና ሞግዚትነት ሁለቱም በአንድ ሰው ላይ እንዲያርፉ ማድረግ ተመራጭ የሚሆነውና ህጉም የተቀበለው፡፡

10.5. የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥራ መሠረታዊ ባህርያት

ስለሞግዚትነትና አሳዳሪነት ስናወሳ የአገልግሎቶቹ ሦስት መሠረታዊ ባህርያት መጥቀስ ጠቃሚ ሆኖ ይታያል፡፡ እነዚህም አንደኛ አገልግሎቶቹ ክፍያ የማይጠየቅባቸው (gratuitous office) የነፃ አገልግሎቶች ናቸው[157]፡፡ በርግጥ አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ አገልግሎት የሚያጠፋው ጊዜ ረጅምም ሆኖ ከተገኘ የተወሰነ አበል ሊቆረጥለት እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡ ይህም ቢሆን ግን ከልጁ ጠቅላላ ሃብት የሚታሰብ ሳይሆን ከልጁ ገቢ የሚታሰብ ነው እንዲህም ሆኖ ከገቢው አንድ ሦስተኛ የሚበልጥ ሊሆን እንደማይገባ የህግ ጣሪያ ተበጅቶለታል[158]፡፡ ስለዚህ በመርህ ደረጃ አገልግሎቱ የነፃ አገልግሎት መሆን ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

[157] ዝኒ ከማሁ 250(1)
[158] ዝኒ ከማሁ 250(3)

Scanned by CamScanner

ሁለተኛ ሥራው በውዴታ ወይም በፈቃደኝነት ብቻ የሚያዝ ሳይሆን ሃላፊነቱን እንዲያከናውን ተመርጦ የተሾመ ሰው ሥራውን የማከናወን ግዴታ[159] (compulsory) እንዳለበት መደንገጉ ነው፡፡ ምናልባትም ተግባሩን ማከናወን በራሱ ላይ ከበድ ያሉ ችግሮችን፣ በአጠቃላይ ኑሮው ላይም እንቅፋት የሚያስከትልበት ከሆነ ይህንኑ ችግሩን ለፍርድቤት አቅርቦ ሥራው እንዲተርለት ሊያመለክት ይችላል እንጂ በራሱ የተናጠል እርምጃ ሃላፊነቱን አልቀበልም ማለት አይችልም፡፡ እንዲያውም ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ሃላፊነቱን ለሌላ ሰው እንዲያስተላልፍና ሊላኛው ሰውም ሥራውን እስኪጀምር ድረስ ክፍተት ሊፈጠር ስለማይገባ ሌላው ሰው ተተክቶ ሥልጣኑን እስኪረከበው ድረስ የተሰጠውን ሥራ ለጊዜው የማከናወን ግዴታ አለበት[160]፡፡

ሦስተኛ የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ የሩቯሚው የግል ሃላፊነት (personal) ስለሆነ ወደ ወራሾቹ የሚተላለፍ አይደለም[161]፡፡ ይህም ማለት ልጁ አካለመጠን ሳይደርስ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ተብሎ የተሾመለት ሰው ቢሞት የዐቹ ወራሾች ሃላፊነቱን ተረክበው እንዲያከናውኑ አይጠበቅባቸውም፡፡ ከእነርሱ የሚጠበቀው ግለሰቡ እንደሞተ ወዲያውኑ እላይ በተመለከተው የህጉ የቅደም ተከተል ዝርዝር መሠረት ቀጥሎ ላለው ሰው ማስታወቅና ሃላፊነቱን ማስረከብ ሲሆን እንዲህ ዓይነት ሰው ከሌለም ጉዳዩን ለፍርድ ቤት በማስታወቅ ተተኪ ሰው እንዲሾም ማስደረግ ብቻ ነው[162]፡፡

[159] ዝኒ ከማሁ 237
[160] ዝኒ ከማሁ 240
[161] ዝኒ ከማሁ 251
[162] ዝኒ ከማሁ 252

10.6. የአሳዳሪውና የሞግዚቱ ተጠያቂነት

ሃላፊነቱም ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ሲሆን ሃላፊነቱን እንዲያከናውን የተሾመ ሰው የልጁን ገንዘባዊ ጥቅምም ሆነ ደህንነት በተመለከተ እንደመልካም ወላጅ እንዲያከናውን ይጠበቅበታል፡፡ ህጉም ሃላፊነቱን በብቃት ስለመወጣቱ ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ የተለያዩ የቁጥጥር ዘዴዎችን አደራጅቶ ይገኛል፡፡ ለምሣሌ ከፍትሐብሄር ህግ በፊት በነበረን ልማዳዊ ህግ ሥር የሚከተለው ተደንግጎ ይገኝ ነበር፡፡

ህፃናት የሆኑ ልጆች አባታቸው እገሌ ሞግዚት ሆኖ ያሳድግልኝ ብሎ ሳይናዘዝ የሞተባቸው እንደሆነ እናታቸው ደግሞም የእናትና አባት ወገን አቅራቢያ ዘመድ እፍርድ ቤት ሄዶ እገሌ ለእነዚህ ህፃናት ሞግዚት እንዲሆን መርጠነዋል ብለው በፍርድ ቤት ቀርበው የፈረሙ እንደሆነ ሞግዚት የሆነው ሰው የህፃናቶቹን ገንዘብ ሃብት እህል ማንኛውም ሃብታቸውን እንዳይጠፋ ምሎ ዋስ ጠርቶ ሂሳቡን በየጊዜው እፍርድ ቤት እንዲያገባ አስጠንቅቆ ሞግዚት ሆኖ እንዲያሳድግ ፍርድ ቤቱ ሊፈቅድ ይገባዋል ይላል[163] (ሠረዝ የተጨመረ)

በነባሩ የፍትሐብሄር ህግ መሠረትም ሞግዚቱ ሥራ ከጀመረበት ቀን ቀጥለው ባሉት አርባ ቀኖች ውስጥ ቢቻል ከቤተ ዘመድ ምክር ጉባኤ መካከል የተመረጡ በቂ ምስክሮች ባሉበት አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ የሃብት ዝርዝርና የዋጋ ግምት መግለጫ መዝገብ ያዘጋጃል[164] የሚል ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ መሠረትም ሞግዚቱ

[163] 135ኛ የኢትዮጵያ የጥንት ፍርዶች መዝገብ ቁጥር 373/354
[164] የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 281(1)

ሞግዚትነቱን ሥራ ከጀመረ በኋላ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ሦስት ምስክሮች ባሉበት አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ይቆጥራል፤ የዋጋውንም ግምት ያወጣል ተብሎ ተደንግጓል[165]፡፡ የልጁን ሃብት መዝግቦ ከያዘ በኋላም ቢሆን የሞግዚቱ የግል ንብረት ከልጁ ሃብት ጋር እንዳይቀላቀል[166] አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ ማድረግ እንደሚገባው በሞግዚቱ ላይ ተጥሎበታል፡፡ ይህ ሁሉ እንግዲህ ለጥንቃቄ እርምጃ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ላለበት የሃብት አስተዳደር መሠረት መሆኑ ነው፡፡

በአሳዳሪነት ሥልጣኑ በኩልም ተሿሚው የልጁን አስተዳደግ በተለይም ትምህርቱን ጤናውን፣ ማህበራዊ ግንኙነቶቹንና የመሳሰሉትን የመምራትና የመከታተል ሃላፊነት አለበት፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም በልጁ ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ[167] የመውሰድ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ እነዚህን ሃላፊነቶች በሚያከናውንበት ጊዜ አሳዳሪው ምናልባት የሦስተኛ ወገኖች እገዛ ለምሳሌ የፖሊስ፣ የቀበሌ አስተዳደር ወይም የፍርድ ቤትና የመሳሰሉት እርዳታ የሚያሻበት ሁኔታ ሊያጋጥመው ይችላል፡፡ ለምሳሌ አንድ አሳዳሪ የአስራ ስድስት ዓመት ወጣት ልጁን ማህበራዊ ግንኙነት ለመቆጣጠር እርምጃ

[165] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 270(1)

[166] ዝኒ ከማሁ 272

[167] ዝኒ ከማሁ 258 በነባሩ የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 267 ሥር "አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ያደረጋቸውን ጥፋቶች በማመዛዘንና አስተዳደጉንም በመጠበቅ አስተያየት ቀላል የሰውነት ቅጣቶችን አካለመጠን ባላደረሰ ልጅ ላይ ለመፈጸም ይችላል" ተብሎ ነበር (ሠረዝ የተጨመረ) ሆኖም ዘመናዊው አስተሳሰብ ከባድ ተባለ ቀላል በሰውነት ላይ የሚፈጸም ቅጣት ልጁን ድንጉጥና ፈሪ ከማድረግ ውጪ ባህርዩን በአዎንታዊ መንገድ በመግራት ረገድ ፋይዳ ቢስ ነው የሚል ስለሆነ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ውስጥ "ቀላል ቅጣት" የሚለውን ሃረግ በመሰረዝ የአሳዳሪው ሥልጣን የዲሲፕሊን እርምጃ በመውሰድ እንዲገደብ ተደርጓል፡፡ ይህም ከሰውነት ቅጣት በመለስ የሚከናወን መሆን እንዳለበት ይጠቁማል፡፡

ለመውሰድ ሲሞክር ሃይል የተቀላቀለበት ተቃውሞ ከወጣቱ በኩል ሊሰነዘርበት ይችላል ወይም ወጣቱ መኖሪያ ቤቱን ለቆ ሊሄድ ይችላል፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ የፖሊስ ወይም የቀበሌ አስተዳደር አካላት እገዛ ለአሳዳሪው ወሳኝ ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም አሳዳሪው ይህንኑ ዓይነት እገዛ ማግኘት ይችል ዘንድ እገዛውን የሚጠይቅበት የህግ መሠረት በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ውስጥ አካትቶለት[168] ይገኛል፡፡ ይህ ዓይነት ግልጽ ድንጋጌ በነባሩ የፍትሐብሄር ህግ ውስጥ አልነበረንም፡፡

አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ አገልግሎት በሞግዚትነት የተሾመ ሰው እላይ ከተመለከቱት የጥንቃቄ ድንጋጌዎች በተጨማሪ በህጉ ውስጥ የሃላፊነት ገደብ የሚጥሉ የተለያዩ ድንጋጌዎች ተቀምጠዋል፡፡ እነዚህን ገደቦች በመተላለፍ ሞግዚቱ በሚያከናውናቸው ድርጊቶች ምክንያት ጉዳት ከደረሰ ደግሞ በፍትሐብሄር ሃላፊነት ሊጠየቅ እንደሚችልና አልፎ አልፎም ሞግዚቱ የገባው ግዴታ ውድቅ[169] ሊደረግ እንደሚችል ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ለነገሩ በነባሩ የፍትሐብሄር ህግም ሆነ በቅድመ ፍትሐብሄር ህግ በነበረን ልማዳዊ ህግም ተመሳሳይ ድንጋጌዎች ነበሩ፡፡ ከጥንት ህጎቻችን ጥቂቶቹን ብናይ የሚከተሉትን እናገኛለን፡፡

"ለመዋዋልና ለመታረቅ እድሜአቸው የማይፈቅድላቸውን ልጆች ሀብትና ርስት በአደራ የሚጠብቅ ሰው እናትም ሆነች አባት፣ ባእድም ሆነ ዘመድ፣ በአደራ ጠባቂነት ወይም በሞግዚትነት የተቀበለውን የህፃናት ርስትና ሀብት ከሌላ ሰው ጋር

[168] ዝኒ ከማሁ 255

[169] ዝኒ ከማሁ 309(1)

ተስማምተው ቢሸጡም ቢያወርሱም አይረጋም[170] ይላል፡፡(ሠረዝ የተጨመረ)

ሌላው ደግሞ

"ማናቸውም ሰው ለሙት ልጆች ሞግዚትና ወኪል ሆኖ ከተሾመ በኋላ አምኑቱን አጉድሎ የልጆቹን ሃብትና ንብረት ያበላሸ እንደሆነ ነገሩን ፍርድ ቤት ሲያውቀው ከወኪልነቱ ይሻራል ያጠፋው ሀብትም እንዲለ አላፊ ይሆናል[171]፡፡ የሚል ነው፡፡ (ሠረዝ የተጨመረ)

ከዚህ መገንዘብ የምንችለው በድሮ ህጎቻችንም ቢሆን አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ ሃብት አስተዳደር ከፍተኛ ጥንቃቄና የሃላፊነት ስሜት የሚጠይቅ እንዲሁም በዚሁ መሠረት ሥራውን አለማከናወን በሃላፊነት የሚያስጠይቅ ድርጊት እንደነበር ሲሆን ድርጊቱም ውድቅ የሚሆን እንደነበር ነው፡፡

ከዚህ ቀጥለን ይህንን ምዕራፍ ከማጠቃለላችን በፊት የሞግዚትነትና የአሳዳሪነት ሥራዎች ቀሪ ስለሚሆንባቸው ሁኔታዎችን ይዘት ለማየት እንሞክራለን፡፡ በጥቅሉ ሲታይ ሃላፊነቱ ቀሪ የሚሆኑባቸው ሁለት ታላላቅ ምክንያቶች ሲሆኑ ሃላፊነቱ በተሰጠው ሰው ምክንያትና አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ምክንያት ተብለው ሊመደቡ ይችላሉ፡፡

[170] 107ኛው የኢትዮጵያ የጥንት ፍርዶች መዝገብ ቁጥር 316

[171] ዝኒ ከማሁ 320

10.7. የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥራ ቀሪ ስለሚሆንበት ሁኔታ

10.7.1. ሥራውን እንዲያከናውን በተሾመው ሰው ምክንያት ቀሪ ስለሚሆንበት ሁኔታ

ሃላፊነት በተሰጠው ሰው ምክንያት ሥራው ቀሪ የሚሆንበት አንደኛው ምክንያት ሃላፊነት የተሰጠው ሰው በራሱ አነሳሽነት ሥራው ቀሪ እንዲሆንለት ለፍርድ ቤት አቤቱታ ጥያቄ ሲያቀርብ ነው[172]፡፡ ጥያቄው ቀርቦ በፍርድ ቤት ተቀባይነት ካገኘ ከአሳዳሪነት ወይም ከሞግዚትነት ወይም ከሁለቱም ሃላፊነቶች ሊሰናበት ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተሿሚውን ከስራው እንዲሰናበት ሲወስን የተለያዩ ነገሮችን ግምት ውስጥ እንዲያስገባ የሚጠበቅበት ሲሆን በተለይም ሃላፊነቱ በተሿሚው ላይ ከበድ ያሉ ችግሮችን በአጠቃላይ ኑሮውም ላይ እንቅፋት የሚያስከትልበት ስለመሆኑ ፍርድቤቱን የሚያሳምን ምክንያት ሊያቀርብ ይገባል፡፡ ይህ እንግዲህ ጥቅል ሃረግ ስለሆነ እንደጉዳዩ ክብደትና ቅለት እየታየ የሚወሰን ይሆናል ማለት ነው፡፡ በተለይም ሥራው የግዴታ እንጂ የውዴታ አይደለም የሚለው ቀደም ሲል የተገለጸ ስለሆነ ሃላፊነቱ ይቅርልኝ ያለ ሁሉ በቀላሉ እንዲገላገል ከተፈቀደለት ይህንኑ የግዴታ መርህ የሚሸረሽር ስለሚሆን ብርቱ ጥንቃቄ ይጠይቃል፡፡

ሌላው ሞግዚቱ ወይም አሳዳሪው ስራው እንዲቀርለት አቤቱታ የሚያቀርብበት ሁኔታ ከእድሜው ወይም በመደበኛነት ከሚያከናውነው ሥራ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይኸውም ዕድሜው ቢያንስ ስድሳ አምስት ዓመት የሞላው ወይም እድሜው የቱም ያህል ቢሆን በውትድርና ሥራ የተሰማራ ሰው ከሆነ ከአብራኩ ለተወለዱ ልጆች ካልሆነ በቀር ሞግዚት ወይም አሳዳሪ እንዲሆን

[172] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 238

እንዳይገደድ ህግ የሚፈቅድለት[173] ስለሆነ ይህንኑ መሰረት በማድረግ ከሃላፊነቱ እንዲነሳ ጥያቄ ሊያቀርብና ከሃላፊነቱ እንዲሰናበት ሊፈቀድለት ይችላል[174]፡፡ ይህ እንግዲህ ሥራው የግዴታ ነው ለሚለው መርህ ልዩ ሁኔታ (exception) መሆኑ ነው፡፡ ልዩ ሁኔታ ደግሞ በጠባቡ መተርጎም እንዳለበት ቀደም ሲል ደጋግመን ገልጸናል፡፡

ሁለተኛው ሃላፊነቱ በተሰጠው ሰው ምክንያት ሃላፊነቱ ቀሪ የሚሆንበት ሁኔታ ተጂሚው (ሞግዚቱ ወይም አሳዳሪው) ከፈቃዱ ውጪ ከሃላፊነቱ የተሻረ እንደሆነ ነው[175]፡፡ ቀደም ሲል ይህ ሥራ በከፍተኛ የሃላፊነት ስሜትና በጥንቃቄ መከናወን እንዳለበት ጠቁመናል፡፡ በመሆኑም አሳዳሪው ልጁን በተገቢው ሁኔታ በትምህርትና በሞራል ታንጾ እንዲያድግ ካላደረገ፣ ሞግዚት ሆኖም ሲሰራ የልጁን ሃብት በመጥፎ ሁኔታ ካስተዳደረና እንዲባክን ካደረገ የሃላፊነቱ መሰረታዊ ግብ አላሳካምና ከሃላፊነቱ እንዲሻር ፍርድ ቤት ሊወስንበት የሚችልበት ሁኔታ አለ፡፡ በዚህ ምክንያትም ሃላፊነቱ ቀሪ ሊሆን ይችላል፡፡

ሦስተኛው የሃላፊነት ቀሪ ማስደረጊያ ምክንያት ሃላፊነት የተሰጠው ሰው ችሎታ ያጣ እንደሆነ ነው[176]፡፡ አንድ ሰው ችሎታ አጣ የሚባልባቸው ሁኔታዎች፣ ሥርዓቱና ውጤቱ

[173] ዝኒ ከማሁ 239
[174] እዚህ ላይ ምናልባት "ውትድርና" ሲባል የፖሊስ ሰራዊት አባላትንና የሚሊሺያ አባላትን ይጨምር ይሆን ወይ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችል ይሆናል በኛ እምነት መልሱ አይደለም ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሥራዎች በባህርያቸው ሲቪል ጥበቃዎች ስለሆኑና ከመኖሪያ አካባቢ ራቅ ብሎ መሄድን በመርህ ደረጃ የማያስከትሉ ናቸው በመሆኑም "ውትድርና" በሚል ሥር የሚካተቱ አይደሉም፡፡
[175] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 245 እና 246
[176] ዝኒ ከማሁ 243

በፍትሐብሄር ህጉ አንደኛ መጽሐፍ ሥር ተደንግጎ የሚገኝ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ነጥብ እዚያው ካሉ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር አብሮ መታየት ያለበት ነው፡፡ በተለይም አንድ ሰው በሕመም ወይም በአደጋ ምክንያት ባጋጠመው የአካል ወይም የአእምሮ ጉድለት ምክንያት በፍርድ እንዲከለከል ሊወሰንበት ይችላል፡፡ ይህ ክልከላ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሁሉ ግለሰቡ እንኳንና አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ አስተዳደግ ሊመራ፣ ሃብትና ንብረቱን ሊያስተዳድር ይቅርና የራሱንም ጉዳይ እንዲያከናውን አይፈቀድለትም፡፡ የራሱን ጉዳይ የሚያከናውነው ፍርድ ቤት በሚሾምለት ሞግዚትና አሳዳሪ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ እያለ የሌላ ሰው አሳዳሪና ሞግዚት ሊሆን ስለማይችልና ክልከላው ችሎታውን ስለሚያሳጣው ሃላፊነቱ ቀሪ እንዲሆን ይደረጋል ማለት ነው፡፡

አራተኛው ምክንያት ደግሞ ሃላፊነት የተሰጠው ሰው ለዚህ ሃላፊነት ብቁ አይደለም ተብሎ ሲወሰን ነው[177]፡፡ አንድ ሰው በፍርድ መከልከሉ የሚወሰነው በፍትሐብሄር የክስ ሂደትና በፍትሐብሄር ችሎት ነው፡፡ በርግጥ አንድ ሰው ብቁ አይደለም ተብሎ የሚወሰነውም በፍርድ ቤት ነው፡፡ ሆኖም ችሎቱ የወንጀል ችሎት ሥርዓቱም በወንጀል ክስ ሂደት በማለፍ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ነጥብ ከወንጀል ድርጊት መፈጸም ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በዋነኛነትም ከግለሰቡ የባህርይ ወይም የሥነ-ምግባር ችግር በመነጨ ምክንያት የሚወሰን ውሳኔ ነው፡፡ በወንጀል ህጉ ውስጥ "ፍርድ ቤቱ በጥፋተኛው ላይ ቅጣት ሲወስን የጥፋቱ ዓይነትና የአፈጻጸሙ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ከዋናው ቅጣት በተጨማሪ በቤተ ዘመድ ላይ ካለው መብት በተለይም ሞግዚትነት ወይም አሳዳሪ (አስተዳዳሪ) ከመሆን መብት ሊሽረው" እንደሚችል ተመልክቶ ይገኛል[178]፡፡ አሳዳሪ ወይም

[177] ዝኒ ከማሁ 244
[178] የወንጀል ህግ (አዋጅ ቁጥር 414/96) አንቀጽ 123(ለ)

ሞግዚት የነበረው ሰው እንዲህ ዓይነት ይዞት ያለው ቅጣት ሊያርፍበት ብቱ አይደለም ተብሎ ከሃላፊነቱ ይሸራል ማለት ነው። በመሆኑም በዚህ አገላለጽ አንድ ሰው ከሞግዚትነት ወይም ከአሳዳሪነት ሃላፊነት በፍትሐብሄር ችሎት ብቻ ሳይሆን በወንጀል ችሎትም በኩል ሊኛር እንደሚችል ይገባል። ልዩነቱ የፍትሐብሄሩ ችሎት "ችሎታውን ያጣዋል" መገንዘብ የወንጀሉ ችሎት ግን "ብቱ አይደለም" ይለዋል በውጤታቸው ግን ተመሳሳይ ናቸው።

አምስተኛውና የመጨረሻው ምክንያት ሃላፊነት የተሰጠው ሰው ሲሞት ነው[179]። እንደሚታወቀው አንድ ሰው ሲሞት ህጋዊና ተፈጥሮአዊ ሰውነቱን ያጣል። ስለሆነም የሌላ ሰው ጉዳይ ይቅርና የራሱ ጉዳይም ማስተዳደር አይችልም። ለነገሩ በሟቹ እግር ተተክተው አንዳንድ ህጋዊያን ወራሾች እንደሚያከናውኑ ድርጊቶች ይታወቃል። የሞግዚትነት ወይም የአሳዳሪነት ሥራ ግን ላይ እንደገለጽነው የሟቹ ግላዊ ሃላፊነት (personal responsibility) ስለሆነና ወደወራሾቹ የማይተላለፍ መሆኑ በህግ በግልጽ የተቀመጠ ስለሆነ[180] ወራሾቹ በሟቹ እግር ተተክተው ሃላፊነቱን የሚሸከሙበት ሁኔታ የለም። በመሆኑም የሞግዚትነት ወይም የአሳዳሪነት ሃላፊነቱ በሞት ምክንያት ቀሪ ይሆናል ማለት ነው።

10.7.2. አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ከመነጨ ምክንያት ሃላፊነቱ ቀሪ ስለሚሆንበት ሁኔታ

አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ በመነጨ ምክንያትም የሞግዚትነትና የአሳዳሪነት ሃላፊነት ቀሪ የሚሆንበት ሁኔታ

[?] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 241(2)
[?] ዝኒ ከማሁ 251(1)

አለ። አንደኛው ምክንያት ልጁ አካለመጠን ከደረሰ የሞግዚቱ ወይም የአሳዳሪው ሃላፊነት ቀሪ ይሆናል የሚለው ነው[181]። ይህ ግልጽ ስለሆነ ብዙ ትንተና የሚፈልግ አይደለም። መጀመሪያውኑ አሳዳሪና ሞግዚት እንዲሾምለት የተደረገበት ምክንያት አካለመጠን ያልደረሰ ስለሆነና በዚሁ ደረጃ የሚወስዳቸው እርምጃዎች የሚያስከትሉት ህጋዊ ውጤት በአግባቡ ላይገነዘብ ይችላል ከሚል ስጋት ነው። አካለመጠን መድረሱ ከተረጋገጠ ግን በህጉ እምነት ይህ ስጋት ተወግዶአል ማለት ነው። ጥያቄው የሚሆነው አንድ ሰው አካለመጠን ደረሰ የሚባለው መቼ ነው? የሚል ነው። ለዚህም ህጉ በግልጽ ባይሆንም በተዘዋዋሪ መንገድ መልስ ሰጥቶበታል። ህጉ "አካለመጠን ያልደረሰ ሰው ማለት ጾታ ሳይለይ ዕድሜው አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ልጅ ነው"[182] ይላል። ከዚህ ትርጉም በዘወርዋራ መንገድ (a contrario reasoning) የሚከተለውን ትርጉም መፍጠር ይቻላል። አካለመጠን የደረሰ ሰው ማለት ጾታ ሳይለይ እድሜው አስራ ስምንትና ከዚያ በላይ የደረሰ ሰው ማለት ነው ቢባል አግባብ ይመስለኛል። በመሆኑም ልጁ አስራ ስምንት ዓመት ከሞላው የእርሱን ጉዳይ ለመከታተል የሞግዚት ወይም የአሳዳሪ አስፈላጊነት ቀሪ ስለሚያደርገው ተጨማሪ ሥነ-ስርዓት ሳያስፈልግ በዚሁ ምክንያት ብቻ ተሿሚው ከሃላፊነት እንዲሰናበት ይደረጋል ማለት ነው።

ሁለተኛው አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ በመነጨ ምክንያት የሞግዚትነት ወይም የአሳዳሪነት ሃላፊነት ቀሪ የሚሆንበት ሁኔታ ልጁ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንዲወጣ ሲወሰን ነው[183]። ይህ ነጥብ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ መውጣት

[181] ዝኒ ከማሁ 310(ሀ)
[182] ዝኒ ከማሁ 215
[183] ዝኒ ከማሁ 310(ለ)

ማለት ምን ማለት ነው? ነፃ የሚወጣውስ እንዴት ነው? የሚሉትን ነጥቦች እንድናይ የግድ ይላል፡፡

ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ መውጣት ማለት አካለመጠን ከመድረሱ በፊት አካለመጠን እንደደረሰ ልጁ በመቁጠር ራሱን በራሱ የሚመራበትና ሰው የሚያስተዳድርበት መብት መጎናጸፍ[184] ማለት ነው ተብሎ ሊገለጽ ይችላል ወደ ሁለተኛው ጥያቄ ስናመራ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የሚወጣባቸው ሁለት መንገዶች እናገኛለን፡፡ አንደኛው በጋብቻ ሁኔታ[185] (occurrence of a certain fact or legal situation) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በፍርድ ውሳኔ ነው[186]፡፡

ቀደም ብለን በህግ በግልጽ በተመለከቱት ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር አካለመጠን ያልደረሰ ሰው ህጋዊ ድርጊቶችን ለመፈጸም አይችልም ብለናል፡፡ ጋብቻ ደግሞ ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል ድርጊት በመሆኑ በህግ በግልጽ ካልተፈቀደ በስተቀር አካለመጠን ሳይደርስ ጋብቻ መፈጸም አይችልም፡፡ እንዲያውም ህጉ በግልጽ ወንዱም ሆነ ሴት አስራ ስምንት ዓመት ሳይሞላቸው ጋብቻ መፈጸም አይችሉም ብሎ ደንግጓል[187]፡፡ ይህም ሆኖ ግን ህጉ ራሱ "ከባድ ምክንያት" ሲያጋጥም ተጋቢዎች ወይም የአንዳቸው አሳዳሪ በሚያቀርቡት ጥያቄና በፍትሕ ሚኒስትሩ ፈቃድ አሥራ ስምንት ዓመት ሳይሞላው በአስራ ስድስት ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ጋብቻ ሊፈጽም የሚቻልበት ጠባብ ዕድል ፈጥሮአል[188]፡፡ በመሆኑም

[184] ዝኒ ከማሁ 313

[185] ዝኒ ከማሁ 311

[186] ዝኒ ከማሁ 312

[187] ዝኒ ከማሁ 7(1)

[188] ዝኒ ከማሁ 7(2)

እንዲህ ዓይነት ጋብቻ ህጉን ተከትሎ ተፈቅዶ የተፈጸመ ከሆነ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ለመውጣት አንዱ ሁኔታ ነው፡፡ ምክንያቱም ጋብቻ መስርቶ ህይወቱን መምራት ለጀመረ ሰው በላዩ ላይ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ሾሞ መቀጠል ምክንያታዊ (rational) ስለማይሆን ነው፡፡

ሌላው ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የሚወጣበት ሥርዓት በፍርድ ውሳኔ ሲሆን ልጁ አስራ አራት ዓመት ከሞላው ጊዜ ጀምሮ ሊከናወን የሚችል ነው[189]፡፡ ለፍርድ ቤቱ ጥያቄው ማቅረብ ያለባቸው የልጁ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ወይም ያገባኛል የሚል ሰው[190] ሲሆን ልጁ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ሊወጣ ይገባል የሚሉበትን አሳማኝ ምክንያት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ በፍርድ ቤቱ እምነት የልጁ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ መውጣት ለልጁ የሚጠቅም ሆኖ ካገኘው ይሁንታ የሚሰጥበት ነው፡፡ አስራ አራት ዓመት ቀደም ባለው ምዕራፍ እንዳየነው አንድ ሰው የስራ ውል ለመፈራረም የሚችልበት ዝቅተኛው ዕድሜ ስለሆነ በዚያውም በራሱ ገቢ መኖር የሚጀምርበት ወቅት ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ በውጤቱም አንድ ሰው ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ መውጣቱ በጋብቻ ወይም በፍርድ ከተወሰነ በኋላ ጋብቻው ቢፈርስ እንኳ የማይሻር ነው[191]፡፡ የፍርድ ውሳኔውም

[189] ዝኒ ከማሁ 312(1) በነባሩ የፍትሐብሔር ህግ መሠረት ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ማውጫ ዝቅተኛው ዕድሜ አስራ አምስት ዓመት ነበር (ፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 330(1) ይመለከቷል) የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ይህንኑ ዕድሜ ወደ አስራ አራት ዓመት ዝቅ አድርጎታል፡፡ ይህ የተደረገበት ምክንያት "የዘመኑ ልጅ የልጅ አዋቂ ነው" ከሚል እሳቤ ሳይሆን የአሠሪና ሠራተኛ ህጉን የቅጥር ውል ዝቅተኛ ዕድሜ አስራ አራት መሆኑ ግምት ውስጥ በማስገባትና ከዚሁ ጋር ለማጣጣም ታስቦ ነው፡፡

[190] ያገባኛል የሚል ሰው (interested party) ማን እንደሆነ በዚህ መጽሐፍ በቅጽ አንድ ውስጥ የጠቀስነው ስለሆነ ይህንኑ ትርጉም እንደያዘ መቀጠሉ መገንዘብ ይገባል፡፡

[191] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 314

ፀንቶ የሚቀጥል ነው፡፡ በዚሁም ልጁ በህግ አካለመጠን እንደደረሰ ሰው ተቆጥሮ ራሱን በሙሉ ነፃነት ያስተዳድራል፡፡

ሦስተኛውና የመጨረሻው አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ምክንያት ኃላፊነት ቀሪ የሚሆንበት ሁኔታ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የሞተ እንደሆነ ነው፡፡ የዚህ ምክንያቱ ግልጽና ቀላል ነው፡፡ ልጁ ከሞተ የልጁ መልካም አስተዳደግና ደህንነት ብሎ ነገር ስለሌለ አሳዳሪ አያስፈልግም ሃብቱም ቢሆን ወራሾቹ ተረክበው የሚከፋፈሉትና የሚያስተዳድሩት ስለሆነ የሞግዚት አስፈላጊነትም በዚሁ ቀሪ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ስለዚህ የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ኃላፊነት በተለያዩ ምክንያቶች ቀሪ ሊሆን እንደሚችልና ውጤቱም እንደምክንያቱ የተለያየ እንደሆነ መገንዘቡ ተገቢ ነው፡፡

---------------- // ------------------

አባሪዎች

Scanned by CamScanner

አባሪ አንድ
ምዕራፍ ዘጠኝ
ስለመወለድ
ክፍል 1
አባትነትንና እናትነትን ስለማወቅ
ንዑስ ክፍል 1
አጠቃላይ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 123 የሕጉ ድንጋጌዎች አስገዳጅ ስለመሆናቸው

ሕጉ በግልጽ የሚፈቅድ ካልሆነ በስተቀር አባትነትና እናትነትን ስለማወቅ የተመለከቱት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች በስምምነት ሊለወጡ አይችሉም፡፡

አንቀጽ 124 ስለእናትነት

እናት የተባለችው ሴት ልጁን የወለደችው በመሆንዋ ብቻ እናትነቷ ይታወቃል፡፡

አንቀጽ 125 ስለአባትነት

1. ልጅ በሚፀነስበት ወይም በሚወለድበት ጊዜ በእናትየዋና በአንድ ወንድ መካከል በሕግ የታወቀ ግንኙነት መኖሩ በመረጋገጡ ምክንያት አባትነት ይታወቃል፡፡
2. አባትየው ልጁን ልጄ ነው ሲል በመቀበሉ ምክንያትም አባትነት ሊታወቅ ይችላል፡፡
3. በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔም አባትነት እንዲታወቅ ሊደረግ ይችላል፡፡

ንዑስ ክፍል 2
አባትነት በሕግ ግምት የሚታወቅ ስለመሆኑ

አንቀጽ 126 ባል አባት ነው ተብሎ የሚገመት ስለመሆኑ

በጋብቻ ውስጥ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባቱ ነው የሚባለው ባልየው ነው፡፡

አንቀጽ 127 የግምቱ አጠቃላይነት

1. ከልጁ ጋር ያለው የእናት ግንኙነት በየትኛውም ዘዴ የተረጋገጠ ቢሆንም በአንቀጽ 126 የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡
2. የልጁ የልደት ምስክር ወረቀት ባልየው አባት አለመሆኑን ወይም የልጁ አባት ሌላ ሰው መሆኑን የሚያመለክት ቢሆንም እንኳን ይኸው ድንጋጌ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡
3. ከዚህ በላይ የተመለከተው ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ የልደት ምስክር ወረቀቱ እንዲታረም ይደረጋል፡፡

አንቀጽ 128 እርግዝናው ስለሚቆይበት ጊዜ

1. ጋብቻው ከተፈጸመ ከ180 ቀናት በኋላ ወይም ጋብቻው በፈረሰ በ300 ቀናት ውስጥ የተወለደ እንደሆነ ልጁ በጋብቻው ውስጥ እንደተፀነሰ ይቆጠራል፡፡
2. ለዚህ ተቃራኒ የሆነ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

አንቀጽ 129 የባልየው መጥፋት

በዚህ ሕግ ስለአባትነት የተደነገጉት የሕግ ግምቶች በሕግ አባት ነው የሚባለው ሰው መጥፋቱ በተነገረበት ፍርድ ላይ ስለመኖሩ ወሬ የተሰማበት የመጨረሻ ቀን ነው ከተባለበት ከ300 ቀናት በኋላ ለተወለደ ልጅ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

አንቀጽ 130 ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር

1. ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባት በዚሁ ግንኙነት ከእናትየዋ ጋር አብሮ የሚኖረው ሰው ነው፡፡
2. በዚህ ሕግ አንቀጽ 127 እና 128 ስለግምቱ አጠቃላይነት እርግዝናው ስለሚቆይበት ጊዜ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ ለተመለከተው የሕግ ግምትም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

ንዑስ ክፍል 3
ልጅነትን ስለመቀበል

አንቀጽ 131 (1) መሠረቱ

ከዚህ በላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የልጁ አባት ሊታወቅ ያልቻለ እንደሆነ አባትየው ልጄ ነው ሲል በመቀበሉ ሊታወቅ ይችላል፡፡

አንቀጽ 132 (2) ትርጓሜ

አንድ ሰው አንድን የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ የእርሱ ልጅ መሆኑን እምነ በመቀበል ቃሉን የሰጠ እንደሆነ የልጁ አባት መሆኑን ተቀበለ ይባላል፡፡

አንቀጽ 133 (3) ሥርዓት (ፎርም)

አንድ ሰው የክብር መዝገብ ሹም ፊት በመቅረብ አባት መሆኑን በመግለጽ በሚሰጠው ቃል ወይም በጽሁፍ በሚያደርገው ነገሩ ወይም በሌላ በማናቸውም ሥልጣን በተሰጠው ባለሥልጣን በተረጋገጠ ሰነድ አማካይነት አባት መሆኑን በመግለጽ ልጅነትን ለመቀበል ይችላል፡፡

አንቀጽ 134 ስለወኪልነት

1. አካለመጠን ያልደረሰ ቢሆንም እንኳን ልጄ ነው ሲል ቃል ለመስጠት የሚችለው አባት ብቻ ነው፡፡
2. ቃሉን ሌላ ሰው እንዲሰጥለት ማድረግ የሚችለው በፍርድ ቤት የፀደቀ ልዩ የውክልና ሥልጣን በመስጠት ብቻ ይሆናል፡፡
3. በፍርድ የተከለከለ ሰው ቃሉን በራሱ ወይም ፍርድ ቤት ሲፈቅድ በእርሱ ስም በሕጋዊ ወኪሉ አማካይነት ሊሰጥ ይችላል፡፡

አንቀጽ 135 የአባትየው መሞት

የልጁ አባት የሞተ ወይም ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል በሆነ ጊዜ ከአባትየው ወላጆች አንዱ በእርሱ ስም ልጁን ሊቀበል ይችላል፡፡

አንቀጽ 136 እናት የተቀባዩን አባትነት ስላለማመንዋ

1. የልጁ እናት የተቀባዩን አባትነት እውነትነት ያለው መሆኑን ካላመነች በስተቀር አባት ልጄ ነው ሲል የሚሰጠው ቃል በሕግ ፊት ውጤት አይኖረውም፡፡
2. የልጁ እናት የሞተች ወይም ፈቃድዋን ለመግለጽ የማትችል ሆና የተገኘች እንደሆነ የእምነት ቃሉ ከልጁ እናት ወላጆች በአንደኛው ሊሰጥ ይችላል፡፡
3. የልጁ እናት ወላጆች በሌሉ ጊዜ ወደላይ በሚቆጠር ሌላ ወላጅ ወይም በፍርድ በተከለከለው ሰው አሳዳሪ ሊሰጥ ይችላል፡፡

አንቀጽ 137 ስለ ልጁ አካለ መጠን መድረስ

ልጅነትን የመቀበሉ ተግባር የተከናወነው ልጁ አካለ መጠን ከደረሰ በኋላ የሆነ እንደሆነ አባት ልጁን መቀበሉ ውጤት የሚያገኘው ልጁ አባትነቱን የተቀበለ እንደሆነ ነው፡፡

አንቀጽ 138 እምነ የመቀበሉ ሁኔታ

በዚህ ሕግ አንቀጽ 136 እና 137 የተመለከቱት ሰዎች የመቀበሉ ድርጊት መከናወኑን ካወቁበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ክርክር ያላነሱ እንደሆነ እምነው እንደተቀበሉ ይቆጠራል፡፡

አንቀጽ 139 የልጁ መሞት

ልጅየው ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆችን ተክቶ ካልሞተ በስተቀር ልጅነቱን አውቆ መቀበል አይቻልም፡፡

አንቀጽ 140 ቃልን ስለመሻር

1. ልጄ ነው ሲል አባት የሰጠውን ቃል መሻር አይችልም፡፡
2. አሳዳሪው አስቀድሞ ስምምነቱን ካልሰጠ በስተቀር ልጅነትን የተቀበለ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ አካለ መጠን ከመድረሱ በፊት እና አካለ መጠን ከደረሰ በኋላም እስከ አንድ ዓመት ጊዜ ድረስ ልጄ ነው ሲል የሰጠውን ቃል ሊሽር ይችላል፡፡
3. ልጄ ነው ሲል የተቀበለበትን ቃሉን ለመሻር ብቸኛ መብት ያለው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ብቻ ነው፡፡ የልጁ ሕጋዊ ወኪሎችም ሆኑ ወራሾቹ በዚህ መብት መጠቀም አይችሉም፡፡

አንቀጽ 141 ስለማፍረስ

1. ልጅነትን ለመቀበል የተነገረ ቃል በኃይል የተሰጠ መሆኑን በማስረዳት ሊፈርስ ይችላል፡፡
2. ልጄ ነው ብሎ ከተቀበለው ሰው ሊፀነስ የማይችል ለመሆኑ ልጅነትን የመቀበሉ ከማያሻማ አኳኋን ካልተረጋገጠ በስተቀር ድርጊት በስህተት ወይም በማታለል የተደረገ ነው በማለት ሊፈርስ አይችልም፡፡

አንቀጽ 142 አንድን ልጅ ብዙ አባቶች ሊቀበሉት ስላለመቻላቸው

ካልተደረገ ቀደም ሲል የተሰጠ ልጅነትን የመቀበል ቃል እንዲፈርስ በስተቀር ሌላ ሰው ልጄ ነው ሲል የሚሰጠው ቃል ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

Scanned by CamScanner

ንዑስ ክፍል 4
በፍርድ ቤት ውሳኔ አባትነት እንዲታወቅ ስለማድረግ

አንቀጽ 143 (1) በፍርድ ስለሚነገር አባትነት

ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የልጁ አባት ያልታወቀ ወይም የተካደ እንደሆነና ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ አባትነት በፍርድ ውሳኔ ሊታወቅ ይችላል፡

ሀ) ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ በእናቲቱ ላይ የመድፈር ወይም የመጠለፍ ተግባር የተፈፀመባት ሲሆን

ለ) ሆን ተብሎ በተደረገ የተንኮል ድርጊት ሥልጣን ያለአግባብ በመጠቀም አገባሻለሁ ሲል የተሰፋ ቃል በመስጠት ወይም በሌላ ተመሳሳይ መንገድ ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ በእናቲቱ ላይ የማሳት ተግባር የተፈፀመባት ሲሆን

ሐ) አባት ነው በተባለው ሰው የተጻፉና በማያሻማ ሁኔታ አባትነቱን የሚያረጋግጡ ደብዳቤዎች ወይም ሌሎች ጽሑፎች ሲኖሩ

መ) በሕግ የታወቀ ግንኙነት ሳይኖራቸው የልጁ እናትና አባት የተባለው ሰው በሕግ በተመለከተው የእርግዝና ጊዜ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አብረው የኖሩ እንደሆነ

ሠ) አባት ነው የተባለው ሰው ልጁን በመንከባከብ ወይም በማሳደግ ላይ እንደአባት በመሆን የተሳተፈ እንደሆነ፡፡

አንቀጽ 144 (2) አባትነትን በፍርድ ለማረጋገጥ ስለሚቀርብ ክስ

ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ አባትነት በፍርድ እንዲነገር የሚቀርብ ክስ ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ባሉ ጊዜ ተቀባይነት አይኖረውም

ሀ) ሌላኛው ሰው የልጁ አባት ላለመሆኑ በደም ምርመራ ወይም በሌላ አስተማማኝ የህክምና ዘዴ ካልተረጋገጠ በስተቀር በሕግ በተወሰነው የእርግዝና ጊዜ ውስጥ እናቲቱ ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀምዋ የተረጋገጠ እንደሆነ፡

ለ) አባት ነው የተባለው ሰው በሕግ በተወሰነው የእርግዝና ጊዜ ውስጥ በመጥፋቱ ወይም በአደጋ ምክንያት አባት ሊሆን የማይችልበትን ሁኔታ ሲያረጋግጥ፤

ሐ) አባት ነው የተባለው ሰው በደም ምርመራ ወይም በሌላ አስተማማኝ የህክምና ዘዴ የልጁ አባት ሊሆን የማይችል መሆኑን ሲያረጋግጥ፡፡

አንቀጽ 145 ሌላ ሁኔታ ስላለመኖሩ

በዚህ ሕግ አንቀጽ 143 ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጪ አባትነት በፍርድ ቤት ውሳኔ ሊታወቅ አይችልም፡፡

ክፍል 2
አባትነት በመወሰን ላይ ስለሚኖረው የሕግ ግምት

አንቀጽ 146 አባትነት ስለመወሰን (1) መሠረቱ

ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተፈጻሚ በማድረግ

አንድ ልጅ ከአንድ በላይ አባቶች አሉት ከተባለ የልጁ አባትነት በሕግ በሚሰጣቸው ሰዎች መካከል በሚደረግ ስምምነት ሊወሰን ይችላል፡፡

አንቀጽ 147 (2) ሥርዓት (ፎርም)

1. የአባትነት ውሳኔ የሚያሰጠውን ስምምነት ሦስት ምስክሮች ሊያረጋግጡትና ፍርድ ቤት ሊያፀድቀው ይገባል፡፡
2. ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካጋጠመ በስተቀር የልጁን እናት ቃል መስማት ይገባል፡፡

አንቀጽ 148 የህግ ግምት

ስለአባትነት በሚደረገው ክርክር ስምምነት ያልተገኘ እንደሆነና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ከዚህ ተገልፀው ያሉትን ሁለት የሕግ ግምቶች በመከተል ይፈፀማል፡

ሀ) ጋብቻ ሳይፈጽም እንደ ባል ከሚኖር ሰው ይልቅ ህጋዊው ባል ይመረጣል፡፡

ለ) ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ ከነበረው ባል ወይም ከሴትየዋ ጋር አብሮ ይኖር ከነበረው ሰው ይልቅ እናቲቱ ልጁን ስትወልድ የነበራት ባል ወይም አብሮ የሚኖር ሰው የልጁ አባት ነው ማለት ይገባል፡፡

አንቀጽ 149 (1) አባትነትን በስምምነት ስለማስተላለፍ

1. ልጁ የተወለደው ጋብቻው ከተፈፀመ ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ከተጀመረ እንስቶ በ210 ቀናት ውስጥ የሆነ እንደሆነ ባልየው ወይም ከሴትየዋ ጋር እንደባል አብሮ የሚኖረው ሰው የልጁ አባት እኔ ነኝ ለሚል ሌላ ሰው በስምምነት አባትነቱን ሊያስተላልፍለት ይችላል፡፡

Scanned by CamScanner

2. እንዲሁም ልጁ ከጋብቻው መፍረስ ወይም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖሩ ከተቋረጠበት ቀን በኋላ 210 ቀኖችን አሳልፎ ተወልዶ እንደሆነ ባለቤቱ ወይም እንደባል አብሮ የኖረው ሰው ከዚህ በላይ የተነገረው መብት ይኖረዋል።

አንቀጽ 150 (2) ሥርዓት (ፎርም)

1. በስምምነት የሚደረግ አባትነትን የማስተባበል ድርጊት ሁለት ምስክሮች ሊያረጋግጡትና ፍርድ ቤት ሊያፀድቀው ይገባል።
2. ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር የእናቲቱ ቃል መሰማት አለበት።

አንቀጽ 151 ስለወኪልነት

1. በዚህ ክፍል የተመለከቱትን ስምምነቶች አካለ መጠን የደረሱና በፍርድ ያልተከለከሉ ባለጉዳዮች ራሳቸው መፈረም አለባቸው።
2. ስምምነቱን ሌላ ሰው እንዲያከናውንለት ማድረግ የሚቻለው በፍርድ ቤት የፀደቀ ልዩ የውክልና ሥልጣን በመስጠት ብቻ ነው።

አንቀጽ 152 ቃልን ስለመሻር

አባትነትን በስምምነት የመወሰን ወይም የማስተባበር ድርጊት ሊሻር አይችልም።

አንቀጽ 153 ስለማፍረስ

1. ልጅነትን ለመቀበል የተደረገ ስምምነት በኃይል ድርጊት የተሰጠ መሆኑን በማስረዳት ሊፈርስ ይችላል።
2. ልጄ ነው ብሎ ከተቀበለው ሰው ሊሆንስ የማይችል ለመሆኑ በማያሻማ አኳኋን ካልተረጋገጠ በስተቀር ልጅነትን የመቀበሉ ስምምነት በስህተት ወይም በማታለል የተደረገ ነው በማለት ሊፈርስ አይችልም።

ክፍል 3
ስለልጅነት ማስረጃ

አንቀጽ 154 የልደት ምስክር ወረቀት

በአባትነት ወይም በእናትነት በኩል የአንድ ሰው ልጅነት የእገሌ ልጅ ነው የሚል የልደት ምስክር ወረቀት በማቅረብ ይረጋገጣል።

አንቀጽ 155 የልደት ምስክር ወረቀት በሌለ ጊዜ ስለሚቀርብ ማስረጃ

የልደት ምስክር ወረቀት የሌለ እንደሆነ የልጅነት ሁኔታ በመኖሩ ልጅነት ይረጋገጣል።

አንቀጽ 156 የልጅነት ሁኔታ መኖር (1) ትርጓሜ

አንድ ሰው የልጅነት ሁኔታ አለው የሚባለው በማኅበረሰቡ ዘንድ የእርሱ ወይም የእርሷ ልጅ ነው እየተባለ የሚገመት ሲሆን ነው።

አንቀጽ 157 ልጅነትን በልጅነት ሁኔታ ስለማስረዳት

1. ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ መሠረት የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት የተቻለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ልጁ ነው ሲል የሕግ ግምት ይወስዳል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ግምት ልጁ የተባለው ሰው ልጅ ሊሆን እንደማይችል በማስረዳት ማፍረስ ይቻላል።

አንቀጽ 158 ተወላጅነትን ለማስረዳት ስለሚቀርብ ክስ

1. የልጅነት ሁኔታ የሌለ እንደሆነ ተወላጅነትን በምስክሮች ወይም ማናቸውንም ዓይነት ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይቻላል።
2. ተወላጅነትን የማረጋገጥ ክስ ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሊቀርብ አይችልም።
3. ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ለሚቀርበው ክስ ፈቃድ የሚሰጠው ፍርድ ቤቱ ክሱን እንዲቀበል የሚያደርጉ ተፈፃሚነት ካላቸው ተግባራት የሚመነጩ ግምቶች ወይም ምልክቶች ሲኖሩ ብቻ ነው።

አንቀጽ 159 ክስን ስላለመቀበል

ተወላጅነቱን ለማረጋገጥ የሚፈልገው ሰው ስለመወለዱ ከተሰጠው የልደት ምስክር ወረቀት ጋር የሚስማማ የልጅነት ሁኔታ ያለው እንደሆነ ከሌላ ሰው ተወላጅነቱን ለማረጋገጥ ክስ ለማቅረብ አይፈቀድለትም።

አንቀጽ 160 ስለ ከሳሽ

1. ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ክስ ለማቅረብ የሚችሉት ልጁ ወይም አሳዳሪው ወይም ወራሾቹ ናቸው።
2. እንደዚሁም የልጁ አባት ወይም እናት ነን የሚሉት ሰዎች ክስ ለማቅረብ ይችላሉ።

Scanned by CamScanner

አንቀጽ 161 ክስ ስለሚቀርብበት ጊዜ

1. ልጁ በሕይወት እስካለ ድረስ ተወላጅነቱን ለማረጋገጥ ክስ ለማቅረብ ይችላል።
2. የልጁ ወላጆች ወይም አሳዳሪዎች ልጁ አካለ መጠን ባልደረሰበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር ክስ ለማቅረብ አይችሉም።
3. ልጁ ሃያ ዓመት ሳይሞላው የሞተ እንደሆነ እርሱ ከሞተ በኋላ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር ወራሾቹ ክስ ለማቅረብ አይችሉም።

አንቀጽ 162 ስለ ተከሳሽ

1. ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ክሱን ያቀረበችው እናት ነኝ የምትል ሴት በሆነች ጊዜ ክሱ የሚቀርበው በልጁ ላይ ነው።
2. ሆኖም ክሱ የቀረበው በሌላ ሰው ሲሆን ክሱ የሚቀርበው እናት ነች በተባለችው ወይም በወራሾችዋ ላይ ነው።

ክፍል 4
በተወላጅነት ላይ ስለሚነሳ ክርክርና ስለመካድ
ንዑስ ክፍል 1
በተወላጅነት ላይ ስለሚነሳ ክርክር

አንቀጽ 163 መሠረት

በእናት በኩል ያለው ተወላጅነት በማንኛውም ባለጉዳይ በማንኛውም ጊዜ ሁሉ ክርክር ሊደረግበት ይችላል።

አንቀጽ 164 ክስን ስለመቀበል

1. በተወላጅነት ላይ ስለሚደረገው ክርክር የሚቀርበው ክስ ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሊቀርብ አይችልም።
2. በተወላጅነት ላይ ክርክር ለማድረግ ለሚቀርበው ክስ ፈቃድ የሚሰጠው ፍርድ ቤቱ ክሱን እንዲቀበል የሚያደርጉት ተጨባጭነት ካላቸው ተግባራት የሚመነጩ ግምቶች ወይም ምልክቶች ሲኖሩ ብቻ ነው።

አንቀጽ 165 ክስን ስላለመቀበል

ልጁ ተወላጅነቱን የሚያረጋግጥ የልደት ምስክር ወረቀትና ከዚህ ጋር የሚስማማ የልጅነት ሁኔታ ያለው እንደሆነ በተወላጅነቱ ላይ ለመከራከር ፈቃድ አይሰጥም።

አንቀጽ 166 ስለ ተከሳሽ

1. በተወላጅነት ምክንያት የሚቀርበው ክስ በተወላጅነቱ ላይ ክርክር በተነሳበት ሰው ላይ ወይም በወራሾቹ ላይ ይመሰረታል።
2. የልጁን እናት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የልጁን አባት ክርክሩ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ንዑስ ክፍል 2
ስለ መካድ

አንቀጽ 167 መሠረት

በአባት በኩል ያለን መወለድ መቃወም የሚቻለው የመካድ ክስ በማቅረብ ብቻ ነው።

አንቀጽ 168 ከልጁ እናት ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ስላለመኖር (1) መሠረት

የልጁ አባት ነህ ተብሎ በሕግ አባትነት የሚሰጠው ሰው ልጁ ከመወለዱ በፊት በ300ኛውና በ180ኛው ቀናት መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ከልጁ እናት ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ላለመፈጸሙ በማያጠራጥር ሁኔታ ያስረዳ እንደሆነ የተባለውን ልጅ ልጄ አይደለም ለማለት ይችላል።

አንቀጽ 169 (2) የሕግ ግምት

1. ከሁለቱ አንዱ ባቀረበው የመፋታት ጥያቄ መሠረት ወይም በሁለቱ መካከል በተደረገው የመለያየት ስምምነት ምክንያት ባልና ሚስቱ በእውነት ተለያይተው በነበሩበት ጊዜ በመካከላቸው የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት እንዳልተደረገ ይገመታል።
2. ለዚህ ተቃራኒ ሆኖ የሚቀርበው ማስረጃ በማናቸውም ምክንያቶች ቢሆን ይሰማል።

አንቀጽ 170 አባት ለመሆን ስለአለመቻሉ (1) መሠረት

በሕግ የልጁ አባት ነህ የተባለው ሰው የዚህ ልጅ አባት ሊሆን አለመቻሉን በማያጠራጥር አኳኋን በማስረዳት ለመካድ ይችላል።

Scanned by CamScanner

አንቀጽ 171 (2) ክስን ለመቀበል ስለመቻል

1. ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ መሠረት የሚቀርበው የመካድ ክስ ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሊቀርብ አይችልም፡፡
2. ፈቃዱም የሚሰጠው ፍርድ ቤት ክሱን እንዲቀበል የሚያደርገው በቂና አስተማማኝ ከሆነ መረጃ የሚመነጭ የሀሊና ግምት ወይም ከባድ ምልክት ሲኖር ብቻ ነው፡፡

አንቀጽ 172 (3) ስለ ሀሊና ግምቶችና ከባድ ምልክቶች

1. የሀሊና ግምቶችና ከባድ ምልክቶች የሚባሉት ልጅነ ነው ከተባለው ሰው አባትነት ጋር የማይስማሙ ለመሆናቸው በላይገለ እውቀት ተለይተው የሚታዩ ተጨባጭ መረጃዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
2. እንዲሁም እነዚህ ነገሮች ሲቲቱ በሰውየው አባትነት ላይ ጥርጣሬ በሚያሳድር አኳኋን የልጁን መወለድ ወይም እርግዝናቀን ከሰውየው ከደበቀችበት ድርጊት ሊመነጩ ይችላሉ፡፡

አንቀጽ 173 (4) ስለ ሴሰኝነት (በባል ላይ ስለሚደረግ ዝሙት ወይም ስለ እናቲቱ ማመን)

እናቲቱ በባልዋ ላይ ያደረገችው የሴሰኝነት (የዝሙት) ሥራ ወይም ልጁ የሌላ ሰው ለመሆኑ የምትሰጠው የእምነት ቃል ብቻ እንደ ከባድ ምክንያት ሊቆጠሩ አይችሉም፡፡

አንቀጽ 174 ስለ ከሳሽ

1. የእኔ ልጅ አይደለም ብሎ የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚችለው የልጁ አባት ነህ ተብሎ በህግ ግምት የሚሰጠው ሰው ብቻ ነው፡፡
2. በዚሁ ጉዳይ በተለይ እናቲቱ አባት ነኝ ባዩ አቃቤ ሕግ ወይም ልጁ ራሱ ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም፡፡

አንቀጽ 175 በፍርድ የተከለከለ ሰው

1. በፍርድ የተከለከለ ሰው ፍርድ ቤትን አስፈቅዶ የመካድ ክስ ለማቅረብ ይችላል፡፡
2. እንዲሁም በፍርድ የተከለከለው ሰው አሳዳሪ ይህንኑ የፍርድ ቤት ፈቃድ ከተቀበለ በኋላ በፍርድ በተከለከለው ሰው ስም ሆኖ የመካድ ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡

አንቀጽ 176 ክስ ስለሚቀርብበት ጊዜ (1) መሠረቱ

1. የእኔ ልጅ አይደለም የሚል የመካድ ክስ የልጁን መወለድ ካወቀበት ወይም ማወቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ በ180 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡
2. እናትነት የተወሰነው ተወላጅነትን ለማረጋገጥ በቀረበ ክስ ሲሆን የመካድ ክስ የሚቀርበው ተወላጅነትን ለማረጋገጥ የቀረበውን ክስ የሚወስን የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ ጀምሮ ባሉት 180 ቀናት ውስጥ ነው፡፡

አንቀጽ 177 (2) ልዩ ሁኔታ

1. በሕግ ግምት የልጁ አባት ነህ የሚባለው ሰው የሞተ ወይም የመካድ ክስ ለማቅረብ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ችሎታውን ያጣ እንደሆነ ከተወላጆቹ አንዱ በእርሱ ፋንታ ሆኖ የመካድ ክስ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. ተወላጆቹ የሌሉ እንደሆነ አባትና እናቱ እነዚህም የሌሉ እንደሆነ ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ አንዱ መብቱን ሊሰራበት ይችላል፡፡
3. ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች የሌሉ እንደሆነ የተባለውን መብት ማንኛውንም ሌላ ወራሽ ወይም ወኪልን ሳይጨምር ከወንድሞቹ ወይም ከእህቶቹ አንዱ ሊሰራበት ይችላል፡፡

አንቀጽ 178 ክስን ስላለመቀበል

ባልየው በጽሁፍ በሰጠው ፈቃድ መሠረት ልጁ በሰው ሰራሽ ዘዴ የተፀነሰ ለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡

አንቀጽ 179 ስለ ተከሳሾች

1. የመካድ ክስ በልጁ ላይ እርሱም ሞቶ እንደሆነ በወራሾቹ ላይ ይቀርባል፡፡
2. የልጁን እናት በሚቀርበው ክስ ውስጥ እንድትገባ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
3. ልጁ አካለ መጠን ያልደረሰ ከሆነ ፍርድ ቤት በተለይ ለዚህ ጉዳይ የመረጠው ሞግዚት ወኪል ይሆንዋል፡፡

ምዕራፍ አስር
ስለ ጉዲፈቻ

አንቀጽ 180 ስለጉዲፈቻ ዝምድና (1) መሠረቱ

በአንድ ሰውና በአንድ ልጅ መካከል በሚደረግ ስምምነት የጉዲፈቻ ዝምድና ሊፈጠር ይችላል።

<u>አንቀጽ 181 (2) ውጤቱ</u>

በዚህ ሕግ አንቀጽ 182 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጉዲፈቻ ልጅ በማናቸውም ረገድ ቢሆን እንደ ጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ ይቆጠራል።

<u>አንቀጽ 182 (3) ልዩ ሁኔታ</u>

1. ጉዲፈቻ የጉዲፈቻውን ስምምነት በግልጽ የተቃወሙትን ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆችን ወይም ወደጎን የሚቆጠሩ ዘመዶችን በሚመለከት ውጤት አይኖረውም።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ተቃውሞ ስምምነቱ በፍርድ ቤት መጽደቁ በታወቀ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በፍርድ ቤት መዝገብ ካልተመዘገበ በስተቀር አይፀናም።

<u>አንቀጽ 183 የጉዲፈቻ ልጅ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት</u>

1. የጉዲፈቻ ልጅ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ያለው የዝምድና ግንኙነት እንደተጠበቀ ይቆያል።
2. የጉዲፈቻ ልጅየው ሚስት/ባል እና ተወላጆችም ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር የዝምድና ግንኙነት ይኖራቸዋል።
3. በቀደምት ቤተሰቦቹና በጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ መካከል መምረጥ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ለጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ ቅድሚያ ይሰጣል።

<u>አንቀጽ 184 የጉዲፈቻ አድራጊው ዕድሜ</u>

1. ዕድሜው ከ25 ዓመት ያላነሰ ማንኛውም ሰው የጉዲፈቻ አድራጊ ሊሆን ይችላል።
2. ጉዲፈቻ አድራጊዎች ባልና ሚስት በሆኑ ጊዜ የአንዳቸው ዕድሜ 25 ዓመት የሞላ ከሆነ በቂ ነው።

<u>አንቀጽ 185 የጉዲፈቻ ልጅ ዕድሜ</u>

ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነና ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ያልወጣ ማንኛውም ሰው የጉዲፈቻ ልጅ ለመሆን ይችላል።

<u>አንቀጽ 186 ያገባ ሰው ስለሚያደርገው የጉዲፈቻ ስምምነት</u>

1. ጉዲፈቻ አድራጊው ያገባ በሚሆንበት ጊዜ ባልና ሚስቱ በጋራ ልጁን የጉዲፈቻ ልጃቸው የሚያደርጉት ካልሆነ በስተቀር የጉዲፈቻ ስምምነት ለማድረግ አይቻልም።
2. የጉዲፈቻው ልጅ የጉዲፈቻ አድራጊው ባል ወይም ሚስት ልጅ በሆነ ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነት አይኖረውም።
3. እንዲሁም ከባል እና ከሚስት አንደኛው ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል ሲሆን ተፈፃሚነት አይኖረውም።

<u>አንቀጽ 187 የተፀነሰ ልጅ የጉዲፈቻ ልጅ ስለማድረግ</u>

1. የተፀነሰን ልጅ የጉዲፈቻ ልጅ ማድረግ ይቻላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም ልጁ በተወለደ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ እናቲቱ ስምምነቱን በገዛ ፈቃድዋ ብቻ ለመሰረዝ ትችላለች።

<u>አንቀጽ 188 ስለጉዲፈቻ አድራጊው ልጆች</u>

1. ጉዲፈቻ አድራጊው ከአብራኩ የተገኙ ልጆች ያሉት መሆን የጉዲፈቻ ስምምነት ከማድረግ የሚያግደው አይሆንም።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ከማጽደቁ አስቀድሞ ጉዲፈቻ አድራጊው ከአብራኩ የተገኙ ልጆች ያሉት መሆን በጉዲፈቻ ልጁ መልካም አስተዳደግና ጥቅም ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተፅዕኖ ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

<u>አንቀጽ 189 አንድ ልጅ ከአንድ በላይ ጉዲፈቻ አድራጊ ሊኖረው የማይችል ስለመሆኑ</u>

1. ባልና ሚስት ካልሆኑ በስተቀር ማንኛውም ልጅ ለብዙ ሰዎች የጉዲፈቻ ልጅ ሊሆን አይችልም።
2. ጉዲፈቻ አድራጊው የሞተ እንደሆነ ግን አዲስ የጉዲፈቻ ስምምነት ለማድረግ ይቻላል።
3. ልጅየው የባልና ሚስት የጉዲፈቻ ልጅ ከሆነና ከባልና ሚስቱ አንደኛው የሞተ እንደሆነ በሕይወት ካለው ሰው ጋር የሚጋባው አዲስ ተጋቢ የጉዲፈቻ ልጅ ሊያደርገው ይችላል።

<u>አንቀጽ 190 ስምምነቱን ስለሚያደርጉ ወገኖች</u>

የጉዲፈቻው ስምምነት በጉዲፈቻ አድራጊውና በልጁ አሳዳሪ መካከል ይደረጋል።

Scanned by CamScanner

አንቀጽ 191 የጉዲፈቻው ልጅ ወላጆች ፈቃድ

1. የልጁ አባትና እናት በሕይወት ያሉና የታወቁ ከሆነ ልጁ የጉዲፈቻ ልጅ እንዲሆን ፈቃዳቸውን እንዲሰጡ ያስፈልጋል፡፡
2. ከወላጆቹ አንደኛው የሞተ፣ የጠፋ የማይታወቅ እንደሆነ ወይም ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል ሲሆን ሌላኛው ወላጅ ፈቃዱን ይሰጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ከወላጆቹ አንዱ ፈቃዱን ለመስጠት ያልፈለገ እንደሆነና የልጁ ዕድሜ 10 ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ያንደኛውን ወላጅ ፈቃድና የልጁን አስተያየት በመጠየቅ ጉዲፈቻውን ሊያፀድቀው ይችላል፡፡
4. ልጁ ፈቃዱን ለመስጠት የሚችል ወደላይ የሚቆጠር ወላጅ የሌለው እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ለልጁ ያለውን ጠቃሚነት ግምት ውስጥ በማስገባት የጉዲፈቻ ስምምነቱን ሊያፀድቀው ይችላል፡፡

አንቀጽ 192 ስለመንግሥት ወይም የግል ዕጓለማውታን አሳዳጊ ተቋሞች

1. የመንግሥት ወይም የግል ዕጓለማውታን አሳዳጊ ተቋሞች እያሳደጉት ያሉትን ማንኛውንም ልጅ ለጉዲፈቻ አድራጊዎች በስምምነት ለመስጠት ይችላሉ፡፡
2. ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ተቋሞች አንድን ልጅ በስምምነት ከመስጠታቸው በፊት የሕፃናትን ደህንነት ለመከታተል ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካል ስለልጁ ማንነት ተቋሙ በምን ሁኔታ እንደተረከበውና ስለጉዲፈቻ አድራጊው ግላዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቋም መግለጫ ማቅረብ አለባቸው፡፡

አንቀጽ 193 ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን

1. ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን
ለመከታተል ሥልጣን የተሰጠው አካል ስለጉዲፈቻ አድራጊው ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን የሕፃናትን ደህንነት ግላዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቋም አግባብ ያላቸውን መረጃዎች በማጠናቀርና በመመርመር ስምምነቱ ቢደረግ ለልጁ ጠቃሚነት ይኖረዋል ሲል አስተያየቱን ካልሰጠ በስተቀር የጉዲፈቻውን ስምምነት ፍርድ ቤት ሊያፀድቀው አይችልም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ ስምምነቱ ለልጁ ጠቃሚነት አይኖረውም ሲል የገመተ እንደሆነ የባለሥልጣኑን አስተያየት ባለመቀበል ስምምነቱን ላያፀድቀው ይችላል፡፡

3. ፍርድ ቤቱ ከባለሥልጣኑ የቀረበለት መረጃ በቂ መስሎ ያልታየው እንደሆነ አዲስ ምርመራ በማከናወን ተጨማሪ መረጃ እንዲቀርብለት ባለሥልጣኑን ለማዘዝ እንዲሁም ሌሎች ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች አስፈላጊ መስሎ የሚታያቸውንና በእጃቸው የሚገኘውን መረጃ እንዲያቀርቡ ወይም እንደአስፈላጊነቱ የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ለማዘዝ ይችላል፡፡

አንቀጽ 194 የፍርድ ቤት ሥልጣን

1. የጉዲፈቻ ስምምነት ፍርድ ቤት ካላፀደቀው በስተቀር ውጤት አይኖረውም፡፡
2. ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ከማፅደቁ አስቀድሞ በውነኛ መልኩ ለልጁ መልካም አስተዳደግና ጥቅም የሚበጅ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. በዚህ ሕግ በአንቀጽ 192 እና 193 የተመለከቱትና የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ከማፅደቁ በፊት የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡
ሀ) ልጅየው ስለጉዲፈቻ ስምምነቱ ያለውን አስተያየት
ለ) አስቀድሞ ፈቃዱን ያልሰጠ ከሆነም የአሳዳሪውን አስተያየት፣
ሐ) ጉዲፈቻ አድራጊው ልጁን ለማሳደግና ለመንከባከብ ያለውን ብቃት፣
መ) ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን ልጅየው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚያድግበት ሁኔታ አለመኖሩን
ሠ) ጉዲፈቻ አድራጊው እንደልጁ አድርጎ እንደሚያሳድገውና አላግባብ መጠቀሚያ እንደማያደርገው ለመገመት የሚያስችል መረጃ መኖሩን፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በፊደል ተራ (መ) የተመለከተውን በሚያጣራበት ጊዜ ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

አንቀጽ 195 የጉዲፈቻ ስምምነት የማይሰረዝ ስለመሆኑ ንዑስ አንቀጽ (2)

1. የጉዲፈቻ ስምምነት በዚህ አንቀጽ
ከተመለከተው ሁኔታ ውጪ ሊሰረዝ አይችልም
2. ጉዲፈቻ አድራጊው በጉዲፈቻ የተቀበለውን ልጅ እንደልጁ በማሳደግ ፋንታ በባርነት ወይም ባርነትን በሚመስል ሁኔታ ወይም ከግብረ ገብ ውጪ በሆነ ተግባሮች እንዲሠማራ

Scanned by CamScanner

በማድረግ መጠቀሚያ ያደረገው እንደሆነ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የልጁን የወደፊት ሕይወት ክፉኛ በሚጎዳ አኳኋን የያዘው መሆኑን የተረጋ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ለመሠረዝ ይችላል፡፡

አንቀጽ 196 የጉዲፈቻ ስምምነቱ እንዲሰረዝ አቤቱታ ስለማቅረብ

1. የጉዲፈቻው ልጅ ራሱ የሕፃናትን ደህንነት ለመከታተል ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካል ወይም በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ማንኛውም ሰው ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ የተደነገገውን መሠረት በማድረግ የጉዲፈቻው ስምምነት እንዲሰረዝ አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት አቤቱታ ሲቀርብለት ፍርድ ቤቱ ጉዲፈቻ አድራጊውን ከማስቀረቡ በፊት ለአቤቱታው ምክንያት ናቸው የተባሉት መረጃዎች እውነት ሆነው ቢገኙ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ለማፍረስ በቂ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ምዕራፍ አስራ አንድ
ቀለብ የመስጠት ግዴታ

አንቀጽ 197 ስለግዴታው ይዘት

በዚህ ሕግ አንቀጽ 198 ድንጋጌዎች መሠረት ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው እንደባለጉዳዮቹ ሁኔታና እንደ አካባቢው ልማድ የሚስማማውን በመከተል ለቀለብ ተቀባዩ ምግብ፣ መኖሪያ፣ ልብስ ጤናውን የሚጠብቅበትና እንደሁኔታው ለትምህርት አስፈላጊ የሆነውን ነገር መስጠት አለበት፡፡

አንቀጽ 198 ግዴታው በእነማን መካከል ስለመሆኑ

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀለብ የመስጠት ግዴታ የሚኖረው በተጥታ ወላጆችና ተወላጆች ወይም በቀጥታ የጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ነው፡፡
2. እንዲሁም በወንድማማቾች እና እህትማማቾች መካከልም ቀለብ የመስጠት ግዴታ ይኖራል፡፡

አንቀጽ 199 ግዴታው ስለማቀርበት ሁኔታ

ጋብቻው የፈረሰው በሞት ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ያለው ቀለብ የመስጠት ግዴታ ቀሪ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 200 ቀለብ ተቀባዩ መብቱን ስለሚያጣበት ሁኔታ

ቀለብ ተቀባዩ በቀለብ ሰጪው ወይም በዚህ ሰው ወደላይና ወደታች በሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ተወላጆች ወይም ባል ወይም ሚስት ሕይወት ወይም ንብረት ላይ የወንጀል ተግባር የፈጸመ ወይም ለመፈጸም የሞከረ እንደሆነ ቀለብ የመቀበል መብቱን ያጣል፡፡

አንቀጽ 201 ግዴታው እንዲኖር አስፈላጊ ሁኔታዎች

ቀለብ የመስጠት ግዴታ ተፈጻሚ የሚሆነው ቀለብ ጠያቂው ሠርቶ ለኑሮው አስፈላጊ የሆነ ገቢ ለማግኘት አቅም የሌለውና በችግር ላይ የወደቀ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

አንቀጽ 202 ስለግዴታው አፈጻጸም

1. በመሠረቱ ቀለብ የመስጠት ግዴታ የሚፈጸመው ቀለብ ሰጪው ለቀለብ ተቀባዩ የቀለቡን ገንዘብ በመስጠት ነው፡፡
2. የቀለቡ መጠን የሚወሰነው ቀለብ ጠያቂው ያለበትን ችግር እና የቀለብ ሰጪውን አቅም በማመዛዘን ነው፡፡

አንቀጽ 203 ሁኔታውን ማሻሻል የሚቻል ስለመሆኑ

ቀለብ ሰጪው ወይም ተቀባዩ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ስለቀለቡ መጠን ወይ ስለቀለብ ተቀባዩ መኖሪያ የተሰጠውን ውሳኔ በማናቸውም ጊዜ ማሻሻል ይቻላል፡፡

አንቀጽ 204 ቀለቡ ስለሚከፈልበት ቦታ

ቀለቡ የሚከፈለው በተቻለ መጠን ለቀለብ ተቀባዩ በሚያመቸው ቦታ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 205 (1) የቀለብ ገንዘብ ሊተላለፍና ሊያዝ የማይችል ስለመሆኑ

1. ለቀለብ የሚከፈል ገንዘብ ሊተላለፍ ወይም ሊያዝ አይችልም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ለቀለብ የሚከፈል ገንዘብ የሚከፈልበት ጊዜ ከመድረሱ አስቀድሞ የሚከፈል ገንዘብ የሚከፈልበት ጊዜ ከመድረሱ አስቀድሞ

Scanned by CamScanner

3. እንዲሁም የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ለቀለብ ተቀባዩ ኑሮ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ያበደሩ ሌሎች ሰዎችን በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

<u>አንቀጽ 206 (2) የቀለብ ገንዘብ የማይጠራቀም ስለመሆኑ</u>

ቀለብ ተቀባዩ ለኑሮው አስፈላጊ መሆኑን ካላረጋገጠ በስተቀር የቀለቡን ገንዘብ መቀበል ካለበት ቀን ጀምሮ በተከታዮቹ ሦስት ወራት ውስጥ ያልተቀበለው ወይም ሳይጠይቀው የቀረ እንደሆነ የተጠራቀመው ቀለብ እንዲሰጠው መጠየቅ አይችልም፡፡

<u>አንቀጽ 207 ቀለብ ተቀባዩን በቀለብ ሰጪው ቤት ለማኖር ስለመቻል</u>

1. ቀለብ ሰጪው ቀለብ ተቀባዩን በመኖሪያ ቤቱ ተቀብሎ በማስቀመጥ ቀለብ በመስጠት ግዴታውን ሊፈፅም ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስለተመለከተው ጉዳይ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የነገሩን የአካባቢ ሁኔታዎች በመመልከት ተገቢ መስሎ የታየውን ይወስናል፡፡
3. ቀለብ ሰጪው ቀለብ ተቀባዩን በመኖሪያ ቤቱ እንዲያስቀምጥ ምንግዜም ቢሆን አይገደድም፡፡

<u>አንቀጽ 208 ስለቀለብ ሰጪዎች ብዛት (1) መሠረቱ</u>

ለቀለብ ተቀባዩ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ብዙ የሆኑ እንደሆነ ቀለብ ተቀባዩ ከእነርሱ መካከል አንዱ ቀለቡን እንዲሰጠው ሊጠይቀው ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 209 (2) ስለአቤቱታ</u>

1. ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ብዙ ሆነው ከእነርሱ መካከል አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑት ቀለቡን የከፈሉ እንደሆነ ሳይከፍሉ የቀሩት ድርሻቸውን እንዲከፍሏቸው ለመጠየቅ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስለተመለከተው ጉዳይ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተከሳሾቹ ያላቸውን ሀብትና ከከሳሽ ጋር ያላቸውን የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ደረጃ በማመዛዘን ተከሳሾቹ የቀለቡን ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲከፍሉ ሊወስንባቸው ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 210 (3) ለቀለብ ሰጪዎች የሚሰጥ ከፍ,ይነት ተራ</u>

በዚህ ሕግ አንቀጽ 198 መሠረት ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ቅደም ተከተል፡

ሀ) በመጀመሪያ ደረጃ፣ ባል ወይም ሚስት

ለ) በሁለተኛ ደረጃ ተወላጆች፣ እንደየደረጃቸው

ሐ) በሦስተኛ ደረጃ፣ ወደላይ ሚቆጠሩ ወላጆች እንደየደረጃቸው

መ) በአራተኛ ደረጃ፣ ወንድማማችና እህትማማቾች

ሠ) በአምስተኛ ደረጃ፣ የጋብቻ ተወላጆች እንደየደረጃቸው

ረ) በስድስተኛ ደረጃ፣ የጋብቻ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች እንደየደረጃቸው፡፡

<u>አንቀጽ 211 በጋራ ቀለብ ሰጪዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት</u>

1. የጋራ ቀለብ ሰጪዎች እርስ በእርሳቸው ስለእሳቸው ግንኙነት ለጋራ ቀለብ ተቀባያቸው ከእነርሱ መካከል አንዱ ቀለቡን እንዲሰጠው በማለት የሚፀና ስምምነት ለማድረግ ይችላሉ፡፡
2. ቀለብ ተቀባዩ ስምምነቱን ወዶ የተቀበለ እንደሆነ ይህንን ስምምነት የሚያከብርበት ከባድ ምክንያት ካልተገኘ በስተቀር ቀለቡን ከሌሎች ቀለብ ሰጪዎች መጠየቅ አይችልም፡፡

<u>አንቀጽ 212 ስለጉዲፈቻ ልጅ ልዩ ሁኔታ</u>

1. የጉዲፈቻ ልጅ ባል ወይም ሚስትና የቀጥታ መስመር ተወላጆች የጉዲፈቻ አድራጊው ቤተዘመዶች ቀለቡን መስጠት በማይችሉበት ሁኔታ ካልተገኙ በስተቀር የሥር ወላጆቹን ቤተዘመዶች ቀለብ ለመጠየቅ አይችሉም፡፡
2. የቀደምት ቤተሰቦቹ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ቀለብ ለማግኘት ከዘመዶቻቸው አንዱን ለመጠየቅ የማይችሉ ካልሆነ በስተቀር በጉዲፈቻ የሰጡትን ልጅ ቀለብ ሊጠይቁት አይችሉም፡፡

<u>አንቀጽ 213 ስለ ሥርዓተ ቀብር ወጪ</u>

1. ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው ለዚህ ለተባለው ሰው ሥርዓተ ቀብር የወጣውንም ወጪ ለመክፈል ይገደዳል፡፡
2. ይህን ወጪ ያደረገው ሰው ወጪውን እንዲተካለት ቀለብ ሰጪውን ለመጠየቅ ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 214 ልዩ ስምምነቶች</u>

ልዩ ስምምነቶችን በማድረግ በዚህ ምዕራፍ የተጻፉትን ድንጋጌዎች ለመለወጥ አይፈቀድም፡፡

Scanned by CamScanner

ምዕራፍ አሥራ ሁለት
አካለ መጠን ስላልደረሱ ሰዎች
ክፍል 1
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 215 ትርጓሜ

አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ማለት ጾታ ሳይለይ ዕድሜው አስራ ስምንት ያልሞላው ልጅ ነው፡፡

አንቀጽ 216 አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ የሌለው ስለመሆን

1. አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ስለመልካም አስተዳደጉና ደህንነቱ ጉዳይ በአንድ አሳዳሪው እየተጠበቀ ይቆያል፡፡
2. ንብረት ነክ ጥቅሞቹንና በአጠቃላይ የንብረቱን አስተዳደር በሚመለከት በሞግዚቱ ይወከላል፡፡
3. በሕግ በግልጽ ለተመለከቱት ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር አካለመጠን ያልደረሰ ሰው ሕጋዊ ድርጊቶችን ለመፈጸም አይችልም፡፡

አንቀጽ 217 የዕድሜ ማስረጃ

1. የአንድ ሰው ዕድሜ የሚረጋገጠው በልደት ምስክር ወረቀት ነው፡፡
2. የልደት ምስክር ወረቀት የሌለ እንደሆነ ዕድሜውን በአስተማማኝነት ለማረጋገጥ ያስችላሉ በሚባሉ ሰነዶች ወይም ከሁለት ያላነሱ ምስክሮችን ቃል መሠረት በማድረግ ፍርድ ቤት ዕድሜውን ይወስናል፡፡

አንቀጽ 218 ውሳኔ ሰጪ አካላት መከተል ስላለባቸው መርህ

በዚህ ምዕራፍ መሠረት በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ የሚሰጡ ውሳኔዎች ሁሉ ለልጆች ደህንነትና መልካም አስተዳደግ የሚበጁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ክፍል 2
አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ስለሚጠብቁ ተቋሞች

አንቀጽ 219 የወላጆች ሥልጣን

አባትና እናት ጋብቻቸው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሁሉ አካለመጠን ላልደረሱት ልጆቻቸው የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት የጋራ ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡

አንቀጽ 220 ከወላጆች የአንዱ ብቻ አለመሆን

1. ከወላጆቹ አንዱ የሞተ፣ ችሎታ ያጣ፣ የተገዚነት መብት ያጣ ወይም ከቤተሰብ አስተዳዳሪነት መብቱ የታገደ እንደሆነ የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥልጣኑን ይዞ የሚቆየው እንደኛው ወገን ብቻ ይሆናል፡፡
2. እንዲሁም የልጁ አባት ያልታወቀ በሆነ ጊዜ የዚህን ሥልጣን ሥራ የምትፈፅመው እናቱ ብቻ ትሆናለች፡፡

አንቀጽ 221 የልጁ አባትና እናት መፋታት

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 77 መሠረት ባልና ሚስት በስምምነት ሲፋቱ የልጆቻቸውን አሳዳሪነትና ሞግዚትነት በተመለከተ በስምምነት ይወስናሉ፡፡
2. በማናቸውም የፍቺ ሁኔታ የልጆቻቸውን አሳዳሪነትና ሞግዚትነት ባልና ሚስቱ በስምምነት ሊወስኑ ካልቻሉ ፍቺውን የወሰነው ፍርድ ቤት ስለልጆቹ አሳዳሪና ሞግዚትም አብሮ ይወስናል፡፡

አንቀጽ 222 በኑዛዜ ቃል የተመረጠ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት (1) መሠረቱ

1. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ በህይወት ያለው ወላጅ ከጊዜ ሞቱ በኋላ ልጁን የሚያስተዳድር ወይም ለልጁ ሞግዚት የሚሆነውን ሰው በመጨረሻ የኑዛዜ ቃል ለመምረጥ ይችላል፡፡
2. እንዲሁም የአሳዳሪውን ወይም ሞግዚቱን ሥልጣን ለመወሰንና የአሳዳጊነቱን የሥራ አመራር ሥልጣን በተወሰነ ሁኔታ ብቻ ለመስጠት ይችላል፡፡

አንቀጽ 223 (2) አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ለመሾም የሚፈፀም ግዴታ

አባት ወይም እናት በህይወት ሳሉ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ የአሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት ሥራ ያካሂድ የነበረ ካልሆንና በዚሁም ጊዜ በገዛ ፈቃዱ ሥልጣኑን አውቆ የተወ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ሕግ አንቀጽ 222 ለአባት ወይም ለእናት የተሰጠው መብት አይኖረውም፡፡

አንቀጽ 224 (3) ለፍርድ ቤት አቤቱታ ስለማቅረብ

Scanned by CamScanner

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ጥቅም የሚያስገድድ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ስለ አሳዳሪው ወይም ስለሞግዚቱ አባቱ ወይም እናቱ ያደረጉትን ውሳኔ ፍርድ ቤት ሊሽረው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

አንቀጽ 225 የልጅን አሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥልጣን ሊይዙ የሚገባቸው ዘመዶች (1) ሊከተሉት የሚገባ ቅደም ተከተል

አንድ ልጅ አባትና እናት የሌለው እንደሆነና ከሁለቱ በመጨረሻ የሞተው ወላጅ በሚገባ ሁኔታ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ሳያደርግለት ቀርቶ እንደሆነ ለልጁ አሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት በሕጉ መሠረት የሚመረጡና ይህ ሥልጣን የሚሰጣቸው ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ሰዎች ናቸው፡

ሀ) የልጁ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች

ለ) እነዚህ በሌሉ ጊዜ አካለመጠን የደረሱ የልጁ ወንድሞች ወይም እህቶች

ሐ) እነዚህ በሌሉ ጊዜ የልጁ አጎት ወይም አክስት፡፡

አንቀጽ 226 (2) ይህ ቅደም ተከተል ስለሚለወጥበት ሁኔታ

1. ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ሥልጣን በሚሰጠው ሰው ምትክ ለልጁ የሥጋ ዝምድና ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ማንኛውም ሰው የአሳዳሪነቱን ወይም የሞግዚትነቱ ሥልጣን ይሰጠኝ ሲል ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ይህም ጥያቄ መቅረብ የሚገባው ቅደም ተከተሉ ለሚመለከታቸው ዘመዶች ሲሆን ስምምነት ካልተገኘ ግን ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ይቀርባል፡፡
3. ጥያቄው መቅረብ ያለበት አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ይህን ሥልጣን መያዙ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡
4. ጥያቄውን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል መሠረት የሚሆነው የልጁ ደህንነትና ጥቅም ሊሆን ይገባል፡፡

አንቀጽ 227 በሕግ የሚመረጡ ዘመዶች መታጣት

1. ከዚህ በላይ ባሉት አንቀጾች የተመለከተውን መሠረት በማድረግ ለልጁ አንድ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ለማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ ይህ ሥራና ሥልጣን ፍርድ ቤት ለመረጠው ሰው ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ይህን ጉዳይ ለመወሰን የልጁ ዘመድ በሆነ ወይም ባልሆነ ያገባኛል ባይ በሚቀርብ ጥያቄ ሊመሰረት ይችላል፡፡

3. የሕፃናትን ደህንነት ለመከታተል ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካልም ጉዳዩን ለፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

አንቀጽ 228 የፍርድ ቤት ምርጫ (1) አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመዶች

ፍርድ ቤት ለልጁ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት እንዲሆን የሚመርጠውና ይህን ሥልጣን የሚሰጠው የልጁ የቅርብ የሥጋ ዘመድ የሆነን ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለውንና በተቻለም መጠን ይህን ሥራ ለማከናወን ችሎታና ፈቃደኝነት ያለውን ሰው ነው፡፡

አንቀጽ 229 (2) የበጎ አድራጎት ድርጅት

ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነቱን ሥልጣን ለዚህ ዓይነት ጉዳይ ለተቋቋመ የበጎ አድራጎት ድርጅት ሊሰጥ ይችላል፡፡

አንቀጽ 230 ተመሳሳይ ሁኔታዎች

ከዚህ በላይ ለተጻፉት ድንጋጌዎች አፈፃፀም አንድ ሰው በሕግ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ተግባሮቹን ለማከናወን የማይችል እንደሆነ እንደሌለ ይቆጠራል፡፡

አንቀጽ 231 የአሳዳሪው ወይም የሞግዚቱ መታወቂያ

1. በመሠረቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ አሳዳሪ እንዲሆን ሥልጣን ተሰጥቶት የልጁን አሳዳሪነት የተቀበለው ሰው ሞግዚቱም ነው፡፡
2. የነገሩ ሁኔታ ተቃራኒ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በህይወት ያለው አባት ወይም እናት ወይም ፍርድ ቤት ለልጁ የሚሾሙት ሞግዚት ወይም አሳዳሪ ሁለቱንም ሥልጣን እንደያዘ ይቆጠራል፡፡

አንቀጽ 232 ለአባትና እናት የተሰጠ መብት

አባት ወይም እናት ጉዳዩ ጠቃሚ መስሎ የታያቸው እንደሆነ የልጃቸውን አሳዳሪነት ሥልጣን ራሳቸው ይዘው ሞግዚት ለመሾም ይችላሉ፡፡

አንቀጽ 233 ለፍርድ ቤት የተሰጠ ሥልጣን

Scanned by CamScanner

ፍርድ ቤት የልጁን አሳዳሪና ሞግዚት የመሾም ሥልጣን በያዘበት ጊዜና ይህን ለማድረግ አሳማኝ ምክንያት ሲኖረው ከአሳዳሪው በተጨማሪ ሌላ ሞግዚት ለመሾም ይችላል፡፡

አንቀጽ 234 ምትክ ሞግዚት (1) በሞግዚቱና አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ መካከል ስለሚነሳ የጥቅም ግጭት

1. በሞግዚቱና አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ መካከል የጥቅም ግጭት የተነሳ እንደሆነ ፍርድ ቤት አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ምትክ ሞግዚት ይሾምለታል፡፡
2. ምትክ ሞግዚት የሚመረጠው በሞግዚቱ ወይም ከሚቆጠሩ የልጁ ወላጆች ወይም ወደላይ ወንድሞቹና እህቶቹ በእንዳቸው ጥያቄ አቅራቢነት ነው፡፡

አንቀጽ 235 (2) አካለመጠን ባልደረሱ በብዙ ልጆች መካከል ስለሚነሳ የጥቅም ግጭት

1. አካለመጠን ባልደረሱ በብዙ ልጆች መካከል የጥቅም ግጭት የተፈጠረ እንደሆነና የነዚህም ተጠሪ ወኪል አንድ የጋራ ሞግዚት ብቻ በሆነ ጊዜ ከዚህ በላይ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ (አንቀጽ 234)
2. የጥቅም ግጭቱ የሚፈታውም በሞግዚቱና በምትክ ሞግዚቱ መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት ይሆናል፡፡

አንቀጽ 236 የሥራው አጀማመር

1. የአሳዳሪነቱ ወይም የሞግዚትነቱ ሥራ የሚጀመረው አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ በሕጉ መሠረት ወይም በፍርድ ውሳኔ ተመርጠው እንደተሾሙ ወዲያውኑ ነው፡፡
2. ሆኖም የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ የተሰጠው መሆኑን ከማወቁ በፊት አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ይህን ሥራውን ሳይጀምር ለደረሰው ጉዳት ሁሉ በኃላፊነት ሊጠየቅ አይችልም፡፡

አንቀጽ 237 ሥራው የግዴታ ስለመሆኑ

የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራዎች እንዲያከናውን ተመርጦ የተሾመው ሰው ሥራውን የማከናወን ግዴታ አለበት፡፡

አንቀጽ 238 ሥራው እንዲተርለት የሚቀርብ ጥያቄ

1. አንድ ሰው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ተግባርን ማከናወን በራሱ ላይ ከባድ ያሉ ችግሮችን በአጠቃላይም ኑሮውም ላይ እንቅፋት የሚያስከትልበት ከሆነ ሥራው እንዲተርለት ፍርድ ቤትን ሊጠይቅ ይችላል፡፡
2. እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ከተሰጠው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራው እንዲሻር ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡

አንቀጽ 239 በሕግ አግባብ የሚሰጥ ልዩ አስተያየት

በዚህ ሕግ መሠረት ለአሳዳሪነት ወይም ለሞግዚትነት ስለሚመረጡ ሰዎች የተደነገገው ቢኖርም ከዚህ የሚከተሉት ሰዎች በአሳዳሪነት ወይም በሞግዚትነት እንዳይሾሙ ወይም እንዲሻሩ ጥያቄ ካቀረቡና ይህም ጥያቄ የራሳቸውን ልጆች የሚመለከት ካልሆነ በስተቀር የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ እንዲሰሩ አይገደዱም፣

ሀ) ዕድሜው ስድሳ አምስት ዓመት የሞላው ሰው

ለ) በውትድርና የተሰማሩ ሰዎች

አንቀጽ 240 ለጊዜው ሥራውን የማከናወን ግዴታ

1. የልጁ አሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት ሥራ ችግር ያደርስብኛል ብሎ ምክንያት በማቅረብ ይህ ኃላፊነት እንዲወገድለት የሚጠይቅ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት በዚህ ሥራ ሌላ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ተተክቶ ሥልጣኑን እስኪረከበው ድረስ የተሰጠውን ሥራ ለጊዜው የማከናወን ግዴታ አለበት፡፡
2. እንዲሁም በሹመቱ ላይ ተቃውሞ የተነሳበት አሳዳሪ ወይም ሞግዚትም ተመሳሳይ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

አንቀጽ 241 ስለ ሥራው መቅረት

1. የአሳዳሪው ወይም የሞግዚቱ ሥራ ቀሪ የሚሆነው የሚጠበቀው ልጅ የሞተ እንደሆነ ወይም አካለመጠን በደረሰ ጊዜ ወይም ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ በወጣ ጊዜ ነው፡፡
2. እንዲሁም አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ሲሞት ወይም ችሎታ ሲያጣ ወይም ብቁ ያለመሆኑ ሲገለጽ ወይም ከሥራው ሲሻር ቀሪ ይሆናል፡፡
3. አዲስ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ሲሾምለትም የቀድሞዎቹ ተሿሚዎች ኃላፊነት ያበቃል፡፡

አንቀጽ 242 ችሎታ ማጣት (1) አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ

Scanned by CamScanner

የራሱን ልጆች በሚመለከት ጉዳይ ካልሆን በስተቀር አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራን ለማካሄድ ችሎታ የለውም፡፡

<u>አንቀጽ 243 (2) በፍርድ የተከለከሉ ሰዎች</u>

1. በፍርድ የተከለከለ ማንኛውም ሰው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራን ለማከናወን አይችልም፡፡
2. ይህን ሥራ ያከናውን የነበረ አንድ ሰው ችሎታ ያጣ መሆኑ በፍርድ ቤት ውሳኔ የተገለፀ እንደሆነ የዚህ ሰው ሞግዚት በሕግ መሰረት የተከለከለውን ሰው ስራ ተረክቦ በምትክነት ማካሄድ ለሚገባው ሰው ወዲያውኑ ማስታወቅ አለበት፡፡
3. እንዲህ ያለ ሰው የሌለም እንደሆነ በፍርድ የተከለከለው ሰው ምትክ እንዲደረግለት ሞግዚቱ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡

<u>አንቀጽ 244 ብቁ ስላለመሆን</u>

1. አንድ ሰው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራን ለማካሄድ ብቁ አይደለም ብሎ ፍርድ ቤት ለመወሰን የሚችለው የወንጀል ተግባር በመፈፀሙ የግል ነፃነትን የሚከለክል የእስራት ወይም የሞት ቅጣት የተፈረደበት ሲሆን ነው፡፡
2. ፍርድ ቤት የዚህን ዓይነት ቅጣት በአንድ ሰው ላይ በሚወስንበት ጊዜ ነገሩ ተገቢ መሆኑን የገመተ እንደሆነ የተፈረደበት ሰው ለዚህ ሥራ ብቁ አለመሆኑን ጭምር ለመወሰን ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 245 (1) የአሳዳሪው መሻር</u>

1. አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ አሳዳሪ እንዲሆን የተሾመ ሰው ልጁ ለጤናው አስፈላጊ የሆነውን ጥበቃ ሳያገኝ ወይም ከሞራል ጋር የሚስማማ የአእምሮ አስተዳደግ ወይም ከችሎታው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ትምህርት እንዲያገኝ ሳያደርግለት የቀረ እንደሆነ አሳዳሪው እንዲሻር ፍርድ ቤት ሊወስን ይችላል፡፡
2. ይህንንም ውሳኔ ለመስጠት አሳዳሪው የሚኖርበትን የአካባቢ ሁኔታና ጊዜውንም መመርመርና መሠረት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡
3. በተለይም ፍርድ ቤቱ አሳዳሪውን ለመሻር የሚችለው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወንጀል መስራቱ የተረጋገጠ ሲሆንና ይህንንም ወንጀል የፈፀመው በመጥፎ አስተዳደግ ወይም

በአሳዳሪው ጉድለት ተገቢውን የግብረ ገብ ትምህርት ለማግኘት ባለመቻሉ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

<u>አንቀጽ 246 (2) የሞግዚቱ መሻር</u>

አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ ሞግዚት የሆነ ሰው እንዲሻር ፍርድ ቤት የሚወስነው ሞግዚቱ የልጁን ንብረትና ሀብት በመጥፎ ሁኔታ ያስተዳደረና አጠባበቁም በቂ ያልሆነ እንደሆነ ወይም ልጁን በሞግዚትነት እንዲያስተዳድር ሥልጣን የሰጠው ሰው ወይም አካል የሰጠውን መመሪያና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ሳይጠብቅና ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ወይም ዕዳ ለመክፈል ያለመቻሉ በፍርድ ውሳኔ የተረጋገጠ እንደሆነ ነው፡፡

<u>አንቀጽ 247 (3) የወላጆች መሻር</u>

1. የልጁ አባት ወይም እናት ወይም ሌሎች ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ከልጆቻቸው አሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት ስራቸው እንዲሻሩ መወሰን ሲያስፈልግ ፍርድ ቤቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ በዚህ ጉዳይ ላይ የሰጠውን ውሳኔ በተሻረው ወገን ጠያቂነት በማንኛውም ጊዜ እንደገና ለመረምረው ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 248 (4) ሥነ ሥርዓት</u>

1. አንድ አሳደሪ ወይም ሞግዚት እንዲሻር የሚቀርበው ጥያቄ በማናቸውም በጉዳዩ ያገባኛል ባይ ወገን ወይም በአቃቤ ሕግ በኩል ሊቀርብ ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ አሳዳሪውን ወይም ሞግዚቱን ለመሻር ከመወሰኑ በፊት በርሱ በኩል ያለውን ሀሳብ ሊያዳምጠው ይገባል፡፡
3. ሆኖም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተውን ሲያከናውን በልጁ ደህንነት ወይም ሀብት ላይ ተጨማሪ ጉዳት ይደርሳል ተብሎ የሚገመት ከሆነ ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የታየውን ጊዜያዊ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 249 የፍርድ ቤት ኃላፊነት</u>

1. ፍርድ ቤት አንድን ሰው አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ አሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት ለመሾም ሲመርጥ ወይም የተሾመውን ከሥራው ሲሽር ከውሳኔው በፊት በተቻለ መጠን ከልጁ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች፣ አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ ጋር መመካከር ይገባዋል፡፡

Scanned by CamScanner

2. አስፈላጊ መስሎ ሲታየው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ያለውን ሀብት ሊያዳምጥ ይችላል፡፡
3. ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን ሲሰጥ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ጥቅም የሚይጓደልበትን አሠራር ብቻ መከተል እንጂ የቀረቡለትን ሀሳቦች የመቀበል ግዴታ አይኖርበትም፡፡

<u>አንቀጽ 250 ሥራው የሰከፍያ የሚከናወን ስለመሆኑ</u>

1. የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥራ የሚከናወነው ማናቸውም ዋጋ ሳይከፈልበት በነፃ ነው፡፡
2. ሆኖም አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ሥራውን ለማከናወን ረጅም ጊዜ የሚወስደው የሆነ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ አንድ የተወሰነ አበል ሊቆረጥለት ይችላል፡፡
3. ይህም አበል አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ የሀብት ገቢ ላይ ካልሆነ በስተቀር ከሌላ ሀብት ሊወሰድ አይችልም የአበሉም ልክ ከጠቅላላው የሀብት ገቢ ሲሶ ሊበልጥ አይችልም፡፡

<u>አንቀጽ 251 የሥራው አካሄድ የግል ስለመሆኑ</u>

1. የአሳዳሪነቱ ወይም የሞግዚትነቱ ሥራ የግል ጠባይ የያዘ ስለሆነ ሥራውን የሚያከናውነው ራሱ እንጂ ለአሳዳሪው ወይም ለሞግዚቱ ወራሾች ሊተላለፍ አይችልም፡፡
2. ወራሾቹ በኃላፊነት የሚጠየቁት አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ በፈፀመው የሥራ አካሄድ ጉድለት ብቻ ነው፡፡ ይኸውም በውርስ ህግ መሠረት ይወሰናል፡፡

<u>አንቀጽ 252 የወራሾች ግዴታ</u>

1. አንድ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ወራሾች አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ እንደሞተ ወዲያኑ በዚህ ሕግ አንቀጽ 225 በተመለከተው መሠረት ለሟቹ ምትክ ሊሆን ለሚገባው ሰው ማስታወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡
2. የዚህ ዓይነት ሰው የሌለ እንደሆነ በሟቹ ምትክ የሚመረጠው ሰው እንዲሾም ለፍርድ ቤት ማስታወቅ አለባቸው፡፡
3. የአሳዳሪው ወይም የሞግዚቱ ወራሾች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከቱትን ግዴታዎች እስኪወጡ ድረስ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅም ሆነ ለሌላ ሦስተኛ ወገኖች ኃላፊዎች ሆነው ይቆያሉ፡፡

<u>አንቀጽ 253 የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ማስረጃ</u>

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አሳዳሪነቱን ወይም ሞግዚትነቱን የሚያስረዳለት ጽሑፍ እንዲሰጠው አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ፍርድ ቤትን ለመጠየቅ ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 254 ከሞግዚት ጋር የሚመሳሰል ሁኔታ</u>

ሞግዚትን የሚመለከቱት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች በምትክ ሞግዚት ጉዳይም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

<u>ክፍል 3</u>
<u>የአሳዳሪውና የሞግዚቱ ሥልጣን</u>
<u>ንዑስ ክፍል 1</u>
<u>አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አስተዳደግና ጥበቃ</u>

<u>አንቀጽ 255 አሳዳሪው የመንግሥት ተቋማትን እገዛ መጠየቅ ስለመቻሉ</u>

አሳዳሪው ከዚህ በታች በተመለከቱት አንቀጾች የተሰጠውን ሥልጣን በሥራ ላይ ለማዋል እንዲችል አግባብነት ያላቸውን የመንግሥት ተቋሞች እገዛ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 256 አካለመጠን ስላልደረሰ ልጅ መኖሪያ ቦታ</u>

1. አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ መኖሪያ ቦታ ይወስናል፡፡
2. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ያለአሳዳሪው ፈቃድ የተመደበለትን መኖሪያ ቦታ ሊተው አይችልም፡፡
3. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የተመደበለትን መኖሪያ ቦታ ትቶ የሄደ እንደሆነ አሳዳሪው ወደ መኖሪያ ቦታው እንዲመለስ ሊያስገድደው ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 257 አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ጤና አጠባበቅ</u>

1. አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ጤንነት ሁኔታ ይከታተላል፡፡
2. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ሲታመም ከህመሙ እንዲፈወስ አስፈላጊውን ሁሉ እርምጃ ይወስዳል፡፡

<u>አንቀጽ 258 አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አስተዳደግ</u>

1. አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ አስተዳደግ ይመራል፡፡

Scanned by CamScanner

2. አሳዳሪው አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ መልካም አስተዳደግ ተገቢነት ያለውን የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ ይችላል፡፡

አንቀጽ 259 አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ማህበራዊ ግንኙነት

1. አሳዳሪው አካለመጠን ያደረሰውን ልጅ ማህበራዊ ግንኙነት ይመራል ይቆጣጠራል፡፡
2. ሆኖም አሳዳሪው በቂ ምክንያት ሳይኖረው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ ጋር ግንኙነት እንዳያደርግ ሊያግደው አይችልም፡፡

አንቀጽ 260 አጠቃላይ እና የሙያ ትምህርት የመስጠት ግዴታ

አሳዳሪው አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ዕድሜና ችሎታ ተመጣጣኝ የሆነ አጠቃላይ ትምህርት ወይም የሙያ ሥልጠና እንዲያገኝ ማድረግ አለበት፡፡

አንቀጽ 261 አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ገቢ (1) መሠረቱ

1. አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ገቢዎች በመቀበል ለልጅየው ጥቅም ያውላል፡፡
2. አሳዳሪው ገንዘቡን ለምን አገልግሎት እንዳዋለው መግለጫ ለመስጠት አይገደድም፡፡

አንቀጽ 262 (2) ከፍተኛ ስለሆነ ገቢ

1. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ገቢ ከፍተኛ ሲሆንና አሳዳሪው የልጁ አባት ወይም እናት ያልሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤት በዚህ ሕግ አንቀጽ 261(2) የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ እንዳይሆን ሊያግድ ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ትዕዛዙን በሚሰጥበት ጊዜ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ አስተዳደግና ለትምህርቱ በቂ ነው የሚለውን የገንዘብ መጠንና የሚከፈልበትን ጊዜ በመወሰን ለአሳዳሪው እንዲሰጠው ያደርጋል፡፡
3. ተራፊውን ገንዘብ በአትራፊ ሥራ ላይ እንዲያውለው በሞግዚቱ እጅ ተቀማጭ ይደረጋል፡፡

አንቀጽ 263 (3) አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ከሥራው ስለሚያገኘው ገቢ

1. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ዕድሜው ከ14 ዓመት በላይ ሲሆን ከሥራው የሚያገኘው ገቢ እራሱ ይቀበላል፡፡

2. ለራሱ ቀለብ የሚሆነውን ለአሳዳሪው ከሰጠ በኋላ ቀሪውን ገንዘብ በዚህ ሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሊጠቀምበት ሙሉ ሥልጣን አለው፡፡

አንቀጽ 264 (4) በስጦታ ወይም በውርስ ስለተላለፉ ሀብቶች

1. አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ሀብት የሚያስተላልፍ ሰው ልጁ አካለመጠን ሳይደርስ አሳዳሪው ተቀብሎ ጥቅም ላይ እንዲያውለው ሊያገ ይችላል፡፡
2. በስጦታው ውል ወይም በኑዛዜው ስለንብረቱ አስተዳደርና ስለሚገኘውም ገቢ የተመለከቱ ኃይለ ቃሎች ተፈፃሚ መሆን አለባቸው፡፡

አንቀጽ 265 የመክፈያ ጊዜያቸው ያልደረሱ ገቢዎች

የመክፈያ ጊዜያቸው ያልደረሱ ገቢዎችን አሳዳሪው ግዴታ ሊገባባቸው አይችልም፡፡

አንቀጽ 266 ስለወላጆች ሥልጣን

1. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ አባትና እናት በጋራ አሳዳሪዎቹ በሆኑ ጊዜ የአሳዳሪነት ተግባራቸውን በመመካከርና በመግባባት ይወጣሉ፡፡
2. አባት እና እናት ያለመግባባታቸውን በግላቸው ወይም በሽምግልና ለመፍታት ያልቻሉ እንደሆነ ከሁለት አንደኛው በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ፍርድ ቤቱ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት ውሳኔ ይሰጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አባትና እናት በአሳዳሪነታቸው በሚሰጡት ውሳኔ ላይ አቤቱታ ሊቀርብበት አይችልም፡፡

አንቀጽ 267 የወላጆች መለያየት

ወላጆች በመለያየታቸው ምክንያት የአሳዳሪነቱ ሥልጣን የአንደኛው ወላጅ ብቻ የሆነ እንደሆነ ይኸው ወላጅ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የአሳዳሪነት ተግባር በማከናወን ላይ የሌለው ወገን ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ ወይም አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ አንዳቸው አቤቱታ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ፡፡

አንቀጽ 268 አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወላጅ በማይሆንበት ጊዜ

Scanned by CamScanner

አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወላጅ ያልሆነ እንደሆነ በልጁ አስተዳደግ ረገድ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ከወላጆቹ አንዳቸው ወይም ሌላ በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ሰው ወይም ዐቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

ንዑስ ክፍል 2
አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ንብረት ስለማስተዳደር

አንቀጽ 269 መሠረቱ

1. ሀብቱንና ንብረት ነክ ጥቅሞቹን በተመለከተ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ በሞግዚቱ ይወከላል፡፡
2. ሀብቱንና ንብረት ነክ ጥቅሞቹን በማስከበርና በማስተዳደር ረገድ ሞግዚቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

አንቀጽ 270 የንብረት ቆጠራና የዋጋ ግምት (1) ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራውን ከጀመረ በኋላ

1. ሞግዚቱ የሞግዚትነቱን ሥራ ከጀመረ በኋላ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ሦስት ምስክሮች ባሉበት አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ይቆጥራል፤ የዋጋውንም ግምት ያወጣል፡፡
2. ሞግዚቱ አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ የሚጠይቀው ዕዳ ሲኖር በንብረት ቆጠራው መዝገብ በወቅቱ ካላሰፈረው በስተቀር የዕዳው ክፍያ ቀሪ ይሆንበታል፡፡

አንቀጽ 271 (2) አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የውርስ ሀብት

1. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወራሽ በሚሆንበት ጊዜ ሞግዚቱ ስለልጁ ሆኖ ውርሱን ከመቀበሉ አስቀድሞ ሦስት ምስክሮች ባሉበት የውርስ ንብረቱን ቆጠራ ያከናውናል፤ የዋጋውንም ግምት ያወጣል፡፡
2. ሞግዚቱ ከውርሱ ሀብት ውስጥ ድርሻ ያለው እንደሆነ ይህንኑ በንብረት ቆጠራው መዝገብ ያላሰፈረው እንደሆነ ድርሻው ቀሪ ይሆንበታል፡፡
3. የንብረት ቆጠራው ባለመከናወኑ ወይም በአግባቡ ባለመሠራቱ ለሚደርስ ጉዳት ሞግዚቱ በኃላፊነት ይጠየቅበታል፡፡

አንቀጽ 272 የሞግዚቱ ንብረት አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ንብረት ጋር ስለሚተሳሰርበት ሁኔታ

1. ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ከግል ንብረቱ ጋር እንዳይቀላቀል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ ማድረግ አለበት፡፡
2. በተለይም አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ገንዘብ ሞግዚቱ በራሱ የባንክ ሂሳብ ማስቀመጥ ወይም እንዲቀመጥ ማድረግ አይፈቀድለትም፡፡

አንቀጽ 273 የገንዘብ ሰነዶችና ሌሎች ውድ ዕቃዎች ስለሚቀመጡበት ሁኔታ

አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት በማስተዳደር ረገድ ችግር የሚፈጥር ካልሆነ በስተቀር የገንዘብ ሰነዶችን ውድ ዕቃዎችን ጠቃሚ ጽሑፎችንና ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን ሁሉ ሊጠፉ ወይም ሊባክኑ በማይችሉበት አስተማማኝ ስፍራ ማስቀመጥ አለበት፡፡

አንቀጽ 274 የፍርድ ቤት ሥልጣን

1. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ሞግዚት የልጁ ወላጅ ባልሆነ ጊዜ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብት መልካም አስተዳደር በሚመለከት ለሞግዚቱ መመሪያ እንዲሰጥ የልጁ ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆች ወይም አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹ ወይም እህቶቹ አንዳቸው ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
2. ፍርድ ቤቱም አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብት አጠቃላይ ሁኔታ፣ የሞግዚቱን ችሎታና የልጁየውን ጥቅም በማመዛዘን ስለሀብቱ አስተዳደር ጠቃሚ መስሎ የሚታየውን መመሪያ ይሰጠዋል፡፡

አንቀጽ 275 አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ስለሚተላለፍ ንብረት

1. አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ንብረት የሚያስተላልፍ ሰው የንብረቱን አስተዳደር በሚመለከት ተገቢ ናቸው የሚላቸውን የአሠራር መመሪያዎች ሞግዚቱ እንዲከተል ሊያዝ ይችላል፡፡
2. የአሰራር መመሪያዎቹን ተከትሎ ለመስራት የማይችል ወይም አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያደርስበት መስሎ የታየው እንደሆነ ሞግዚቱ መመሪያዎቹ እንዲስተካከሉለት ፍርድ ቤትን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

አንቀጽ 276 ስለንግድ ድርጅቶችና ሌሎች መሰል ድርጅቶች

1. የንግድ የኢንዱስትሪ ወይም ሌሎች መሰል ድርጅቶች አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብት አካል የሆኑ እንደሆነ ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ ወይም አካለመጠን ከደረሰ ወንድሞቹና እህቶቹ እንዳቸው በሚያቀርቡት ጥያቄ የልጁ አባት ወይም እናት ያልሆነው ሞግዚት ንብረቱን እንዲያጣራ ወይም እንዳለ እንዲቀጥል እንዲያደርግ ፍርድ ቤት ሊያዘው ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ይህንን ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ሞግዚትነቱ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ የሞግዚቱን ችሎታና አካለመጠን ያደረሰውን ልጅ ጥቅም ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

<u>አንቀጽ 277 አንዳንድ ንብረቶችን ስለመሸጥ</u>

1. ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት የሆኑ የሚንቀሳቀሱ ግዙፍ ንብረቶች አክስዮኖችንና የገንዘብ ሰነዶችን ለመሸጥ ይችላል፡፡
2. በልጁ አባት ወይም እናት ላይ ካልሆነ በስተቀር በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ማንኛውም ሰው ጥያቄ ሲያቀርብለት ፍርድ ቤት ስለሽያጩ መመሪያ ለመስጠት ወይም ሽያጩ እንዳይካሄድ ለመከልከል ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 278 ለአምጪው እንዲከፈል ስለሚሉ ሰነዶች</u>

1. አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አባት ወይም እናት ያልሆነ ሞግዚት ለአምጪው እንዲከፈል የሚሉ ሰነዶች የልጁ ሀብት ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ በሦስት ወራት ውስጥ እንዲሸጡ ወይም በልጁ ስም በተመዘገቡ ሰነዶች እንዲለወጡ ማድረግ አለበት፡፡
2. ሞግዚቱ ጥያቄ ሲያቀርብለት ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው ግዴታ ነፃ እንዲሆን ሊያዝ ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 179 ዕዳዎችና ገቢ ገንዘቦች</u>

1. ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ዕዳዎች ከልጁ ሀብት በመቀነስ ይከፍላል፡፡
2. አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ መከፈል የሚገባውን ካፒታል እና ሌላ ገቢ ይቀበልለታል ስለመቀበሉ በማረጋገጥም ደረሰኝ ይሰጣል፡፡

<u>አንቀጽ 280 ካፒታልን አትራፊ በሆነ ሥራ ላይ ስለማዋል (1) የሞግዚቱ ግዴታ</u>

1. የገንዘቡ መጠን ከ500 ብር በላይ የሆነ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ካፒታል ሞግዚቱ አትራፊ በሆነ ሥራ ላይ ማዋል አለበት፡፡
2. ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን የገንዘብ መጠን ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 281 (2) የጊዜ ገደብ</u>

1. ካፒታሉ በሞግዚቱ እጅ በገባ በሦስት ወራት በአትራፊ ሥራ ላይ መዋል አለበት፡፡
2. ፍርድ ቤቱ የጊዜውን መጠን ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 282 ኃላፊነት</u>

1. በአትራፊ ሥራ ላይ ላላዋለው ገንዘብ ሞግዚቱ ሕጋዊ ወለዱ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ መክፈል አለበት፡፡
2. አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝም ተጨማሪ የጉዳት ካሣ እንዲከፍል ሊፈረድበት ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 283 ገቢዎች</u>

1. አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ገቢዎች ገቢዎቹ በቂ ሆነው የማይገኙ ሲሆንም ከሀብቱ ቀንሶ ለአስተዳደጉና ለትምህርቱ አገልግሎት እንዲውል ሞግዚቱ ለአሳዳሪው ይሰጠዋል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በስተቀር ለዚሁ አገልግሎት የሚውለው ገንዘብ በየወሩ ለአሳዳሪው ይከፈላል፡፡
3. የአከፋፈሉ ሁኔታ በአሳዳሪውና በሞግዚቱ ስምምነት ወይም በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔ መሠረት ሊሻሻል ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 284 የኪራይ ውሎች</u>

በፍርድ ቤት ፈቃድ የተደረጉ ካልሆኑ በስተቀር ሞግዚቱ የሚያደርጋቸውን የኪራይ ውሎች ልጅየው አካለመጠን ከደረሰ ከሦስት ዓመታት በኋላ እንዲፈጸሟቸው አይገደድም፡፡

<u>አንቀጽ 285 ስለውርስ</u>

1. ልጁ በውርስ የሚያገኘውን ንብረት ሞግዚቱ ይቀበላል፡፡
2. ሞግዚቱ የውርሱ ሀብት ዕዳውን ለመክፈል ፈጽሞ የማይችል ካልሆነ በስተቀር ውርሱን አልፈልግም ለማለት አይችልም፡፡

Scanned by CamScanner

አንቀጽ 285 በስጦታ

1. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የሚሰጠው ስጦታ ጠቃሚነት የሌለው በሚሆንበት ካልሆነ በስተቀር ሞግዚቱ አልቀበልም ማለት አይችልም፡፡
2. በተለምዶ ከሚሰጡ አነስተኛ ስጦታዎች ውጪ ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት በልጁ ስም በስጦታ ለመስጠት አይችልም፡፡

አንቀጽ 287 የሦስተኛ ግዴታ መግባት የማይቻል ስለመሆኑ

ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ለሌላ ሰው ዕዳ በዋስትና ሊያሲዝ አይችልም፡፡

አንቀጽ 288 በስ ግልግል

ከርክር የሚደረግበት ጥቅም ከ 1ሺ ብር ያነሰ ካልሆነ ወይም አካለመጠንያልደረሰውን ልጅ ጥቅም በሚመለከት ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሞግዚቱ ጉዳዩን በግልግል መጨረስ አይችልም፡፡

አንቀጽ 289 ሞግዚቱ አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ጋር ስለሚያደርጋቸው ውሎች

1. ሞግዚቱ ፍርድ ቤት ካልፈቀደለት በስተቀር አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ለመግዛት በኪራይ ለመጠቀም ወይም ሌላ ማናቸውንም ውል ከእርሱ ጋር ለመፈፀም አይችልም፡፡
2. እንዲሁም ሞግዚቱ በፍርድ ቤት ካልተፈቀደለት በስተቀር አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ላይ ማናቸውንም መብት ወይም ገንዘብ የሚጠይቅበትን መብት ለመቀበል አይችልም፡፡

አንቀጽ 290 ስለብድር

ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሞግዚቱ አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ስም የብድር ውል ለመዋዋል አይችልም፡፡

አንቀጽ 291 አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ጋር መመካከር ስለማስፈለጉ

1. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ዕድሜ ከ14 ዓመት ያነሰ ካልሆነ በስተቀር ሞግዚቱ የልጁ ዕድሜ በሚፈቅድለት መጠንና እርሱን የሚመለከቱ ከፍተኛ ጉዳዮች በተነሱ ጊዜ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ማማከር አለበት፡፡

2. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ፈቃዱን መስጠቱ ሞግዚቱን ከተጠያቂነት አያድነውም፡፡

አንቀጽ 292 ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ እንዲሠራ ስለሚሰጠው ፈቃድ (1) መሠረቱ

1. አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ዕድሜና የገንዘብ አቅም መሠረት በማድረግ የዕለት ጉዳዮችን የሚመለከቱ ውሎችን ብቻ እንዲያደርግ ሞግዚቱ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡
2. ይኸው ፈቃድ በዝምታም ሊሰጥ ይችላል፡፡

አንቀጽ 293 (2) የዕለት ጉዳዮች

1. ድርጊቱ እንዲፈፀም የፍርድ ቤት ፈቃድ የሚያስፈልገው እንደሆነ በምንም መንገድ የዕለት ጉዳይ ሊባል አይችልም፡፡
2. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ከ300 ብር በላይ ግዴታ እንዲገባ የሚያስገድደው ሲሆን ድርጊቱ የዕለት ጉዳይ ነው ሊባል አይችልም፡፡

አንቀጽ 294 (3) በሞግዚቱ ላይ ስለሚኖረው ውጤት

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ በሞግዚቱ ፈቃድ ለሚገባቸው ግዴታዎች ሞግዚቱ ለሦስተኛ ወገኖች ዋስ ነው፡፡

አንቀጽ 295 ጋብቻ

1. ሞግዚቱ አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ስም ጋብቻ ሊያደርግ አይችልም፡፡
2. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ 16 ዓመት ሳይሞላው ጋብቻ ማድረግ አይችልም፡፡
3. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ 16 ዓመት ሳይሞላው የሚያደርገው ጋብቻ 16 ዓመት ከሞላው በኋላ ባይሰርዘውም ውጤት አይኖረውም፡፡

አንቀጽ 296 ንብረት ለማስተዳደር ሞግዚቱ ስለሚያደርገው ወጪ

ሞግዚቱ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ጥቅም ሲል ከግሉ የሚያወጣቸው ወጪዎች እንዲተኩለት መብት አለው፡፡

አንቀጽ 297 አካለመጠን ስላልደረሰው ልጅ ሀብት አስተዳደር ሪፖርት ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ

1. ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብት አስተዳደር ሁኔታና ሂሳቡን የሚያመለክት ሪፖርት አዘጋጅቶ መያዝ አለበት፡፡
2. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወይም አካለመጠን የደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ በጋራ ወይም በተናጠል ጥያቄ ሲያቀርቡለት ሞግዚቱ የአስተዳደርና ሂሣብ ሪፖርቱን እንዲመለከቱት ያደርጋል፡፡

አንቀጽ 298 ተፈፃሚነት

በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 264 እስከ 267 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለሞግዚትም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

ክፍል 4
አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ለመጠበቅ የተመለከቱትን ደንቦች መጣስ ስለሚያስከትለው ውጤት

ንዑስ ክፍል 1
አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ሥራዎች

አንቀጽ 299 መሠረቱ

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ከሥልጣኑ በላይ የሚፈጽማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ሁሉ ፈራሽ ይሆናሉ፡፡

አንቀጽ 300 እንዲፈርስ ስለመጠየቅ

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ የፈፀማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች እንዲፈርሱ መጠየቅ የሚችሉት አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወይም ወራሾቹ ወይም ወኪሎቹ ናቸው፡፡

አንቀጽ 301 ስለተዋዋዩ ቅን ልቦና

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 299 የተደነገገው ቢኖርም ሌላው ተዋዋይ ወገን ከልጁ ጋር የተዋዋለው ይህንን እንዲያደርግ ፈቃድ አለው ብሎ በቅን ልቦና በማመን የሆነ እንደሆነ ውሉ የፀና ይሆናል፡፡
2. ሌላው ተዋዋይ በልጁ አሳሣቂነት የተጠቀመ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

አንቀጽ 302 ስለሚመለስ ገንዘብ

1. አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ የተከፈለ ገንዘብ ሊመለስ የሚችለው ውሉ እንዲፈርስ ክስ በተረበበት ቀን በልጁ በተገኘው መጠን ብቻ ይሆናል፡፡
2. ከዚህ ሁኔታ ውጪ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ለመመለስ አይገደድም፡፡

አንቀጽ 303 ከውል ውጪ ስለሚደርስ ኃላፊነትና ያለአግባብ ስለመበልጸግ

(1) መሠረቱ

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ሕገወጥ በሆኑ ሥራዎች ያለአግባብ የበለፀገ ወይም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ በፍትሐብሄር ሕግ ውስጥ ከውል ውጪ ስለሚደርስ ኃላፊነትና ያለአግባብ ስለመበልፀግ በተደነገገው መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 304 (2) አካለመጠን ሳይደርስ ደርሻለሁ ማለት

1. አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አካመጠን ሳይደርስ ደርሻለሁ ብሎ ቢናገርም እንኳን ይህን መናገሩ ብቻ አካለመጠን ባለመድረሱ ምክንያት የሚጠቀምበትን መብት አያጣም፡፡
2. እንዲሁም አካለመጠን ደርሻለሁ ማለቱ ከውል ውጪ የሆነ ኃላፊነት የሚያመጣ ጥፋት ሆኖ አይቆጠርበትም፡፡

ንዑስ ክፍል 2
የሞግዚቱ ሕጋዊ ድርጊቶች

አንቀጽ 305 በደንብ ስለተፈፀሙ ድርጊቶች

1. ሞግዚቱ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ የፈፀማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ሁሉ ልጁ አካለመጠን በደረሰ ጊዜ እንደፈፀማቸው ተቆጥረው በኃላፊነት ያስጠይቁታል፡፡
2. ሞግዚቱ በኃላፊነት እጠየቅበታለሁ ሲል ግዴታ የገባበት ወይም በሕግ መሠረት ግዴታ የተጣለበት ካልሆነ በስተቀር አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ሲል ለፈፀማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ኃላፊ አይሆንም፡፡

አንቀጽ 306 የሕግ ድንጋጌዎች ስለመተሳሰፍ

የሕግ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ሞግዚቱ ለሚፈፅማቸው ድርጊቶች ወኪል የሆነ ሰው ከተሰጠው ሥልጣን በላይ በሚሠራበት ጊዜ አግባብነት ያላቸው የውክልና ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

አንቀጽ 307 ስለሦስተኛ ወገኖች

1. ፍርድ ቤት ለሞግዚቱ የተሰጠውን መመሪያ ሦስተኛ ወገኖች ካላወቁ ወይም ማወቅ የሚገባቸው ካልሆነ በስተቀር ሞግዚቱ መመሪያውን መተላለፉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም፡፡
2. አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ ንብረቱን የሰጠ፣ የተናዘዘ ወይም የተወ ሰው ለሞግዚቱ መመሪያ በሰጠ ጊዜም የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 308 ስለምትክ ሞግዚት

በዚህ ንዑስ ክፍል የተመለከቱት ድንጋጌዎች በምትክ ሞግዚትም ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

ንዑስ ክፍል 3
በኃላፊነት ሊያስጠይቁ ስለሚችሉ ድርጊቶች

አንቀጽ 309 ስለሞግዚት

1. ሞግዚቱ በፈፀመው የንብረት አስተዳደር ጉድለት ምክንያት ወይም መመሪያ ባለማክበሩ ወይም የእርሱ ጥቅም አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ጥቅም ጋር የሚጋጭ ሆኖ እያለ ድርጊቱን በመፈፀሙ አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ሁሉ በኃላፊነት ይጠየቃል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ድንጋጌ በምትክ ሞግዚትም ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ክፍል 5
አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ ማጣት ስለመቅረቱ

አንቀጽ 310 ችሎታ ማጣት ስለሚቀርባቸው ምክንያቶች

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ የለውም መባሉ የሚቀረው

ሀ) አካለመጠን ሲደርስ ወይም

ለ) ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ይውጣ ሲባል ነው፡፡

ንዑስ ክፍል 1
ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ስለመውጣት

አንቀጽ 311 ጋብቻ

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ በዚህ ሕግ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው መሠረት ጋብቻ የፈፀመ እንደሆነ በጋብቻው ምክንያት ብቻ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ይወጣል፡፡

አንቀጽ 312 በልዩ ሁኔታ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ስለመውጣት

1. አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ 14 ዓመት ሲሞላው አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ወይም ያገባኛል የሚል ሌላ ሰው ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንዲወጣ መጠየቅ ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤት ጥያቄው ሲቀርብለት የልጁን ሁኔታና ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንዲወጣ የተጠየቀበትን ምክንያት ተመልክቶ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ መሆኑ ለልጁ የሚጠቅም ሆኖ ካገኘው ጥያቄውን ተቀብሎ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

አንቀጽ 313 ውጤቶቹ

ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የወጣ ልጅ በሕግ አካለመጠን እንደደረሰ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

አንቀጽ 314 የማይሻር ስለመሆኑ

1. አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንዲሆን የተሰጠ ፈቃድ ሊሻር አይችልም፡፡
2. በጋብቻ ምክንያት የተገኘው ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የመሆን ሁኔታ ጋብቻው ቢፈርስም እንኳን ውጤቱ እንደተጠበቀ ይቀራል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም ጋብቻው የፈረሰው ሲጋባ የተፈቀደው ሕጋዊ ዕድሜ ባለመጠበቁ ምክንያት የሆነ እንደሆነ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ መውጣቱን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የታየውን ሊወስን ይችላል፡፡

ንዑስ ክፍል 2
የሞግዚትነት ሥራ ሂሳቦችን ስለማስታወቅ

አንቀጽ 315 መሠረቱ

Scanned by CamScanner

1. ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራው ሲያበቃ ሞግዚት ሆኖ ለአስተዳደረው ሰው ወይም ለወራሾቹ ያስተዳደረበትን ሂሳብ ማቅረብ አለበት፡፡
2. እንዲሁም በሞግዚትነት ያስተዳደረውን ሰው ንብረት ሁሉ ማስረከብ፣ የመብቶቹን ሁኔታና የሚገደድባቸው ዕዳዎች ካሉም ማስታወቅ አለበት፡፡

<u>አንቀጽ 316 የንብረቶች በመዝገብ አለመግባት</u>

1. ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራውን በያዘበት ጊዜ ወይም አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ በውርስ ሀብት ሲሰጠው የንብረቶቹን ዝርዝር በመዝገብ ከመያዝ ቸል ያለ እንደሆነ የልጁን ንብረት በውርስ ወይም በስጦታ ያገኘውን ሀብት በማናቸውም ሁኔታ ለማስረዳት ይቻላል፡፡
2. ሌላ ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር ምስክሮች በሚሰጡት ቃል እንደ ንብረት አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

<u>አንቀጽ 317 ሂሳቦችን ስለማፅደቅ</u>

1. ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የወጣው ልጅ የሞግዚቱን ሥራ ሂሳቦች ያጸደቀ እንደሆነና ዕድሜው 18 ዓመት ያልሞላው ከሆነ ሂሳቦቹን ካፀደቀ በኋላ እስከ አንድ ዓመት ድረስ አጽድቆት የነበረውን ሂሳብ ራሱ ሊያፈርሰው ይችላል፡፡
2. ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የወጣው ልጅ ሂሳብ እንዲያቀርብ ለሞግዚቱ ፈቃድ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ከዚህ በላይ ያለው ድንጋጌ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡
3. አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ አካለመጠን የደረሱ ሲወርሱት እነዚህ ወራሾች የልጁ ሞግዚት ያደረገውን ሂሳብ ያጸደቁት ወይም ሞግዚቱን ሂሳብ ከማቅረብ ነፃ አውጥተውት እንደሆነ ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ጠቅሰው ለመከራከር አይችሉም፡፡

<u>አንቀጽ 318 ስለ ይርጋ</u>

1. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወኪሎች ወይም ወራሾቹ በሞግዚትነት ሥራ ምክንያት በሞግዚቱ ላይ ስለኃላፊነት የሚያቀርቧቸው ማናቸውም ክሶች ሞግዚቱ የሞግዚትነት

ሥራውን ከተወበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ሳያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ በይርጋ ይታገዳሉ፡፡
2. ሆኖም አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረቶች እንዲመለሱለት ለመጠየቅ ክስ የማቅረብ መብቱ ከዚህ በላይ የተመለከተው ጊዜ ካለፈ በኋላም ቢሆን አይከለከልም፡፡

----------------------- // -----------------------

Scanned by CamScanner

አባሪ ሁለት - የዋቢ ሰነዶች ዝርዝር

I. የህጎች ዝርዝር

1. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት፡ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ አንደኛ ዓመት ቁ.1 አዋጅ ቁጥር 1/1987
2. የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ 6ኛ ዓመት ልዩ ዕትም አዋጅ ቁጥር 213/1992
3. የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግስት የፍትሐብሄር ህግ ነጋሪት ጋዜጣ በተለይ የወጣ 19ኛ ዓመት ቁጥር 2/1952
4. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ አዋጅ ቁጥር 414/1996
5. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ 10ኛ ዓመት ቁጥር 12 አዋጅ ቁጥር 377/1996
6. የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ 9ኛ ዓመት ቁጥር 65 አዋጅ ቁጥር 345/1995
7. የፌደራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ 8ኛ ዓመት ቁጥር 80 አዋጅ ቁጥር 262/1994
8. የህፃናት መብት ኮንቬንሽን ኅዳር 1984 በኢትዮጵያ የፀደቀ
9. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤተሰብ ህግ ነጋሪት ጋዜጣ ትግራይ 7ኛ ዓመት ቁጥር 33 አዋጅ ቁጥር 33/1991
10. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤተሰብ ህግ ዝክረ ህግ 8ኛ ዓመት ቁጥር 3 አዋጅ ቁጥር 79/1995
11. የኢትዮጵያ የጥንት ፍርዶች መዝገብ (ያልታተመ) አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ህግ ፋክልቲ ቤተ መጻህፍት

II. የፍርድ ውሳኔዎች ዝርዝር

1. የፍትሐብሄር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 936/80
2. የጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍ/ይ/መ/ቁጥር 1880/79
3. የጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍ/ይ/መ/ቁጥር 683/76
4. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍ/ይ/መ/ቁጥር 1354/1641/88
5. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍ/ይ/መ/ቁጥር 12046
6. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍ/ይ/መ/ቁጥር 1536/88
7. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍ/ይ/መ/ቁጥር 1768/85
8. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍ/ይ/መ/ቁጥር 901/88
9. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 03814

10. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገብ ቁጥር 17361

III. የሌሎች ሰነዶች ዝርዝር

1. Lasok, Polish Family Law, 1986
2. ዶ/ር ክፍሌ ታደሠ በኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ህግ የቤተሰብ ህግ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የታተመ (1990)
3. አቶ መንበረ ፀሃይ ታደሠ Filiation under Ethiopian Law, Senior thesis, 1986
4. አቶ ኪዳነማሪያም ሐጎስ Cessation of Disability under Ethiopian Law, Senior Thesis, 1986
5. አቶ ተድላ ድረሴ የጉዲፈቻ አገልግሎት በኢትዮጵያ (ያልታተመ) በ1991 የቀረበ
6. አቶ ተድላ ድረሴ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ከኢፌዴሪ መንግሥት ህጎች አንፃር (ያልታተመ) በ1991 የቀረበ
7. አቶ ሲሳይ ታደሰ የኢፌዴሪ መንግሥት እና በፍትሐብሄር የቤተሰብ ህግ ስለመወሰድ ያሉት ድንጋጌዎች (ያልታተመ) በ1991 የቀረበ
8. Andrew Bainham, The International Survey of Family Law, London, 1996
9. Jaffe Peter G. "Child custody and Domestic Violence: a call for safety and accountability."

Scanned by CamScanner